ባለቤት አልባ ከተማ



የሁሉምየሆነች ፣ የማንምያይደለች•••

(የ ግል ማስታወሻ)

በኤርምያስ ለገሰ

2006 ዓ•ም•

ባለቤት አልባ ከተማ
Copyright 2006 ዓ•ም•
የደራሲው መብት የተጠበቀ ነው።

ምስጋና

ዳንኤል ማስታወሻዎቼን ጊዜ ሰጥቶ አንብቧቸዋል። ተወያይተንበታል። አናም በማስታወሻዎቹ ላይ የሰፈሩት ቁምነገሮች የግልና ቤተሰብ ወግ ብቻ ሳይሆን የህዝብ ሀብት ናቸው በማለት በየእለቱ ይሞግተኝ ነበር። እንድፅፉቸውም አበረታቶኛል።ዳንኤል ማስታወሻዎቼን ጊዜ ሰጥቶ አንብቧቸዋል። ተወያይተንበታል። አናም በማስታወሻዎቹ ላይ የሰፈሩት ቁምነገሮች የግልና ቤተሰብ ወግ ብቻ ሳይሆን የህዝብ ሀብት ናቸው በማለት በየእለቱ ይሞግተኝ ነበር። እንድፅፉቸውም አበረታቶኛል።ረቂቁን ለዳንኤል ሰጠሁት። ጊዜ ወስዶ በመጽሀፉ ይዘት፣ አቀራረብና የቋንቋ አጠቃቀም ላይ ሰፊ ሙያዊ አስተያየት ሰጠኝ። መስተካከል የሚገባውንም መስመር በመስመር እየለቀመ አስተካከለው። በመሆኑም የቅድሚያ ምስጋናዬ ለወንድሜ ዳንኤል ለገሰ ይሁን።

ቤተሰቦቼ እንደ ትላንትናው ሁሉ ዛሬም " ከስጋ ድሎት ይልቅ በንፁህ ህሊና መኖር ይሻላል " በማለት ከጐኔ ነበሩ። በዚህም ባለቤቴ ኪያ፣ ልጆቼ ኖህሚንና ቃልኪዳን አመሰግናችኃለሁ።———— ይቀጥላል።

የስደት ኑሮ ረሱን የቻለ ትልቅ ፈተና ነው። መሸቶ በነጋ ቁጥር ለእለት ህይወት የሚደረግ የማያቆም ሩጫ አለበት። ከእለታት በአንዱ ቀን የምትገኝ ሽርፍራፊ ሰአትም ቢሆን ከቤተሰብ ጋር ለማሳለፍ ፕሮግራም የሚያዝበት ነው... ባለቤት፣ልጆች፣ወንድም፣ ወዳጆች ...

ታዲያ ከቤተሰብና ወዳጆች ጋር ስገናኝ ሁሉም የኢትዬጲያ ጉዳይ ያስጨንቀዋልና የወጋችን ማጠንጠኛ በልባችን ተሸክመን የምንዞራት ሀገራችን መሆኗ አልቀረም። ሁሉም ስለ ኢትዬጲያ ሲያስብ ሆድ ሆዱን ይበላዋል። ሁሉ ሞልቶ በተረፈበት ሀገር እየኖረ በሀገሩ ፍቅር ይጠማል። ይራባል። ጋር በተገናኘን ቁጥር አልፉና አሜጋችን ያቺ ማጭድ ለመዋስ የተዘጋጀች መዲናችን ሆናለች: - ያቺ! እትብታችንን የቀበረች... ከቄስ አስከ ኮሌጅ ያስበጠሰች፣...አፍቅረን የተፈቀርንባት... ወልደን የከበድንባት... የእናቶቻችንን መቃብር የያዘች ከተማ ።

እነዚህ የህይወት ገጠመኞች ሁሉም ሰው ቢጽፉቸው ራሳቸውን የቻሉ መጽሀፍት ይሆናሉ። አንዳንዶች ደግሞ ከግል አልፈው የሀገር ታሪኮች የሚሆኑበት አጋጣሚ አለ። የህይወት እጣ ፋንታ ሆኖ የእኔም ገጠመኞች ሀገራዊ ይዘታቸው ያጋድላል። አስገራሚ የሆኑ ቦታዎች ላይ ኖሬያለሁ።

በኢትዬጲያ ታሪክ ውስጥ ዳግም የመከሰት እድላቸው እጅግ ጠባብ በሆኑት ዝዋይ ህጻናት አምባ እና ጦላይ። በኢትዬጲያ ፓለቲካ ውስጥ መሳተፍ የጀመርኩት በወጣትነት የአፍላ ዘመኔ ነበር። በ21 አመቴ። ከአራት ኪሎ ዬንቨርስቲ ሳይንስ ፋክልቲ የመጀመሪያ ዲግሪ በማቲማቲክስ እንዳገኘሁ በመከላከያ ሚኒስቴር በሚገኙት አዳሪ ትምህርት ቤቶች በመምህርነት ተቀጠርኩ። ዉሎና አዳሬ ከቀድሞ ታጋዬች ቀጥሎም የኢትዬጲያ መከላከያ ሰራዊት ከፍተኛ መኮንኖች ጋር ሆነ። የአሁኖቹ ጀነራሎች እነ ፍስሀ መንጁስ፣ ወዲ መድህን፣ ወዲ ነ ጮ፣ አራንሺ ተማሪዎቼ ነበሩ። በተቋሙ የምንገኝ መምህራን ከአካዳሚው ስልጠና በተጨማሪ የሰራዊቱ ልሳን የሆነችውን "ወጋገን " ጋዜጣ የማወያየት ሀላፊነት ነበረብን። የጋዜጣዋ ትኩረት ወታደራዊና ፓለቲካው ስለሆኑ በተገላቢጦሽ መኮንኖቹ አስተማሪዎቻችን ነበሩ። እርስ በራስ የሚያደርጉት ክርክር ዲሞክራሲያዊ ይዘት ስለነበረው ይመስጠኝ ነበር። በተለይም ግርግዳ ከምጋራው ሜጀር ጀነራል ፍስሀ መንጁስ ጋር እስከ እኩለ ለሊት መወያየት ቀጠልን። ኢህአድግ በረሀ ላይ የጻፉቸውን ጽሁፎች ሳይቀር እንዳነበው አዋሰኝ። አብዬታዊ ዲሞክራሲን ያጠመቁኝ እነሱ ናቸው። ...

ይቀጥላል

አንድ ሺህ ማይል በአንድ እርምጃ ይጀመራል እንዲሉ ራሴው

ታይፒስትና ተያቢ በመሆን አዘጋጀሁት። ረቂቁን ለዳንኤል ሰጠሁት። ጊዜ ወስዶ በመጽሀፉ ይዘት፣ አቀራረብና የቋንቋ አጠቃቀም ላይ ሰፊ ሙያዊ አስተያየት ሰጠኝ። መስተካከል የሚገባውንም መስመር በመስመር እየለቀመ አስተካከለው። በመሆኑም የቅድሚያ ምስጋናዬ ለወንድሜ ዳንኤል ለገሰ ይሁን።

ከበሮ በሰው እጅ ያምር እንደሚባለው በዚህ መጽሀፍ ዝግጅት ላይ ብዙ ጊዜዬን ያጠፉው ታይፕ ማድረጉ ነበር። እናም የፈጀውን ጊዜ ይፍጅ ብዬ በራሴገባሁበት። በቀን አንድ ገጽ በመጻፍ የተጀመረው ረጅም ጉዞ አሁን የደረሰበት ደረጃ ደረሰ። ይህም ቢሆን ለቤተሰቤ ልሰጥ የሚገባውን ጊዜ ወስዶብኛል። ———— ይቀጥላል።

መታሰቢያነቱ : ለእናቶቼ እቴነሽ ቸርነትና ብዙነሽ በቀለ

(ከመቃብር በላይ በሆነው መስዋታችሁ ዘወትር እየዘከርናችሁ እንኖራለን!!)

ማዉጫ

ክፍል አንድ : የአርማጌዶ ዘመን (ምርጫ 92 ••• ምደባ 95)

ምእራፍ አንድ :

1• የህዝቦቿን ሉአላዊነት የተገፈፈች ከተማ

2• "ደህና ሰንብች መቐለ !"

3• ባህታዊ የመራው የካዛንችሱ መንግስት!

4• ዶንቦስኮና ሞንጆሪኖ!

5• ኢህአድግን ከአዲሳባ ያባረረው ምርጫ 92•••

6• "ህገ - መንግስት በጠረባ "

7• እውን ታሪክ እራሱን ደገመ ?

8• ዘባተሎው -ፕሬዝዳንት

9• የጥፋት ቅብብሎሽ : - ከመመሪያ ቁጥር አንድ ወደ ሁለት ወደ •••

ክፍል ሁለት : የሐማውያን ዘመን (ምደባ 95 •••ምርጫ 97)

ምእራፍ : " The Big Lie Theory ": የጉብልስ ትእዛዛት ማጠንጠኛ

1• ከተማ ቀመስ

2• ታጌላው

3• የስዬ ምስክር

4• ቆርኪው ሲላጥ

5• "ባንክና ታንክ "

6• " ጨነቀን ያየ በፊደል አይቀልድም!"

7• የጨረባ ተገኳር

9• ቀራንዬ !

10• ጉንጭ አልፉው ግምገማ : "ዉሻ በቀደደው•••"

11. ከንቲባነት በእጅ አዙር

ክፍል ሶስት : የተገላበጠው ድርጅትና አገራዊ አደጋ

1•

2•

3•

4•

ምእራፍ: የተስፉ ጉህ

1• የመዲናይቱ ወኪሎች

2• የተቃውሞ ድምጽ (Protesting Vote)

3• ኢህአድግን ያባረረው የኢህአድግ ጉባኤ

4• የቆሰለው ጅብ ተረት

እንደ መነሻ

አቶ በረከት በሁለት ምርጫዎች ወግ ብሎ በዓፈው መጽሀፉ ምእራፍ ሶስት ስር አዲሳባን በተመለከተ የሚመለከተውን ማዕከላዊ መልዕክት ዕፎ እናገኛለን:

"••• የአዲስ አበባን የምርጫ ውጤት እየሠማን ባለንበት ሠአት በከተማው ከተመደቡት ጓዶች አንዱ የሆነውና መልካም ሰራ በመስራት በቅንነትና በታማኝነት ሲፈጋ የከረመው ጓድ በአዲሳባ ውጤት ተበሳጭቶ ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ:: የአዲስ አበባ ህዝብ ለምን ይጠላናል የሚል ጥያቄ አነሳ:: አህአድጎች በአሰቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ሰናልፍም ቢሆን ፈተናውን ወገባችንን ጠበቅ አድርገን ማለፉችን የተለመደ ነው::ብዙውን ሰው የሚያደናግጡ ወይም የሚያሸብሩ ጉዳዪችን ፣ የኢህአድግ አባላት ሲሆን እንደ ቀላል አሊያም ጥርሳቸዉን ነክሣው ያልፉሉ እንጂ ማልቀሳቸውን የተለመደ አይደለም:: ••• የኢህአድግ አባላት ህዝብ በአንድ ወቅት በሚያሳልፉቸው ውሳኔዎች ወይም ከእኛ የተለዪ አቋሞች በመበራገግ ይህን የመሰለ መደምደሚያ ላይ አንደርሰም::እናም በቅንነቱ የሚታወቅና በጣም ታታሪ የሆነው ጓድ የነባሮችን ያህል በከባድ ፈተናዎች ውስጥ ያለፈ ስላልነበረ ያነሳው ጥርጣሬ እንደሆነ በመገንዘብ ለብቻ ወስደን ቀስ አድርገን ለማግባባት ጥረት ማድረግ ጀመርን::ህዝብ እንደማይጠላን በምርጫው አዲሳባ ላይ የተገኘው ውጤት በምንም መልክ የህዝብን ዘላቂ ስሜትና ፍላጎት እንደማያሳይ ልናስረዳው ሞክርን::ግድ የለህም ከአመት ሁለት አመት በኋላ የህዝቡን መንፈስ ታየዋለህ ብለን አጽናናነው:: በእርግጥም ሁላችንም ህዝቡን ወደእኛ መልሶ መምጣት የጊዜ ጉዳይ ብቻ እንደሆነ እናምን ነበርና::" ይላል::

ከዚሁ መፅሀፍ ምዕራፍ ሶስት (ድምፅ መስጠት፣ቆጠራና ያልተገመተ የምርጫ ውጤት) ከሚለው ርእስ ሳንወጣ በገፅ 104 ላይ የሚከተለው ተዕፎ እናገኛለን : -

" ••• ምርጫ 97 በአዲስ አበባና በአንዳንድ ትላልቅ ከተሞች የኢህአድግን መሸነፍ ቢያስከትልም በጠቅላላ የድምፅ ብልጫ ኢህአድግ አሸንፎ

የፌደራልና የክልል ምክር ቤቶችን አብላጫ ወንበሮች ሊቆጣጠር የቻለው በወሳኝነት በገጠር አርሶ አደሩ በሰጠው ድምፅ ነበር። የኢትዬጲያ አርሶ አደር የታደገው ግን ኢህአድግን ብቻ አይደለም። አርሶ አደሩ እንደገና አገሩንም ታደጋት... ተቃዋሚዎች አብዛኛውን የፓርላማ መቀመጫ ቢወስዱት ኖሮ የኢትዬጲያ እጣ ፈንታ ይህን ግዜ ምን ሊሆን እንደሚችል ለመገመት አይከብድም ።። "

***

በአቶ በረከት የሁለት ምርጫዎች ወግ መፅሀፍ ላይ አለ ሲራጅ ሳይጠቀስ ጓድ በሚል የወል ስም እንዲተካ ተደርጓል፣ አለ ሲራጅ የኦህዴድ ማእከላዊ ኮሚቴና የአዲሳባ ኢህአድግ ክንፍ ስራ አስፈፃሚ ነበር።... በእርግጥም አቶ በረከት እንደገለፀው አለ የምርጫ 97 ማታ " የአዲሳባ ህዝብ ለምን ይጠላናል?" የሚል ጥያቄ አንስቶ እንባዉን ረጭቷል፣...ይህ ልብ ኮርኳሪ ጥያቄ በእሱ ሳይወሰን ወደ መዲናይቱ የኢህአድግ ካድሬና አባላት ተሸጋግሮ በየመድረኩ የመዲናይቱ ህዝብ ይጠላናል የሚል ድምዳሜ ላይ ተደርሶ ነበር፣••• ከዛም አልፎ ህዝቡን ለመበቀል እንቅስቃሴ ያካሔዱ ካድሬዎች ራሳቸውን ባጋለጡ ወቅት ድርጊቱን ለመፈፀም ያነሳሳቸው የህዝቡን ጥላቻ በማየታቸው እንደሆነ ተናግረዋል፣... በተለይም የህውሀት ነባር ታጋይና የኮልፌ ካድሬዎች አለቃ የነበረው ነጋ በርሔ ግለሂስ ያደረገው በዘግናኝነቱ ይታወሳል። ...ነጋ, አቶ በረከት በሚመራው ግምገማ " እንባዬ የሚደርቀው አንድ ቅንጅት ስገድል ነው " በማለት በምርጫው ማግስት ሽጉጥ ይዞ ሲዞር እንደነበር በፀፀት ተውጦ ነግሮናል...

አቶ በረከት የየዋሁ አለ ሲራጅ ለቅሶ መንስኤ እንደ እነ ነጋ በከባድ ፈተናዎችና እሳት ተፈትኖ አለማለፉ እንደሆነ " *...በቅንነቱ የሚታወቅና በጣም ታታሪ የሆነው ጓድ የነባሮችን ያህል በከባድ ፈተናዎች ወስጥ ያለፈ ስላልነበር ...* " በማለት ይገልፀዋል። ይሁን እንጂ ምርጫ 97 የሀዘን ዕልማሞትና በቀል ገንፍሎ የፈሰሰው በነባሩ የኢህአድግ ካድሬ በተለይም የህውሀት ተጋዬች ላይ ሆኖ ሳለ ለምን አለ ተለይቶ ቀረበ የሚለው ትልቅ ጥያቄ የስነሳል።

በምርጫ 97 ማግስት አራት ኪሎ ኢህአድግ ቢሮ የሔድን ካድሬዎች የነበረውን አጋጣሚ እስከወዲያኛው አንረሳውም፣... ሁኔታው የኢትዩ _ኤርትራ ጦርነት ካለቀ በኃላ የነበረውን የመርዶ ዜና ያስታውሰናል ፣ ...

በ1993 አጋማሽ ላይ በኢትዬ - ኤርትራ *ጦርነቱ የሞቱትን የማርዳት ሂደት የተከናወነው የሰፈር ሰፋፊ ሜዳዎችን በመምረጥ (ጃንሜዳ ጨምሮ) በጅምላ ነበር ፣...የከተማዋ ወጣቶች ህልፈተ ህይወት አስደንጋጭ በሆነ መልኩ መዘገብ እየተገለጠ የተነበበበት... የጦርነትን መጥፎ ገፅታ !...አዲሳባ ማቅ የለበሰችበት ቀን ! በቡድን ደረት የተደለቀበት አሳዛኝ ወቅት !* ነበር።

በምርጫው ማግስት የሆነው ይህ ነበር፣ ..." በደማችን ያገኘነውን ስልጣን በትምክህተኞች ተነጠቅን " "ኢትዬጲያ አለቀላት "፣ "ኢንተርሀምዌይ በትግራይ ህዝብ ላይ ታወጀ "፣ "ሻዕቢያ በእጅ አዙር አሸነፈ "...የሚሉ አደገኛ ቃላት በእንባ ታጅቦ የተወረወረበት፣ ... ሴት ተጋዳሊቶች ከያሉበት ተጠራርተው በምጣት ነጠላ አዘቅዝቀው ሙሾ ያወረዱበት ፣ ዲሞብላይዝድ የኢህአድግ ወታደሮች በየቤታቸው የደበቁትን የጦር መሳሪያ ይዘው የወጡበት አጋጣሚ ነበር...

(**በነገራችን ላይ በአዲሳባ ከአስር ሺህ በላይ ዲሞብላይዝድ የሆኑ የህውሀት ታጋዬችና ከኢትዬ ኤርትራ ጦርነት በኃላ የተቀነሱ ወታደሮች ሲኖሩ በእያንዳዳቸው ቤት በነፍስ ወከፍ አንድ የጦር መሳሪያ ይገኛል። ...ይህ ቁጥር የአዲሳባ ፓሊስ ካለው በብዙ እጥፍ ይበልጣል።*)

ሀቁ ይህ ሆኖ ሳለ ለምን ኦህዴዱ አሊ ሲራጅ ብቻ ?

***

አቶ በረከት በሚሚሻ መፅሐፉ ላይ " የአዲሳባ ህዝብ አይጠላንም፣ ጠልቶንም አያውቅም " ሲል መጀመሪያ አካባቢ ከተዛባ ኢንፎርሜሽን ሊሆን ይችል እንደሆነ ተጠራጠርኩ፣... በቅርበት ከሚያውቁት ሰዎች አንዱ ስለሆንኩና ምን አይነት መረጃዎች እንደሚደርሱት ስለማውቅ ጭምር። ... ትንሽም ሳልቆይ በዚሁ መፅሀፍ ሌላ ክፍል ላይ "...እኛ ኢህአድጎች እንደ ህዝብ የምንፈራው የለንም ፣ ጌታችንም ህዝባችን ነው፣ ባለፉት አመታት በጐ ነገር በመስራት ሉአላዊ የስልጣን ባለቤት የሆነውን የአገሪቱ ጌታ ለማስደሰት ጥረት አድርገናል ... " የሚል ተፅፎ ሳነብ ደነገጥኩ። ... ስለ የትኛው ኢህአድግና ህዝብ እያወራ እንደሆነ ግራ ገባኝ ። እነዚህ ህዝብ የተባሉት ውስጥ በቅርብ የማውቃቸው የአዲሳባ ነዋሪዎች ፊት ለፊቴ ተደቀኑ... የአዲሳባ መከራና ብሶት ኖሬበታለሁ። ...ኢህአድግ የመዲናይቱን ነዋሪዎች በመናቅና በማዋረድ የሰራውን ወንጀሎች አይቻለሁ ፣... በከተማዋ ነዋሪዎች ላይ የተፈፀሙ ፀረ _ዲሞክራሲ ተግባሮች ተነግረው አያልቁም። የከተማዋ ችግር ከአመት አመት ሲባባስ እንጂ ሲሻሻል አይታይም።

በዘመነ ኢህአድግ ከቀድሞዎቹ አምባገነን መንግስታት በባሰ የመሬት ዝርፊያና ወረራ ተካሂዷል። ከመሬት ወረራው ጋር ብቻ በተያያዘ ከሀያ ቢሊዬን ብር በላይ የሚጠጋ የመዲናይቱ ህዝብ ገንዘብ ተዘርፉል። ... ለጆሮ የሚሰቀጥጥ ቢሆንም የህዝብ መሬት የተቸበቸበው የከተማዋን ማስተር ፕላን ሰርቆ በማውጣት ጭምር የተፈፀመ ነበር። የአሁኑ ጠቅላይ ሚኒስትር ሀይለማርያም ደሳለኝ ለዚህ እማኝ ይሆናል።...የፕላኑን ኮፒ ዱባይ ድረስ በመሔድ በአምስት ሚሊዬን ብር ገዝቶ ያመጣው እሱ ነበር።

በየጊዜው የተቋቋመው አስተዳደር ንቅዘት በሁሉም ዘርፎች የሚታይ ነበር : - በገቢ ማሰባሰብ፣ ህግን ያልተከተለ የግዥ አገልግሎት፣ የፍትህ እጦት፣ በብልሹ አሰራሮች ምክንያት የነዋሪው መንገላታት የደረሰበት።

***

አቶ በረከት በመፅሀፉ ውስጥ የአዲሳባና የሀገሪቷ ትላልቅ ከተማ ነዋሪዎች በምርጫ 97 ተቃዋሚን መምረጣቸው ሀገሪቷን አደጋ ላይ ጥለው እንደነበር በወቀሳ መልክ አቅርቧል።...እነዚህ የከተማ ነዋሪዎች ኢህአድግን ብቻ ሳይሆን የኢትዮጲያን እጣ ፋንታ አጨልመውት ነበር ብሏል።... ገበሬው ባይኖር ኖሮ በከተማው ህዝብ ውሳኔ ምክንያት ኢህአድግ ብሎም ኢትዮጲያ እንደ ሀገር የመቀጠል አጣብቂኝ ውስጥ ይገቡ እንደነበር ትንቢቱን ነግሮናል፣... አርሶ አደሩ ኢህአድግን መርጦ ሀገሩን በድጋሚ ስለታደገ ምስጋና እንደሚገባው አስገንዝቧል ...

መጀመሪያ የከተማ ህዝብ አጥፍቶ አርሶ አደሩ የታደገው መቼ እና የት እንደሆነ ባይገልፅልንም!

በዚህ የአቶ በረከት አገላለፅ ውስጥ በርካታ ቁምነገሮችን ማንሳት ይቻላል...ኢህአድግ በምርጫ 97 አሳካዋለው ብሎ ያስቀመጠው አላማና ግብ ፣... የኢህአድግና ኢትዮጲያ መሳኪ እድል ተጃምለው የቀረቡበት ምክንያት ፣... የኢትዮጲያ ገበሬና ከተሜ ለሀገራቸው ያነገቡት ራእይና ተግባር በተቃራኒው የሚጓዝ እንደሆነ...

ምርጫው ፍፅም ዲሞክራሲያዊና እንከን የለሽ እንደሚሆን፣ ...ማንኛውም ዜጋ የመሰለውን መምረጥ እንደሚችል ፣... ውጤቱ ምንም ሆነ ምን በፀጋ መቀበልና በጋራ ለመስራት ዝግጁ መሆን እንደሚያስፈልግ...የምርጫውን ዲሞክራሲያዊነት የሚያደናቅፍ ስራ ሰርቶ የተገኘ ካድሬ ሀላፊነቱን ራሱ እንደሚወስድ ያስጠነቀቀን እሱ ነበር፣... በመላ ሀገሪቱ ለሚገኙ አባላትም የስነ - ምግባር መመሪያውን በፕላዝማ ያሰለጠነው ራሱ በረከት ስምኦን ነበር።

ይህንን ተከትሎ በከተማ የሚኖረው ህዝቡ የፈለገውን መረጠ ፣... በገጠር የሚኖረውም እንዲሁ! ... የምርጫው ውጤት የሀገሪቷን የዲሞክራሲ ጉዞ አፋጠነው እንጂ ህልውናዋን አልተፈታተነም።... ከተሜው ኢትዮጲያን የማጥፋት፣ ገጠሬው ደግሞ የመታደግ ሚና ይዘው በተቃራኒ አልተንቀሳቀሱም... ይህ ለሰሚ ግራ የሚያጋባ አመክንዬ ነው፣... ባይሆን አሁን ባለንበት የስልጣኔና መረጃ ዘመን በከተማ የሚወሰዱ እርምጃዎች የገጠሩ ህዝብ በተመሳሳይ ይከተላቸዋል... የኢትዮጲያም አርሶ አደር ከዚህ ውጭ አይደለም፣... የመረጃ ፍሰቱ ከከተማ ወደ ገጠር የሚሆንበት አድል ለብዙ አመታት ተጠናክሮ ይቀጥላል።... በመሆኑም አሁን ባለችው ኢትዮጲያ : -የከተሜው አፍንጫ ሲመታ የገጠሬው አይን ያለቅሳል ... ገበሬው ሲራቆት ከተሜው ይራባል...

አንድም ሁለትም ናቸው።

በመሆኑም የከተሜው ህዝብ ለብቻው የኢህአድግና ኢትዮጲያ ጠላት ተደርጐ የሚወሰድበት እድል የለም፣ ... በተለይም እንደ አዲሳባ ያሉ ከተሞች አሳማኝ የሆነ ፓለቲካዊ ምክንያቶች እንዳላቸው እየታወቀ ሀላፊነት በጐደለው ሁኔታ የተገለፀውን በትክክለኛ ምስሉ ማሳየት የዜግነት ግዴታ ይሆናል።

በመሆኑም የዚህ መፅሀፍ አላማ በዝች ባለቤት አልባ በሆነች ከተማ ተዛብቶ የቀረበውን ታሪክ በትክክለኛ ገፅታው ማሳየት ይሆናል። ...ይህ መጽሀፉ የአዲሳባ ህዝብ ኢህአድግን የጠላው በተጨባጭ ምክንያቶች ላይ ተመስርቶ መሆኑን በመረጃዎች ላይ በመመስረት ለማሳየት ይሞክራል።...የአዲሳባና አህአድግ መፋታት ከጥላቻ በዘለለ የአይዲኦሎጂና መርህ ልዮነት መሆኑን ለመግለፅ ጥረት ያደርጋል። የዚህ ማስታወሻ ፀሀፊ ኢህአድግ በመዲናይቱ ከሞግዚትነት ያለፈ ሚና እንደማይኖረው ለማመላከት ይሞክራል።

አቶ በረከትን ጨምሮ በሱ መፅሀፍ ላይ ድርሻ ያላቸው ሰዎች ከስሜት በፀዳ መልኩ እንደሚያነቡት ተስፉ አደርጋለሁ፣ ...እያዘጋጅ ባሉት ቁጥር ሁለት መጽሀፍ ላይ ማረሚያዎችን በማድረግ እንደሚጀምሩ ምኞቴ ነው። ... ከእንግዲህም እውነትን ዋጋ ከማሳጣት እንደሚቆጠቡ ተስፉ አደርጋለሁ...በዚህ ሀቅ ላይ ተመስርተው ይቅርታ የሚጠይቅ ልቦና መፍጠር ከቻሉ ደግሞ የኢትዮጲያ ትንሳኤ ይበሰራል ፣ ...ይቅርታ ለእርቀ ሰላም የመጀመሪያ እርምጃ ነው ...

ከህሊና ቁስል ይፈውሳል ፣ ራስን ያነፃል...

ይቅርታ የትላንትን መጥፎ ግንኙነት ለታሪክ ትቶ ዛሬና ነገን "በለውጥ ተሀድሶ ፈረስ "በጋራ ለመጓዝ በር ይከፍታል ። ሁልጊዜም መኖር ያለበት ፓለቲካ ልዩነቱ እንዳለ ሆኖ!...

ይቅርታ የአርቆ አስተዋይነትና በራስ መተማመን ምልክት ነው...ጊዜም አያልፍበትም!

የዚህ መፅሀፉ ግብም ይህና ይህ ብቻ ነው።

" ሰው ሰውን ለመጉዳት ገፍ የሚሆንበት ጊዜ አለ ! "

(መክብብ 8:9)

ምእራፍ አንድ: የአርማጌዶን ዘመን

ወይ አዲስ አበባ ወይ አራዳ ሆይ ፣
አለ አሊ አብዶ አላየሽም ወይ።።

(ሪፓርተር ጋዜጣ)

የህዝቦቿን ሉአላዊነት የተገፈፈች መዲና!

ቦሌ መንገድ የሚገኘው የኦሮሚያ ምክር ቤት (ጨፌ) ለአስቸኳይ ስብሰባ በመጡ የመዲናይቱና እንግዳ ካድሬዎች ተጨናንቋል፣ ሁሉም ጥጋጥጉን ይዞ ያወራል፣...አጀንዳው ስላልተነገረ ብዙዎች መላምት ይሰጣሉ...ውስጥ ያውቃሉ የተባሉት ደግሞ በየቦታው ተከበዋል።... የአዲሳባ ቻርተር ለመተግበር እንቅስቃሴዎች በመጀመራቸው ምክንያት በከተማው ብዙ ወሬዎች ተናፍሰዋል፣... የተወሰኑ ሚስጥሮች ሾልከው ወጥተዋል:-...

የከተማው ኢህአድግ መዋቅር እንደሚፈርስ፣የካቢኔ አባላት ፕሬዝዳንት አሊ አብዶን ጨምሮ እንደሚባረሩ፣ የሚታሰሩ ባለስልጣናት እንደተለዩ... የካድሬው ሹክሹክታና መነጋገሪያ ከዚህ አልዘለለም፣ ... ወሬ የተራበ ካድሬ! ... ሁሉ ነገር ሚስጥር በሆነበት ፓርቲ ውስጥ መኖር የመረጃ ረሀብተኛ ያደርጋል። በዛ ላይ ፀጉረ ልውጦች መታየታቸው ውጥረቱን አባብሶታል።...

የአቶ አሊ ከሰልጣን መባረር ሁሉም በጉጉት የሚጠብቀው ነበር። በብዙዎች ዘንድ የአሊ አብዶ የስልጣን ወቅት "የአርማጌዶን ዘመን" በመባል ይታወቃል። ...ሌጋሲዉ በህዝቡ ጫንቃ ላይ ተጣብቆ እንደከረመ መቸርገር ሊታሰብ የሚችል ነው ፣ የዘረጋው ኔትወርክ ጥፋትን በጥፋት እያረመ በማያቋርጥ የወንጀል ኡደት ዉስጥ እንዲጓዝ ያደረገ ...

የጨለማ ዘመን !

ወደ ስብሰባው አዳራሽ እንድንገባ ተነገረ።

... አቶ አሊ አብዶና አባይ ፀሀዬ ወደ መድረክ ወጡ፣...አሊ የሰብሰባው አላማ በልማትና ፓለቲካ ስራ ያለፉትን ሁለት አመታት ለመገምገም የተጠራ መሆኑንና በከተማዉ የተናፈሰው ወሬ ከእውነት የራቀ እንደሆነ ፣ የጥፋት ሀይሎች እንዳሰራጩት አስረዳ (*በአሊ አብዶ መዝገብ ላይ የጥፋት ሀይሎች ተብለው ከተጠቀሱት ውስጥ ግንባር ቀደሙ ንግድ ም/ቤት ሲሆን ተከታዩ የኦርቶዶክስ ሀይማኖት ተቋም ነው።) ...*በድርጅቱ አሰራር መመሪያ መሰረት ምደባና ሽግሽግ የሚካሔደው ከግምገማ በኃላ እንደሆነ አብራራ።...መድረኩን የሚመሩት እሱ ፣ምክትል ፕሬዝዳንቱ ደሳለኝ ሸሹና አባይ ፀሀዬ እንደሚሆኑ ተናገረ።

ደሳለኝ ሸሹ ከቀናት በፊት ሶስት ጉልቻ መስርቷል፣ ... የደሳለኝን ደመቅ ያለ የጋብቻ ድግስ በልተናል። ... ድምቀቱን በመገምገም ስጋው ተቦጭቋል። ... እሱም ዋዛ አይደለም የቀረበበትን ሀሜት ወደ ጉን ትቶ ደስታውን በማራዘም ለጫጉላ ሽርሽር ባህር ማዶ ተሻግሯል። ... የሆዱን ሳናውቅ " ከሳምንት በህዋላ ሂሱን በሀኒ ሙን ሙድ ያወራርዳል " ብለን ተሳለቅን ...የአራዳውን ልጅ! ...ያውም የልደታ! ...ደሳለኝ ሸሹ ሸሸ! ...ሒሳቡን በአሜሪካ ሬዲዬ ጣቢያ አወራረደ...

አባባሉስ ቢሆን "የትም ተወለድ ልደታ እደግ !" አይደል።

***

"መዲናችን እናድሳት" የሚለው ሰነድ በጨፌው ለተሰበሰብን ካድሬዎች ተበተነ... በተናጠል እንድናነብ ሙሉ ቀን ተሰጠ። ...ሰነዱ በከተማዋና ካድሬዎቿ ላይ ውርጅብኝ ነበር...

ሠድቦ ለሠዳቢ የሚዳርግ ...

መዲናይቷን በተመለከተ " በማያቋርጥ የማሽቆልቆል ጉዞ የምትገሰግስ የበሰበሰች ከተማ"; ..." በድህነት የተተበተበችና እርቃኗን የቀረች መዲና"; ..."ከበግ ጉረኖ ያልተሻሉ ቤቶች የተከማቹባት..."..." የአፍሪካ ማፈሪያ "... በአጠቃላይ ወደ አሳዛኝ የቁራ አሟሟት እያመራች ያለች ከተማ...አዲስ አበባ!!... በተመሳሳይ የመዲናይቱ ካድሬዎች ላይ ግርፊያ ቀረሽ ስድብ ተጽፎአል።... አንዳንዶቹ የወረዱ የመንደር ቧልቶች ናቸው፣ መረን የለቀቁ መደዴዎች...

"ስራ ተብሎ የተሰጠውን መስራት የማይችል _ዳተኛ!"...

"በረዶ ፊቱ ላይ ተረጭቶበት የማይነቃ_እንቅልፋም!"...

"የሰው ሰጋ መብላት የቀረው_ ማሽንክ!"...

" ከኪሎው በላይ ወሮ የሚበላ _አንበጣ!"...

"ተነሳ ሲሉት የሚነሳ ፣ተኛ ሲባል የሚተኛ _አድርባይ!"...

"የራሱ ሀሳብ የሌለው _ቱቦ "..."አስኳላ የሚጠላ_ የፊደል አርበኛ!"...

"ሲሾም ያልበላ ሲሻር ይቆጨዋል በሚል መርህ የሚመራ– ቀማኛ!"...

በነበረን የምሳ ሰአት ካድሬዎች ምን እንደተሰማቸው ይጠያየቃሉ። ...በአብዛኛው ተመሳሳይነት ያላቸውን አስተያየቶች ይሰጣሉ።

አንደኛው "በሠነዱ ላይ የተቀመጠው ሀቅ ቢሆንም እንደዚህ እስኪሆን ለምን ተጠበቀ?"፣...

ሌላኛው "የተጠያቂነቱን አንበሳ ድርሻ ሰነዱን ያዘጋጀው ክፍል መውሰድ አለበት?"፣...

ደሞ ሌላው " ትምህርት ቤት በመመራያ እንዳትገቡ ተብሎ ፣ በድፍረትም የገቡት ለመቀጣጫ ተባረው ዛሬ እንዴት መገምገሚያ ይሆናል? "...

በተለይም አንዱ ካድሬ በተበሳጭ አንደበት " ይህ ሰነድ በአፍሪካ ህብረት ስብሰባ የሴኔጋሉ ፕሬዝዳንትና መሀመድ ጋዳፊ አዲሳባን በተመለከተ ካቀረቡት ሪፓርት በምን ይለያል ?" በማለት ሲናገር ሰምቼ ቀልቤን ሳበው። ...እነዚህ ፕሬዝዳንቶች የአፍሪካ መዲና መቀየር እንዳለበት ሽንጣቸውን ገትረው የተከራከሩት ከላይ የቀረቡት በከተማዋ የታዩት ችግሮችን በመጥቀስ ነበር። ... እነ ጋዳፊ የኢትዬጲያን ታሪካዊነት አልካዱም።... ቀኝ ገዥዎችን ማንበርከካችንን በተለያዩ ወቅቶች ገልጸዋል፣ ...በተባበሩት መንግስታት ብቻችንን እንደነበርን አልዘነጉትም፣... ኒልሰን ማንዴላን ማሰልጠናችንን እንዲሁ።... እነሱ የተከራከሩት የማይካዱ ሀቆች በማንሳት ነበር። ...ጋዳፊ ከፍተኛ የአክሲዬን ባለቤት በሆነባቸው አለም አቀፍ ሚድያዎች ሳይቀር ዘመቻውን በመረጃ በማስደገፍ አጧጡፎት ነበር።... በመዲናይቱ የበሰበሱ አካባቢዎችን ፣ ...በከተማዋ የሚገኙ ሆቴሎችየብዛትና ጥራት ችግር፣ ...የጐዳና ተዳዳሪዎች፣...የህዝቡን የጉስቁልና ደረጃ፣...የጸጥታ ስጋት...ወዘተ የሚያሳዩ ዶክመንተሪዎች አ ንዲዘጋጅ ድጋፍ በማድረግ በአለም ዙሪያ አ ንዲታዩ አድርጓል። ...

ለዚህም ነው አቶ መለስ ያቀረበው መከራከሪያ ውሀ አይቋጥርም የተባለበት... የቀድሞ ታሪክና ወቅቱ የሚጠይቀውን ይዞ መገኘት እርስ በራስ ይመጋገባሉ።... እነ ጋዳፊ አሁን ላይ ተመስርተው "አዲሳባ የፀጥታ ስጋት አለባት "ሲሉ፣ ...አቶ መለስ ወደ ድሮ ሐሌዶ (ድሮን ይወድ ይመስል!) " በተባበሩት መንግስታትና ፀጥታው ምክርቤት ብቻችንን ነበርን" ይላል፣...እነሱ ዛሬ ላይ ሆነው "አዲሳባ አለም አቀፍ ስብሰባ ለማስተናገድ አቅም የላትም" ሲሉ ፣ አቶ መለስ ደግሞ ሰገሌን ጐትቶ "ሙጋቤንና ማንዴላን ያሰለጠነው ማነው ንጉሱና መንግስቱ አይደሉምን?" የሚል ምላሽ ይሰጣል...ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ እንዲሉ!...

ደግነቱ መሪዎቹ የአፍሪካ ናቸው!!...

***

መዲናችንን እናድሳት የሚለውን ሰነድ አንብቦ የጨረሰ እንዲሔድ ስለተፈቀደ አጠገቤ ከነበረው ፍስሀ ዘሪሁን (መአሲ) ጋር ተያይዘን ወጣን። ...ፍስሀ የቅርብ ጓደኛዬ ነበር፣...በየጊዜው እየተገናኘን በሀገርና ግል ጉዳዬች በግልፅ እንጫወታለን፣...የወዳጅነት መንፈሳችን እድሜ ፣ዘርና የስልጣን እርከን አለያየውም ... ፍስሀ ማንኛውም ሰው ቀርቦ ሊያናግረው የሚችል ቀላል ሰው ነው። ...ነገሮችን ከስር መሰረቱ ገላልጦ ማየት ባህሪው ነው።...ሰውን በሰውነቱ የሚመዝንና የሰዎችን ጥቃት ማየት የማይፈልግ ነበር። ከህውሀት ካድሬዎች በተለየ መልኩ አዲስ ነገሮችን ለመስማትና ለመቀበል ዝግጁ ነው... አልተቸነከረም!

"ተከርቸም" የሚባለው ግምገማ ገብቶ ሰለነበር ለሁለት ሳምንት አልተያየንም።... ተከርቸም በኢህአድግ ውስጥ ጫፍ የደረሰ ዝግ ስብሰባ ነው።...እንደ አቶ በረከትና አባይ ፀሀዬ የመሰሉ ፕሮፌሽናል ገምጋሚዎች ይመሩታል።... አጀንዳዎቹ በጥብቅ ሚስጥር ይያዛሉ፣ ተሰብሳቢዎች ከማንም ጋር ግንኙነት እንዲያደርጉ አይፈቀድም።...እንደዚህ አይነት አሰራሮች በህዉሀት የተለመዱ ናቸው... በተለይ በአደጋ ጊዜ (*የኢትዬ_ኤርትራ ጦርነት ውሳኔዎችን የህውሀት ስራ አስፈፃሚ ብቻ በተከርቸም እንደወሰነ ልብ ይሏል*።)

ፍስሀ መአሲ አዲሳባን በንብረትነት ከተሰጣቸው ሶስት የህውሀት ነባር ታጋዬች አንዱ ነበር። ካዛንችስ በሚገኘው አዲስአባ ኢህአድግ ጽ/ቤት በመቀመጥ፣ ... ፍስሀ አካዳሚክ እውቀቱ ጠለቅ ያለ ነው፣ ማንበብ በአሉ ነው። ጐበዝና ታታሪ ። ...በአጭር ጊዜ ውስጥ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ ገብቶ በኢኮኖሚክስ የመጀመሪያ ዲግሪ አግኝቷል። ትምህርቱን የተከታተለው በኢህአድግ ቢሮ ስልጠና ክፍል በተደራቢነት እየሰራ ነበር። ...የሰልጠና ስራው በየክልሉ እየሄደ አብዬታዊ ዲሞክራሲን ማጥመቅ ነበር... የኦሮሚያ ፕሬዝዳንቱን አለማየሁ አቶምሳና የፕሮፓጋንዳ ካድሬው አበራ ሀይሉ ኮትኩቶ ያሳደጋቸው እሱ ነው ... ቅርርባቸው ዘር ሳይገድበው የወንድም ያህል ሆኗል...

የህውሀት ለሁለት መሰንጠቅ በፍስሀ ፓለቲካ ህይወት ላይ መጥፎ አሻራ አሳረፈ።... የእነተወልደ ቡድን አባል በመሆንና ስምሪት ከአባይ ፀሀዬ በመውሰድ የአዲስአባን ህውሀት አባላት በፀረ– መለስ ሲያደራጅ ከነበሩት ቀንደኛው እሱ ነበር።...አፍታም ሳይቆይ ተልኳኮ ሲሰጠው ከነበረው አባይ ፀሀዬ ጋር መለስን ይቅርታ ጠይቆ ተመለሰ። ...ፍስሀ ከመለስ በላይ አባይ ላይ ልዩ እምነት አለው። የማይጠርቁት ሚስጥር የለም።... ሲርበው እንኳን ወደ አባይና ሚስቱ ሞንጆሪኖ ይሄዳል... እሱ የጡት አባቱ ፣ እሷ ደግሞ እናቱ ናት።

ፍስሀ በታጋዩ ዘንድ "መአሲ" በሚል በረሀ ስሙ ይታወቃል። ። ...መአሲ ማለት በትግርኛ የለፉ ቆዳ እንደሆነና ከሲታ መሆኑን ለመግለፅ እንደተጠቀሙበት አጫውቶኛል። ...

ርግጥም አንጆቱ የታጠፈ ነው...

ደቃቃ!

ከራሱ አልፎ የሰው አምሮት ይዘጋል፣ ሳይበላ ይጠግባል ...በውሀው አካባቢ ግን አይታማም። በተለይ ቅርብ ከሚላቸው ሰወች ጋር መጠጣትና መጨፈር ይወዳል። ...ለዚህም ነበር ከጨፈ ተጠቃቅሰን የወጣነው ።...በዛ ላይ ተከርቸም በመሰንበቱ ቋንጣ ያልሆኑ ወሬዎች አ ጁ ላይ አሉ ።...በስልክ እየተካሔደ በነበረው ግምገማ ደስተኛ እንዳልሆነ ጠቆም አድርጐኛል። ላለማስጨነቅ ብዙ አላነሳሁበትም።... አሁን ግን ስብሰባው ስላለቀ ጸሊያወጋኝ እንደፈለገ ገብቶኛል።...ተያይዘን ወደ ለመድነው ሜክስኮ ራስ ሆቴል ሔድን።

...ፍስሀ ቁመናው ተዳክሟል።...የመኪናውን መሪ እንኳን ማሟዟር አቅቶታል... አስር ጊዜ የቀኝ እጆቹ መሪውን ይደበድባሉ... ፊቱ ላይ የጭንቀት መስመሮች ተሰምረዋል...የተናደደበት ነገር እንዳለ ያስታውቃል።... ሆቴል እንደደረስን መጠጥ ብቻ አዘዘ ...አጠጣጡ ከወትሮው የተለየ ሆነብኝ፣...ያለ ትንፋሽ ይጋተዋል ።...

ለረጅም ጊዜ አቋርጦት የነበረውን ሲጋራ በየደቂቃው ይጠጣል።

" ፊሽ !ግምገማው የተስማማህ ይመስላል የበለጠ ሸንቀጥ አድርጐሀል።" አልኩት።

" ልትጠፉ ነው ማለት ከብዶህ ነው?"

"ከሚጠፉት ወገን እንዳልሆንክ እያወቅኩ " ቀለድኩበት።

"ሊያጠፉኝ መጥቶ እያየሁ ?"

" ማነው? "

" አዲሱ ከንቲባህ...አርከበ እቁባይ !"

"እየተወራ ያለው እውነት ነው እንዴ?"

" ምን በሌለበት አይሸትም ሲባል አልሰማህም።"

" የሚሆን ነገር ስላልመሰለኝ ነው። እንደምታውቀው የከተማው ቻርተር ከንቲባ የሚመረጠው ከምክር ቤት አባላት ውስጥ እንደሚሆን ይደነግጋል።" የሚያውቀውን ደገምኩለት።

" አንዱ ያበሳጨኝ ይህ ነው። ለመጽደቅ በተዘጋጀው አዲሱ ቻርተሩ ላይ ፓርላማው ምክር ቤቱን መበተን እንደሚችል ተቀምጧል።... የምክርቤቱ የአይን ቀለም ካላማረው ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ያፈርሰዋል። ይህ ፍጽም ፀረ ዲሞክራሲ ነው። ...የህዝቦችን ሉአላዊ መብት ይጥሳል። ...ከአራት ሚሊዬን በላይ የአዲሳባ ህዝብ ይመራኛል ብሎ የመረጠውን ምክርቤት ከሌላ ቦታ ተመርጦ የመጣው ሲበትነው።"

" ፊሽ! እንደዚህ ማድረጉ! ለምን አስፈለገ? "

"ድርጅቱ በመርህ መመራት አቁሟል።... ከውስጥ ሊመጣ የሚችለውን እሳት በመፍራት የህዝብ መብት መደፍጠጥ ስራዬ አድርጐታል።" ...

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የኢህአድግ ከፍተኛ ካድሬዎች ድርጅቱ ብለው ሲጠሩ አቶ መለስ ማለታቸው ሆኗል።... የአቶ መለስ የወል ስም "ድርጅቱ " ነው። ...አቶ መለስ ራሱ አንድ ነገር ሲፈቅድ "ድርጅቱ ፈቅዷል" ሲከለክል ደግሞ " ድርጅቱ አልፈቀደም" ይላል።

" ስለዚህ ምክር ቤቱ ሊበተን እንደሆነ እየነገርከኝ ነው?... የኢህአድግ አባላት ይሁን ፣ከ30 በላይ ህዝብ የመረጣቸው የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት እንዳሉበት ለምን ግምት አይገባም!" ጠየኩት።

" የምክርቤቱ ጉባኤ ተጠርቶ በክብር ይሰናበቱ የሚል ሀሳብ ቀርቦ ነበር። ...ድርጅቱ አልተቀበለውም...መልስ የሌላቸው ጥያቄዎች አንስተው ያጋልጡናል የሚል ፍራቻ አለው"

" ምን ጥያቄ ይኖራቸዋል?"

" የምክር ቤት አባላት ተጠያቂነታቸው ለህገ መንግስቱ፣ ለመረጣቸው ህዝብና ለህሊናቸው ነው።"

" ይህ የሚሰራው ለፓርላማው ብቻ እነዳይሆን..."

" ፓርላማ ሆነ!... ክልል ሆነ!...አዲሳባ ምን ልዩነት አለው? ... ህዝቡ ይሆነኛል ያለውን ከመረጠ ሳያቅማሙ መቀበል ነው።"

" ፊሽ! ከአሊ አብዶ እንኳንም ህዝቡ ተገላገለ።"

" እኔ እያነሳው የለሁት ከእሱ ጋር የተያያዘ አይደለም።... እሱ መጀመሪያም ህዝቡ እንዳልመረጠው ድርጅቱ የውቃል"

" ረስቼው! ሊያጠፉኝ ስትል! ምን አዲስ ነገር አለ?"

" ወደ ድሬደዋ በቅርብ እኔም ምድብ ከንቲባ ሆኖ እንደምሔድ አባይ ነገረኝ።"

" ለምን ድሬደዋ?"

" አህዴድና ሶህዴፓ በየኔናት ጥያቄ ተፋጠዋል። ... እስካሁንም ምላሽ አላገኘም። ድርጅቱ ገለልተኛ ይምራት ብሎ ወስኗል።"

ከፍስሀ ጋር በነበረን ቆይታ ብዙ ነገሮችን አንስተን ጣልን።...ወጋችን እንደ ጌንዱለም ሆነ። ...ኢህአድግን ከአዲሳባ ያባረረው ምርጫ 92፣...የካዛንችሱ ስውር መንግስት፣...ዶንቦስኮ፣...የአሊ አብዶ የጨለማው ዘመን፣...የአርከበ እቁባይ ወደ መዲናይቱ የመምጣት ሚስጥር፣... የአቶ መለስ በአንድ ድንጋይ ሶስት ወፍ ለምታት መዘጋጀት ጊዜያችንን ወሰዱ።

እኩለ ለሊት ሲቃረብ ቀሪ ወጋችንን ለይደር አቆየን። ያልፀደቀውን የከተማ ቻርተር በሚስጥር እንዳነበው ሰጠኝ።...ጉን ለጉን የተሰፉ ድርጅት የሚባል መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ፕሬዝዳንት የሆነው ዶክተር ህሩይ የሚመራው ኮሚቴ ተቋቁሞ ለመነሻ ያዘጋጀውን ቻርተር አይቻለሁ።... በብዙ ጉዳዬች ተመችቶኝ ነበር ፣ በተለይም የማዘጋጃ ቤት በከፍተኛ ሙያተኛ እንዲመራ ለማድረግ የቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ኢህአድግን የሚያስመሰግነው ነበር... ዶክተሩ ባቀረበው መሰረት ቢፀድቅ ለመዲናይቱ ስራ አስኪያጅ የሚሆን ሰው በአለም አቀፍ ደረጃ ማስታወቂያ ተለቆ በነፃ ውድድር ሙያና የቀድሞ ፕሮፉይል ላይ ያተኮረ ይሆናል...

ፓለቲካና ሙያ ለየቅል ይሮጣሉ!...

ወደ ቤቱ እየሔድኩ ድብልቅልቅ ያለ ስሜት ተሰማኝ ፣ ...በአንድ በኩል ለይስሙላ አጥኝ ቡድን እየተባለ በርካታ ገንዘብ ይፈሳል፣ በሌላ በኩል ድርጅቱ የራሱን ሰርቶ ለተመረጡ ካድሬዎችያሳውቃል...

ኢህአድግ መጀመሪያ አካባቢ የህዝቦች መብት ያለገደብ በሚል ባዘጋጀው

የሽግግር መንግስት አዲሳባን የክልልነት ስልጣን እንዲኖራት አድርጐ ነበር፣... ክልል 14 ።

ብዙም ሳይቆይ በህገ_ መንግስቱ ላይ ኢህአድግ በዘረጋው ዘር ላይ የተመሰረተ የክልል ስልቻ ውስጥ ማስገባት እንደማይቻል ሲያውቅ አዲሳባ የሁላችንም ናት በሚል ሒሳብ ክልልነቷን ተነጥቃ የፌደራል መንግስት ሆነች። ... ህገ _መንግስቱ መዲናይቱን የሚጨቁን የመጀመሪያው የቃል ኪዳን ሰነድ ሆኖ ተመዘገበ። ... ህገ_መንግስቱ በወረቀት ደረጃ ስልጣን በፌደራል ደረጃ እንዳይሰበሰብና ክልሎች ብሔር ተኮር መንግስት እንዲመሰርቱ ፈቅዶ ሲያበቃ አዲሳባን ነፈጋት። ... ይባስ ብሎ ህገ መንግስቱን የመተርጐም ስልጣን በተሰጠውና በሀገሪቷ ዋነኛው የዜሮ ድምር ማጫወቻ ተቋም በሆነው የፌዴሬሽን ምክር ቤት ውክልና እንዳይኖራት አደረገ።... የአዲሳባ ህዝብ አንድን ህግ ወይም ውሳኔን ህገ _መንግስታዊ አሊያም ኢ _ህገ መንግስታዊ ነው ብሎ በሚወሰንበት ቦታ ወንበር የለውም። ... የመዲናይቱ ህዝብም ሆነ መስተዳድሩ ኢፍታዊ ናቸው ብሎ የሚያምንባቸውን ነገሮች በቡድን የመቃወም እድል የለውም።

ቻርተሩ የአዲሳባን የወደፊት ራዕይና ግቦቿን ለማሳካት የምታደርገውን ፓለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴ ለማሳካት የምትመራበትእሳቤዎች ፣መርሆዎችና አደረጃጀቶች የሚደነገግበት የህልውና ሰነድ ነው። የአንድን ከተማና ህዝቦቿን ህልውና የሚወሰን ቻርተር ሲዘጋጅ ደግሞ መፈፀም ያለባቸው መሰረታዊ ጉዳዬች አሉ። ... በመጀመሪያ ደረጃ ቻርተሩ ሲረቀቅ የአዲሳባ ጉዳይ ያገባናል የሚሉ የህብረተሰቡ ተወካዬች ፣በተለያዩ ዘርፍ የተሰማሩ ምሁራን፣ የፓለቲካ ድርጅቶች፣ መንግስታዊ የሆኑና ያልሆኑ አደረጃጀቶች ፣ የንግዱ ማህበረሰብ አመራሮች ፣ መገኘት ይኖርባቸው ነበር: ... ለአዲሳባ ይህ መርህ አልሰራም !

ቀጥሎ የሚመጣዉ ጉዳይ በያገባኛል ባዬች የተረቀቀው ቻርተር የከተማዋ ባለቤት ለሆነው ነዋሪ እንዲመክርበት መቅረብ ነበረበት።... ከውይይቱ በኃላ ህዝቡ ሊካተቱ አሊያም ሊቀነሱ ብሎ ያመነባቸውን ቁምነገሮች በመጨመር ወይም በመቀነስ የባለቤትነት መንፈስ መፈጠር ነበረበት፣ ... ይህም ቢሆን አልተደረም... ሊደረግም አይችልም። ...ሂደቱ ግልፅና አሳታፊ ቢሆን በርካታ ፀረ ዲሞክራሲያዊ አንቀፆች አጣብቂኝ ውስጥ ይገባሉ... የኢህአድግ ዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት ይጋለጣል።

ወደ ቤቱ ስደርስ ረቂቅ ቻርተሩን ማንበብ ጀመርኩ፣ ...በመጀመሪያዉ ገፅ ቻርተሩን ማሻሻል ያስፈለገበት ምክንያቶች ዘርዘር ብለው ቀርበዋል : ከእነዚህ ውስጥ ቀልቤን የሳበው አዲሳባ የኢትዬጲያ ርዕሰ ከተማ፣ የአፍሪካ ኅብረትና የተለያዩ አለም አቀፍ ተቋማት መቀመጫ በመሆኗ፣ ... የአዲሳባ ነዋሪ ራሱን በራሱ የማስተዳደር ሙሉ ስልጣኑን እንዲጠቀም ለማስቻል፣...የአዲሳባ ከተማን አደረጃጀትና አመራር ከዲሞክራሲያዊ መርሆዎችና ከመልካም አስተዳደር ስርአት መርሆዎች ለማጣጣም የሚሉት አንቀፆች ነበሩ።

ከዚህ በተጨማሪም የፓለቲካና የማዘጋጃ ቤት ሙያዊ ስራዎች ተነጣጥለው እንዲሄዱ ፣ የስራ አስኪያጅነት ምደባ በከተማ አመራር ሙያዊ ብቃት ላይ

የተመሰረተ እንአሚሆን፣ ...በከተማዋ የሚካሔደውን ሌብነት ለመቀነስ የአዲሳባ ፀረ - ሙስና ኮሚሽን እንደሚቋቋም ታሳቢ መደረጉ ለከተማዋ መለወጥ ተስፉ እንድጨብጥ አደረገኝ።

ቻርተሩን ዘልቂ ማንበብ ስቀጥል በዝርዝር የተጠቀሱት ቁም ነገሮች በመግቢያው ከተቀመጡት የሚጣሉ ናቸው : ... የከተማውን ነዋሪ መብት በመንጠቅ የአዲሳባ ምክር ቤት በፓርላማ ሊበተን እንደሚችል ይገልፃል።...የሚፈርስበት ምክንያት ደግሞ ህገ _መንግስቱን አደጋ ላይ የሚጥል ተግባር በከተማው ምክርቤት ሲፈፀም ወይም የከተማው አስተዳደር ፀጥታና ድንገተኛ ሁኔታን መቆጣጠር ሲያቅተው አንደሆነ ያትታል።... ይህ ከመዲናይቱ ህዝብ ሉአላዊነት ጋር የሚጋጭ ነው።... የከተማዋ ህዝብ ሉአላዊነት (ፓለቲካዊ) ተረጋግጧል የሚባለው ነዋሪዎቿ የመጨረሻውን የወሳኝነት ስልጣን ባለቤቶች ሲሆኑ ነው፣... ፓለቲካዊ ሉአላዊነት የህዝብ ስልጣን እየተለካ የሚሰጥ ሳይሆን ከራሱና መራጩ ህዝብ የሚመነጭ ነው።... በተጨባጭ የታየው ግን የከተማው ህዝብ የሚያስተዳድሩትን ተወካዬች የሚመርጥበት ፣ ሲያሻው ደግሞ የሚሸርበት ስርአት ተሸራርፉል...

(*** ከምርጫ 97 ውጤት በኃላ በአዲሳባ ኢህአድግ እንዴት ይቀጥል የሚለውን ለመወሰን ሶስት ቡድኖች ተቋቁመው ጥናት በማካሔድ የተናጠል ውሳኔ አስተያየት አምጥተው ነበር።... ከእነዚህ ቡድኖች አንዱ የሆነውና በአርከበ እቁባይ የሚመራው ቡድን ይህንን ጊዜ ጠብቆ እንዲፈነዳ የተዘጋጀ አንቀፅ በማጣቀስ ፣ ቅንጅት መዲናይቷን በተረከበ በሁለት አመት ውስጥ የተለያዩ አመፃችን በማስነሳት ፀጥታውን መቆጣጠር አልቻሉም ብለን የከተማውን ምክር ቤት በፓርላማ እንበትነው የሚል አማራጭ አቅርቦ ነበር። ... የሚገርመው ነገር ቅንጅት ሊወነጀልበት የተዘጋጀው የፀጥታ ችግር ለእሱ ተጠሪ ካልሆነው ከፓሊስ ጋር የተያያዘ መሆኑ ነበር።***)

...ቻርተሩ የአዲሳባ ፓሊስ ኮሚሽን ተጠሪነትን ለፌዴራል ፓሊስ ኮሚሽን ሰጥቷል።... የከተማው ፓሊስ ኮሚሽነርና ምክትል ኮሚሽነር የሚሾሙት በከንቲባው ሳይሆን በፌዴራል ጉዳዬች ሚንስትር እንደሚሆን ይገልፃል።... ይህም መዲናይቷ የእኔ የምትለው የፓሊስ ሀይል እንዳይኖራት ያደረገ ታሪካዊ ሰነድ ሆኖ ተመዘገበ ... አስቂኙ ነገር ለከተማው ህዝብ በቀጥታ ተጠሪ ያልሆነው ተቋም አጠቃላይ በጀቱ ፣ ደሞዙን ጨምሮ የሚመድበውና የሚከፍለው የከተማው ነዋሪ ነው።

ቻርተሩ በጥቃቅን ጉዳዬች ሳይቀር አስተዳደሩን ስልጣን ነፍጓል ፣... የከተማው አስተዳደር የፌዴራል መንግስት ካልፈቀደለት በስተቀር ከሀገር ውስጥ የፋይናንስ ምንጮች መበደርም ሆነ የዋስትና ሰነዶችን በመሸጥ ሊበደር አይችልም ፣... የአለም አቀፍ የገንዘብ ምንጮችን አፈላልጐ ቢያገኝ እንኳን የሚበደርለት ፌዴራል መንግስት ብቻ ነው።... በሌላ በኩል የአዲሳባ ህዝብ አስተዳደር እንደሌሎች ክልሎች በህግ የተደነገገና በቀመር የተሰላ ድጐማ ከፌደራል መንግስት ማግኘት አይችልም ፣... በቻርተሩ ላይ የፌደራል መንግስት በራሱ መልካም ፍቃደኝነት ብቻ አንደአስፈላጊነቱ የፋይናንስ እገዛ ለአስተዳደሩ ሊያደርግ የሚችልበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል ደንግጓል። ...

በከተማው ከሚኖሩ ግለሰብ ነጋዴዎች እና ከተማዋ ባለቤት የሆነቻቸው ድርጅቶች የተጨማሪ እሴት ታክስ በፌደራል መንግስት ብቻ ይሰበሰባል… በመሆኑም ቻርተሩ ከተማይቷን ከገንዘብም አንፃር እግር_ከወርች በማሰር ያሽመደመደና የፌደራል ፍርፋሪ ጠባቂ እንድትሆን ያደረገ ሆኖ በታሪክ ተመዘገበ።

ቻርተሩ በግልጽ ቢያስቀምጥም መዘዛቸውን በመፍራት እስከ ዛሬ ድረስ ወደ ተግባር ያልተለወጡ አሉ። ከእነዚህ ውስጥ አንዱ የአዲሳባ የስነ ምግባርና ፀረ - ሙስና ኮሚሽን ማቋቋም ይገኝበታል… ኮሚሽኑ የጣልቃ ገብነትና ነጻነት ችግር እንደሚያጋጥመው ቢጠበቅም በተባራሪ አግኝቶ የሚመዛቸው ክሮች ኢህአድግን ይገለባብጥ ነበር…በመሬት ፣ገቢ፣ የግዥ አፈጻፀም፣ መንግስታዊ አሰራርን ባልተከተለ ገንዘብ አጠቃቀም ብቻ ከ ሀያ ቢሊዬን በላይ የህዝብና መንግስት ገንዘብ ተዘርፉል። … የተፈፀመው ሌብነትና ህግን ያልተከተለ አሰራር በገለልተኛ ኦዲተር ቢጣራ በቅድሚያ የፍርድ ቤት ሳጥን ውስጥ የምናገኛቸው አቶ መለስና አርከበ እቁባይ ይሆኑ ነበር።

***

በምርጫ 97 እነ ዶክተር ብርሀኑ አስተዳደሩን ቢረከቡት እንደፈለጉ ወስነው ከተማዋ ከተዘፈቀችበት አረንቋ ሊያወጧት አይችሉም የተባለበት ሌላኛው ምክንያት ይህ ነበር፣… የፌዴራል መንግስቱ ከሀገር ውስጥ የፋይናንስ ተቋማት እንዲበደሩ እንደማይፈቅድላቸው ሳይታለም የተፈታ ነው፣… ከወጭ ተቋማት ፌዴራል እንደበደርላቸው መጠየቅም አፍን ከማበላሸት አያልፍም ፣ … የፌደራል መንግስቱ በህግ የሚገደድበት የድጐማ ስርአት በሌለበት ሁኔታ እጁን ፈታ አድርጐ በተቃራኒው ለቆመው ከተማው አስተዳደር መና ይወረውራል ብሎ መጠበቅ ማሞ ቂሎነት ነው። … አስተዳደሩ የሚያመነጨው ገቢ ደግሞ እንኳን ትላልቅ ካፒታል ፕሮጀክቶችን ሊሰራ ቀርቶ የሰራተኛ ደሞዝ ለመሸፈን በየአመቱ የሚንገታገት ነው፣…

በእንቅርት ላይ እንዲሉ በምርጫው ማግስት በአቶ መለስ ቀጭን ትእዛዝ የከተማዋ ውልና ማስረጃ እንዲሁም የአንድ ከተማ የደም ስር ተደርገው ከሚቆጠሩት አንዱ የሆነው ትራንስፓርት ክፍል ተቀምቷል፣ … አቶ መለስ አጥር ሲያፈርስ የተመለከቱት እነ አባዱላና ግርማ ብሩ የግዛት ማስፋፋት እቅድ አውጥተው ሲሶውን የአዲሳባ መሬት ለመውረር ተንቀሳቀሰዋል ፣…ይህም አልበቃ ብሎአቸው በህገመንግስቱ መሰረት ኦሮሚያ ልዩ መብት አላት የሚለውን ዝርዝር አፈፃፀም አስደንጋጭ በሆነ መልኩ እና የአዲሳባን ህዝብ ሉአላዊ መብት ለመንጠቅ በሚያስችል ደረጃ ዶሴ አዘጋጅተው ነበር (ይህ አስገራሚ ታሪክ ለኃላ ወግ ይቆይልን!) …

እናም እነ አቶ አርከበ ባቀረቡት ጥናት መሰረት ቅንጅት አዲሳባን በተረከበ በሁለት አመት ውስጥ መዲናይቱ ከተማ አቀፍ ኪሳራ (Bankruptcy) በማወጅ የድሬደዋ ተከታይ ትሆናለች።… ይህንንም ተከትሎ የእነ አርከበ ቡድን አዲሳባን እንደ ነውጥ መሳሪያ በመጠቀም መሬት አንቀጥቅጥ ተቃዉሞዎችና አመፆች በጥቅም ላይ ይውላሉ… ግጭቶች በህዝቡና አስተዳደሩ በማይቆጣጠረው ፓሊስና ፀጥታ ሀይሉ መካከል ይሆናል

፣ ...የህዝብና ሀብትና ንብረት ይወድማል፣ ...
የሰዉ ደም እንደ ጐርፍ ይወርዳል...
ቀዩ መስመር ታለፈ በሚል አስተዳደሩ ይበተናል።

***

ደህና ሰንብች መቐለ !

እነ አርከበ ወደ አዲስአባ ከመምጣታቸው ጥቂት ወራት በፊት በህውሀት ውስጥ መደናገጥ ተፈጥሮ ነበር።...የህውሀት ዳግም የመሰንጠቅ አደጋ።...ምክንያቱ በወ /ሮ አዜብና አርከበ ቡድኖች መካከል አለመግባባቶች መፈጠራቸው ነበር። ... መነሻው መረን የለቀቀ የጥቅም ግጭት ሲሆን አላማው የህውሀት ኢንዶውመንቶችን የመቆጣጠር ታሳቢ ያደረገ ነበር። ቡድኖቹ ይህንን ልዮነት ወደ ፊት ሳያወጡ በሌሎች ጉዳዬች ላይ መገታተር ጀመሩ። ...ፀቡ የተገለፀበት አግባብ ለየቅል ሆነ።

የአቶ አርከበ ቡድን በመቀስቀሻነት የኢትዬ-ኤርትራ ጦርነትና ህውሀት እየተገፉ ነው የሚለውን ተጠቀመ። ... በመጋቢት ወር 1993 አ•ም• የህዉሀት መሠንጠቅ ምክንያቱ የኢትዬ-ኤርትራ ጦርነት ላይ የተነሳው ልዮነት እንደሆነ፣ የአልጀርሱ ስምምነትና እሱን ተከትሎ የተሰጠው የፍርድ ቤት ውሳኔ ትግራይን ለመጉዳት የታሰበ መሆኑ፣...መለስ የትግራይን መሬት ለኤርትራ አሳልፎ መስጠቱ፣... የባድመ ጉዳይ እንዳለቀለት ውስጥ ለውስጥ አሰራጩ። ...አብዛኛው የህውሀት ካድሬ አቶ መለስ በኤርትራ ጉዳይ ላይ በያዘው አቋም ደስተኛ ስላልነበረ በአርከበ መስመር ተሰለፈ። በሠውየው ላይ ያለው እምነት እየተሸረሸረ ሔደ።... ጦርነቱ ግማሽ ላይ የቆመበት ምክንያት የመለስ ተንበርካኪነት እንደሆነ መተማመን ተደረሰ። የትግራይ ህዝብም ተቀብሎ አስተጋባ።

ሁለተኛው የአርከበ ቡድን ዘመቻ የህውሀት ካድሬዎች ከፌደራል ስልጣን እየተገፉ እንደሆነ የሚገልጽ ነበር። ...መለስ እያስጠቃን ነው የሚለው ከመቐለ አልፎ አዲስአባ ድረስ ተዛመተ። ...በረከት ህውሀትን ወደ ገደል ገፍትሮ ሊጥላት ነው ተባለ።...በህውሀት ህዋሳትና መሰረታዊ ድርጅቶች ዋነኛ መነጋገሪያው ሆነ: ...አዲግራት ውስጥ የምትገኝ አንዲት የቀበሌ ህዋስ የሚኒስትሮች ውክልና ትግራይን አግሏል ብላ አቋም ትወስዳለች፣ ... መቐሌ ላይ የምት ገኝ መሰረታዊ ድርጅት ከሀያ በላይ ሚኒስትሮች ባሉበት ሁኔታ ውጭ ጉዳይና ጤና ጥበቃን ብቻ ለትግራይ መስጠት ፍትሀዊ አይደለም የሚል ሪፓርት ታስተላልፉለች፣... የተምቤን ወረዳ ህውሀት ጽ /ቤት መለስ የራሱን ስልጣን ከሌሎች ጋር አደላድሎ ህውሀትን ገፍትሮ ጣለ በማለት አጀንዳ ቀርጻ ትነጋገራለች፣...ኢህአድግ ቢሮ በፅዳት ሰራተኝነት የምትሰራ የህውሀት አባል ቢሮው በብአዴን ካድሬዎች ተወረረ ብላ ቅሬታ ታቀርባለች።...አቶ አርከበ ይዞ ብቅ ያለው መቀስቀሻ የካድሬውንና አባሉን ቁስል የነካ በመሆኑ ተቀባይነት

አገኘ፣... በትግራይ ፕሮፓጋንዳና ድርጅት ተመድበው የሚሰሩ ቁልፍ ካድሬዎች ተቀላቀሉት።

ወ/ሮ አዜብ በበኩሏ አርከበና ቡድኖቹ በሙስና ተዘፍቀዋል የሚል ክስ ይዛ ብቅ አለች።...አርከበ በሚስቱና ቤተሰቦቹ የያዘውን ንብረት በመረጃ አስደግፋ አራገበች:– ላውንደሪ ቤት፣ ፋርማሲ፣ ክሊኒክ፣ ሱፐር ማርኬት፣ መስታወት ማስመጣትና መሸጥ...። በትግራይና አዲስአባ የተፈጠሩት አዳዲስ ባለሀብቶች የአርከበና ቡድኖቹ እንደሆኑ በስም ዝርዝር አሳወቀች። ...በወቅቱ ሁለቱም ቡድኖች "ያለ ኢኮኖሚ የበላይነት የፓለቲካ የበላይነት አይመጣም " የሚል ፓሊሲ ቀርፀው የህውሀት ባለሀብቶችን ለመፍጠር ተንቀሳቅሰዋል። በአንድ ለሊት ከሹፌርነት ወደ አስመጪና ላኪነት ... ከገራዥ ሰራተኝነት ወደ የመኪና እቃ መለዋወጫ አስመጭነት፣...ከታጋይነት ወደ ሪልስቴት ባለቤትነት...ከወታደርነት ወደ ፋብሪካ ባለቤትነት፣... ከህውሀት ምድብተኛ ካድሬነት ወደ ግል ባንክ ከፍተኛ አክሲዬን ባለድርሻነት የተቀየሩ ሰወችን መስማት የተለመደ ነበር።

የሀይል ሚዛኑ እያደር ወደ አርከበ ቡድን አዘነበለ። መቐሌ የሚገኘው የህውሀት ጽ/ቤት ለሁለት ተከፈለ። የወ/ሮ አዜብ የምንጊዜም ደጋፊ የሆነውና የፕሮፓጋንዳ ሀላፊው ቴዎድሮስ ሀጐስ በአንድ በኩል ፣ እነ አርከበ በሌላ በኩል ተሰለፉ። በጽ/ቤቱ የሚያዙ አቋሞች አስደንጋጭ ሆኑ። አዲሳባ ከሚገኘው ኢህአድግ ቢሮ ራሳቸውን አገለሉ። ከ1993 አ•ም• ጀምሮ ለስምንት አመታት የኢህአድግ ቢሮ ከፓርቲው መተዳደሪያ ውጭ የሶስት ብሔር ድርጅቶች ጥምረት ሆነ። ...ስራ አሰፈፃሚውን ደግሞ ሙሉ ለሙሉ ብአዴኖች ተቆጣጠሩት(*ቁንጮው ካድሬ በረከት ስምኦን ፣ ስልጠና ክፍሉን ታደሰ ካሳ (ጥንቅሹ) ፣ ፖሊሲ ክፍሉን ፍሬህይወት አያሌው፣ ህዝብ ግንኙነቱን ሴኮቱሬ ፣ የአዲሳባ ክንፍ ሀላፊ ዩሴፍ ፣ ፋይናንሱን ተሰማ ድብርቱ*) ያዙት። ለኢህአድግ ቢሮ ከህውሀት ውስጥ በአስፈጻሚነት የሚሰራ ወደ አዲስ አበባ እንዲልኩ በተደጋጋሚ ሲጠየቁ በድምጽ ብልጫ የለንም የሚል ምላሽ ሰጡ... በምርጫ 2000 ለአዲሳባ ከንቲባና ምክትል ሊወዳደሩ የሚችሉ እጩዎችን ከማእከላዊ ኮሚቴ መልምላችሁ ላኩልን ተብለው ቢጠየቁ " ለፊደራል የምናዋጣው የለንም ያልን ለከተማ እንዴት ይኖረናል?" የሚል መልስ በመስጠት ከመዲናይቱም ራሳቸውን አገለሉ...

(በምርጫ 2000 ብአዴን ለከንቲባና ምክትልእንዲወዳደሩ የገቢዎች ሚኒስትሩ መላኩ ፋንታ እና ከሚዲያ ቋማት ከፍያለው አዘዘን፣...አህዴድ ለከንቲባነት ኩማ ደመቅሳን፣ ...ወ/ ሮ አዜብ መስፍን ደግሞ ለከንቲባነት ኦህዴዲን አስቱር ማሞ በእጩነት አቀረቡ... ደኢህዴን ከፓለቲካ ጨዋነት አልተላቀቀም ተብሎ በድጋሚ ተዘለለ ።)

መቀሌ በተገላቢጦሽ ህውሀት በኢህአድግ መገለል እየተፈፀመባት እንደሆነ በሰፊው መነገር ተጀመረ...ህውሀቶች ከሌላው በተለየ የቀረበላቸውን እድል እየገፉ "ጅራፍ ራሱ ገርፎ... " እንደሚባለው ሆኑ... ከኢህአድግ እህት ድርጅቶች ውስጥ እንደ ህውሀት አኩራፊ የለም... ምክንያቱ ደግሞ ህውሀት የተቃኘው "ሁሉን ማግኘት አለያም ሁሉን እርግፍ አድርጐ መተው ! " በሚባለው የዜሮ ድምር ፓለቲካዊ እሳቤ የተጠናወታቸው በመሆኑ የመጣ ነው።

ሁሉንም ቦታ ጠቅልለውና ሙጥጥ አድርገው መያዝ ይፈልጋሉ፣ ካልሆነ ደግሞ ሁሉንም ለማጣት ተግተው ይሰራሉ።

ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ የነበረው አቶ መለስ የህውሀት ካድሬዎች ጭላሽት ከመቀባት ተቆጥበው ድርድር እንዲቀመጡ አሳሰበ፣...ጥሪውን ተቀብለውና ወደ አራት ኪሎ መጡ...

ግምገማው ተጀመረ።

ህውሀቶች የያዙትን ሀሳብ በእብሪት ተወጥረው የቋጠሯትን መተኮስ ጀመሩ "ብአዴን የህውሀትን መሰንጠቅና መዳከም እንደ ጥሩ አጋጣሚ በመውሰድ ኢህአድግ ቢሮን በቁጥጥር ስር አውሏል "የሚል መከራከሪያ እስከ ስም ዝርዝሩ አቀረቡ... በረከት! ፣ጥንቅሹ፣ህላዌ፣ፍሬህይወት...

አቶ በረከት ብልጭ አለበት ፣ ሲናደድ ደግሞ የሚናገረውን አያውቅም :

" ህውሀት ውስጥ ብእርና ወረቀት አጋጥሞ ሶስት ገፅ መግፍ የሚችል ካለ የእኔን ወንበር ዛሬውኑ መውሰድ ይችላል !" ብሎ የስድብ ውርጅብኝ አወረደ ...በፌዝና ንቀት ገረፋቸው።

ርግጥም በረከት ትክክል ነበር።

ከመለስና አባይ ውጭ ያሉት የህውሀት ካድሬዎች በምላሳቸው ወፍ ያሚያረግፉ ፣ ወደ ብእርና ወረቀት ሲመጣ ደግሞ ጨዋ ናቸው ።...

እብሪታቸው ሳይፈነዳና ድርድሩ ሳይሳካ ህውሀት ከአራት ኪሎ ኢህአድግ ቢሮ ራሱን እንዳገለለ ቀረ።... የድርጅቱ ህገ ደንብ " የጽ/ ቤቱ አስፈጻሚዎች ከሁሉም የብሄር ድርጅቶች የተውጣጣ ይሆናል" የሚለው እንደተጣሰ ቀረ።

አቶ መለስ ይቺ ባቄላ በማለት ስራውን ውስጥ ለውስጥ ጀመረ፣ ...የአርከበ ቡድንን የዝርፊያ ዶክመንቶች አሰባስቦ በጉንዬሽ እንዲደርሳቸው አደረገ።...አቶ መለስ ለማስፈራሪያ እንጂ በሙስና አሳቦ እግረ መቅ ሊያጠልቅላቸው እንደማይፈልግ ይታወቃል። የዛ አካሔድ በነ ስዬ አብርሀ ዘመን ብዙ ዋጋ አስከፍሎታል።... የህውሀት ካድሬ የእነ ስዬን ንቅዘት እያወቀና በአይኑ በብረቱ እያየ አላጋነነውም። ... በመቀሌ የሚገኘው ካድሬ አልፎ ሔዶ "ሁላችሁም አንድ ናችሁ ፣ አንዱ ሌላውን በሌብነት ለመክሰስ የሞራል ብቃት የለውም " ብሎ እንደነበር ያስታውሳል።... እናም የተለመደውን የሙስና ክስ ይዞ መምጣት የመለስ ምት እንደሚኖረው አውቋል።... ከዚህ በተጨማሪም የህውሀት ካድሬዎች ዘንድ ሌብነትን በተመለከተ አደገኛ አመለካከትና አዝማሚያ እንዳለ ያውቃል። ...የህውሀት አባላት በትግራይ ክልል ሙስና ከሞላ ጐደል በቁጥጥር ስር ውሏል፣ ሌብነት የስርአቱ አደጋ አይደለም ብለው ያምናሉ። ... በሌላ በኩል ፌደራልና አዲስአባ ተመድቦ የሚሰራ የህውሀት ካድሬ ሰረቀ ሲባል አያጋንኑም ...በእነዚህ ተቋማትና አዲሳባ መመደብ ሎተሪ እንደደረሰው ይነገራል፣...እንኳን ደስ አለህ ይባላል።... ዘርፈው ሲገኙም እንደሌላው ባለስልጣን ድርሻቸውን እንደወሰዱ ይቆጠራል።...ብዙዎች ከፌደራልና አዲሰአባ በዘረፉት ገንዘብ መቀሌ ላይ አፍ የሚያስከፍቱ ቪላዎችን ገንብተዋል።... በተለይም በአካል ተገኝቼ ያየኃቸው ሐውልቲና ገረብ የሚባሉት አካባቢዎች የምእራቡ አለምን ህንጻዎች የሚያስንቁ ናቸው።

ሁኔታው አሳፋሪ ደረጃ ደረሰ...

የትግራይ ህዝብ ማጉተምተም ጀመረ፣ አቶ መለስ የህዝቡን ስሞታ በማየት ለመቆጣት መቀሌ ወረደ። ... ስብሰባው ሲጀመር ባልተጠበቀ ሁኔታ ግምገማው ተገለበጠ...

የበሰበሰ ዝናብ አይፈራም...

ካድሬዎቹ የግምገማው አድማስ በትግራይ የሚገኙትን ብቻ ሳይሆን በሁሉም ቦታ የተመደቡትን የህውሀት ባለስልጣናት ማካተት እንደሚኖርበት ተከራከሩ።... የፊደራል፣ የደህንነት፣ የፓሊስና መከላከያ ባለስልጣናት እንዲካተቱ ጠየቁ። ...ግምገማው በሌብነት ላይ ብቻ ከሚንጠለጠል ያለፉት ሁለት አመታት አጠቃላይ ጉዞ መመልከት ወቅታዊ እንደሆነ በተደራጀ መንገድ አሳሰቡ፣...የኢትዬ_ኤርትራ ጦርነት (ጦርነቱ የቆመበት ምክንያት፣ የአልጀርሱ ስምምነት፣ባድመና የአለም አቀፍ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ፣ የኤርትራውያን ንብረት አመላለስ)፣...የኤፈርት የፉይናንስና ኦዲት ሪፓርት፣...የባለስልጣናት የሀብትና ንብረት ደረጃ ፣...የምደባና ሹመት ግልጸኝነት፣ፀረ ዲሞክራሲ በግምገማው ይካተቱ የሚል አቋም ወሰዱ።...

አቶ መለስ የካድሬዎቹ አካሔድ ስለገባው መውጫ መንገድ ፈለገ፣...ሳይከራከር ካድሬው የያዘው አቋም አብዬታዊና የሚደገፍ እንደሆነ አስረዳ። ...ይህ ተራማጅ አስተሳሰብ ከህውሀት ውጭ ማንም ሊደፍረው እንደማይችል በኩራት ገለፀ። ...ግን ደግሞ ህውሀት የሻይ ቤት ውይይት ክበብ ስላልሆነ ያለ ቅድመ_ዝግጅት መገባት እንደሌለበት አሳወቀ። ...የሚደረገው ግምገማ በግልም ሆነ በድርጅት ደረጃ ተጠናክሮ የሚወጣበት እንጂ፣ ጠላቶች በድጋሚ እንዲሳለቁ እድል የሚሰጥ መሆን እንደሌለበት አብራራ። ...የሁለት አመቱን ጉዞው የቀጣይ አቅጣጫ የሚያሳይ ሪፓርት ፓሊት ቢሮ በቅርብ አዘጋጅቶ ግምገማው እንደሚጀመር መተማመን ተደረሰ...

የጦዘውን ካድሬ ውሀ ቸለሰበት!

አቶ መለስ ከኃላ እየተሸረበበት መሆኑን ተገንዝቦ የአርከበን ቡድን ከመቐለ ጠራርጐ ማስወጣት ጊዜ የሚሰጠው እንዳልሆነ ተረዳ... ለጊዜው ባለቤት የሌላት ከተማ አጠገቡ አለች። ...ከተማዋን መለወጥ በራሱ አንገብጋቢ ሆኗል። ስለዚህም በአንድ ድንጋይ ሶስት ወፍ ለምታት አልሞ ተነሳ:– የአፍሪካ ተቀናቃኞቹን አፍ ማዘጋት፣...መዲናይቱን በልማት ማዕበል በመምታት የነዋሪውን አቅጣጫ ማስቀየር፣...አርከበና የቡድኑ መሪ ካድሬዎችን ከትግራይ ማስወጣት። ለዚህ እንዲረዳ "መዲናይቱን እናድሳት" የሚል ሰነድ ተዘጋጀ።

"የመዲናይቱ እናድሳት "እሳቤ የሚመነጨው ከእነዚህ ሶስት ውጫዊ ምክንያቶች እንጂ ፣_ ኢህአድግ በአዲሳባ ላይ ውስጣዊ የአመለካከት ለውጥ ስላመጣ አልነበረም:- የድርጅቱ "ከተማን በገጠር ስሌት" መምራት አቅጣጫ አልተቀየረም፣...አዳዲስ ከተሞችን መፍጠርና ማመጣጠን የሚለው ስትራቴጂ እንደነበረ ነው... ከዛም አልፎ የትምክህተኛ መከማቻ ከተሞችን ማዳከም ከሚለው ጐራ ውስጥ አዲሳባ የመጀመሪያው መስመር ውስጥ የነበረች ናት።

መዲናይቱን እናድሳት የሚለውን ሰነድ ተከትሎ በአዲሳባ ከፍተኛ ንቅናቄ እንደሚቀጣጠል ታወጀ። ... የትራንስፎርሜሽኑ መሀንዲስ አባይ

ፀሀዬ እንዲሆን ተደረገ።... ድርጅቱና አባይ ከደኢህዴን በስተቀር ለሶስቱ ብሔር ድርጅቶች ከተማና ዞን መምራት የሚችሉ ካድሬዎች እንዲያዋጡ ትዕዛዝ ሰጡ። ደኢህዴን አንኳን ሊያዋጣ ቀጥ ብሎ የሚቆምበት አንድ እግር የለውም ተብሎ ተዘለለ...

የፓለቲካ ጨዋ! ...ያሳፍራል።

አንዳንድ የጉራጌ ካድሬዎች ቅሬታቸውን ይዘው ወደ አለቃቸው ዶክተር ካሱ ኢላላ ቢሮ ሔደው ነበር ፣... ዶክተሩ ለትዝብት በሚጥለው መንገድ " ስራውን የሚሰሩት መለስና በረከት ስለሆኑ ጥያቄ ማንሳቱ ተገቢ አይደለም... እነሱ ሁሌም ትክክል ናቸው !" ብሎአቸው እርፍ አለ፣ ... በእርግጥ የጉራጌ ካድሬዎች "አስጠቂው "የሚል ስያሜ አስቀድመው ስለሰጡት ብዙም በምላሹ አልተገረሙም... ከታሪክ ተጠያቂነቱ እና ለህሊና በሽታው አስቀድመው ከማዘን ውጭ...

"አስጠቂው ዶክተር!"

በአጠቃላይ ግን ከሀያ ሚሊዬን በላይ የደቡብ ኢትዬጲያ ህዝቦችን ለማስተዳደር ስልጣን የተረከበ ፓርቲ ሀያ ሰዎችን ለማዋጣት አቅም ያንሰዋል ሲባል በርካታ ጥያቄዎች አስነስቶ ነበር : ደኢህዴን በካድሬነት የሰበሰበው እነማንን ነው ? ፣ የደቡብ ክልል በምን አይነት ሰወች እየተዳደረ ነው ? ፣ ከአዲሳባ ህዝብ ብዛትአንዳንዴ ሁለተኛ ሌላ ጊዜ ሶስተኛ የሆነው የደቡብ ኢትዬጲያ ብሔረሰብ ለሚያነሳው ጥያቄ ምን ምላሽ ይሰጣል ?...

በረከትና ብአዴን በበኩላቸው ህላዌ ዬሴፍ አዲሱን ከንቲባ በአይነ ቁራኛ እንዲጠብቅ መመሪያ ሰጥተው ወደ መዲናይቱ አዘዋወሩት። ...የኘሮፐጋንዳ ክፍሉን እንዲቆጣጠር አደረጉ።...የህላዌ ምደባ በአማራ ልማት መህበር (አልማ) ጋር ተያይዞ ጥያቄ አስነስቶ ነበር። ...ባህርዳር የሚገኘው የአልማ ጽ/ቤት በእሳት ቃጠሎ ሙሉ ለሙሉ እንዲወድም ካደረጉት ውስጥ የህላዌና ታደሰ ካሳ (ጥንቅሹ) ስም በሰፊው ይነሳ ስለነበር... የማጣራቱ ሂደት ሳይጠናቅ ሁለቱም እንዲሸሹ መደረጋቸው ተቃውሞ ገጥሞት ነበር።...ጥንቅሹ የባህርዳር ህዝብ አላስቀምጥ ብሎት አስቀድሞ አራት ኪሎ በሚገኘው ኢህአድግ ቢሮ እንዲከትም ተደርጓል። ...ህላዌ ደግሞ ቀኑን ጠብቆ ለሚዛን ጥበቃ ወደ ትውልድ ቦታው መጣ። ... በመሆኑም መዲናይቱን የማደስ እርምጃ በአባይ ፀሀዬ የጡት አባትነት፣ በአርከበ እቀባይ ፊት አውራሪነት፣ በህላዌ ደጅ አዝማችነት ተጀመረ።

***

በንጋታው ጠዋት ጨፌ ኦሮሚያ ንባቡን ጨርሶ በመጣ ካድሬ ተጥለቀለቀ።... ፀጉረ ልውጥ ካድሬዎች አብረው ከመጧቸው ተመሳሳይ ዘንጋቸው ጋር ተሰባስበው ተቀመጡ። ...የመዲናይቱን ነባር ካድሬ መጠየፋቸው ከፊታቸው ያስታውቃል።... ቢያዋሩን ሌብነትየሚጋባባቸው ይመስላል። ...የአዲስአባ ጨልሌ ቢሸጠንስ ብለው ጠርጥረዋል። ...ያነበቡት "መዲናይቱን እናድሳት "የሚለው ሰነድ አግራሞት ፈጥሮባቸዋል። ...በዘ ላይ በከተማዋ የሚገኙ ካድሬና አባላትን ጠራርገው ማባረር እንዳለባቸው የወሰዱት አረንቴሽን

በበላይነት ስሜት አሳብጧቸዋል። አንዳንዶቹ መዲናይቷን ረግጠዋት ስለማያውቁ ግራ መጋባታቸው ያስታውቃል።... ይቁለጨለጫሉ። ...አለባበሳቸውም ቢሆን ገጠር ቀመስ እንደሆነ ያሳብቃል።... ኢህአድግ ከተማን በገጠር ስሌት ለመምራት እንዳሰበ አመላካች ሆነው

***

" ስናይፐር ተኳሽ "

የጨፌው ምክር ቤት ለመዲናይቱ ተሀድሶ ተዘጋጅቷል። አዳራሹ እስካፍንጫው ሞልቷል። ...ሰፊውን ክፍል በሚይዘው የመሀለኛው ቦታ የከተማው ፣በስተግራ ፌደራል ፣ በቀኝ ደግሞ አዲሶቹ ካድሬዎች ተቀምጠዋል። ...

ውጥረት ሰፍኗል:

የአዲሳባ ነባር ካድሬዎች ባነበቡት ሰነድ ደስተኛ እንዳልሆኑ ፊታቸው ያሳብቃል። ...ቅጥ አምባሩ የጠፉበት ፅሁፍ አበሳጭቷቸዋል። ...ጭፍግግ ብለዋል ፣... ሊበሏት ያሰቡትን አሞራ ... ሆኖባቸዋል።...

በሹክሹክታ ያወራሉ፣... በተለይ በቅንነት ሲሰሩ የነበሩት ተብሰክሰክስከዋል።... ምንም ጥሪት ያላሰባሰቡት ከተከፉይ ካድሬነት ቢባረር ምን ይውጣቸዋል?... ያውም በዝጉብኝ እየተጠጣ ፣ በየቀኑ ታናሽና ታላቅ እየተቆረጠ። ...ቤተሰብም ቢሆን በሰፊው ለምዷል። ...ከአካባቢው በተሻለ የኑሮ ሁኔታ መኖር ጀምረዋል። ልጆች ደረጃውን የጠበቀ ትምህርት ቤት ገብተዋል።...

በተቃራኒው መውደቂያ ያዘጋጅት ነባር ካድሬዎች በሰላም መሰናበት ፈልገዋል። ...ሰርቀው ያከማቹትን ንብረት ከኢህአድግ ሳይጣሉ ለመብላት። ... አንዳንዶቹ በመሀል ከተማ በአከራይ ተከራይ ስም ነባሩን ነጋዴ አስለቅቀው የቤተሰብ ቢዝነስ ከፍተዋል። ...ኢትዬጲያ ሆቴል አካባቢ ቡድን ቡቲክ ከፍተው የጥቁር ገበያ ዶላርመመንዘሪያ ያደረጉም አሉበት። ያስፈራቸው ነገር አንድ ብቻ ነው፦ አወጫጭኙ ከድርጅት አልፎ ወደ ህዝብ ከወረደ።... " ሁሉን እናውቃለን" ያለው ህዝብ የተነፈሰ እለት መጨረሻቸው የት እንደሚሆን ተገንዝበዋል። ...ከህዝብ የተደበቀ አንዳችም ነገር ስለሌለ።

ከፌደራል ተቋማት አሥር የህውሀት ፕሮፌሽናል ገምጋሚዎች ስብሰባውን ለማጋጋል ተመደቡ። ዘርአይ አስገዶምና ኢሳያስ ጠርናፊያቸው ሆኑ

(**ዘርአይ የኢቲቪ ስራ አስኪያጅ፣ ኢሳያስ ደግሞ የደህንነት ሹማምንት ናቸው)

...ካድሬዎቹ ወደ ጨፌ ሲመጡ ከድርጅቱ ስልቶች አንዱ የሆነውን "ገሎ መዳን" ለመተግበር ልዩ ተልእኮ ወስደው ነበር... በነገራችን ላይ ከድርጅቱ የግምገማ ስልቶች በብዛት ስራ ላይ የሚውሉት "ገሎ ማዳን "እና "አድኖ መግደል" በመባል ይታወቃሉ። ... ሁለቱም የዜሮ ድምር መጫወቻ ቴክኒኮች ናቸው፣...አንዱን ለማዳን ሌላውን መግደል ...

የአብዬታዊ ዲሞክራሲ ጨዋታ! ...

አቶ መለስ የዜሮ ድምር ጨዋታ መሀንዲስ ነበር፣...መቼና በምን መልኩ እንደሚተገብረው ይቀይሳል፣...

የዜሮ ድምር ጨዋታ(Zero sum game) እንደ ኢኮኖሚክስ ባሉ የማህበረሰብ ሳይንሶች ከተለመዱ ሀልዬቶች አንዱ ነው፣...በዚህ የጨዋታ ህግ መሰረት አንዱ ሙሉ ለሙሉ ለማሸነፍ ሌላኛው መሸነፍ ፣ ...አንደኛው ሊያተርፍ ሌላኛው መክሰር፣ ...አንዱ ሊበለፅግ ሌላኛው መደህየት ይኖርበታል... በዜሮ ድምር ጨዋታ የጋራ ድል (Win-Win) የሚባል ነገር አይሰራም... ዋነኛ ባህሪው ጥሎ ማለፍ ነው።

አቶ መለስ በአንድ ወቅት ዛሬ ወደ ጨፌ የላከውን ዘርአይ አስግዶምን አጫውቶታል።በህውሀት ካድሬዎች ፊት ... ታሪኩ እንደዚህ ነው፦ በህውሐት መሰንጠቅ ተደናግጦ መሀል ላይ ከቆሙት ካድሬዎች አንዱ አባይ ፀሀዬ ነበር። ... የአንጃው ማዕበል ካለፈ በኃላ የፓርቲው ጉባኤ ተካሔደ። ...አባይ ለማዕከላዊ ኮሚቴ ተጠቆመ።... በክፍፍሉ ወቅት አሸናፊውን አይተው በጊዜ ከተሸበለሉት አንዱ የሆነው ዘርአይ አስግዶም ለተቃውሞ እጁን ከፍ አደርጉ :

"አባይ መመረጥ የለበትም፣ የአላማ ፅናትና የራሱ አቋም የለውም!!" አለ። ... ቀዩ የመቐለ አዳራሽ በሳቅ ተናወጠ። ...

የሚሉሽን በሰማሽ ገበያ ባልወጣሽ !!

ህውሐቶች ዘርአይን የሚያውቁት እሱ አባይ ላይ በሰነዘረበት ትችት ነው። የሳቁ እንድምታ የገባው መለስ " አባይ ለፈስፋሳ እንደሆነ እናውቃለን፣ ግን ደግሞ የጀርባ አጥንቱን የሚደግፍ የእንጨት መቀርቀሪያ ካስገባንለት ከማናችንም በላይ በወሬ ማቀባል የተሰማራ ሳይሆን የተግባር ታጋይ ነው። " ብሎ ዘርአይን በመወረፍ ማዕከላዊ ኮሚቴ አስመረጠው። በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ ! አባይ ከዛን ቀን በኃላ ወገቡን ጠበቅ አርጐ መስራት ቀጠለ።...በሀገሪቱ ችግር በተፈጠረበት ቦታሁሉ አባይ አለ። ሱማሌ...ጋምቤላ ... አፋር ይሯሯ ጣል። አባይ የሲኖዶሱም ፣የመጂልሱም አባል እስኪመስል ድረስ ከተቋማቱ አይጠፉም።

ለገሎ ማዳን ጨፌ የተገኘው ዘርአይ አስግዶም የተወረፈው በአቶ መለስ ብቻ አይደለም፣ ...ቀዳማዊ እመቤቷም ሒሳቡን ሰጥታዋለች፣ ...እመቤት አዜብ በካድሬው ፊት " ዘርአይ ማለት የራሱ ሀሣብ የሌለው ፣ ተኛ ሲሉት የሚተኛ፣ ተነስ ሲሉት የሚነሳ ፣...አስተላላፊ ቱቦ ነው " ብላዋለች። ...እሱም ቁልፍ ችግሬ "ቱቦነትና አድርባይነት ነው" ብሎ ራሱን ወቀሰ፣ አይለመደኝም አለ። ...በድርጅቱ ማህደር እንዲሰፍር ተደረገ። ...ሁለት አመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ራሱን የኮነነበትን ስራ ለመስራት ተከታዬች አፍርቶ ጨፌ ተገኝቷል...

አሊ አብዶን ገሎ ድርጅቱን ለማዳን ፣...

"ድመት መንኩሳ አመሏን አትረሳ " ...

ብዙሀኑ ከገጠር የመጡት አዳዲስ ካድሬዎች ግራ መጋባት ይታይባቸዋል ፣የከተማዋ አዙሪት አለቃቸውም። ... አብዛኛቹ የገጠር ከተማ አስተዳዳሪዎች ስለሆኑ አዲሳባ ውቅያኖስ ሆናባቸዋለች...

ለሰው እንግዳ ላገሩ ባዳ !

በእርግጥ ድርጅቱ "ከተማን በገጠር ስሌት መምራት " ለሚለው ስትራቴጂ ማስፈጸም ባያንሱም። ...አንዳንዶቹ በተለይም ኦህዴድ የላካቸው ለምን እንደመጡ እንኳን የተነገራቸው አዲስአባ ከደረሱ በኃላ ነው:... የአካባቢው ህዝብ አይናቸውን አያሳየኝ በማለቱ በግድ የመጡ አሉ። ...ከሌሎች አስተዳዳሪዎች በመጣላታቸው "እስቲ ዞር ይበልልን" ተብለው በቅጣት የተመደቡ ይገኙበታል። ...ብአዴን መልምሎ የላካቸውም ተመሳሳይ ይዘት ነበራቸው። ...ከሁሉም የሚገርመው ብአዴንን ጨምሮ የመንዲ አማርኛ መናገር የማይችሉ በውስጣቸው ነበሩበት...

የከተሜ አማርኛ አለመቻል የግል ድክመት አይደለም። ግን ደግሞ ለማስተዳደር እየተዘጋጁ ያሉት ይህንን ቋንቋ ተናጋሪውን ክፍል ነው። ...መቼስ ወፍ ለሚያዘንበው የመዲናይቱ ቢሮክራሲ በቱርጁማን ትእዛዝ አይሰጡ! ::

***

ፍስሀ መአሲና አባይ እየተነጋገሩ ወደ አዳራሽ ገቡ። ...ፍስሀ በአይኑ ሲፈልገኝ አይቼ እጄን አሳየሁት። ተሰናብቶት ወደ እኔ መጣ።

"አባይ እምነት የምትጥልበት የግምገማ ቃል አቀባይ ስጠኝ ብሎኝ የአንተን ስም ሰጥቸዋለሁ " አለኝ " በኢህአድግ ውስጥ ስኖር የግምገማ ቃል

አቀባይ ሲባል ሰምቼ አለውቅም"

"ህዝቡ አዲሱን የእነአርከበን ቡድን እንዲደግፍ የተዘየደ ነው። "

"ለምን ሌላ ሰው አትፈልግም፣ አለ በክፉ አይኑ እንደሚያየኝ እያወክ?"

" የተፈለገው ሁለት ካድሬ ነው። አለ የራሱን ሰው መድቧል፣ አባይ በተቃራኒው ፈልጐ ጠይቆኝ ነው "

ከፍስሀ ጋር እየጨቃጨቅን ወደ መድረክ አለ አብዶና አባይ ፀሀዬ ወጡ። ...

አባይ ዲስኩር ጀመረ...

ቃለ _ጉባኤ እንድንይዝ እኔና ሉልሰገድ ይፍሩ መመረጣችንን ገለፀ። ...ሉልሰገድ በአለ አብዶ ኔትወርክ ውስጥ ያለ ካድሬ ነው። ለግምገማው ቃል አቀባይነት የመረጠው እሱ ነው። የእኔ ስም ሲጠራ የአለ ፊት ሲቀያየር ተመለከትኩ። ...አባይ ሰነዱን በድጋሚ ቃል በቃል አብራራ። ...ወደ ኃላ ሔዶ የህውሐትን መከፋፈል ዋነኛ ምክንያት የቤተሰብ ገዥ መደብ (ቦናፓርቲዝም) መሆኑን በሰፊው ገለፀ። ይህ ገዥ መደብ ማዕከሉ አዲስአባ እንደነበር እና ያልተበጠሰ ኔትወርክ እንዳለው ተናገረ። ከአዲስአባ እስከ መቐለ የተዘረጋው የጥፋት ሀይል ፀረ ዲሞክራሲና ፀረ ልማት እንደነበር አስረዳ። ...ቫንጋርድ ፓርቲው ይህንን ሀይል ጠራርጐ ከትግራይ ቢያስወጣውም እንደ ቻይናው ኮሚንታግ ፓርቲ አዲስአባ ላይ መመሸጉን አስገነዘበ፣ ...ይህ ግምገማ ምሽጉን እንደሚደረምስ በኩራት ገለፀ።

ቀጥሎ ወደ አዲሳባ አስተዳደር ችግሮች እንድንዲገባ እድሉን ለቤቱ ዘረጋ።... ነባሩ የከተማ ካድሬ የተመካከረ እስኪመስል ፀጥ አለ። ...በተለያየ መንገድ ቢጐተጉት ቤቱን ከዝምታ ማውጣት አቃተው። ቁስቀሳው ይበልጥ ማጉረምረምን አስከተለ። ግራ ተጋባ። የተለመደ ባህሪውግን አልተቀየረም። ተረጋግቶ ይናገራል፣ እስከመጨረሻው ያዳምጣል። ግልፍተኛ አይደለም። ከአፉ የሚያወጣቸው ቃላት የተመዘኑ ናቸው። አውቆና ለክቶ ይናገራል። አይስትም።አይደበላልቅም።...ከመለስ ጋር የሚለያዩት በዚህ ባህሪው ነው። ...የህውሀት ካድሬዎች አባይን "ስናይፐር ተኳሽ" ይሉታል። ኢላማውን አስቀድሞ በመለየት ተኩሶ የማይስት ...። ፍስሀ መአሰ በበኩሉ "አባይ የቋጠረውን፣ አባይ ብቻ ይፈታዋል " ይላል።

የመዲናይቱ ካድሬ በቶሎ ቀበቶውን ሊፈታ አልቻለም። ድርጅቱ ከጀርባ እየሸረበ ያለውን አውቋል።... ከብዙ ውትወታ በኃላ ግምገማውን ምልዑነት ለማረጋገጥ ይቀራሉ የተባሉ ነገሮች ተነሱ። በተለይ ከዚህ ቀደም መዲናይቱ በስውር ሲያሸከረክሩ የነበሩ ካድሬዎች መገኘት እንደሚኖርባቸው አስተያየት ተሰጠ ። " ይጠሩ! ፣ይምጡና ይገምገሙ!" የሚለው ቃል ከየአቅጣጫው ተስተጋባ። ...አርከበ እቁባይ የካድሬዎችን አስተያየት በመደገፍ ተናገረ። ይህ ዲስኩር ወደ አዲስአባ ከተዘዋወረ በኃላ የመጀመሪያው ሆኖ ተመዘገበ። ... አባይ ጥያቄው የሁሉም መሆኑን በመመልከቱ ለመወሰን ተቸገረ። ...አርከበ ሀሳቡን አጠንክሮ የገፋበት ምክንያት ገብቶታል። ...በከተማው ስውር መንግስት ውስጥ የአባይ እጅ ነበረበት። ከራሱ በላይ ሲወዳት በነበረችው ሚስቱ አማካኝነት። ...ደግነቱ ለትምህርት ውጭ ሀገር ልኳታል። የተቀረው ፍስሀ

መአሲ ነው። እሱ ደግሞ ከአርከበ ጋር መስራት አልችልም ብሎ ከምደባ ውጭ ሆኗል። በግምገማውም ተገኝቷል።... አዲስአባ እየኖረ ያልተገኘው የስውር መንግስቱ የበላይ ካድሬ ተስፉማርያም ብቻ ነው። ተስፉማሪያም ከህውሐት መሰንጠቅ በኃላ የአልጋ ቁራኛ ሆኗል።...እንዲመጣ የተወሰነበትበዚሁ ሁኔታ ላይ እንዳለ ነበር።...ፍስሀ መአሲ ሊያመጣው ሐዲ። ...እስከዛ የሻይ እረፍት ሆነ።

ተስፉማሪያም በፍስሀ ተደግፎ ወደ አዳራሽ ገባ። ...ብዙ ሰው ደነገጠ። ...ከፊቱ ተቀምጣ የነበረችዉ ፀሀይቱ ባህታ እጆቿን ወደ ጭንቅላቷ ልካ ጮኸች።... የአዲሳባ ሚሊሻ ጽ/ቤት እንድትሆን ከመቀሌ ያዘዋወራት እሱ ነበር። ... የየወረዳዉ ሚሊሻ ሀላፊዎች እሷን ተከትለው አለቀሱ። ሀላፊዎቹ ዲሞብላይዝድ ተጋዳሊቶች ናቸው።... የእሱ ቀኝ እጆች ነበሩ።

ተስፉማርያም በቁመ አልቋል ...የጉንጮቹ አጥንቶች ቆዳውን በስተው ሊወጡ ይታገላሉ።... ፀጉሩ ተኗ፣ ሲጉረጠረጡ የሚያስፈሩት አይኖቹ ተደብቀዋል፣... እጆቹ ከመሰለላቸው የተነሳ ከዘራው ከብዷቸዋል ...የምግብ ጉዳት እንዳጋጠመውለ ሰውነቱ ይመሰክራል።... መልአከ ሞት ቀርቦታል!...

አዳራሹ በሀዘን ተዋጠ።

አባይ ቤቱን አረጋግቶ ወደ ስብሰባዉ ተመለሰ። ግምገማው ካዛንችስ በሚገኘው የአዲሳባ ኢህአድግ ቢሮ አመራር ላይ ተጀመረ። ...አሳዛኝ ታሪኮች ተደመጡ። በሀያ አንደኛው ክ/ዘመን ተፈፅመዋል ብሎ ለማመን የሚያስቸግሩ ታሪኮች ተዘከዘኩ:: ብዙዎቹን የምውቃቸው ቢሆኑም "ከፈረሱ አፍ " መስማቱ ሌላ ትእይንት ነበር።... በባህታዊ የሚመራው ሁሉን አድራጊና ፈጣሪው : -የካዛንችሱ መንግስት፣... የስርአቱ መጨቆኛ ቦታ : -ዶንቦስኮ፣ ... ኢህአድግን ከመዲናይቱ ያባረረው : -ምርጫ 92 •••

***

ባህታዊ የሚመራዉ የካዛንችስ መንግስት!

ራሷን የተወችው ካዛንችስ የከተማውን ኢህአድግ ጽ/ቤት ተሸክማለች። ...ካዛንችስ ከፒያሳው ማዘጋጃ ቤት በላይ ግዙፍ ውሳኔዎች ታሳልፉለች። ...ፒያሳ ሲጨልም ካዛንችስ ይነጋል። ስራዎቿን በምሽት ትጀምራለች።...ካዛንችስ የማትሰራው የለም፣...ለመዲናይቱ ፕሬዝዳንት (ከንቲባ) ትመድባለች። ...ከንቲባውን ተክታ የካቢኔ አባላት ታዘጋጃለች። ...ፍርድ ቤት ሆና ብይን ትሰጣለች፣ ትገመድላለች። ...የቀረባትን ታስደስታለች፣ የራቃትን ታስለቅሳለች።

በእሷ ለሚታመኑት ሁሉ ጋሻና መከታ ትሆናቸዋለች!

ውስጥ አዋቂዎች ጉዳያቸው ፒያሳ ከተንጓተተ አቆራርጠው እሷ ጋር ይመጣሉ። ለወራት የተንከራተቱበት በአንድ ቀን ያልቃል። ...በቀጭኑ ሽቦ ወደ ፒያሳና እንግልት ወደ ፈጠረው ተቋም መደወል ብቻ በቂ ይሆናል። ...ይህን ተከትሎ ለቅሬታ አቅራቢዎቹ " የማዘጋጃ ቤትን አቀበት አትውጡ፣...አትውረዱ

" በመባል፣ ውሳኔው እቤት ድረስ ይላክላቸዋል። ሰዎቹም ወደ ካዛንችስ ያደረሳቸውን ካድሬ ያመሰግናሉ።

ግና ! ወደ ካዛንችስ መንግስት መግቢያው መንገድ ጠባብ ነበር...

እንደ ገነት ።።

ማንም እንዳፈተተው መምጣት አይችልም። በቀጠሮም የማይታሰብ ነው። ...በር የሌላት ካዛንችስ በውስጧ ለያዘችው ስውር መንግስት ቀን ከሌት ዘብ ታቆማለች። ...መንግስቱን ለመጠበቅ ያቆመቻቸው ዋርድያ " ተሻግረህ ሒድ" የሚል ወፍራም ትእዛዝ ያስተላልፉል። ... ትእዛዙን ያላከበረ የማርያም ጠላት ይሆናል፣...የታክሲ ሹፌር በሩ ላይ አቁሞ ካወረደ በቆመጥ ይደበደባል... "ማቆም አይቻልም የሚል ምልክት የለም " ብሎ ከተከራከረ አለቀለት:- መንጃ ፍቃዱን ይቀማል፣ መቀመጫው እስኪተላ ይገረፉል... የቆመጥ ጡጫ ይዘንብበታል... ትንሽ ያጉረመረመና የመብት ጥያቄ ያነሳ ደግሞ በጠመንጃ ሰደፍ አናቱ ይቦረቀሳል...ጀርባው ይጠናል...

ከእለታት በአንዱ ቀን በስውር መንግስቱ ፅ/ቤት እየተካሔደ ያለው ስብሰባ ተራዘመ። ...እስከ እኩለ ለሊት... ሰለቸኝ...ንፉስ ለመውሰድ ወደ ጓሮ ሒድኩኝ። ...በጀርባ ያለውን መፀዳጃ ቤት ከፍቼ ስገባ ያየሁት ነገር አስደነገጠኝ።... አንድ ሰው ራቁቱን ተንበርክኳል። ...ሁለት እጆቹ ወደ ኃላ የፊጥኝ ታስረዋል። ጭንቅላቱ ተዘቅዝቆ በመፀዳጃ ቤቱ አፍ ውስጥ ተደፍቋል ።... አንደኛው ዋርድያ በጮማ ውሀ ያፈስበታል። ሌላኛው ወገቡን በቆመጥ ይተለትላል።... ከደፈቁት ቀና ሲያደርጉት አፉ ውስጥ ጨርቅ ተጠቅጥቋል። ምን አድርጉ እንደሆነ ጠየኳቸው።... አንደኛው ዋርድያ " ሁል ጊዜ ሲሰክር አህአድግ ሌባ፣ መለስ ዘረኛ እያለ ይጮሀል " አለኝ። ተበሳጭቼ " መብቱ ነው! ልቀቀው" አልኩት ።... አንደኛው ፊቱን ወደ እኔ አዞረ። ሊበላኝ ደረሰ። ተጨቃጨቅን።... ከእነሱ ጋር ተነጋግሮ መተማመን እንደማይቻል ስገነዘብ ወደ ውስጥ ገብቼ ለፍስሀፀ መአሲ ነገርኩት። ...ተቆጥቷቸው ሰዉየውን አሰናበተው።

የካዛንችሱ መንግስት በሶስት የህውሐት ካድሬዎች ይመራ ነበር። ...ተሰፋ ማርያም፣ ሞንጆሪኖ፣ እና ፍስሀ መአሲ። ...ተስፋማርያም የበላይ ሹም ነው። ...ህዝቡ ሳይሆን እነ ተወልደና ስዬ የቀቡት።... ነዋሪው የት አውቆት?... የት አይቶት ? ...ተስፋማርያም የቀደምት ህውሐት ታጋይ ነበር። በብረት ትግሉ ወቅት በፓለቲካ ዘርፍ ተመድቦ ህዝብ አደራጅቷል። ...ከደርግ ውድቀት በኃላ አዲስአባ ተሰጠችው: እንደ ግል ንብረቱ ቆጠራት። ...ለከተማዋ ካድሬ ይመድባል፣ ያባርራል።...ሰው ያሳስራል፣ ያስፈታል።...መሬት ይሰጣል፣ ይቀማል።...ግብር ይጨምራል፣ ምህረት ያደርጋል። ለከተማዋ በጀት ይደለድላል፣ ይቀንሳል... መስኪድና ቤተ ክርስትያን እንዲሰራ ይፈቅዳል ፣ያስፈርሳል። ታዲያይህን ሁሉ የሚያደርገው በስውር ነበር። ...ከከተማ ካድሬዎች በአካል የምናውቀው ጥቂቶች ነበርን።...ብዙሀኑ አይቶት አያውቅም። በስሙ ብቻ ይርድለታል።...በድሮ ጊዜ "ንጉሱ ምን አሉ?" ተብሎ እንደሚጠየቀው ሁሉ፣ እኛም የተስፋማርያምን ትዕዛዝ ለመስማት እናነፈንፉለን። ...ትዕዛዙ የንጉስ ነበር : በተባለው ቀን የሚፈፀም።

የመዲናይቱ ካድሬዎች ተስፋማርያምን "ባህታዊው " ብለን እንጠራዋለን። ...በትክክልም የከተማ ያውም የመሀል ካዛንችስ መነኩሴ ነበር። ...በሶስት አመት ውስጥ: አንድ ጫማ፣ ... ሁለት ሱሪ፣ ጃኬትና ሸሚዝ ብቻ የነበረው። ...ጫማውን ሳይቀይር አንዱን ሳምንት አንድ ልብስ ሌላ ሳምንት የተቀረውን ይለብሳል።

አንድ ጊዜ ጫማ ለውጦ "ባህታዊዉ ጫማ ቀየረ " ተብሎ ለወራት የወሬ ማሟሻ ተደረገ። ...ይህ በሁለት ልብስ ላይ ተጣብቆ መቅረቱ በአብዬታዊነት አስቆጠረው።... "ተስፋማሪያም እኮ እውነተኛ ታጋይ ነዉ! የለ አንድ ጫማና ልብስ የለውም " ተብሎ ዝናው ከእንጦጦ እስከ ቂልንጦ ተራራ ተነገረ። ... በዞንና ወረዳዎች እሱን መምሰል የሚፈልጉ ተከታዬች አፈራ።... የሚዘንጥና እራሱን የሚጠብቅ እንደ ቢሮክራት ተቆጠረ: ስራ የማይችል። ...አንዳንዶች ሰውነታቸውን ሲያኩ እንኳን የእሱ ግልባጭ ሆኑ። ... ተስፋማርያም የማያቋርጥ ፎካች ነበር ... አንድ እጁ ብእር ጨብጦ ሌላኛው ከብብቱና ጭኖቹ ስር አይጠፉም።

ተስፋማርያም ምግብም ላይ ተመሳሳይ ባህሪ ነበረው...የእለት ቀለቡ እንጀራ በሽሮ ወጥ ነበር።... ምግብ የሚያዘጋጅለት፣ ልብሱን የሚያጥብለትና ፀጉሩን የሚከረክምለት ደሱ በርጋጋ የሚባል ሎግላጋ ጭሎ ነበረው።... ደሱ ጮበዝ ነው... ሳይታክት ሽሮ ያንደከድካል፣ ... ለውጥ ካስፈለገ ደግሞ ቲማቲም ይከትፋል። ...ይህን ሁሉ የሚያደርገው ካዛንችስ በሚገኘው ጽ/ቤት ነበር... ምድር ላይ በምትገኘው ትንሿ አዳራሽ...ተስፋማሪያም ለመኖሪያ ትልቅ ቪላ ቢሰጠውም በብዛት አይኖርበትም... ቢሮው አልጋ ዘርግቶ ይተኛል።

ባህታዊዉ አራት ኪሎ እነ ተወልደ ወልደማርያም ጋር በመሔድ የስራ መመሪያ ይቀበላል። ከዛ ውጭ ከካዛንችስ አይወጣም። ... አልፎ አልፎ ከተወልደ ጋር ሻይ ይጠጣል። ...እሱንና ተወልደ በብዙ ነገር ይመሳሰላሉ : ... የጋራ ባህሪያት አላቸው።

ላባቸው አንድ የሆነ ወፎች...!

አመራር ባህሪያቸው ተመሳሳይ ነበር ።...በእነሱ ዘመን የመንግስት ተቋማት የስራ ትዕዛዝ የሚወስዱት ከፓርቲው ጽ/ቤት ነበር። እቅድ ኢህአድግ ቢሮ በእነ ተወልደና ስዬ ተዘጋጅቶ በመመሪያ መልኩ ለእነ መለስ ይወርዳል። ... የእዝ ሰንሰለቱ ከድርጅት ወደ መንግስት ይፈሳል።... ይህ አይነቱ አሰራር የአብዬታዊ ዲሞክራሲ መሰረታዊ መርህ ሲሆን ደሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት በመባል ይታወቃል...

በዚህ መሰረት ተወልደ መለስን፣ ...ተስፈማሪያም ደግሞ አሊ አብዶን የስራ ስምሪት ይሰጣሉ። ...አቶ መለስም ሆነ አሊ አብዶ እነዚህ ካድሬዎች ካዘዟቸው ውጭ ዝንፍ አይሉም ። ...ለሀገሬውና መዲናይቱ ህዝብ መግለጫ እንኳን ሲሰጡ ተጽፎ የተሰጣቸውን አይለቁም: ...እነ ተወልደ ለጋዜጠኛው ጥያቄ አውጥተው ይሰጡታል፣ ለአቶ መለስ ደግሞ ቃል በቃል የሚናገረውን ይልኩለታል።... አላመንኩበትም የሚባል ነገር አይሰራም። ... የተጻፈውን የራስ አድርጐ ከማነብነብ ውጭ! ... ዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት!...አቶ መለስ የኢትዬ ኤርትራ ጦርነት ወቅት ከተሰጠው ወጣ እያለ አስቸግሮ ነበር። ተወልደ

እየጠራው ቢቆጣውም አልመለስ አለ። ...ይህም ልዩነቱን እያሰፋው ሔደ። ... ስዬ አብርሀ የኢህአድግ ቢሮ የሚሰሩ የህውሐት ምድብተኛ ካድሬዎችን በመሰብሰብ " ጥጃው አስቸግሯል ፣ሻዕቢያ እንዳይደመሰስ እንቅፋት ሆኗል " ብሎ ተናገረ ...ስዬ አቶ መለስ ላይ ያለውን ንቀት ለማሳየት " ጥጃው " እያለ ይጠራው ነበር።

ጥጃው!...

ስዬ ለሰበሰባቸው ካድሬዎች " ሻዕቢያ የትግራይ ጣላት ነው፣ ካልተደመሰሰ በስተቀር ትግራይ ሰላም አታገኝም "ብሎ ለሰበሰባቸው የህውሀት ካድሬዎች ተናገረ... "ሻዕቢያን ከዚህ ምድር ጠራርገን እንዳናጠፋ ጥጃው አንድ ጊዜ ጦርነቱን ኢኮኖሚያችን መሸከም አይችልም ፣ ሌላ ጊዜ የኤርትራን ከቀኝ ግዛትነት ነፃ መውጣት አለም ሳይቀድመን አውጀን እንዴት ድንበሯን ዘልቀን እንገባለን የሚል ተልካሻ ምክንያት እየሰጠ ነው "በማለት በተለመደው እብሪቱ ተወጥሮ ዘከዘከ።

ውጤቱ ግን በተቃራኒው ሆነ። ... ጥጃ ያሉትን ለምሳ ሊጠብሱት አስበው እሱ በቆረጣ ለቁርስ አደረጋቸው!...የኢትዮጲያ ታሪክም ራሱን ደገመ...

ካርል ማርክስ እንዳለው "መጀመሪያ አሳዛኝ ቀጥሎ ቧልት በሚመስል መንገድ!!"። የመጀመሪያው ታሪክ የመንግስቱ ሀይለማርያም ነው። መንግስቱ ሊገለብጡት የነበሩትን "ለምሳ ያሰቡንን ለቁርስ አደረግናቸው " ብሎ እንደወረደ ተናገረ። አቶ መለስ ደግሞ እነ ተወልደን ሲያሰናብት በኢህአድግ ውስጠ ድርጅት ስብሰባ "ጃኬታቸውን እያስወለቅን ሸኘናቸው። ምንም እንኳን የነተበ ጃኬት ቢሆነም " ብሎ ተሰብሳቢውን አስደመመ። ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ ደግሞ ሁለቱን ታሪኮች ለማዋደድ ፈልገው አቶ መለስን በዛው ስብሰባ " አሁንስ መንግስቱ ሀይለማርያም መሰልከኝ! " አሉ።... በዶክተሩ አስተያየት ክፉኛ ስሜታቸው የተነካው ሚኒስትር ገነት ዘውዴ ስቅስቅ ብለው አለቀሱ። ሚኒስትር ገነትም ቢሆን ታሪክ ደጋሚ ናቸው።

በአዲሳባ የተስፋማርያምና አሊ አብዶ ግንኙነት ከእነመለስና ተወልደ በከፉ ሁኔታ የጌታና ሎሌ ስርአት የነገሰበት ነበር። ...የአሊ የእለት እንቅስቃሴ ክካዛንችስ በሪሞት ኮንትሮል ክትትል ይደረጋል። ... ካቢኔው ተስፋማሪያም የወሰነውን መንግስታዊ ሰነድ አድርጐ የፀድቃል። ...አቶ አሊ በአስተዳደሩ ምክር ቤት የሰጠው ምላሽ ተስፋማርያም ቢሮው በዴክ ይከታተላል። ...እሱ ካለው ዘነፋ ካለ ይቆጠዋል። ...በነገራችን ላይ በጨፌ ግምገማ ወቅት ለአሊ " ተስፋማርያምን ትፈራዋለህ ... ትሰግድለታለህ" የሚል ትችት ቀረበበት፣...እሱም " እንዴት አልፈራው! እንዴት አልሰግድለት! የሰጠኝ የመዲናይቱ ቁልፍ አርቴፍሻሉን ነው " ብሎ መልስ ሰጥቷል።

ተስፋማርያም ሲወሳ የማይቀር ትዝታ አለው...በየሳምንቱ ይዘንለት የምንሔደው ሪፓርት፣...ለስራው ከምናጠፋው ጊዜ በላይ ለምንጽፈው እንጨነቃለን። ...እሱም የአንድን ሪፓርት ጥራትና ደረጃ የሚለካው በክብደቱና ወረቀት ብዛቱ ነበር። ...ሪፓርቱን በእጁ መዳፍ ላይ አስቀምጦ እንደሚዛን ይለካል፣... በዛ ብሎ የእጁን መዳፍ ገድገድ፣ ገድገድ ካደረገው የረፓርቱ ባለቤት ስራውን በአግባቡ ሰርቷል... ምስጋና ይቸረዋል ።...የገጽ ቁጥር ካነሰና ቀትረ

ቀላል ከሆነ ሪፓርቱን ያመጣው ካድሬ እንደ ውሻ ተሰድቦ አዲስ ሰርተህ ና ይባላል።

የህውሀት መሰንጠቅ የተስፉማርያምን አገዛዝ እንደያከትም አደረገው።...ትልቁ ዛፍ ወደቀ... ምሳርም በዛበት።...በስሙ ብቻ ሲርድ የነበረው ካድሬ የከተማዋን ችግሮች በሙሉ በእሱ ላይ ደፈደፈ። ... በተለይ ካሊድ አብድርሀማን የተባለ የካቢኔ አባል የቀረበው አስገራሚ ነበር።... ወይዘሮ ጥጉ የምትባል የአዲሳባ ሴቶች ማህበር ፕሬዝዳንት ካሊድ ላይ " ትሰክራለህ፣ ትማግጣለህ... መቀሌ ለስብሰባ ይዘሀቸው ከሔድከውን የማህበሬ አባላት ከአንዷ ጋር ተኝተህ ወሮታውን ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ በማስገባት መልሰሀል!" የሚል ሐሲ ታቀርብበታለች። ...ካሊድም ሐሱን ዉጦ የችግሩ ምንጭ ተስፉማርያም የፈጠረበትን ጭንቀት ለመቀነስ እንዳደረገው ተናገረ፣...ባህታዊው ለወሲብ ሴሰኝነት ተጠያቂ ሆነ...

ቀን ሲገለበጥ ውሀ ወደ ላይ ይፈሳል እንዲሉ።

ሲያልቅ አያምር!

***

ተስፉማርያምን ለመጨረሻ ጊዜ ያየሁት ከጨፈው ግምገማ ሁለት አመት በኃላ ከፍስሀ መአሲ ጋር ልንጠይቀው ሔደን ነበር። ፍስሀ የተጣለ ሰዉ አይረሳም። ... ከድሬደዋ ለስብሰባ መጥቶ ነበር ወደ ባህታዊው ቤት የሔድነው።...የተንጣለለው ቪላ ቤት ክፍሎቹ በሙሉ ባዶ ናቸው። ...በሳሎኑ ትልቅ ጠረጴዛ ያለ _ወንበር ተቀምጧል። ...በመኝታ ቤቱ ከአልጋው ውጭ ቴሌቪዥን አለ። ... ቤቱ ሊባላ ደርሷል።ብዙ ሰአቱን ከአልጋው አይወርድም። ...እኔን አላወቀኝም።...ከፍስሀ ጋር የበረሀ ትዝታዎች ተጫወቱ። ... ከዛ መልስ ያለውን ረስቶታል፣አሊያም ማስታወስ አይፈልግም። ...ተክለ ሰውነቱ ጨፈ ካየሁት በዙም አልተለወጠም።... እጆቹ አግጠው ያልደረቀ አፅም መስለዋል...በአካል ካወኩት ጀምሮ ቤቱ እስካገኘሁት ድረስ አብራው የኖረችውን አንዲት አመል አልተዋትም።... መሀል አናቱን በሌባ ጣቱ መፈተግ ፣... በገዙባት ነው መሰል ለብቻዋ ጥቁር ብላለች።

***

ሞንጆሪኖ አታረጅም...

ሁልጊዜም ወጣት ናት። ...ማንም አይቷት አስቸጋሪውን የዱርና ቆንጥር ዘመናት አሳልፋለች ብሎ ማመን አይቻለውም፣ ...ተራራን ያንቀጠቀጠች ፣ቋጥኝ የደረመሰች አትመስልም...የእጆቹ ልስላሴ ከብዙዎቹ ተጋዳሊቶች የተለየ ነው : ቃታ ሲስብ መኖሩን ረስቶታል።... ሞንጆሪኖ ከአለቃዋ በተቃራኒ ዘናጭ ናት፣... አዲስ የወጡ የአውሮፓ ፉሽኖች አያመልጧትም፣ ...የአይን መነፅሮቿ በትእዛዝ የሚሰሩ ናቸው። ...የበረሀ ውጣ ውረዱን ማሳበቁን ማቆም ያልቻሉት የእግሮቿ ጡንቻና ተረከዟ ብቻ ናቸው። ...ይህ ደግሞ በብዙሀኑ ነባር ተጋዳሊቶች የሚታይ ነው። ...ደንዳና ጡንቻና የተሰነጣጠቀ ተረከዝ። ... አንዳንዶች የትግል ዘመን ለማወቅ የስንጥቁን ብዛት መቁጠር በቂ ይሆናል የሚሉ አሉ። ...የሞንጆሪኖ መሬት መርገጫ ካልሲ ተለብሶበት እንኳን ስንጥቃቱ አምስት- ስድስት እየተባለ ይቆጠራል።

ሞንጆሪኖ ከተስፉማሪያም ቀጥላ ወደ አዲሳባ ኢህአድግ ቢሮ በመዘዋወር የካዛንችሱን መንግስት ተቀላቅላለች። ... የፕሮፐጋንዳ ዘርፉን እንድትመራ ተሰጣት። ...በተለይም ዶንቦስኮ እየተባለ የሚጠራውን የካድሬ ማሰልጠኛ በበላይነት ተቆጣጠረች።... በላፍቶ ሳር ቤት አካባቢ በጫካና ወንዝ የተከበበው ዶንቦስኮ የስርአቱ ዋነኛ መጨቆኛ ቦታ ነበር። ...በመዲናይቱ ካድሬ ሆኖ ለመመደብና የመንግስት ስልጣን ላይ ለመቆየት በየጊዜው ዶንቦስኮ እየተገባ መሰልጠንና መገምገም ግዴታ ነበር። ለመጀመሪያ ዙር ለሁለት ወራት በአዳሪነት መሰልጠን የማይታለፍ ነው። ...በቋሚ አሰልጣኝነት ለካዛንችሱ መንግስት ታማኝ የሆኑ ካህሳይ የሚባሉ ሞክሼዎች ተመድበዋል። ...ሁለቱም ነባር የህውሀት ታጋዬች ናቸው። ...የተመረጡትም በፕሮፌሽናልገምጋሚነት ብቃታቸው ነበር።

የዶንቦስኮ ካሪኩለም የሚዘጋጀው በካዛንችስ ሲሆን ትኩረቱ በአብዬታዊ ዲሞክራሲ መርሆዎች ላይ ነበር: መስቀለኛ መንገድ ላይ ቆማ የነበረችውን ኢትዬጲያ ኢህአድግ እንዴት እንደታደጋት ፣የብሔርና መሬት ጥያቄ፣ ዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት ፣ ጠባብና ትምክህተኝነት ዋነኛ አጀንዳዎች ናቸው። ... በየካሪኩለሙ ማጠቃለያ ላይ ሰልጣኞች የአቋም መግለጫ ያወጣሉ : " አንቀፅ 39 የአንድነታችን መሰረት ነው!"፣ "የመሬትና ብሔር ጥያቄ ተነጣጥለው አይታዩም!"... "ማእከላዊነት የዲሞክራሲያችን መገለጫ ነው ! " " እንደ አነግና መአድ ያሉ ድርጅቶች የጥበትና ትምክህት አቀንቃኞች ናቸው ! "...

አዳር ስልጠናው ሊጠናቀቅ ሁለት ሳምንት ሲቀረው ግለሰባዊ ግምገማ ይጀመራል።... በዚህን ወቅት ሞንጆሪኖ ከአህአድግ ቢሮ፣ የበረሀ ጓደኛዋ ማሚት ከማዘጋጃ ቤት ይመደባሉ።...ማሚት በማዘጋጃ ቤት ሶስተኛ ሰው ስትሆን ዋና ስራዋ አሊ አብዶን መቆጣጠር ነበር። ...በአሊ ፊርማ የሚወጡ ደብዳቤዎች ፣ ...ያናገራቸውን ባለጉዳዬች ፣ ያደረጋቸውን የስልክ ልውውጦች በመጥለፍ ለባህታዊው ተስፉማርያም ታስተላልፋለች።

ዶንቦስኮ በታቀደ መልኩ የከተማውን ካድሬዎች ወኔ ለመስለብ

የተዘጋጀ መጨቆኛ ተቋም ነበር። ...ካድሬዎችን አሰቀድሞ በማደንዘዝ ምንም ጥያቄ እንዳያነሱ፣...የህዝቡን ብሶት አባላት ተጋርተው እንዳያስተጋቡት ከወዲሁ እንደ እባብ አናታቸውን ለመቀጥቀጥ በማሰብ የተዘጋጀ ። ... ይህን ለማስፈጸም ቅድመ ዝግጅቱ አስቀድሞ ይጀመራል:-...ሰልጣኞች ተቋሙ ከመግባታቸው በፊት የጀርባ ታሪካቸው ይጠናል። ይህን ጥናት የሚሰሩት የወረዳ የካድሬ አለቆች፣ የሚሊሻ ጽ/ቤት ሀላፊዎችና የሀገር ውስጥ ደህንነቶች በመቀናጀት ነበር።...እጩ ሰልጣኙ ተወልዶ ያደገበት፣...የት/ት ደረጃውና የሰራበት ቦታዎች፣... የፓለቲካ ተሳትፎው ፣...የቤተሰቦቹና ጓደኞቹ የኃላ ታሪክ ፣...የሚያዘወትርበት መጠጥ ቤት፣...ዝሙተኝነቱ በዶሴ ይዘጋጃል: ...ለእነ ሞንጆሪኖ ፣ ማሚትና ካህሳይ እንዲደርስ ይደረጋል።

ምርቃቱ ሁለት ሳምንት ሲቀረዉ ግምገማ ይጀመራል። ...ሰልጣኙ አሰቀድሞ ኑሃዜውን እንዲያቀርብ እድል ይሰጠዋል። ቅንጥብጣቢ ያቀርባል፣...በደንብ እንዲናዘዝ እነ ሞንጆሪኖ ያስፈራራሉ። ...ከደበቃት ትንሽ ይጨምራል።...አሁንም በደንብ እንዲያወጣ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል። ...የለኝም ይላል... እነ ሞንጆሪኖ አስቀድሞ የተዘጋጀውን ዶሴ በመገላለጥ አውጫጭኙን ይጀምራሉ።

ዶንቦስኮ ብዙ ሰው ፃታና ዘር ሳይለይ ጨርቅ አሰጥሏል። ...በስልጠና ላይ እያለ ከተኛበት ዶርም በለሊት ልብሶቹን አውልቆ ወንዝ ሊገባ ሲል የተያዘ ባለስልጣን ነበረ። ...የምን ማስተርስ በማለት ፈረንጅ ሀገር ያገኘዉን ዲግሪ የቀዳደደም ይገኛል።

ዶንቦስኮ ለዘመናት ተደብቀው የነበሩ ወንጀሎችን እንዲወጣ አድርጓል።...በደርግ መዋቅር ውስጥ ሆኖ አንድ ወጣት ተኩሶ የገደለ ለሊት ባሰማው ቅዠት ምክንያት እውነቱን እንዲያወጣ ተወጥሮ በመያዙ ፣ ድርጊቱን የፈፀመበት ቦታ ሐዲሮ አሳይቷል።...ክፍለ ሀገር በሚሰራ ሰአት ሚስት አግብቶ ሁለት ልጅ ወልዶ በመጥፉት አዲሳባ ሌላ ትዳር መስርቶ የሚኖር ካድሬ ተጋልጧል።...ዶንቦስኮ ብዙ ቤቶች አፍርሷል።... አራት ልጆች የወለዱ ባለትዳሮች ከዶንቦስኮ ግምገማ በኃላ ወረቀታቸውን በፍርድ ቤት ቀደዋል። ... በግፍ ስማቸው የጠፉት በርካታ ናቸው። ... የኮልፌ ወረዳ አሰተዳደር የነበረችው ቆንጆየዋ ንግስቲ"ሌላ የተደበቀ አመል ቢኖርብሽ እንጂ ባልሽን ፈተሽ ፣ልጆችሽን ይዘሽ ቤተሰብ ጋር አትገቢም " ተብላ አንድ ሙሉ ቀን ተገምግማለች። ...በኤች አይ ቪ ኤድስ መያዙንና ባለቤቱን በበሽታው ማጣቱን በመናገሩ "ያየሁት አይለፈኝ ስለሆንክ ነው " ተብሎ ወቀሳ የደረሰባት የከተማው ቁልፍ ባለስልጣን ነበረ። ...ዶንቦስኮ በሰላም ተመርቆ መውጣት ግመልን በመርፌ ቀዳዳ እንደሚባለው ነበር። ...ከምርቃቱ በኃላ እውነተኛ ስማቸው ተትቶ በወጣላቸው ቅፅል የሚታወቁ አሉ። ...እስቲ ስላንዳንዶቹ የጨለማው ዘመን ሰለባዎች ጥቂት እናውጋ :

***

በአንድ ወረዳ ላይ አስተዳደር ሆነው የሚሰሩ ሁለት የቅርብ ጓደኛሞች ነበሩ። ...ብዙ የጋራ ሚስጥሮች ነበሩዋቸው። ...ተራቸው ይደርስና አብረው ዶንቦስኮ ይገባሉ። ...አንደኛው በግምገማዉ ሙቀት ይግላል። ...ጓደኛውን ይህን አልተናዘዝክም በማለት መቆሚያ መቀመጫ የሳጣዋል። ...እነ ካህሳይ ማንቁርቱ ላይ ይቆማሉ። ...እናም አንድ ለሊት ጓደኛሞቹ ካደሩበት ዶርም የድረሱልኝ ጩኸት ይሰማል። ...ካድሬው ተሯሩጦ ሲደርስ ወለሉ በደም ተጨማልቋል።...ገምጋሚው የተሰነጠቀች ጆሮውን በእጁ ደግፎ ይንፈራፈራል። ...ተገምጋሚው የዘነጠለበት አፉ ቫንፓየር አስመስሎታል!...ከዛን ቀን በኃላ ሁለቱም የዳቦ ስም ወጣላቸው: ...ተገምጋሚው ታይሰን ! ገምጋሚው ሆሊፊልድ!

***

አንድ የማዘጋጃ ቤት ሹምና በእሱ ስር ያለች ኤክስፐርት ዶንቦስኮ ይገባሉ። ...የሹሙ ግምገማ ይደርሳል። ...ኤክስፐርቷ አለቃዋ በደንብ እንዳላወረደ ገልፃ እሱ ላይ ያላትን ሐሰ ታቀርባለች። ...በወጣ በገባ ቁጥር እነደሚያስቸግራት ፣ በረባ ባልረባው ቢሮው እንደሚጠራት ፣ የሚሰጣት ስጦታ በእሱ ደሞዝ የማይታሰብ እንደሆነ ትገልፃለች። ...መጀመሪያ አካባቢ እሷም እንደተቸገረችለትና ባለትዳርና የልጆች አባት በመሆኑ በድርጊቷ እንደተፀፀተች የራሷን ጨምራ ትናዘዛለች። ...በዚህ ምክንያት እንደተጣሉና በእሷ መደብ ላይ ሌላ ተረኛ ሴት ለመመደብ እየሞከረ እንደሆነ ትገልፃለች። ሹሙ ይክዳል። አለመግባባት የተፈጠረው ስራዋን በአግባቡ ስላልሰራች እንደሆነ ያስረዳል።...መስቀለኛ ጥያቄ ከግራ ቀኝ ተወረወረለት።...አላመነም።...የሶስት ቀን ማሰላሰያ ጊዜ ተሰጠው።
ቀኑ ደርሶ ቢጠየቅ ለውጥ የለም። ...ደንቦስኮዎች ስራ ጀመሩ።

" ከስድስት ወር በፊት አዋሳ ሐዲሀ ነበር? ለምን ሐድክ ? ከማን ጋር?"

"ከኤክስፐርቷ ጋር፣ ለስብሰባ።"

" ስብሰባው ማን የጠራው ? በምን አጀንዳ ላይ? የትኛው አዳራሽ? አንተና እሷ ገንዘብ ለመቆጠብ ነው በአንድ ሆቴል ተመሳሳይ ቤርጮ ያዛችሁት?" ጥያቄዎች ተዘረገፉ ፣የሆቴሉን ሰምና የማደሪያ ቁጥሩ ሳይቀር ተነገረዉ።

ሹሙ ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ። ...ያሳለፈውን ጊዜ ዘከዘከ። ...ዋሸቶ ገዜ ስላጠፉ ይቅርታ ጠየቀ። ...ካድሬው በተለመደ መልኩ ሹሙን _ክሊንተን፣ ኤክስፐርቷን_ ሞኒካ ሊኦንስኪ ብሎ ሰየመ።

***

አንለይ የምትባል የአቃቂ መስተዳድር ካቢኔ አባል ነበረች።...እሷን ጨምሮ የአቃቂ ካድሬዎች የግንቦት 20 በአል ምክንያት በማድረግ የምግብና መጠጥ ተሀድሶ ያዘጋጃሉ። ...ከድርጅት ወጭ አድርገው ሁለት የበግ ጥቦት በመግዛት ጠባብሰው ይበላሉ፣ ይጨፍራሉ።

ግብዣው አልቆ ወደ ቤቷ ለመሐድ መኪና ልትገባ ስትል ጥቦቷን ያረደው የጥበቃ ጓድ ወደ እሷ መጥቶ የበግ ቆዳውን ምን ላድርገው ብሎ ይጠይቃታል።...ትዝ ሲላት ጠላ ሻጭ አሮጊት ጎረቤቷ የደንበኞቻቸውን ምቾት

ለመጠበቅ በቆዳ ላይ ቆዳ መደቡ ላይ ያነጥፉሉ። ... እናም ዘበኛውን ማንም ስጠኝ ቢልህ እንዳትሰጥ ትለዋለች። በሚስማር ወጥሮ እንዲያደርቅላት ታዘዋለች።...ከሳምንት በኃላም ደበሎወን ለአሮጊቷ በመስጠት ምርቃቷን ትቀበላለች።

ክብርት አስተዳዳሪዋ ዶንቦስኮ ስትገባ የአርጊቷ ምርቃት ወደ እርግማን ተቀይሮ ጠበቃት•••ይህ ዶንቦስኮ ነው! ...የእነ ሞንጆሪኖና ካህሳይ አገር!...

የአንለይ አፈርሳታ ላይ ያቺ ቁርበት እንደ ጅብ ቆዳ የሜርኩሪ ዋጋ ተሰጥቷት ብቅ አለች። "ከሌብነት እንዳልፀዳሽ ያመላክተታል" ተባለች። ...መወጠሩ ሲበዛባት "መውሰድ አልነበረብኝም ፣ ... ይህም ያልተሻገርኩት የሌብነት አመለካከት ስላለብኝ ነው" ብላ የቀረበላትን ሐሰ ትሰለቅጣለች...የሰማይ ስባሪዋ አንለይ!...እንቁራሪትን ዝሆን የምታሳክለው ዶንቦስኮ በዋሣ አለቀቻትም :

" አንለይ በትንሹ ስላልታመንሽ ...ለትልቁ ህዝብ አስተዳዳሪነት እምነት ልንጥልብሽ አንችልም " ተባለች። ...ዶንቦስኮን ተሰናብታ ወጣች።

***

ዶንቦስኮ ለትላልቅ ባለስልጣናትም አልተመለሰችም። በተለይም የካቢኔ አባል የነበረችው ጣይቱ አሊ (የቀድሞ ትምህረት ሚኒስትር ገነት ዘውዴ እህት) ግምገማ በካድሬዎች የትውስታ ግድግዳ ላይ ተፃፎ ቀርቷል።...ለተተኪው ካድሬ በቅቅብሎሽ ህግ መሰረት እየተላለፈ አመተ -አለም ተሻግሯል።

የጣይቱን ግምገማ የመሩት ሁለቱ ካህሳዩች ነበሩ :

ቀዩ ካህሳይ " ጣይቱ መጀመራያ የት ትሰሪ ነበር"

"ሴቶች ማህበር "

" ከዛ በኃላስ "

"የዞን ስራ አሰፈፃሚ "

ጥቁሩ ካህሳይ "ማነው ወደ ዞን ያመጣሽ "

"የዞኑ ፕሮፕጋንዳ ሀላፊ፣ ...< ዴት>... እንደራረግ ነበር "

"ቀጥሎስ ? "

" የከተማውን ካቢኔ ተቀላቀልኩ። ...የብአዴን ስራ አሰፈፃሚ ከሆነውጋር ግንኙነት ነበረን..."

ቀዩ ካህሳይ " የእኛ ክሊአፓትራ! እንኳንም ስሙን አልጠቀሽ።"

...በእለቱ ተባረረች። ...ሻንጣዋን ሸክፉ ወደ ቤቷ ሐዴች።

ከዛ ቀን ጀምሮ ካድሬው ከጣይቱ ጋር በተናጠል ማውራት ፈራ። ...አቶ አርከበ እቁባይ ወደ መዲናይቱ ተመድቦ ሲመጣ መልካም ግንኙነት ፈጠሩ፣ ... ድጋሚ የማህበራት ማደራጃ ቢሮ ሀላፊ አድርገው ሾማት። ...ብዙም ሳትቆይ እሷ "ተከድኖ ይብሰል " ባለችው ምክንያት አባረራት።

...ከሁለት አመታት በኃላ ኢህአድግ ቢሮ ተመድቤ በምሰራበት ወቅት አንዲት ጠዋት አለቃዬ ወደ ነበረው ህላዌ ዬሴፍ ቢሮ ሐዴኩኝ። ... ያለወትሮው የቢሮው በር ብርግድ ብሎ ተከፍቷል። ገና ኮቴዬን ሲሰማ ጠርቶ አስቀመጠኝ። ... ተግባባን። ...ጣይቱ እንግዳ ማረፊያ ሶፉላይ ተቀምጣለች። ... በስጦታ ወረቀት የተጠቀለለ ነገር እያሳየኝ አሜሪካን ሀገር ለእረፍት ሐዳ መምጣቷን

ነገረኝ~ለጣይቱ አሜሪካን የውሀ መንገድ ነው። ...አፍታም ሳትቆይ አርከበ እቁባይ እንዴት ደጅ እንዳስጠናትና እንዳንከራተታት በእንባ ታጅባ ዘረገፈችው። ህላዌ አፅናናት።...ለጓዶች ንገሪያቸው አላት። በመሀል ስልክ መጥቶበት ማወራት ጀመረ።

እኔና እሷ ተጋጠምን... ፊራኃት...

መጥፎ ስም !

የማወራው ግራ ሲገባኝ "ትዳር መሰረትሽ እንዴ ተስማምቶሻል" አልኳት። ... "ባገባማ ማንም የሚስቱ ጭን ሙቀት ሲበርድበት እቶኑን ለማስተንፈስ አያንከራትተኝም" አለች።

"ታዲያ ለምን አታገቢም?"

" እድሜ ለዶንቦስኮ ስሜ ከአዲሳባ እስከ አሜሪካ ጠፉ!...ሰንቱ በአደባባይ የሚሰራው ጉድ እያለ የሰው ይፈተፍታል" አለች፣ ...

እውነቷን ነበር።

ከጥቂት ቀን በኃላ በየትኛው መንገድ እንዳለፈች ባላውቅም የአዲሳባ ኢህአድግ ሴቶች ሊግ የመስራቾች ፕሬዝዳንት ሆና ከእኛ ጋር ተቀላቀለች : ...

" I am a single lady! " የእሷ ጓደኛና የስራ ባልደረባችን ገጣሚ ፍሬህይወት አያሌው በዛፈችው ግጥም እንደገለፀችው።

***

(ጦላይ : ኮረኔል ነጋሽ) – – – የሚጻፍ

***

የደኢህዴን ማእከላዊ ኮሚቴ ...የአዲሳባ ምክትል ፕሬዝዳንት... የአብዬታዊ ዲሞክራሲ ዲያቆን ጓድ ካሊድ አብድርሀማን።

ካሊድ ደንበኛ አክሮባት ሰሪ ነበር። በተለምዶ በኢህአድግ ግምገማ ላይ ቀድሞ የተናዘዝ ራሱን ለማየት ዝግጁ ነው ተብሎ ያለምንም ቅጣት ይታለፋል። ለሌሎችም በአርአያ የሚጠቀስ ይሆናል። የካሊድ መገለባበጥ ይህንን ታሳቢ ያደረገ ነበር።

ይህ ለዶንቦስኮ አይሰራም። የእነ ካህሳይ፣ ማሚት፣ ሞንጆሪኖ ግዛት።

ማሚት " ካሊድ ስለትምህርት ደረጃህ ንገረን። ኢህአድግን ስትቀላቀል ዲግሪ አለኝ ብለህ ፣ እኛም የምርጫ መወዳደሪያ ፓስተር ላይ ከፎቶግራፍህ በታች በፓለቲካል ሳይንስ ዲግሪ ብለን ልደታን በአንተ ፓስተር አጥለቀለቅናት።"

ካሊድ " የፓርላማ ማህበራዊ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴው ዶክተር አህመድ ነው ያታለለኝ። ከካናዳ ስለመጣህ ኢህአድግና የመዲናይቱ ህዝብ እንደተማረ ይቆጥርሀል ፣ በንግግርህ ውስጥም ጠንካራ እንግሊዘኛና አብዬታዊ ቃላት ተጠቀም አለኝ።"

ማሚት " አትዘባርቅ! የተጠየከው የትምህርት ደረጃህ ስንት ነው ? እሱን ብቻ መልስ።

" ዲፕሎማ ! "

ማሚት " የምን ዲፕሎማ?"

" High School "

ማሚት " ነገ አምጥተህ ልታሳየን ትችላለህ?"
ካሊድ " ዶክመንቶቼን ክካናዳ ገና አልአስመጣሁም። ጊዜ ከተሰጠኝ በቅርብ ጊዜ አስመጣለሁ።"

እነ ማሚት የፓርላማው ማህበራዊ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው ዶክተር አህመድም ጉዳይ እንዲጣራ ለኢህአድግ ቢሮ አስተላለፉ... ካሊድ ብቻውን ሞቶ አያውቅም።

***

የኢትዬጲያን ፓርላማ ለአስር አመታት የተከታተለ ሰው የአንድ ትልቅ አዛውንት ገፅታ ከፊቱ ላይ አይጠፉም። የፀጉሩ ጮፈሬ፣ ገብስማነትና አበጣጠሩ የናይጀሪያውን ታዋቂ ፀሀፊ ወሌ ሾይንካም ስለሚመስል የእሱም ቅጽል ስም ይሄ ምሁር ሆኗል። ፀሀፊ ወሌሾይንካም የኖቬል ተሸላሚና የፓለቲካ አቀንቃኝ ነው። ለአፍሪካ ስነ ጽሁፍ እድገት ላበረከተው አስተዋጽኦ የአዲሳባ ዩንቨርስቲ የክብር ዶክትሬት አበርክቶለታል።

የኖቬል ተሸላሚውን ቅፅል እንደተሰጠው የሚያውቀው የእኛ ሰው ቢያንስ በወር አንድ ቀን በፓርላማ ውስጥ ተቋማትን ሲያፋጥጥ ይታያል። ለፓርላማ አባላት አለም አቀፍ ህጐችንና ተሞክሮዎችን የአቅም ግንባታ ይሰጣል። ይህ ብርታቱ ከምሁርነቱ ጋር ተደምሮ የማህበራዊ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ሆነ። በተጨማሪም ከፓርላማ እየተወረወረ የአዲሳባን ፓለቲካ ስራ ድጋፍ እንዲሰጥ ተመደበ..."ዶክተር!" አህመድ።

ይህ ከምእራቡ አለም የመጣ ምሁር የኢህአድግን ክብር ከፍ አደረገ። ከእነ ዶክተር ካሱ ኢላላ ቀጥሎ ኢህአድግ አለኝ ከሚላቸው አብዬታዊ ምሁራን ጐራ ውስጥ ተቀላቀለ። ደኢህዴን ደረቷን ነፉች። ሁላችንም ክብርና ሞገስ አጐናፀፍነው።

ከእለታት በአንዱ ቀን ለፓርላማው የህግ ጉዳዬች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ለሆነው አባይ ነብሶ ከዶንቦስኮ መልእክት ደረሰው። አባይ ሰውየውን ጠርቶ " ዶክተር አህመድ ዶክትሬትህን ለማህደር ስለፈለግነው ነገ ይዘህ በአስቸኳይ እንድትመጣ " አለው።

ሰውየው ደነገጠ። ታሞም ለጥቂት ቀናት ተኛ። የማይቀር እዳ ነውና አባይ ነብሶ ጋር ቀርቦ:
" በተለምዶ ሰዎች ዶክተር ስለሚሉኝ ነው እንጂ ዶክትሬት የለኝም " አለው። እንግዲያውስ አለኝ የምትለውን ዶክመንት ይዘህ ና ተባለ። የተከበሩ አቶ አህመድ ስድስት ወር የሰለጠነባትን ሰርተፍኬት ይዞ መጣ... ኢትዬጲያዊው ወሌሾይንካም!!

***

በኢኮኖሚ ነክ ጉዳዬች ላይ ኢህአድግ፣ ተቃዋሚዎችና የንግዱ ማህበረሰብ አመራሮች ክርክር እያደረጉ ነው። ኢህአድግን ወክለው የቀረቡት ግለሰብ ሚኒስትር ናቸው። በኢኮኖሚክስ የሙያ ዘርፍ የዶከተሩ ሚኒስትር! የደኢህዴን ቁንጮ ካድሬ !

ክርክሩ እየጋለ ሲሄድ አንዲት መርዘኛ ጥያቄ ወደ ክብር ሚኒስትሩ ተወረወረች። ቴሌን ለምን ፕራቬታይዝ አታደርጉትም የምትል። ዶክተሩም ፈገግ

ብለው " ቴሌን ለግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ መልቀቅ የፈርንጅ ላም እንደመስጠት ይቆጠራል " የሚል ምላሽ ሰጡ። አዳራሹ ሳቀባቸው። እሳቸውም የጐፈረ ጺማቸውን እየጐተቱ አብረው ሳቁ።

የዶክተሩ መልስ የከነከነው አንድ የምጣኔ ሀብት ባለሙያና የንግድ ምክር ቤት አመራር " ክቡር ሚኒስቴር ለካስ ድርጅቶችን ወደ ግል የማዞራችሁ መርህ የሚመነጨው በፈረንጅና አባሻ ላምነት በመከፋፈል ነው ? " የሚል ጥያቄ አነሳ። የክቡር ሚኒስትሩ አፍ በማስትሽ ተጣበቀ።

አቶ መለስ ጊዜ ማጥፋት አልፈለገም። ለአባይ ነብሶ ደውሎ " እባክህ የአህመድን እንዳጣራኸው ሁሉ በነካ እጅህ የካሱ ኢላላንም አጣራልኝ " አለው።

ተጣራ። በትክክልም ሚኒስትሩ ዶክተር ናቸው።

***

***

በሰፈሩት ቁና ሆነና ነገሩ የህውሀት መሰንጠቅ የሞንጆሪኖን ፍጹማዊ አገዛዝ አንዲያከትም አደረገዉ። ... በእርግጥ የተስፈማርያምን የህል ውግዝ ከማርዬስ አልደረሰባትም: ከአቶ መለስ ተግሳፅ ውጭ ። አቶ መለስ እንዲህ አላት : -

" *ሞንጆሪኖ አዲሳባን የለውጥ ማዕበል ውስጥ አስገብተሽ ታስተካክያለሽ ብለን ነበር የላክንሽ።አንቺ ግን የድርጅቱን አደራ በልተሽ ከጀርባ ሰታደራጂ ከረመሽ። ኧረ ለመሆኑ ምን ጐድሎብሽ ነው? እነ ስዬን ሳታዉቂያቸው ቀርተሽ ነው፣ አብረሽ ድርጅቱ ላይ ገመድ ልታጠልቂ የነበረው?"*

ሞንጆሪኖ ተንሰቅስቃ አለቀሰች። ...ስጋ ስውአትን ጠርታ ሁለተኛ እንደማይለመዳት ቃል ገባች። ... እግሩ ላይ ተደፍታ ይቅርታ ጠየቀች፣ ...ከእነተወልደ ጋር እንዴት እንደተሰማጠረች ዘከዘከች፣...የህቡዕ እንቅስቃሴው ከስድስት ወር በፊት በአዲሳባ መጀመሩን አስረዳች።... በአዲሳባ ያሉት የዞን ሊቀ መናብርት ትልቁ ስራቸው ይህ መሆኑን ገለፀች ፣...ካድሬዎቹ አባዝተው ስለበተኑት ወረቀት ዘከዘከች።... አቶ መለስ አመናት።

ፊቱን ወደ እሷ አነሳ...

ራራላት።

...እንደ ቀድሞ ባሏ አባይ ፀሀዬ የምህረቱ ተቋዳሽ አደረጋት።...የዘመናዊ እውቀት ማነስ የፈጠረው ችግር ሊሆን እንደሚችል በመግለፅ ፣ የቀለም ትምህርት እንድትማር ፈረንጅ ሀገር ሰደዳት።... ትምህርቷን አጠናቃ እንደመጣች ጓሏን ጠቅልላ መቀሌ ገባች። የትግራይን ካቢኔ ተቀላቀለች። ...ለአቶ መለስ ያላትን ታማኝነቷን በተግባር አሳየች፣ እሱም ካሳውን በቁመ- ተቀበለ።...

ወግን ወግ ያነሳዋል እንዲሉ አቶ መለስ፣ አባይና አዲሱ ለገሰ ተራራ ላንቀጠቀጡት ሚስቶቻቸው የጋራ ቃል ያላት ስም አውጥተውላቸው ነበር :-አቶ መለስ ስለ ሚስቱ ለኢትዬጲያ ህዝብ " እሳት ትተፋለች ያለችውን ከመተግበር ውጭ አማራጭ የለኝም" አለ።... አቶ መለስ ይህን መልእክት ያስተላለፈው በተዘዋዋሪ መንገድ በእመቤቷ ላይ በህውሀት ውስጥ ከፍተኛ ማጥላላት እያነሱ

ለነበሩት ካድሬዎች ነበር።...አቶ አባይ ለካድሬዎች " ሞንጆሪኖ እሳት ታዘንባለች ...እሷ የቤታችን ራስ፣ እኔ ደግሞ ዘውድ ሆነን ኖርን" ሲል አዲሱ ደግሞ ለብአዴን ጓደኞቹ " ሚስቱ እንወይ ገ/መድህን በእሳት መጫወት ትወዳለች" አለ። ...የእሳት ዝናብና ጨዋታ የሰለቻቸው ሁለቱ ጓዶች የበረሀ ውል አፈርሰዋል... በደም የተገነባው ቃል ኪዳን ተረከዘ ሎሚ በሆኑ የከተሜ ቆነጃጅት ተነጥቋል... አባይ መቼም ይዋጣለታል!!

***

የአቶ መለስ ግብአተ መሬት ከተጠናቀቀ በኃላ አልፎ አልፎ ኢቲቪ እመለከታለሁ ...ታዲያ አንድ ምሽት ቲቪውን ወደ ቻናል 280 ሳዞረው የኢትዬጲያ ፓርላማ እየቀረበ ነበር•••የፓርላማ አባላቱ ለአንድ ሚኒስቴር መ/ ቤት ጥያቄ ያቀርባሉ፣ ...ከህዝብ የተሰበሰቡ ጥያቄዎችን እንድታቀርብ ለአንዲት የፓርላማ አባል እድል ተሰጠ። ክብርት የፓርላማ አባሏ መናገር ጀመረች።... የሴትየዋን ድምፁ አውቀዋለሁ።...ካሜራው ቀጥሎ ስሟን አሳየ :•• "ፈትለወርቅ"•• አላውቃትም። ...ቀስ በቀስ ምስሏን ሲያሳይ ሴትየዋ ሞንጆሪኖ ናት ...ለካስ ሞንጆሪኖ ፈትለወርቅ ሆናለች።... የአዲሷ ፈትለ ወጣትነት የድሮዋ ሞንጆሪኖ ነው።...አፍታም ሳይቆይ የህውሀት ጉባኤ በመቐለ ተካሔደ፣ ፈትለወርቅ የህዉሀት መዕከላዊ ኮሚቴና ፓሊት ቢሮ አባል ሆነች። ...የህውሀት ፓሊት ቢሮ የፓርቲው የመጨረሻ ወሳኝ አካል ሲሆን ዘጠኝ አባላት አሉት : ...የክልሉ ፕሬዝዳንት ከሚስቱ ፣ ...አባይ ፀሀዬ ከሞንጆሪኖ እና ወ/ሮ አዜብ በመንፈስ የሀምሳ አመት የህውሀት ጉዞን ከቀየሰው መሀንዲስ ጋር : ...ዘመናዊው ቦናፓርቲስታዊ ዝቅጠት !!

***

ኢህአድግን ከአዲሳባ ያባረረው ምርጫ 92 :

ብዙዎች የአዲሳባ ህዝብ ምርጫ ካርድ በምትባል ሰላማዊ ወረቀት ኢህአድግን የቀጣው በምርጫ 97 አድርገው ይቆጥራሉ። ይህ የተሳሳተ ነው። ... ኢህአድግ ላይ የመዲናይቱ ህዝብ የወሰነው በ2 ኛው አገር አቀፍ ምርጫ 1992 ዓ •ም• ነበር። ...በዚህ ምርጫ ኢህአድግ አሳፋሪ ሽንፈት ተከናንቧል።...ይህ ብዙ ያልተነገለት ታሪክ በወቅቱ መሪ ተዋንያን በነበርን ካድሬዎች ዘንድ የእሳት ዳር ጨዋታ ሆኖ ሰንብቷል...በእንደዚህ መልኩ ለንባብ እስኪበቃ ድረስ።

በምርጫ 92 ኢህአድግ መሸነፉን አስቀድሞ ካረጋገጠ በኃላ የተከተለው ስትራቴጂ የህዝቡን ወሳኔ ባይቀይረውም ለማጭበርበር ጠቅሞታል።... በምርጫው ማግስትም የህዝቡን ተቃውሞ ለማስቀየስ የተለያዩ አገር አቀፍ አጀንዳዎች ተቀርፀው ተግባር ላይ መዋላቸው ጉዳዩ እንዲለዝብ አድርጐታል።...የሐኙ አለም አቀፍ ፍርድ ቤት ባድመ ላይ የሰጠው ብይን ተከትሎ" የጦርነቱ ድል በፍርድ ቤት ተደገመ " የሚል የተሳሳተ መግለጫ በመስጠት የመዲናይቱን ህዝብ መስቀል አደባባይ እንዲወጣ ያደረገው በምርጫው ሳምንት ነበር።

በጨፌ ግምገማ ባልተጠበቀ መልኩ የምርጫ 92 ውጤት ተነሳ፣... አሊ አብዶ በዝረራ በተሸነፈበት ሁኔታ ፕሬዝዳንት መሆኑ ተነገረ።...

በነዋሪው የተቀጣ መሪ ተባለ።

አሊ ለማስተባበል የተሸነፈው በህዝቡ ሳይሆን በአዲሳባ ንግድ ም/ቤት ህቡዕ አደረጃጀት እንደሆነ አስረዳ ...እሱ የተወዳደረበት አካባቢ የሙስሊሙ ማህበረሰብ ስለሚበዛ ፣ ይህ ማህበረሰብ ደግሞ በዘላቂነት የኢህአድግ ደጋፊና መራጭ እንደሆነ ሰለሚታወቅ ወጥቶ እንዳይመርጥ ግፊት ተደርጉበት እንደነበር ገለፀ። ...ይህ ቃል ለአመታት ባህታዊውን ሲያታልልበት የነበረበት ነው። ...ነዋሪውን በብሔር መፈረጁ ሳያንስ በሀይማኖቱ በመከፋፈል የሀይል አሰላለፍ መስራት በኢህአድግ የተለመደ አሰራር ነው። ...አቶ አሊ ይህን ስለሚያውቅ ነበር ማምለጫ መንገድ ያዘጋጀው።

ኢህአድግ በመሸነፉ ላይ ጥያቄ አንስቶ የተከራከረ አልነበረም። ...ይልቁንስ ሽንፈቱን የሚያሳዩ ሰፋፊ መገለጫዎች ቀረቡ። ...የውጤቱ መቀልበስ ተከትሎ በመዲናይቱ ተከስቶ የነበረው አመፅና ነውጥ በአጭሩ ባይቀጭ ሊከሰት የነበረው

አደጋ በሰፊው ተነገረ። ...በተስፉ እጦትና የከተማ ችጋር የተመታው ነዋሪ አደራጅቶ የሚያነቀሳቅስ ተቃዋሚ ቢኖር ኖሮ ዛሬ እንደዚህ ተቀምጦ ስለአዲሳባ የምንነጋገርበት ሁኔታ እንደማይፈጠር ተገለፀ። ...ምርጫውን ለመቀልበስ በተግባር የዋለው ፀረ ዲሞክራሲ ቢሆንም አብዬታዊ ዲሞክራሲን እንደታደገው አስተያየቶች ቀረበ። ...በተለይም የደህንነቱ ሹም ኢሳያስ ወ/ጊዮርጊስ " የታደግናችሁ እኛ ነበርን " ብሎ በኩራት ሲደሰኩር መስማት አስገራሚ ነበር። ...በእያንዳንዱ ወረዳ በእሱ ፊት አውራሪነት የተሰራውን ሸፍጥ በዝርዝር ማቅረቡ አስገመተው : ከአንድ የደህንነት ባለስልጣን የሚጠበቅ አልነበረም፣...ምንም እንኳን ሀቁ ኢሳያስ የተናገረው ቢሆንም።

ኢህአድግ በሁለተኛው አገር አቀፍ ምርጫ በአዲሳባ ክልል ም/ ቤትና የፓርላማ ተወካዬች እንደሚሸነፍ ያረጋገጠው አስቀድሞ ነበር። ... በወቅቱ የቅድሚያ ዳሰሳ ጥናት እንዲሰራ የታዘዘው ዋልታ ኢንፎርሜሽን ማእከል ኢህአድግ ችግር እንደሚያጋጥመው ሲፈራ ሲቸር አቀረበ።... የአዲሳባ ንግድ ም/ ቤት በበኩሉ እንደ ዋልታም ባይሆን የተቃዋሚ እጩዎች በሰፊው ም/ ቤት እንደሚገቡ አመላከተ።

ይህንን ተከትሎ ኢህአድግ የምርጫውን ዲሞክራሲያዊነት የሚያጠፉ ሶስት እርስ በራስ የሚመጋገቡ ስትራቴጂዎች ነደፈ። ...እነዚህ አቅጣጫዎች የከተማውን ህዝብ በመከፋፈል በነፃ ምርጫ የራሱን አስተዳደር እንዳይመሰርት የሚያደርጉ ነበሩ። እስትራቴጂዎቹ : በእጩ ምዝገባ ወቅት በተቃዋሚ ፓርቲ እጩዎች ውስጥ ለኢህአድግ የሚሰራ አሰርጉ ማስገባት ፣ ...በየምርጫ ወረዳ ምርጫ ቦርድ በሚፈቅደው መሰረት የተፎካካሪ እጩዎችን ብዛት እስከመጨረሻው መለጠጥ ፣... በምርጫው የመጨረሻ ቀናት የተቃዋሚ ፓርቲ እጩዎችን በማሳመን ራሳቸውን ከምርጫ እንዲያገሉ ማድረግ የሚሉ ነበሩ።

ይህንን ተግባር በዞን የምንገኝ ካድሬዎችና የደህንነት ሀላፊዎች በጥብቅ ሚስጥር መፈፀም እንደሚገባን ተገለፀ።

(*** በተሻሻለው የኢትዬጲያ የምርጫ ህግ መሰረት በአንድ የምርጫ ክልል ለህዝብ ተወካዬች የሚወዳደሩ እጩዎች ብዛት እስከ አስራ ሁለት ሊደርስ እንደሚችል ተደንግጓል።***)

***

በጨፌው ግምገማ ምርጫ 92 ሙሉ ቀን ፈጅቶ ባለመጠናቀቁ ለበነጋታው ጠዋት ቀጠሮ ተያዘለት።እንደተለመደው ከፍስሀ ጋር ተያይዘን ወደ ራስ ሆቴል ሔድን : _

እውነት እውነቱን ለመነጋገር...

ትኩረታችንም ምርጫ 92 ሆነ፣ ... አድማሳችን ደግሞ እኔ እና አሱ ከመራነው ዞን ሁለት የሚነሳ ሆኖ መላ አዲሳባን የሚያዳርስ...ተጨባጭ መገለጫዎችን አንስተን የኢህአድግን ሽንፈት አረጋገጥን። ከመስቀል አደባባይ _አየር ጤና ; ከፈጥኖ ደራሽ _ላፍቶ የተዘረጋውን ዞን ለመከታተል አራት የዞኑካድሬዎችና ከካዛንችስ ፍስሀ መአሲ በመሆን ወረዳዎችን (ወረዳ 20;21;23;24) ተከፋፈልን፣ ... የአራቱም ወረዳ ውጤቶች ለየቅል ነበሩ :

***

ፍስሀ መአሲ ወረዳ 23(ላፍቶ ክ/ ከተማ) ለመምራት ሳርቤት ከተመ። ... በወረዳ 23 ኢህአድግ ያስቀመጠው የመጀመሪያ እስትራቴጂ በተሳካ ሁኔታ ተፈፀመ። ... መምህር ዳኛ የሚባል የባስሊዎስ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር መኢአድን ወክሎ ለመወዳደር ፍቃደኛ ሆነ ... አሸንፎም ወደ ምክርቤት ገባ...የተሰጠውን ተልእኮ በአግባቡ አከናወነ።

የምክር ቤት ስብሰባ ከመካሔዱ ሶስት ቀን አስቀድሞ መኢአድን ወክሎ የሚናገረው መምህር አንተነህ ምን እንደሚያቀርብ ሪፓርት ይደርሰናል፣ ... እኛም አሰቀድመን ምላሽ በማዘጋጀትና ማን ምን እንደሚናገር በመከፋፈል ሰውየውን እንቀጠቅጣለን። ... ፍስሀ መምህር ዳኛን ከማስገባት ውጭ በሌላው አልተሳካለትም።... በወረዳው የተወዳደሩት (የካቢኔ አባልና የኢኮኖሚ ዘርፍ ሀላፊ የነበረው ቶፊቅን) ጨምሮ በዝረራ ተሸነፉ።

***

እኔና የዞን ደህንነት ሀላፊው የትውልድ ቦታዬ ወደ ሆነው ወረዳ 24 ኮልፌ ቀራንዬ ሔድን። ...ኢህአድግ ያስቀመጠውን ሁለተኛ እስትራቴጂ መተግበር ጀመርን። ... ለፓርላማ መቀመጫ የሚፎካከሩ እጩዎችን ምዝገባው ሊጠናቃቅ አንድ ቀን ሲቀረው ከ6 ወደ 12 አሳደግን። ይህም ... በተለይም ኢህአድግ ሙሉ ለሙሉ ይሸነፍባቸዋል ብለን በለየናቸው አካባቢዎች በቀበሌያቸው ተቀባይነት ያላቸውን ግለሰቦች ለየን፣ ... ግል እጩዎች ሆነው እንዲወዳደሩ አግባባናቸው። ፍቃደኛ የሆኑትን ፒትሽን አባሎቻችንን አስፈርመን ለምርጫ ቦርድ አስረከብን፣ ...ፓርላማ ተመርጠው ሲገቡ የሚያገኙትን ጥቅም አጋነን አሳየናቸው፣ ... የስልጣን ተስፈኞች ሆኑ።

በወረዳ 24 ለፓርላማ የቀረቡት የተቃዋሚ ፓርቲ እጩዎች ከአራት በላይ መሆናቸው እናየራሳቸው ደጋፊ ያላቸው መሆኑ በተጨማሪነት ጠቀመን ...ኢድአፓን ወክሎ የቀረበው ክንፈሚካኤል ደበበ (አበበ ቀስቶ) በወጣቶች ፣ ...ክፍሌ ጥግነህ (የቅንጅት አመራር የነበረ) በምሁራንና ነጋዴው ማህበረሰብ ፣...የትግረ ወርጂው ሀጂ መሀመድ በሙስሊም ዘንድ ተቀባይነት ነበራቸው።... የሰርቶ አደር ጋዜጣ አዘጋጅ የነበረው ታዲዮስ ታንቱ በቀድሞ ስርአት ደጋፊዎችና ወታደሮች ድጋፍ አግኝቷል። ... ሌሎቹ 7 የግል ተወዳዳሪ እጩዎች በእኛ ድጋፍ የቀረቡ ሲሆን ኢህአድግን መምረጥ በማይፈልገው አካባቢ ድምፅ እንዲሻሙ የተዘጋጁ ናቸው። ... ኢህአድግ በእጩነት ዶ/ ር ቶፊቅ አብድላሒን አቀረበ። ለዶክተሩ ታሳቢ የተደረገው የእስልምና እምነት ተከታይ መሆኑና የግል የህክምና ተቋም ባለቤት ስለሆነ ታዋቂነት አትርፉል በሚል ነበር ...

ጉድና ጅራት ከወደኃላ ቢሆንም!

ምርጫ ተጠናቆ ቆጠራው ሲካሔድ የኢህአድግ እጩ 16•% ፣ አበበ ቀስቶ 14•%፣ ክፍሌ ጥግነህ 7% ፣ ታደዮስ ታንቱ 6 % አገኙ። በመሆኑም በአብላጫ ወንበር አሰራር መሰረት ከ84% በላይ ህዝብ ያልመረጠው የኢህአድግ እጩ ወደ ፓርላማ ገባ። ... ከውጤቱ ማየት እንደሚቻለው አግባብተን ካስገባናቸው የግል እጩዎች አንዱ ራሱን ቢያገል ውጤቱ ግልብጥብጡ ይወጣ ነበር፣ ኢህአድግን የወከለው ሰው ፓርላማ አይገባም ነበር።

የዶክተር ቶፊቅን አሸናፊነት ያረጋገጡት የዜሮ ድምር መጫወቻዎቹ የህገ_መንግስት አንቀፅ 54 እና የተፎካካሪ እጩዎችን ብዛት ወደ አስራ ሁለት ያሳደገው የምርጫ ህግ እርስ በራስ ተመጋግበው ነው።

የህገመንግስቱ አንቀፅ 54 (4) የምክር ቤቱ አባላት በአንድ የምርጫ ክልል ውስጥ ከሌሎች ተወዳዳሪዎች መካከል አብላጫ ድምፅ ያገኘ ተወዳዳሪ አሸናፊ የሚሆንበትን ስርአት ይዘረጋል። ... በዚህ ጉዳይ ላይ ኢህአድግ ጨፍኑና ላሞኛችሁ አይነት የመከራከሪያ ጭብጦችን ስለሚያቀርብ ሁኔታውን ገለጥ ለጥ አድርጐ ማየት አስፈላጊ ይሆናል። ... በአቶ በረከት የሁለት ምርጫዎች ወግ መፅሀፍ ላይ የእነዚህ ቁም ነገሮች ጠንካራ ጐን ተብራርቶ ቀርቧል።

ኢህአድግ በመጀመሪያ የሚያቀርበው መከራከሪያ ይህ የህገ_መንግስት አንቀፅ በዲሞክራሲያዊ ሰርአቶች ከሚታወቁት የምርጫ ስርአቶች አንዱ የሆነውን የአብላጫ ድምፅ መጠቀሙን እንደሚያመላክት ነው።...ርግጥም ፓርቲው እንደሚለው በዲሞክራሲያዊ ግንባታ እስከ አሁን የሚታወቁት የምርጫ ስርአቶች የብዙሀን ድጋፍ፣ የተመጣጠነ ውክልና እናየአብላጫ ድምፅ ስርአቶች ሲሆኑ ኢህአድግ የሚጠቀመው በመጨረሻ የቀረበውን ነው፣... ይህ የምርጫ ስርአት ከተወዳዳሪዎች መካከል አብላጫውን ድምፅ ያገኘ አሸናፊ የሚሆንበት ሲሆን በመሰረቱ ዲሞክራሲያዊ ገፅታ ያለውና ምርጫውን ለማስፈፀም ቀላልና ወጪ ቆጣቢ ነው።

የኢህአድግ ሁለተኛ መከራከሪያ በአለማችን የዲሞክራሲያዊ ግንባታ ቁንጮ ላይ የተቀመጡት እነ እንግሊዝና አሜሪካ የሚጠቀሙት የአብላጫ ስርአት እንደሆነ በመግለፅ የዲሞክራሲያዊነቱን መተማመኛ እማኝ እንደሆኑ ማሳየት ነው።

አቶ በረከትና ኢህአድግ ይህንን አመክንዬ ሲያቀርቡ አንድም ጊዜ ከጀርባ በታኮነት ያስቀመጡትን በምርጫ ጣቢያዎች የሚወዳደሩ እጩዎችን ብዛት የሚያሳየውን የምርጫ ህግ አይጠቅሱም። ... ከዚህ በተጨማሪም በእንግሊዝና አሜሪካ የአብላጫ ድምፅ ስርአት ዲሞክራሲያዊ የሆነበት ምክንያት ስንት ፓርቲዎችና ግለሰቦች እረስ በራስ እንደሚፎካከሩ ለመግለፅ አልፈለጉም...በአሜሪካን ከሞላ ጐደል የሁለት ፓርቲ ስርአት የተዘረጋ ሲሆን በምርጫ ወሳኝ ተፎካካሪ ሆነው የሚቀርቡት የሁለቱ ፓርቲዎች እጩዎች ናቸው።... በእንግሊዝም ቢሆን የመድብለ ስርአት ቢዘረጋም በምርጫው ብርቱ ተፎካካሪ የሚሆኑት ከሶስት አይበልጡም።

የኢህአድግ የአብላጫ ስርአት ከምርጫ ህጉ ጋር በመመጋገብ በህዝብ ያልተመረጠን ሀይል እንዴት ወደ ስልጣን እንደሚያመጣ ከብዙሀን የድጋፍ ስርአት ጋር በማወዳደር እንመልከት፣... ለማሳያ እንዲሆን የወረዳ 24 ምርጫ ውጤት ማየቱ የበለጠ ግልፅ ያደርገዋል።

ከዲሞክራሲያዊ የምርጫ ስርአቶች አንዱ የሆነው የብዙሀን ድጋፍ ስርአት የሚመራበት መርህ በአንድ የምርጫ መወዳደሪያ ክልል ውስጥ አሸናፊ ሆኖ የሚመረጠው ከሀምሳ በመቶ በላይ የሆነውን የህዝብ ድምፅ ያገኘ እጩ ነው።... አንድ ተፎካካሪ ከሀምሳ በመቶ የድምፅ ብልጫ ካላገኘ ሁለተኛ ዙር

ምርጫ ይካሔዳል።... በሁለተኛው ዙር በተወዳዳሪነት እንዲቀርቡ የሚደረጉት በመጀመሪያው ዙር በድምፅ ብልጫ አንደኛና ሁለተኛ የወጡትን ተወዳዳሪዎች ይሆናል።... ይህ የምርጫ ስርአት አብዛኛውን የህዝብ ድጋፍ ያገኘ እንዲመረጥ ስለሚያደርግ ተቀባይነት ያለው መንግስት ለመመስረት ያስችላል።

የኢህአድግ የምርጫ ስርአት የብዙሀን ድጋፍ የሚከተል ቢሆን ኖሮ በ92 ምርጫ በወረዳ 24 የሁለተኛ ዙር ተፎካካሪ ሆነው የሚቀርቡት ዶክተር ቶፊቅና አበበ ቀስቶ ይሆኑ ነበር... ምርጫው ቢጭበረበር እንኳን የአበበ ቀስቶ አሸናፊነት ሳይታለም የተፈታ ነው።

በተቃራኒው ኢህአድግ ..... ይቀጥላል

ጨዋታችን የፔንዱለም ጉዞ ነውና ጉድና ጅራት ወደተባለው የዶክተሩ ወግ እንመለስ:

የእጩ ምዝገባ ከተጠናቀቀና መቀየር የማይቻልበት ደረጃ በደረሰበት ወቅት በዶክተር ቶፊቅ አብድላሒ ላይ መረጃዎች መጉረፍ ጀመሩ። ...በየመድረኩ የሚቀርብበት ተጨባጭ ኢንፎርሜሽኖች ጆሮ የሚያቶሉ ሆኑ።... በከፍተኛ ወንጀል የሚያስጠይቁት እስከመሆን ደረሱ፣... ዶክተሩ በቴዎድሮስ አደባባይ አካባቢ ከፍተኛ ክሊኒክ ነበረው። ... በወቅቱ ለሴት እህቶቻችን የድህነት ማምለጫ መንገድ ተደርጐ የተወሰደው ወደ አረብ ሀገር መሔድ ነበር። ... ዶክተሩ ይህን በመገንዘብ ወደ አረብ ሀገር በተለይም ወኪል ፅ/ ቤት አለኝ ብሎ ወደተናገረው የመን ሀገር በቀላሉ እንደሚልክ ያስ ታውቃል። የአጠቃላይ ህክምና ምርመራ ኤድስን ጨምሮ ከእያንዳንዷ ሴት ከአንድ ሺህ ብር በላይ ይቀበላል... ከአምስት መቶ በላይ እህቶቻችን የተጠየቁትን ከፍለው ምርመራውን በመውሰድ ገዞአቸውን ይጠባበቃሉ። ... ተስፉቸው ሲሟጠጥ ቅሬታወደ ማሰማት ይሸጋገራሉ። ... ሁኔታው በዚህ ደረጃ እንዳለ ነበር ዶክተሩ የኢህአድግ እጩ ሆኖ የቀረበው።

አንድ እሁድ እሱንና ሌሎች የክልል ምክርቤት እጩዎችን ለማስተዋወቅ ወረዳ 24 ቀበሌ 15 (አየር ጤና) አዳራሽ የህዝብ ስብሰባ ጠራን። ...አንዲት ሴትእንባዋን እየዘራች ዶ/ ሩ ለክፉ ቀን ያስቀመጠችውን ወርቅ ማሸጡ ሳይበቃ የኤድስ ቫይረስ ሳይኖርባት አለብሽ እንዳላት አጋለጠች... እሱ የሰጣትን የምርመራ ወጤትና ሌላ ክሊኒክ ተመርምራ ነፃ የሆነችበትን ወረቀት አሳየች።

በቀጠለው ሳምንት በቀበሌ 09 (ፈጥኖ ደራሽ) አዳራሽ በጠራነው ስብሰባ ሌላ ሴት ከባለቤቷ ጋር መጥታ ተመሳሳይ ነገር አቀረበች...

አንገታችንን ደፋን...መረጃውን ለካዛንችስ ስውሩ መንግስት ብናቀርብም የድርጅቱ ህልውና ይቀድማል በመባል ውድቅ ተደረገብን።

አቶ በረከት ስምኦን በሁለት ምርጫ ወግ መፅሀፉ በገፅ 126 ላይ " ... ኢህአድግ ከምንም ነገር በላይ ህዝቡን ያከብራል ፣ ይፈራልም። ሁሌም እንደሚለው ከህዝብ ውጭ ሌላ ጌታ የለውም " ይላል፣ ...በዚህ አባባል ግልባጭ ስሌት መሰረት ደ/ ር ቶፊቅ አምስት አመት ያልመረጠውን ህዝብ ወክሎ በፓርላማ ተቀመጠ፣ ቀጥሎም በየመን የኢትዬጲያ ባለ ሙሉ አምባሳደር

ሆኖ በመሾም ለአምስት አመታት አገለገለ፣... በየመን የጀመራትን ስራ ከግብ አድርሶ ወደ ሀገሩ ተመለሰ።

***

ወደ ወረዳ 20 ያመራው ካድሬ የተቃዋሚ አንድ እጩ አስወጥቶም፣ የግል ተወዳዳሪዎች በግፉ አስገብቶም ሳይሳካለት ቀረ። የወረዳ 20 ህዝብ ኢህአድግን ከፓርላማም ከአዲሳባ ክልል ምክር ቤትም አባረረ ... በወጣው እጩ ምክንያት አዘነልኝ የተባለች ጨዋና መልካም ሴት የአዲሳባን ምክር ቤት ተቀላቀለች። አዘነልኝ... አሜሪካን በባህላዊ ሙዚቃ የሚያደምቃት ድምፃዊ ውሽንፍር እህት!!

***

የወረዳ 21/22 ነዋሪም ተመሳሳይ እርምጃ የወሰደ ቢሆንም በቆጠራው ወቅት በተሰራ ማጭበርበር ኢህአድግ ተረፈ።

በወረዳው የትግራይ ህዝብ ይበዛል በማለት " የትግራይ ህዝብ በወረዳ 21 ኢህአድግን ታደገ " የሚል ማጭበርበሪያ እንዲናፈስ ተደረገ።

የወረዳ 21 /22 ምርጫ እንዲመራ የተመደበው ነባር የህውሀት ታጋይ ገ/ እግዚአብሔር "እግዜሩ" ይባላል፣...

መጠሪያውና ግብሩ ለየቅል የሆነ ሰው !!...

አንዳንዴ ስምን ሰይጣን ያወጣዋል ።

የካዛንችሱ ስውር መንግስት ለእግዜሩ ተነግረው የማያልቁ ወንጀሎችን እንዲሰራ ሙሉ ስልጣን ሰጠው... እግዜሩ በስርአቱ ውስጥ ካሉት ሶስት ቁልፍ የዞን ካድሬዎች አንዱ ነበር፣... መቀመጫውን ሜክሲኮ በማድረግ ሰቅጣጭ ግፎችን ሰርቷል : - ብዙ ሰወችን ያለወንጀላቸው አሳስሯል፣ ከስራ አባሯል፣አገር ጥለው እንዲወጡ አድርጓል።... የግለሰቦችን፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ቢሮዎችን በለሊት በመክፈት አስበርብሯል፣ ዶክመንት ኮፒ አድርጐ አውጥቷል።

በእግዜሩ የስለላ መዋቅር የመጀመሪያውን ገፈት የቀመሰው የዞኑ ሊቀመንበር የነበረ መላኩ የሚባል ካድሬ ነበር... መላኩ በከተማዋ በህቡዕ የተቀጣጠለውን የጉራጌ መራሽ አብዬት ከሚመሩት የጉራጌ ልጆች አንዱ ነበር... የአብዬቱ ጥንስስ ወደ አመፅ ተቀይሮ በትላልቅ ሰልፎች መታጀብ ሲጀምር (መስቀል አደባባይን ጨምሮ) መላኩ ግንባር ቀደም መሪ ነበር።...

እግዜሩ በበኩሉ የሊቀመንበሩን እያንዳንዷን እንቅስቃሴ በአይነ ቁራኛ መከታተል ይጀምራል፣ ስልኩን ይጠልፋል፣ ማታ ማታ ቢሮውን ከፍቶ በመግባት ዶክመንቶችን ኮፒ አድርጐ ይወጣል።... መላኩ አማተር አብዬተኛ ነበርና ከላይ እስከ ታች የተዘረጋውን የሚስጥር አደረጃጀት አሳልፎ ይሰጣል...ለጥንስሱ መጨናገፍ አስተዋጽኦ ያበረክታል... የፓለቲካ ህይወቱም በዛው ፍፃሜ ያገኛል።

እግዜሩ በዞኑ ውስጥ የሚገኙና ጥብቅ ክትትል የሚደግባቸውን ተቋማት ማስተር ቁልፍ በማዘጋጀት ዶክመንቶችን ያሰርቃል፣ ኮፒ ያስደርጋል...ቢሮአቸው በየጊዜው እንዲሰበር ካደረጋቸው ውስጥ በወረዳ 21 ጽ/ ቤት ግቢ ውስጥ የሚገኘው የአዲሳባ ሴቶች ማህበር፣የልደታና ጐፋ ቤተክርስትያንና የኢትዬጲያ

ሰብአዊ መብት ጉባኤ (ኢሰመጉ) ይገኙበታል...

የአዲሳባ ንግድ ምክር ቤት ከእግዜሩ የስለላ ወጥመድ ማምለጥ አልቻለም፣ ...የንግድ ምክር ቤቱ የተወያየባቸው አጀንዳዎችና ቃለ ጉባኤዎች በቀጥታ ይደርሱታል። ... ይህንን የሚፈፅምለት ታደለ ይመር የሚባል በንግድ ምክር ቤት ውስጥ ከፍተኛ ስልጣን ላይ የሚገኝ ሰው ነበር...

ልማታዊ ባለሀብት...

(*** ታደለ ይመር በንግድ ምክር ቤት ውስጥ የአገልግሎት ዘርፍ ሀላፊ ነው...ይህ ሲጠሩት አቤት ሲልኩት ወዴት የሆነ ሰው በካድሬው ዘንድ "የእርጉ ዝንብ" የሚል ስያሜ ተሰጥቶት ነበር... የምይገኝበት ቦታ የለም ። በኢትዬጲያ ታሪክ ውስጥ አሳፋሪ ተግባሮች ከፈፀሙ ሰወች አንዱ ነው... በተለይም በኤርትራ መገንጠል ወቅት የኢትዬጲያን ህዝብ ወክለ ተብሎ ኤርትራ በመሐድ " አኛየኢትዬጲያ በተለይም የአማራ ተወላጅ የሆንን ሰወች ስለፈፀምንባችሁ ግፍና በደል ይቅርታ እንጠይቃለን" የሚል ይፋዊ ንግግር አድርጓል...የምንግዜም ተወዳጁ ኢቲቪ ይቅርታውን ተቀብሎ አስተጋብቷል።...ቅሌት አንዴ ከተጀመረ አያልቅምና የኢትዬ-ኤርትራ ጦርነት ሲጀመር ደግሞ ንግድ ምክር ቤቱን በመወከል ጦር ግንባር ድረስ በመሐድ " ሻእቢያ ይደመሰሳል፣ የኤርትራ ህዝብም ልኩን ያውቃል" የሚል ቀራርቶ አሰምቷል...

ታደለ ታድሷል...

የማይጣላ ጭንቅላት

ተሸክሞ ይዞራል ።***)

እግዜሩ ትላልቅ የሚባሉ የኢህአድግ ካድሬዎችን ሳይቀር ደም እንባ አስለቅሷል፣ ...በምርጫ 92 በወረዳ 21 ኢህአድግን ወክላ ለፓርላማ እጩ ሆና የቀረበችው የትምህርት ሚኒስትሯ ወ/ ሮ ገነት ዘውዴ ነበረች፣... እግዜሩ ደግሞ ምርጫውን በበላይነት ከመምራት በተጨማሪ በዚሁ ወረዳ ለከተማ ምክር ቤት እጩ ሆኗል...

ምርጫው ጥቂት ሳምንታት ሲቀሩት የሁሉም ወረዳ እጩዎችን የስራ ስምሪት ለመስጠት ሜክሲኮ ዞን ጽ/ ቤት ጠራናቸው።... ወይዘሮ ገነት ሀገር ሰላም ብላ በስብሰባው ታድማለች... ጠንከር ያሉ የግምገማ ነጥቦች ሲነሱ እሷም ፀሀዩ መንግስታችንን እንዲጠላ ያደረጉት የተበታች ካድሬዎች ናቸው የሚል ወቀሳ አዘል አስተያየት ትሰጣለች... በንግግሯ የተበሳጨው እግዜሩ :

"... ገነት እኔ ህይወቴን ሙሉ ከህዝብ ጋር እየተገናኘው የድርጅትና ፕሮፓጋንዳ ስራ ሰርቻለው... የህዝብ ሀሳባ አዳምጫለሁ፣... እውነቱን ንገረኝ ካልሽ እንዳንቺ ህዝብ የሚጠላው ሰው አጋጥሞኝ አያውቅም!... ከሁሉም የሚያሳዝነው ስትወድቂ እኛንም ይዘሽ መገንደስሽ ነው!" አላት።

ክብርት ሚኒስትሯ ተንሰቅስቃ አለቀሰች።

" እኔ የኢህአድግን የትምህርት ፓሊሲ በቁርጠኝነት ከማስፈፀም ውጭ ምን ያደረኩት ነገር አለ? ፓሊሲው ትውልድ ገዳይ እንደሆነ እየገለፀ ያለው ህዝቡና ምሁራኖች ናቸው፣... እኔ ፓሊሲ የመቀየር ስልጣን የለኝም! ... ስለዚህ

ህዝቡ የጠላኝ በፓሊሲው ምክንያት ነው።... ርግጥ ከኢህአድግ በተቃራኒ የቆመው ዶክተር በየነ ጴጥሮስ " ዬዲት ጉዲት! " የሚል ስያሜ ሰጥቶኝ በህዝቡ ጥላቻ ላይ ቤንዝን ጨምሯል።" የሚል አስገራሚም አነጋጋሪም ምላሽ ሰጠች...

ክብርት ሚኒስትሯ በፓሊሲው ትውልድ ገዳይነት ላይ ጥርጥር የላትም፣ ... ባለስልጣናት ልጆቻቸውን ከተቻለ እንደ ሽማግሌው ስብሀትና አርከበ እቁባይ ከሁለተኛ ደረጃ ጀምሮ ውጭ ሀገር ፣ካልተቻለ ደግሞ የሀገሪቷን የትምህርት ስርአት በማይከተሉ የሀገር ውስጥ ምርጥና ውድ ትምህርት ቤቶች እንደምናስተምር ታውቃለች፣...የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት አስረኛ ክፍል ማለቁ ህብረተሰባዊ ውግዘት እየደረሰበት እንደሆነ ለሁሉም ግልፅ ነው፣...በዩንቨርሰቲ ከሚማሩ ተማሪዎች ስማቸውን በአግባቡ መፃፍ የማይችሉ መኖራቸው ሀቅ ነው... የኢትዬጲያ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ብቃትና አለም አቀፍ ተቀባይነት ቁልቁል ወደ ታች አየተምዘገዘገ እንደሆነ የእለት ሪፓርቷ ሆኗል፣

ነገርን ነገር ያነሳዋል እንዲሉ እስከ 1990 አ• ም• ድረስ በኢትዬጲያ የመንግስት ዮንቨርስቲዎች የመጀመሪያ ዲግሪ ያገኘ ሰው በአሜሪካን ሀገር መጥቶ አቻ ግመታ ቢያሰራ እንደ እኩሌታ ዲግሪ ይገመትለት ነበር።... ከላይ ከተጠቀሰው አመት በኃላ ግን የኢትዬጲያ ዲግሪ እንደ ሶስተኛ አመት ተማሪ ይቆጠራል...ከአሜሪካ ጋር አቻ ለማድረግ የፈለገ ሰው ከአመት ያላነሰ ጊዜ እንደገና ትምህርት ቤት ገብቶ መማር ይጠበቅበታል...

እናም ክብርት ሚኒስትሯ ራሷ ባልፈጠረችውና መቀየር በማትችለው ሽውራራ ፓሊሲ ምክንያት "ዬዲት ጉዲት" የሚል ስያሜ ወጥቶላታል...ፕሮፌሰር በየነም ቢሆን የፈሪ ዱላ ካልሆነ በስተቀር ፓሊሲውን ማን እንደቀረፀው ጠንቅቆ ያውቃል...በነካ እጁ የፓሊሲውን ባለቤት "ግራኝ መሀመድ !" ቢለው የጀግንነት ካባ እናለብሰው ነበር።

ያም ሆነ ይህ የሴትየዋ የለቅሶ ምንጭ ከቁጥጥሯ ውጭ በሆነ ነገር እንደሆነ ቆይቶ የተገለፀለት እግዜሩ" ... ገነት እኔ ያልኩት ጊዜ ሰጥተሽ ከእኛ ጋር እንደ እጨ ተንቀሳቀሽ ነው " ብሎ አለዘባት... ወርቃአበባ የምትባል የዞን ካድሬ አብራት እንድትዞር መደበላት።

ክብርቷ የትምህርት ሚኒስቴር ስራዋን ትታ ወረዳ 21 ሰነበተች።

እግሯ እስኪላጥ ተንከራተተች። በመንደር ውሻ እስከመነከስ ደረሰች።

ምርጫው ሳምንት ሲቀር ባለችው እሁድ አመሻሽ ላይ ሚኒስትሯና ወርቃአበባ ለግምገማ ዞን መጡ። ካድሬዎች እስኪሰባሰቡ ድረስ እኔ ቢሮ አረፍ አሉ...

የሚኒስትሯ አይን ከወትሮው በተለየ እንደ ስጋ ቤት አንፓል አብርቷል...ከጫት ላይ ተነስታ የመጣች ትመስላለች...

ወርቅአበባን ማን ያምናታል!?

ቅስቀሳው እንዴት እየሔደ እንደሆነ ጠየኳቸው...ሚኒስትሯ እንደ ክዋክብት የደመቀ አይኗን ተክላ "የዛሬው የምረጡኝ ቅስቀሳ ቡና አብሮ በመጠጣት ነው ተብሎ ሀያ ቤት ሔጀ ሀያ አንድ ስኒ ቡና ተጋትኩ" አለችኝ።

ወርቃአበባ ከአፉ ተቀብላት "አየሽ አይደል ገነት! ሴቶቹ እንዴት እንደሚወዱሽ!... በተለይ የልደታ ቤተክርስትያንን ችግር እንደምትፈቺላቸው ቃል ስትገቢ የዳዊት ዘር ለዘላለም ይግዛን አሉሽ "በማለት ዉሎአቸውን አዳነቀች...

እኔን ደግሞ በጥቅሻ መታችኝ... የልደታዋ ንግስት!... ወርቅአበባ።

ክብርት ሚኒስትሯ ደስ አላት።

ጨዋታችንን ቋጭተን ወደ ስብሰባ አዳራሹ ስንሔድ ወርቅአበባን ወደ ጎላ ጐተት አድርጌ

" አንቺን ማን ያምናል? በርጫ ወቅጠሽ አጠጣሻት እንዴ? አይኖቿ ጡት መያዣ አስፈለጋቸው " አልኳት።

" የእግዜሩን ግምገማ ለማስቀየስ ነው። ታገል (ባለቤቷ ነው) ከቤት ስንወጣ ለእግዜሩ አንብቢለት ብሎ ከሚወደው ገጣሚ መፅሀፍ ጽፎ ሰጥቶኛል። "

" እስቲ አንብቢልኝ?"

" እግዜሩ ስብሰባ ሲያልቅ ገነትን ወደ ጎላ ካስቀራት አነብልሀለሁ።"

ሳታስበው ወረቀቱን መነጨኳት።

በጠራ ጨረቃ በኩለ ለሊት፣

አይኖቿ ሲያበሩ እንደክዋክብት፣.....

ሳልጨርሰው መለስኩላት። በቃሌ አነበነብኩ።

" አንተና ታገል?..."

" ይልቁንስ ቅድም የዳዊት ዘር? ምናምን ያልሽው። አልገባኝም?"

"ተዋት ባክህ ! የልደታ ህዝብ ምን እያለ እንደሆነ አልገባትም!" በማለት ጣቷን አየቆጠረች ዘረዘረች: -

አፈ ጉባኤ ዳዊት ዩሀንስ የሚኒስትር ገነት ዘመድ፣

የጤና ጥበቃ ሚኒስትር ዶ/ ር ከበደ የሚኒስትር ገነት ባለቤት ፣የምርጫ ቦርድ ሀላፊው አሰፋ ብሩ የሚኒስትር ገነት ዘመድ፣ የአዲሳባ ካቢኔ ወይዘሪት ጣይቱ አለ የሚኒስትር ገነት እህት...

ከብዙ አመታት በኃላ እኔም በተራዬ ለወርቃአበባ በቀጭኑ ሽቦ አንድ በግራ ሌላ በቀኝ ጨምሬ ነገርኳት : -

የኮሙዩኒኬሽን ጽ/ ቤት ጭንቅላት ገነነ አሰፋ የአምባሳደር ገነት ወንድም ፣

የኢህአድግና የበረከት ራስ ምታት ፕሮፌሰር ዳኛቸው አሰፋ የአምባሳደር ገነት ወንድም ...

የዳዊት ዘሮች...

ዘላለም ይግዙን!

***

እግዜሩ በቂርቆስ የትግራይ ተወላጅ ስለሚበዛ ኢህአድግ በአብላጫ ድምፅ እንደሚያሸንፍ አስቀድሞ እንዲሰራጭ አደረገ... የምርጫ አስፈፃሚዎችንና ታዛቢዎችን ከድርጅት መለመለ... ምርጫ ቦርድን ተክቶ ኦረንቴሽን ሰጠ ...የፓሊስ ሀይሉን በስም ዝርዝር ለይቶ በየጣቢያው አስመደበ... የወረዳ 21/22 ከፊል የምርጫ ኮሮጆ አስቀድሞ ተገለበጠ...ተቃዋሚዎች መረጃ ደርሷቸው ለምርጫ ቦርድ ቢያመለክቱም በሬ ወለደ እንደሆነ በምርጫ ቦርድ ሀላፊው አሰፋ ብሩ መግለጫ ተሰጠ...

የዳዊት ዘር!

***

እግዜሩ የካዛንችሱ መንግስት ሲንኮታኮት አብሮ ወደቀ...በአዲሳባ የእነ ተወልደን ቡድን በመደገፍ ቀንደኛ ሆኖወረቀት የበተነውና ካድሬውን በፀረ - መለስ ያደራጀው እሱ እንደሆነ ሞንጀሪኖ አጋለጠች።... የህቡዕ አደረጃጀቱ ማታ ማታ ስብሰባ ሲያደርግ የነበረው በሜክሲኮ እንደሆነ ተረጋገጠ... ማምለጫ መንገድ ሲያጣ አቶ መለስን ይቅርታ ጠየቀ... አቶ መለስ እንደ ሌሎቹ አልራራለትም "በዛገ ቢላዋ የድርጅቱን አንገት ዘክዝከሀል " ብሎ በቅጣት መልኩ የትግራይ በረሀ ሰደደው።

እግዜሩ ለሶስት አመት ያህል የትግራይ ተራራን ሲቧጥጥ ከረመ...መስመር ማስተካከሉና እርምት መውሰዱ ሲረጋገጥ የተዘጋጀለት የሙስና ፋይል በጐንዬሽ አደንዲደርሰው ተደረገ ፣... "ሲያዩህ ሌባ ትመስላለህ" ብሎ እንዳላባረረ የእሱ ንቅዘት የማያልቅ ሆኖበፉይል ተጠርዞ ተሰጠው ... በየአመቱ በሚሊዬን ብሮች የሚዘረፍበትን የአየር ጤና ኬላ (ጉምሩክ) የቅርብ ዘመዱን ሀላፊ አድርጐ ሲያሰራ እንደነበር፣ ...ሲኖርበት የነበረውን የቀበሌ ቤት ለወንድሙ ስም አዙሮ መስጠቱ ፣...ኤርትራዉያን ናችሁ በማለት በግፍ ከቪላ ቤታቸው ካፈናቀለ በኃላ እሱ ገብቶበት መኖር እንደጀመረ፣...በምርጫ 97 ማግስት ኮልፌ ቀራንዬ ላይ አርከበ እቁባይ አይን መሬት እንደሰጠው...
እናም እግዜሩ ይህንን የታሸገ የሙስና ፋይል ይዞ አዲሳባ መጣ፣... አቶ መለስ የኢትዬጲያ ሬዲዬና ቴሌቭዥን የትግርኛ ፕሮግራም ዋና ሀላፊ አድርጐ ሾመው...ከህውሀት የአድርባይ ፊት አውራሪ ከሆነውዘርአይ አስክዶም ጋር ተቀላቀለ...

የኢቲቪ የትግርኛ ፕሮግራም ከእንጨትነት ወደ "አሞራ ስጋነት " ተቀየረ...

እምበር ተጋዳላይ!!

***

እኔና ፍስሀ በቀጥታ ከመራናቸውን አራት ወረዳዎች ተሻግረን ወደ ሌሎቹ ሐዲን። በአብዛኞቹ በከፉ ሁኔታ የተፈፀመባቸው ነበሩ።... በተቃዋሚ እጩነት ይመዘገባሉ ተብሎ የተጠረጠሩ ነዋሪዎች እስከመታሰር የተካሔደባቸው ወረዳዎች እንዲሁ፣ እጩ ሆነው ከተመዘገቡ በኃላ የስም ማጥፉት ዘመቻ ተካሒዶባቸው ረሳቸውን ያገለሉ ነበሩ። ተቃዋሚዎች የምርጫ ታዛቢ እንዳይኖራቸው ተደርጓል። ... በአዲሳባ በሚገኙት 29 የገጠር ቀበሌዎች የተካሔደው ምርጫ አሳፋሪ ነበር : የኢህአድግ ታዛቢ ብቻ የነበረበት ምርጫ- - -ምርጫ አስፈጻሚው፣ቆጣሪው፣ታዛቢው በሙሉ ኢህአድግ... የገጠሪቷ ኢትዬጲያ ትንሹ ግልባጭ።

ይህ ሁሉ የማጭበርበር ስራ ተሰርቶ በነጋዴውና ህዝቡ የተቀናጀ ስራ እነ አሊ አብዶና ምክትሉ የነበረው ካሊድ አብድርሀማን የሸንፈት ፅዋ ተጐንጭተዋል፣ ምንም እንኳን በቆጠራው ሰአት በሰሩት አክሮባት ወደ ምክርቤት ቢገቡም...

በአብዛኛው ምርጫ ጣቢያዎች የተቃዋሚ ታዛቢዎች ባለመኖራቸው ቆጠራ

ተጀምሮ ሳይጠናቀቅ ለሊት ዘጠኝ ሰአት ተቋረጠ ፣ምክንያቱ ደግሞ ታዛቢዎች ስለተዳከሙ እረፍት አድርገው ይምጡ የሚል ነበር። ... በከተማዋ የተሰማራን ካድሬዎች በየዞናችን በማደር የአዲሳባን ውጤት በየደቂቃዋ እንከታተል ስለነበር አስደንጋጭ ውጤቶችን መስማት ጀመርን። ...የመጀመሪያው መርዶ የተፈራ ዋልዋ መሸነፍ ሆነ፣ ለተፈራ ከልቤ አዘንኩኝ...

የዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት እስረኛ።

ቀጥሎ የደረሰን የአሊ አብዶና ካቢኔዎቹ ሆነ ፣ ሁሉም ላይ ህዝቡ በትሩን አሳርፉል : ካሊድ (ም/ ል ፕሬዝዳንት) ፣ ታጋይ ማሚት (አስተዳደር ዘርፍ) ፣ ጣይቱ (የምክር ቤት ሀላፊ)፣ ቶፊቅ (ኢኮኖሚ ዘርፍ) ...

ጠዋት ታዛቢዎች ተመልሰው ቆጠራ ሲካሔድ የነበረው እንዳልነበር ሆነ፣ ... ኮሮጆዎች ግልብጥብጣቸው ወጣ፣... አሊና ካሊድ ቶፊቅና ጣይቱን ትተው አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ከመሀል ኮከብ ያላትን ባንዲራ እያውለበለቡ ማዘጋጃ ቤት ገቡ።

***

ህገ -መንግስት በጠረባ !

ወቅቱ ጥቅምት 1994 አ• ም• ነበር : -የአዲሳባ ምክር ቤት አዳራሽ አስቸኳይ ጥሪ በተደረገላቸው የፌዴራልና ከተማ ካድሬዎች፣ የፍርድ ቤት ባለስልጣናትና ዳኞች፣ የፓሊስ አዛዦች ተሞልቷል... ከዚህ በተጨማሪም የአካል ጉዳተኛ በሆኑት ግለሰብ የሚመራው የአያት መኖሪያ ቤት ስራ ድርጅት ሀላፊዎች በስብሰባው ተገኝተዋል።

አጀንዳው "መሬት ለአልሚዎች በማስረከብ ዙሪያ ያጋጣሙ ችግሮችና መፍትሔዎቻቸው " የሚል ነበር... ህግ አውጭውን፣ ተርጓሚውና አስፈፃሚው በጥድፊያ ያገናኘው አጀንዳ ይህ ነበር።

የፕሬዝዳንት አሊ አብዶ ፕሮቶኮል ሹም ጤናዳም በየሴክተሩ የመጡትን ሹማምንት አቴዳንስ ወሰደ።... ሁሉም መገኘቱ ሲረጋገጥ በውስጥ በር በኩል የፕሬዝዳንቱን ቢሮና አዳራሽ በምታገኘው በር አሊ አብዶ፣ የፌዴራል ጉዳዬች ሚኒስትር አባይ ፀሀዬ ፣የፌደራል ፓሊስ ኮሚሽነሩ ወርቅነህ ገበየሁ ፣የፍርድ ቤቶቹ ፕሬዝዳንቶች መንበረ ፀሀይና ደሳለኝ ፣ የአዲሳባ ፓሊስ ኮሚሽነሩ በፍቃዱ ቶሌራ ተከታትከው ገቡ።

የህግ ምሁሩ ኮሚሽነር በፍቃዱ አጠገቤ መጥቶ ተቀመጠ፣... ቀልደኛና ቀላል ሰው ስለሆነ እንግባባለን፣ የሀይማኖት ተቋማትን አብረን አፍርሰናል። አስገንብተናል።... ሰላምታ አሰጣጡ የወትሮ አ ልሆንብኝ ሲል ወደ ጆሮው ጠጋ ብዬ " አይዞህ ! የምን መበሳጨት ነው ! ግፉ ቢል ወደ ጠመኔህ ትመለሳለህ..." አልኩት...

በአንድ ወቅት የከተማዋ ካድሬዎች በተገኘንበት የሀገር ውስጥ

ደህንነት የበላይ ሹመ ጌታቸው " የኦሮሞ ጠባብነት አለብህ!...የትራፊክ ጽ/ ቤትን በኦነግ በምንጠረጥራቸው ሰዎች አጥለቀለከው" ብሎ ገመገመው።

ርግጥም የትራፊክ ፓሊስ አለቃነት ለኦሮሞዎች ተለይቶ የተሰጠ ይመስል ነበር።ኮሚሽነሩ በጌታቸው እይታ ተበሳጭቶ "...የፓሊስ ዋና ስልጣን የመከላከል ሀላፊ መሆን እንጂ መኪና መጠበቅ አይደለም! የወንጀል መከላከሉ ደግሞ ከፌደራል እስከ አዲሳባ በማን እንደተያዘ ይታወቃል!... የሚሰማህን ንገረኝ ካልክ ከዚህ አስቀያሚ ስራ ወደ ጠመኔዬ ብመለስ ይሻለኛል " የሚል ምላሽ ሰጠ... ያንን ለማስታወስ ነበር በምክር ቤት አዳራሽ ያነሳሁበት።

"የማይሆን ነገር ለሚስትህ አትንገር ሆኖብኝ ነው "በተራው ወደ ጆሮዬ ተጠግቶ መለሰልኝ።

" አለ አብዶ ባለበት ስብሰባ ምን ጥሩ ነገር ትጠብቃለህ? " ኮሚሽነሩ ለአለ አብዶና ምክትሉ ካሊድ አብርሀማን ከፍተኛ ንቀት አለው። በከተማዋ እየተዛመተ ያለው ህገወጥነት ምንጮቹ እነሱ እንደሆኑ ደጋግሞ ይናገራል።

" ኧረ ጉዳዩ ከእነሱ በላይ ነው! ... ተወኝ ባክህ! ... የህግ ሀ - ሁ የቀመሰ ሰው በፓሊስ ሹመት ደጃፍ ማለፍ የለበትም... ዘላለሙን ከራሱ ጋር እንደተጣላ ይኖራል!" አለኝ።

አለ ጉሮሮውን ሞርዶ ስብሰባውን ጀመረ።

አስተዳደሩ በኢንቨስትመንት ደረጃ ከፍተኛ እምርታ እንዳስመዘገበ፣ ይህ አመርቂ ለውጥ የመጣው በሶስቱ የመንግስት አካላት የተቀናጀ ጥረት እንደሆነ፣ ለዚህ ተስፉ ሰጪ ውጤት በከተማዋ ህዝብ ስም ምስጋና ማቅረብ እንደሚፈልግ ተቆጥቶና ፊቱን አጨማዶ ገለፀ። ... ይህም ሆኖ በአንዳንድ የልማት ስራዎች ላይ በተለይም መሬት በማዘጋጀት ለአልሚዎች በመስጠት ዙሪያ ችግሮች እያጋጠሙ በመሆኑ ልማቱ እየተንተተ መሆኑን አስረዳ፣... አባይና ኮሚሽነር ተመሳሳይ ይዘት ያለው ንግግር አደረጉ።

አለ አጋጥመዋል ያላቸውን እንቅፋቶች መዘርዘር ጀመረ : - የከተማው ፓለቲካ ተሿሚዎች ህዝበኝነት... የፓሊስ ቁርጠኝነት ማጣት... የፍርድ ቤቶች ዳተኝነት እንደሆነ ገለፀ፣... በተለይም ዳኞች ለትንሹም ለትልቁም "ሁከት ይወገድልኝ " መስጠታቸው ልማቱ ተንገራግጮ እንዲቆም እያደረገው እንደሆነ ተናገረ።

ከተሰብሳቢው ውስጥ የማጉረምረም ድምፅ ተሰማ።

አለ ተልባ ቢንጫጫ በሚመስል መንገድ ጫጫታውን ወደ ጐን ትቶ የችግሩ ዋነኛ ምንጭ የሆነው " ሁከት ይወገድልኝ " የሚለው የፍርድ ቤት ወሳኔ የስከተለውን ችግር ለመወያየትና ለቀጣይ መፍትሔ ለማስቀመጥ እንደሆነ፣ ... በዚህ የዳኞች ውሳኔ ሰለባ በመሆን ለከፍተኛ ኪሳራ እየተዳረጉ ያሉ ልማታዊ ባለሀብቶች በስብሰባው ስለተጋበዙ ዘርዘር ያለ ማብራሪያ እንደሚሰጡ ገለፀ... የአያት መኖሪያ ቤት ስራ ድርጅትን ወክለው ለመጡት ግለሰብ ተራውን ሰጠ።

የአያት ተወካይ አንድ ሳምሶናይት ሙሉ ዶሴዎችን ለተሰብሳቢው በማሳየት ንግግራቸውን ጀመሩ።... ሰውየው ፉይል እያገላበጡ የመጀመሪያውን የፍርድ ቤት ክስ በንባብ ማሰማት ሲጀምሩ ከተሰብሳቢዎች መሀከል "ስነ -ስርአት " ..." ሰነ - ስርአት "የሚል ቃል ከያቅጣጫው ተስተጋባ።

አለ. እንደለመደው የከተማውን ካድሬ የሰበሰበ መስሎት "አንድ ሰው የጀመረውን ሳይጨረስ ማቋረጥ አግባብ አይደለም፣... ባይሆን የአያት ተወካይ አጠር አድርገው ፍሬ ፍሬውን ይግለፁ " በማለት ተሰብሳቢውን በቁጣ ገሰፀ።

"ስነ - ስርአት! "፣ " ስነ - ስርአት !"... የማያቆም ተቃውሞ።

አለ. አቧራው ታየ!

ፊቱን ወደ አባይ አዙሮ በምን ይሻላል አይኑ ገረመመው... የስነስርአት ጥያቄ ላነሱት እድሉን እንዲሰጣቸው ፈቀደለት።

የመጀመሪያው ተናጋሪ ዳኛ መሆኑን አስቀድሞ በመግለፅ ስብሰባው ህገ - ወጥ መሆኑን ማስረዳት ጀመረ... በኢትዬጲያ ብቻ ሳይሆን በአለም አቀፍ ደረጃ በፍርድ ቤት በተያዘና ብይን ባልተሰጠበት ጉዳይ ላይ አስተያየት መስጠት የፍርድ ሂደቱን ያጨናግፈዋል ተብሎ ስለሚታሰብ የተከለከለ እንደሆነ ገለፀ።... በተለይም ለፍትህ ስርአቱ አጋዥ ይሆናሉ ተብለው ከሚታሰቡት ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት፣ የፓሊስና የፀጥታ ሀይሎች ከዳኞች ጋር የክስ ጭብጦችን እያነሱ መወያየት የፍርድ ቤቶችን እጅ እንደ መጠምዘዝ ይቆጠራል አለ።

ዳኛው የሰጠው አስተያየት ስላልገባኝ ኮሚሽነርን ጠየኩት...

" ይህ የህግ ሐ - ሑ ነው። በፍርድ ቤት በተያዘ ጉዳይ ላይ የፓለቲካ ስልጣኑን የያዘው ፣ ፓሊስና ሌሎች የፍትህ አካላት ከዳኛ ጋር ቁጭ ብለው አይነጋገሩም።... የፍትህ ሂደቱን ያጨናግፈዋል ተብሎ ይታሰባል...ከውሳኔ በኃላ ብዙም ችግር ስለማያመጣ በትምህርት ካሪኩለም ውስጥ ሳይቀር አስገብተው እንደመማሪያነት የሚጠቀሙበት አሉ ።" ብሎ ምላሽ ሰጠኝ።

" አንድ ዳኛ በግልፅ የተፃፈለትን እስከተረጉመ ድረስ ምን ለውጥ ያመጣል?"

" ህግ ማቲማቲክስ አይደለም...አንድ ሲደመር አንድ ሁለት ብለህ አታቆምም"

"አንድ ሲደመር አንድ ሁለት ብቻ ነው ያለህ ማነው? ሶስት የሚሆንበት ጊዜ አለ... ሒሳቡን ለባለቤቱ ተውና ህጉ እንዴት እንደሚጨናገፍ በምሳሌ አስረዳኝ።"

" የምታውቀውን ልንገርህ... እነ ስዬ አብርሀ በሌብነት ተከሰው ፍርድ ቤት እየተመላለሱ እያለ አቶ መለስ በኢቲቪ ቀርቦ ሌብነታቸውን በዝርዝር አቀረበ... አንድ ተጠርጣሪ ከብይን በፊት እንደ ንጹህ ይቆጠራል የሚለውን አፈረሰ... የፍርድ ውሳኔው አስቀድሞ በፓለቲካ ባለስልጣናቱ ተሰጠ... ተናጋሪው በሀገሪቷ የስልጣን ማማ የመጨረሻው ጫፍ ላይ የተቀመጠ በመሆኑና የዳኝነት ስርአቱ ጠንካራ ስላልሆነ የሰውየው ቃላቶች ብይኑን ሊያዛቡት የሚችሉበት እድል ተፈጠረ። ...የህግ ሙያተኞችን ያበሳጨው እነስዬ ሌባ ስላልሆኑ ሳይሆን የአቶ መለስ ዳኛ ሆኖ መገኘት ነበር "

እንደገባኝ ነግሬው ጆሮዬን ወደ ቀጣዩ አስተያየት ሰጪ አሻገርኩት።

ሁለተኛው ተናጋሪ በተመሳሳይ ዳኛ መሆኑን አስቀድሞ በመግለፅ የአያት ተወካይ በንባብ እያሰሙት የነበረውን ጉዳይ በመዳኘት ላይ ያለው እሱ

መሆኑን ተናገረ።... በነጐድጓድ ድምፁ " ... ሌላው ቢቀር ከሳሽና ተከሳሽ በአንድ መድረክ በሌሉበት የአንድ ወገን አቤቱታ አዳምጦ አስተያየት ለመስጠት ህሊናችሁ ማሰቡ በራሱ ጥያቄ ሆኖብኛል!... ይህንን ስብሰባ የጠራችሁ አካላት የዜጐች በፍርድ ቤትና ፍርድ ቤት የመዳኘት መብት ጥሳችኃል" ብሎ ተናገረ።

ሶስተኛው ተናጋሪ በፈዝ አነጋገር " ወትሮ ስንሰማችሁ የነበረው ኢህአድግ መራሹ መንግስት ድሀ ዘመም (Pro- poor) ነው ስትሉ ነበር...በተግባር ደግሞ ለሀብታም ወግናችሁ ደሀን ከመሬቱ እንዴት እንደምናፈናቅለው ምክር ትጠይቃላችሁ ? " ብሎ ተናገረ።

አሊ አብዶ " ህገ - መንግስት ተጥሷል/ አልተጣሰም የማለት መብት ፍርድ ቤቶች የላቸውም " በማለት በአቶ መለስ የተፃፈውን የዲሞክራሲ ጥያቄ በኢትዬጲያ የሚለውን ሰነድ አነበነበ።

" ክቡር ፕሬዝዳንት! ህገ - መንግስት ተጥሷል/ አልተጣሰም ብሎ ብይን የሚሰጥ ፍርድ ቤት የሌለባት ብቸኛ ሀገር ኢትዬጲያ መሆኗን ጠፍቶኝ አይደለም፣... ሌላው ቀርቶ ህገ - መንግስትን በተመለከተ ብይን የሚሰጠው ፌዴሬሽን ምክር ቤት ውስጥ ከአራት ሚሊዬን በላይ የሆነው የአዲሳባ ህዝብም ሆነ ክቡርነትዎ እንዳልተወከሉ አውቃለሁ፣... ነገር ግን የዜጐችን በፍርድ ቤት የመዳኘት መብት የሰጠው ህገ - መንግስት በጠረባ ሲመታ ለማየት ህሊናዬ ስላልፈቀደ ነው። " በማለት ሁለተኛው ዳኛ የመለስ ምት ሰጠ።

ትነሿ አዳራሽ በሳቅ ተነቃነቀች።

አጠገቤ የተቀመጠው ኮሚሽነር በተራው ጠጋ ብሎኝ " አንጀቴ ቅቤ ጠጣ! እኔ ለወንበሬ ፈርቼ ያልተናገርኩትን ተማሪዎቼ አፈረጡት!... ይሔ አድርባይ አለቃህ እያየሁት ሰመጠ!" አለኝ።

በዚህ መልኩ መቀጠል እንደማያዋጣ የተገነዘበው አባይ ፀሀዬ የሻይ ሰአት ረፍት እንድንወስድ በማድረግ ስብሰባው እንዲቋረጥ አደረገ።... በሻይ ሰአት የፕሬዝዳንቱ ፕሮቶኮል ጤናአዳም አየዞረ ስብሰባው ላልተወሰነ ጊዜ እንዲቀር መደረጉንና ለወደፊቱ አስተዳደሩ እንደሚያሳውቅ በመግለፅ ተሰብሳቢው ወደ መጣበት እንዲመለስ መልእክት አስተላለፈ... የከተማና ዙን ካድሬዎች ወደ ኃላ እንድንቀር በተናጠል ነገረን።... አብሮኝ ሻይ ሲጠጣ የነበረው ኮሚሽነር በፍቃዱ "በል ማክሰኞ እንገናኝ! ... ታዲያ አንደ ቆምጬ አንባው ቀኝ እጅህን ለማውጣት ተዘጋጅ!" በማለት ተሰናብቶኝ ሔደ።

ወደ ስብሰባ ተመለስን።

ከመዲናይቱ ካድሬዎች ውጭ አባይ፣ ኮሚሽነርወርቅነህ፣የፍርድ ቤቶቹ ፕሬዝዳንትየሆነው መንበረ ፀሀይ እና የአያት ድርጅት ተወካዬች ተገኙ።

አቶ መንበረ ፀሀይ የጠበቀው ነገር እንዳጋጠመውና እሱ የሚመራው የዳኝነት ስርአት በፀረ - ኢህአድግ እንደተወረረ ገለፀ። መፍትሔ ይሆናል ብሎ የሚያስበው : ህገ - መንግስቱ መሰረት መሬት የህዝብ በመሆኑና የህዝቡን ወክልና ያገኘው ያስተዳደሩ ምክር ቤት በአስቸኳይ ተሰብስቦ ከዚህ ቀደም በፍርድ ቤቶች የሚሰጠው "ሁከት ይወገድልኝ " የሚቀርበትን ውሳኔ ማስተላለፍ እንደሆነ አስረዳ። ...<u>አክሎም አገራችን የምትከተለው የኮንትኔንታል (ሲቪል) ህግ ዘርፍ መሆኑን ነገረን። በዚህ መሰረት ዳኞች አስቀድሞ በህግ አውጭው የወጣ ህግ</u>

ብቻ እንደሚተረጉሙና ስልጣናቸው ህግ አውጭው ያወጣውን አዋጆችና ህጐች የመተርጐምና በዛ ብቻ የመመራት ግዴታ እንዳለበት ሰፊ ማብራሪያ ሰጠ... የአዋጁን ረቂቅ አዘጋጅቶ ለከተማው ፕሬዝዳንት እንደሚሰጥ ቃል ገባ።

አለ. አብዶ በቀጣይ ማክሰኞ በተጠራው የምክር ቤት መደበኛ ስብሰባ ላይ የመጨረሻ አጀንዳ ተደርጐ እንደሚያዝ ገለፀ።

ምክርቤት ተጠራ።

እንደተጠበቀው በምክር ቤቱ ጉባኤ ማጠናቀቂያ ላይ የማለቂያ ሰአት ተጠብቆ እንደ ተራ አዋጅ ቀረበ...

"የከተማዋን ኢንቨስትመንት ለማሳለጥ ሲባል በፍርድ ቤቶች ሲሰጥ የነበረው ሁከት ይወገድልኝ ለማስቀረት የወጣ አዋጅ... "

ግራ እጁን አውጥቼ ህገ - መንግስቱን በጠረባ ከመታው ቡድን ጋር ተቀላቀልኩ... ቀና ስል ኮሚሽነር በታዛቢነት ፎቅ ላይ ተቀምጦ ተመለከትኩት...

ቀኝ እጁን አሳየኝ።

***

የሁከት ይወገድልኝ አዋጅ አያትና ሌሎች መሰል ድርጅቶችን መረን በለቀቀ መልኩ የህዝብ ሀብት መዝረፍ በር ተከፈተላቸው።... እነሱን ተገን አድርገው በመንግስት ውስጥ ማፊያ ቡድኖች ተፈጠሩ።... ሀያት በኢህአድግ ዙሪያ ባሉ ድርጅቶችና እንደ ወይዘሮ አዜብ መስፍንን ከመሳሰሉ ቁልፍ ካድሬዎች ጋር ሽርክና ፈጠረ።

ዝናው ከጫፍ ጫፍ ተናኘ...

አያት! ዞሮ መግቢያዬ!

በመቀጠል አለ. አብዶ ሌላ ህገ -መንግስት የሚንድ ውል ከአያት ጋር ተዋዋለ... ይህ ዉል አያት የመኖሪያ ቤት ስራ ድርጅት የከተማዋን ቦታ እየሸነሸነ መሸጥ የሚያስችል መብት ያጐናፀፈው ሆነ። ... በወቅቱ ከሁለት ሚሊዬን ካሬ ሜትር በላይ የህዝብ ንብረት ለሪል ስቴት በሚል የተሰጠ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ከሲሶ በላይ የወሰደው አያት ሆነ...

ብድር በምድር እንዲሉ አያት የእነ አዜብን ውለታ ለመክፈል ተንቀሳቀሰ :

በትግራይ ውስጥ በሚካሔዱ የልማትና ሌሎች እንቅስቃሴዎች በግንባር ቀደምትነት ተሳተፈ። ... በተለይም የትግራይ ልማት ማህበር ባዘጋጀው "ከዳስ ወደ ክላስ " በሚለው ፕሮግራም ላይ ከሀያ ሚሊዬን ብር በላይ በመመደብ ትምህርት ቤቶችን ገንብቶ አስረከበ... ለጉናና ደደቢት ስፓርት ክለብ በመቶ ሺዎች ለገሰ...ኢህአድግ በግንቦት 20 እና የብሔር ድርጅቶች አመታዊ ክብረ በአልገቢ ማሰባሰብ ላይ በሚሊዬኖች በየአመቱ ከአያት ይቀበላል።... ለኢህአድግ ማእከል ግንባታ ከፍተኛ ገንዘብ ካበረከቱት ባለሀብቶች የመጀመሪያው መስመር ሀያት ተሰለፈ።

ይህንን ተከትሎ አያት ልማታዊ ባለሀብት በመባል ተደጋጋሚ ሽልማቶችን አገኘ...በአስተዳደሩ መሬት አስተዳደር ውስጥ የፈለገውን የሚሾምበት፣ የሚሽርበትና የሚያሳስርበት ደረጃ ደረሰ።... ከመሬት አስተዳደር አልፎ በምክር ቤት የሚገቡ የፓለቲካ ተመራጮችን የሚመርጥበትና የሚጥልበት

በር ወከክ ብሎ ተበረገደለት... በተግባርም አደረገው!

በአቶ በረከት መፅሀፍ ውስጥ "**ታሪክ ራሱን ደገመ : መጀመሪያ አሳዛኝ ቀጥሎ ቧልት በሚመስል መንገድ** " ተብሎ በተገለፀው ወግ በስተጀርባ ካሉት መሪ ተዋንያን አንዱ አያት የመኖሪያ ስራ ድርጅት ነበር... የዚህ ማስታወሻ ባለቤት ሀገር ጥሎ እንዲወጣ አንዱ ምክንያት ይህ አሳዛኝና ቧልተኛ ታሪክ ውስጥ ራሱን ተዘፍቆ በማግኘቱ ነበር...

እናም " እውን ታሪክ ራሱን ደገመ?" የሚል ጥያቄ በማንሳት ወደሌላ ቅሌት የተሸከመ ታሪክ እንሸጋገር... ይህ ትረካ አያት በመዘዘው ሰበብ መክንያት ጌንዱለሚ ያለ ጊዜዋ ወደ መጨረሻው ጥግ ትጮተታለች!!•••

***

ምእራፍ : እውን ታሪክ ራሱን ደገመ ?

በአቶ በረከት የሁለት ምርጫዎች ወግ መፅሀፍ ላይ በ2000 አ• ም• የተካሔደውን የማሞያና አካባቢ ምርጫ በማስመልከት " ታሪክ ራሱን ደገመ ወይስ•••?" በሚለው ርእስ ስር የሚከተለው ተፅፎ እናገኛለን : -

" ... የምርጫው ሂደትና ድምፅ ቆጠራው በሰላም ተጠናቆ ውጤቱ ሲገለፅ ብዙዎች እንደገመቱት ኢህአድግ በአዲስ አበባ ምርጫ ሙሉ በሙሉ አሸናፊ ሆነ። ከመቶ ሰላሳ ስምንት ወንበር መቶ ሰላሳ ሰባቱን በማግኘት። በነገራችን ላይ ቅንጅትም በ97 ምርጫ በመቶ ሰላሳ ስምንት ጣቢያዎች ያሉትን ወነወበሮች ሁሉ አሸንፎ የነበረ ሲሆን፣ አንድ የእነርሱ ተመራጭ በሆነ ምክንያት በመንደሉ ተክታዩን ድምፅ ያገኘው የኢህአድግ ተወካይ የአዲስ አበባ ምክር ቤት አባል ሆኖ ቅንጅት በሚመራው ምክር ቤት ሊሳተፍ ተዘጋጅቶ ነበር። በሞሞያ ምርጫ ላይ የሆነው ተመሳሳይ ነበር። ታሪክ ራሱን ይደግማል፣ መጀመሪያ ላይ አሳዛኝ፣ ቀጥሎም ቧልት በሚመስል መንገድ። " ይላል።

አቶ በረከት በዚህ ፅሁፉ የአዲሳባን ዳግም ምርጫ ባልተጠበቀ ሁኔታ በታሪክ ደጋሚነት እሳቤ መጠናቀቁን ገልጸአል። ካርል ማርክስ የሚታወቅባትን "

ታሪክ ራሱን ደገመ፣ መጀመሪያ አሳዛኝ ቀጥሎ ባልት በሚመስል መንገድ " የሚለውን በመጠቀም።

ከዚህ አንባር ሊነሳ የሚገባው ትልቁ ጥያቄ እውን ታሪክ ራሱን ደግሞል ? የሚለው ይሆናል።... የኢትዬጲያ ፓለቲካ የዜሮ ድምር ጨዋታ በመሆኑ አንዱ ቡድን ደማቅ ታሪክ ብሎ የሚገልፀው ለሌላው አሳፋሪና አንገት የሚያስደፋ ይሆናል... በግለሰብም ደረጃ ተመሳሳይ የሚሆንባቸው አጋጣሚዎች ብዙ ናቸው ... አልፎ አልፎም ቡድኖቹ ግለሰቦችን በመጨፍለቅና በእነሱ ላይ በመረማመድ ታሪክ መስራታቸውን ያውጃሉ። ለዚህ አባባል ግልፅ ማሳያ የሚሆነው በአቶ በረከት ከላይ የተገለፀው አሳዛኝ ታሪክ ይሆናል።

በዚህ አሳዛኝ ታሪክ ወስጥ እኔን ጨምሮ አቶ በረከት፣ ህላዌ ዬሴፍ፣ አዜብ መስፍን፣ አያት የመኖሪያ ቤት ስራ ድርጅትና አዲስ ነገር ጋዜጣ ተሳታፊ ሆነናል። ከላይ የተጠቀስነው በሙሉ በአንድ ግለሰብ ላይ የተረባረብን ቢሆንም ያነገብነው አላማ ለየቅል ነበር...

አቶ በረከት ባልት የተባለውን ታሪክ ለመስራት፣...ወይዘሮ አዜብ እና አያት የነበራቸውን የጥቅም ትስስር በላቀ ደረጃ ለማሳደግ ፣...አዲስ ነገር ጋዜጣ ከውስጥ ድርጅት የተገኘ አዲስ መረጃ በመሆኑ ቅድሚያውን በመውሰድ ትኩስ ዜና ለህብረተሰብ ከማድረስ አኳያ እንደሆነ ይታመናል... ጋዜጣዉ ፓለቲካውንና የጥቅም ትስስሩን ሚስጥር ባለመረዳት ቢሆንም ጋዜጣው በተጐጂው ሰው ላይ ያሳረፈው በትር ግለሰቡ ከህብረተሰቡ እንዳይቀላቀል ፣የእጅ መጠቋቆሚያ እንደሆንና ተሸማቆ አንዲኖር አድርጐታል።

ወደዚህ የህሊና ሸክም ወደ ሆነ ታሪክ ከመግባቴ በፊት ከላይ በአቶ በረከት የምርጫ 97 የአዲሳባ ውጤትን አስመልክቶ በቀረበው ወግ ላይ ተዛንፈው የቀረቡ ታሪኮች በትክክለኛው ገፅታው በማስቀመጥ ልጀምር...

" አንድ ለእናቱ "

ምርጫ 97 ሊካሔድ የሁለት ሳምንት እድሜ ሲቀረው አራት ኪሎ የሚገኘው የኢህአድግ ቢሮ በሽብርና ጭንቀት ተዋጠ... የአዲሳባን ምርጫ እንድናስተባብር የተመደብን ሀያ ከፍተኛ ካድሬዎች በየቀኑ ማታ ማታ ከአቶ በረከት ጋር ግምገማ ማካሔድ ጀመርን። የከተማው ነዋሪ ከኢህአድግ በተቃራኒ መሰለፉን ያልተገነዘበው አቶ በረከት አሀያ የማይሸከመው ስራ በየቀኑ መቆለሉን አጠናክሮ ቀጠለ... እነዚህን እንኳን ለመፈፀም በወረቀት ላይ ለማስፈር የሚከብዱ እቅዶች ሳይጀመሩ ይወድቃሉ።...

ይህንን ተከትሎ በአቶ በረከት የሚቀርበው ዘለፋና ስድብ ለጆሮ የሚሰቀጥጥ ሆነ። ... ካድሬዎቹም ኢህአድግ ቢሮ በየምሽቱ መምጣት ምድራዊ ሲኦል ደርሶ እንደመመለስ ቆጠረ... በተለይም እውነቱን ከመናገር ወደ ኃላ የማይሉ ጥቂቶች ይህ የመከራ ጊዜ የሚያጥርበት ቀን በጉጉት እየተጠባበቁም ቢሆን የህብረተሰቡን ተጨባጭ ፍላጐት ከማንፀባረቅ ወደ ኃላ አላሉም ነበር... ከእነዚህ ካድሬዎች አንዱ ተክሌ ይባላል።

ተክሌ በአዲሳባ አባላት ዘንድ በቅንነት የሚታወቅ ሎግላጋ ወጣት ነበር... በቅርቡ ለምናውቀው ሰዎች ደግሞ በቀላሉ የማይሸበር መንፈሰ ጠንካራና የህዝብ ቅሬታዎችን በአደባባይ የሚናገር ሰው ነበር፣ በአንድ ወቅት እሱ ተወልዶ

ባደገበት አቃቂ አካባቢ የሚካሔደውን የአርሶ አደሮችን የማፈናቀል ስራ በመቃወም ምክንያትአቶ አሊ አብዶ የኦነግ ታጣቂ ለጥፎበት ለረጅም አመታት ከድርጅት ካድሬነትና የመንግስት ስራ አባረረው።

አሊ አብዶ በተራው ውርደት ተከናንቦ ከአዲሳባ ንዙን ጠቅልሎ ሲወጣ በግፉ የተባረሩ ካድሬዎች እንዲመለሱ በተወሰነው መሰረት ተክሌ ድርጅት በድጋሚ ተቀላቀለ። የልደታ ክፍለ ከተማን የፓለቲካ ስራ በበላይነት እንዲመራ ስልጣን ተሰጠው።

በምርጫ 97 ለአዲሳባ ምክር ቤት ኢህአድግን ወክለው በልደታ ከቀረቡ እጩዎች አንዱ ተክሌ ሆነ... በዚህ ሳይወሰን የክፍለ ከተማው ምርጫ ስራ በበላይነት እንዲያስተባብር ይመደባል። በዚህም ምክንያት እንደሌሎቻችን ሁሉ ማታ ማታ ኢህአድግ ቢሮ እየመጣ ለአቶ በረከት ተስፉ አስቆራጭ ሪፓርት ማቅረብ ይቀጥላል... በወቅቱ ከነበረው ሀቅ ጋር ፊት ለፊት መጋፈጥ ውርደት የመሰለው በረከት ከፍ ዝቅ አደረገው "ልደታ ላይ ብንሸነፍ ተያቂው አንተ ነህ!" በሚል ማስፈራሪያ ጭምር አስጠነቀቀው።

ተክሌ ዛቻውን ከቁብ ሳይቆጥር ልደታ ላይ የማሸነፍ እድላችን ከሀምሳ ፐርሰንት አይበልጥም በማለት መከራከሩን ባለማቆሙ ከስብሰባ ታገደ። በምትኩ ከትግራይ አርከበ ይዙት የመጣውና የልደታ ምክትል ከንቲባው ዘሩ እንዲሳተፍ ተደረገ። ዘሩ ከምርጫ በኃላ ተክሌን እንዲያባርረው ተልእኮ ተሰጠው።

የግንቦት ሰባቱ ምርጫ በልደታ ያልተበቀ ነገር ይዞ ብቅ አለ... በደህንነቶች ማስፈራራት ምክንያት ከምርጫው ራሱን ባገለለው የቅንጅት እጩ ምክንያት ስድስት የኢህአድግ እጩዎች እርስ በራስ ተፋጠጡ። ብዙዎቻችን በኢህአድግ ነባር ታጋይነቱ ለሚታወቀው ም/ ከንቲባ ህላዌ ዬሴፍ ግምታችንን ሰጠን፣...በተቃራኒው የልደታ ህዝብ አምስት የቅንጅት እጩዎችን ከመረጠ በኃላ ቀሪዋን ወንበር ለተክሌ ሰጠ።

በአዲሳባ ደረጃ ከነበረው 138 የምክር ቤት ወንበር ውስጥ አንዷን ብቻ ኢህአድግ በተክሌ አማካኝነት አገኘ።... ሌሎቻችን በዝረራ ወጣን።

ስም ከማውጣት ቦዝኖ የማያውቁት ካድሬዎች ተክሌን" አንድ ለእናቱ " አሉት።

ምርጫው በተጠናቀቀ በሳምንቱ ኢህአድግ ደኃፍ እንዳይደርስ ተብሎ ተወስኖበት የነበረው ምስኪኑ ሰው የተለየ ክብር ተሰጥቶት ለሌላ ትልቅ ስራ ተጠራ... ቅንጅት ስልጣን ከተረከበ በኃላ የሚካሔዱ ህገ - ወጥ ተግባራትን እየተከታተለ በምክር ቤት ጉባኤዎች ላይ የማጋለጥ ስራ እንደሚሰራ ተነገረው።... ከደህንነት ቢሮ በየጊዜው ወቅታዊ መረጃዎችን የሚያገኝበት ሁኔታ ተመቻቸለት... አፍታም ሳይቆይ በሚስጥር የተያዙ አስገራሚ መረጃዎች በደህንነት ሀላፊው ኢሳያስ አማካኝነት ይጐርፉለት ጀመር።

ለተክሌ ከተገለፀለት ጥብቅ ሚስጥር መካከል : - ቅንጅትን ወክለው ለአዲሳባ ምክር ቤት ከተወዳደሩት ውስጥ ኢህአድግ አሰርጐ ያስገባቸው ሰዎች መኖራቸው፣ እነዚህ ሰርጐ ገቦች እርስ በእርስ እንደማይተዋወቁ፣... በእንባ ጠባቂ ኮሚሽን የሚመራ " የአዲሳባ ህዝብ ቅሬታ ማስተናገጃ ጽ/ ቤት እንደሚቋቋምና እሱ የበላይ ሀላፊ እንደሚሆን የሚጠቀሱ ናቸው።

የቅሬታ ማስተናገጃው ቢሮ የህዝብ ሮሮዎችንና በተደራጀ መንገድ እንዲያስተናግድ የታሰበ ነበር።... በየቀበሌው ሊመደቡ የተዘጋጁት ቋሚ ምድብተኛ ካድሬዎች ቁልፍ ስራ የህዝብ ብሶቶችን በማሰባሰብ ተክሌ ለሚመራው ቢሮ ማስተላለፍ ይሆናል...

ከዚህ በተጨማሪም ከጐብልስ ቲዎሪ አንዱ የሆነውን "ኩነቶችን በመሪ ቃል መምራት "በሚለው መሰረት "ቅንጅቶች ቃላችሁን ጠብቁ " የሚሉ አስተዳደሩን የሚያስጨንቁ ግፊቶች ይደረጋሉ... ለዚህ ስራ ግብአት እንዲሆኑ ቅንጅት በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት እሰራቸዋለው ብሎ ቃል የገባቸው እቅዶች ዶክመንት ተደረጉ።

የአሮጌና ፊጋ በሬ ጣምራ የሆነው ቅንጅት እንኳን ሊፈፅማቸው በአፍ ወለምታ ሊናገራቸው የማይገባ ቃሎች ባለቤት ነበር...ለተግራሪ ወገን መልስ ለመስጠት በሚል ብቻ ነባራዊ ሁኔታውን ከግምት ሳይገባ የማይፈፀሙ እቅዶችን መናገር ከግምት ይከታል..."በአምስት አመት ውስጥ ግማሽ ሚሊዬን ቤት ገንብቼ የመዲናይቱ ህዝብ ከቤት እጦት አላቅቃለው" በሚለው ቅስቀሳ መካከልና "ወተት በቧንባ " በሚለው መካከል ልዩነቱ ምንድነው?

እናም ተክሌ "ቅንጅቶች ቃላችሁን ጠብቁ! " ለሚለው መፈክር እንዲዘጋጅ ተነገረው...ይህንን ተከትሎ ለከፍተኛ ጭንቀት ተዳረገ... ከእሱ ጋር ቅርበት ከነበረን ካድሬዎች ጋር ተማከረ... አፍታም ሳይቆይ መስከረም ሳይጠባ የሚወዳትን ሀገር ጥሎ ወደ አውሮፓ ተሰደደ።

የተክሌ መኮብለል በኢህአድግ ውስጥ ከፍተኛ መደናገጥ ፈጠረ። እሱን ማፅከል ተደርገው የተቀረፁ እቅዶች ደራሽ ውሀ ወሰዳቸው። በአዲሳባ ምክር ቤት " አንድ ለእናቱ " ተብላ የተሰየመችው የኢህአድግ መቀመጫ ባዶዋን ቀረች።

ሀቁ ይህ ሆኖ ሳለ አቶ በረከት ጽፎ ባስነበበን ወግ ላይ " ... የኢህአድግ ተወካይ የአዲሳባ ምክር ቤት አባል ሆኖ ቅንጅት በሚመራው ምክር ቤት ሊሳተፍ ተዘጋጅቶ ነበር ... " ብሎናል።... የግንቦቱ ምርጫ በተጠናቀቀ በወራት ውስጥ ሀገር ጥሎ የወጣን ሰው ምክር ቤት ሊገባ ተዘጋጅቶ እንደነበር የተገለፀበት ምክንያት ግልፅ ነበር : - ኢህአድግ በተሸነፈበት ሁኔታ የህዝብ ድምፅ እንደሚያከብር፣ በተቃራኒው ተቃዋሚዎች ሙሉ በሙሉ ባሸነፉበት ሁኔታ የህዝብን ድምፅ ወደ ጐን ትተው አስተዳደሩን ለመረከብ እምቢተኝነታቸውን ለማሳየት ነበር...

ለጋራ ድል ያልታደለው የኢትዬጲያ ፓለቲካ!

***

አሳዛኙ ታሪክ

በምርጫ 2000 ኢህአድግ ሁለት የተቀናጁ ስትራቴጂዎችን ቀርጾ በተግባር ላይ አውሏል: - የህዝብ ቀጥተኛ ተሳትፎ ማስፉትና ከምርጫው ሂደት ይልቅ ለውጤቱ ትኩረት መስጠት የሚሉ ።... እነዚህ ስትራቴጂዎች ኢህአድግ ይዘቱን ቀይሮ ቅርፅን ብቻ ይዞ እንዲቀር አድርገውታል...

በመሆኑም ዲሞክራሲው ወደ 300 አመተ አለም ቁልቁል በመምዘግዘግ ማረፊያውን ግሪክ አቴንስ አድርጓል።... አብዬታዊነት ጦሴን ጥንቡርሳሴን በማለት ዝዙን ጠቅልሎ ከኢህአድግ ተሰናብቷል ።... የመድብለ

ፓርቲ ስርአት ግንባታ ወደ " ላም አለኝ በሰማይ ... " ተቀይሯል።... ኢህአድግ ቻይናን ተከታይ አድርጐ በአለም ተወዳዳሪ የሌለው አባላትና ካድሬ ብዛት በመያዝ ጊነስ ቡክ ላይ እንዲሰፍር ጫፍ ላይ አድርሶታል...

በሌላ በኩል እነዚህ አዲስ አቅጣጫዎች ከአጭር ጊዜ አኳያ ኢህድግን ጠቅመዋል...ምርጫ ከመካሔዱ አስቀድሞ ኢህአድግ ሁሉን አሞጦ እንዲወስድ በማድረግ አሸናፊነቱን አረጋግጧል።... በቢሊዬን የሚቆጠር ገንዘብ ከመንግስት ካዝና ወደ ድርጅቱ እንዲገባ አድርጓል።...ተቃዋሚዎች የተሰፋ መቁረጥ ጉዞን እንዲጀምሩ በር ከፍቷል።

ይህ የአዲሳባን ብሎም የአገሪቷን መፃኢ እድል ያጨለመ ታሪክ ወደ ኃላ ላይ በሰፊው ይተረካል።... በዚህ ክፍል ያለጊዜው የተነሳው በአጋጣሚ ሳይሆን የ "አሳዛኙ ታሪክ " መነሻ ስለሆነ ነው።

አሳዛኙ ታሪክ የግለሰብ ታሪክ ቢሆንም።

በድርጅቱ ከፍተኛ ካድሬዎች በደል የደረሰበት ምስኪን !

አይችሎም ይባላል። አይችሎም በአዲሳባ አስተዳደር መሬት አስተዳደር ውስጥ ከፍተኛ ሙያተኛ ነበር። ... ስራ ትጋቱና ቅንነቱ ምክንያት በሰራተኞች ተቀባይነት በማግኘቱ ባለስልጣን ሆነ።...የኢህአድግ አይን አረፈበት። ለድርጅት አባልነት ቢጠየቅ "በየትኛውም ፓርቲ ውስጥ ገብቼ የመንቀሳቀስ ፍላጐት የለኝም" በማለት አሻፈረኝ አለ።... ምርጫ 2000 ሲመጣ የአዲሳባ ምክር ቤት አባል ሆኖ ህዝቡን እንዲያገለግል የቅርብ ጓደኛው በሆነው ካህሳይ የሚባል ካድሬ ተለመነ።... ካህሳይ የአዲሳባ ትራንስፓርት ባለስልጣን ም/ ዴሬክተር ሲሆን የኢህአድግ የመንግስት ተቋማት አደረጃጀት ሀላፊ ነበር።

አይችሎም ከጓደኛው የቀረበበትን ግፊት መቋቋም አቅቶት ኢህአድግን ወክሎ ለምክር ቤት ለመወዳደር ፍቃደኛ ሆነ...ለአዲሳባ ካቢኔ አባልነትም ምርጫው ሳይካሔድ ታጨ።

የ2000 የአዲሳባ ዳግም ምርጫ ኢህአድግ ሙሉ ለሙሉ እንደሚያሸንፍ በመረጋገጡ ምክንያት ፓርቲው ያቀረባቸውን እጩዎችን ለህዝብ ለማስተችት አቀረበ... ከእነዚህ ውስጥ አይችሎም አንዱ ነበር።

አይችሎም በሶስት ቦታዎች ለግምገማ ቀረበ... የመንግስት ሰራተኞች መድረክ፣ ቀጥሎ በሚኖርበት ክፍለ ከተማና ቀበሌ ።... በሶስቱም መድረኮች ኢህአድግ እሱን ይዞ በመቅረቡ ተወደሰ፣... አይችሎምን የመሰለ ሀቀኛና ትጉህ ሰው ፓርቲው በማምጣቱ ምስጋና ቀረበለት።

ኢህአድግ እደግ ተመንደግ !

መሶብህ በእንደዚህ አይነት ሰወች ይሙላ !

አይችሎም ራሱን ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም በከፍተኛ ድምፅ ይዞ መውጣት እንደሚኖርበት ተልእኮ ተሰጠው። እሱም ወደ ህዝቡ እየወረደ " እኔን ብቻ ብትመርጡ ዋጋ የለውም። የምትመኙት ልማት እንዲመጣ ጓደኞቼንም ምረጡ " በሚል ከራስ የዘለለ ምርጫ ቅስቀሳ ተጠመደ...

የምርጫ ቦርድ እጩ ምዝገባ ተጠናቆ ምርጫው ሁለት ሳምንት ሲቀረው አስደንጋጭ ነገር ተከሰተ... የቅርብ አለቃዬ ህላዌ ዬሴፍ ቢሮው ጠርቶኝ " አይችሎም ላይ የሚነሱበት ነገሮች ስላሉ በሁለት ቀን ውስጥ አጣርተህ ና!"

የሚል ትእዛዝ ሰጠኝ።

በሁለተኛው ቀን ከመሬት አስተዳደር ሰራተኞችና የቀበሌ ካድሬዎች አጣርቼ የመጣሁትን ሪፓርት አቀረብኩ... የግለሰቡ ተቀባይነት እያደገ መምጣቱንና በእሱ ምክንያት ሌሎች እጩዎቻችን ይሁንታ እንዳገኙ ነገርኩት።

" ይህቺ አዜብ መስፍን የምትባል ሴትዬ ከየት አምጥታ ነው የምትዘላብደው ? "

" ደሞ ምን አለች?" ጠየኩት።

" እኔ እኮ ግራ የሚገባኝ የእሷ መረጃ ምንጭ ከሌላው የተለየ የሚፈበርክበት ምክንያት ነው! ልማታዊ ባለሀብቶችን አላሰራ በማለት ደንቃራ ሆኗል፣... በመቶ ሺዎች ጉቦ ይጠይቃል ትላለች ... ለማንኛውም ዝርዝሩን ለበረከትና መለስ ነግሬያቸዋለሁ ስላለች ካሚልና ፀጋዬን ይዘሀቸው በረከት ቢሮ እንገናኝ " አለኝ።

ከሰአታት በኃላ ተጠራርተን ወደ በረከት ቢሮ አመራን...

በምርጫ 97 ዋዜማ የነበረውና በተመሳሳይ ወቅት በምርጫ 2000 ያለው በረከት ስምኦን የተለያዩ ናቸው።... አንባራዊ በሆነ መንገድ መረጋጋት ይታይበታል...አስቀድመው የተወሰዱት እርምጃዎች ሀሳቡን አውርደውታል... ርግጥም ከምርጫ ውጤት አንባር የሚያሳስብ አልነበረም... አስቀድሞ ውጤቱ ታውቋል።

የተበላ እቁብ!

በረከትን የጨነቀው አንድ ነገር ብቻ ነው... ይህ ለኢህአድግ ታማኝ ያልሆነ ህዝብ ወደ ምርጫ በመውጣት ይመርጣል ወይ? የሚለው ጥያቄ ፉታ ነስቶታል።... በየሁለት ቀን ከእሱ ጋር በሚኖረን ስብሰባ ማረጋገጫ የሚፈልገው ህዝቡ በነቂስ እንዲወጣ ምን እንደሰራን ማወቅ ነበር... እኛም በየቀኑ በነበረን ዳታ ላይ አስር ሺህ እየደመርን እንመጣለን፣ እሱም የሞባይሉን ካልኩሌተር በመጠቀም የየቀበሌውን በመደመር ፉታ ይነሳታል።

ተጠራርተን በአስቸኳይ የተሰባሰብነው ከወትሮ የተለየ ኢንፎርሜሽን ስለመጣ እንደሆነ በረከት ገለፀልን: -" አንዳንድ ጓዶች አይችሉም በሚባለው እጩ ላይ ችግሮች እያነሱ ስለሆነ እንዲሰረዝ ማመልከቻ ለምርጫ ቦርድ እንድታስገቡ አዘጋጅቼያለሁ " ብሎ ወረቀቱን ሰጠን፣... ጉዳዩን ለውይይት ክፍት ማድረግ እንዳልፈለገ ተረዳን...

ከወይዘሮ አዜብ የመጣ ትእዛዝ ላይ ክርክር ማድረግ ውሀ ቢወቅጡት እንደሆነ ከልምዳችን እናውቃለን።

በምርጫ ቦርድ የጊዜ ሰሌዳ መሰረት እጩ የመቀየሪያ ጊዜ ስላለፈ ምን ማድረግ እንዳለብን ፀጋዬ ጠየቀ።... ፀጋዬ የምርጫውን አስተዳደራዊና ህግ ነክ ጉዳዬች ይከታተላል።

ህላዌ የበረከትን ምላሽ ሳይጠብቅ " የምርጫ 97 ታሪክ በተገላቢጦሽ ይደገማል! " ብሎ ተናገረ።

በረከት ግራ ገባው... ምርጫ 97 በህይወቱ የማይረሳቸውን ትላልቅ ትዝታዎች የህይወት ግርግዳው ላይ ጽፎ ስላለፈ ይህንን መለስተኛ ክስተት ቢዘነጋው የሚገርም አልነበረም።... ይህንን የተረዳው ህላዌ ታሪኩን ወደ ኃላ ተመልሶ ተረከለት።

ባልተጠበቀ መልኩ በረከት ከአዳማጭነት ወጥቶ በደስታና ስሜት በተቀላቀለበት ሁኔታ የካርል ማርክስን : - " **ታሪክ ራሱን ይደግማል፣ በመጀመሪያ ላይ አሳዛኝ ፣ ቀጥሎ ቧልት በሚመስል መንገድ** ! "ብሎ ጮኸ... ቀጥሎም የዚህን ጥቅስ ታሪካዊ አመጣጥ አስረዳን...

ካርል ማርክስ ይህንን ጥቅስ የተናገረው በ19 ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ጀምሮ በፈረንሳይ መካሔድ በጀመረው አብዬት አዲስ ገዥ መደብ የተፈጠረበትን ሁኔታ ለማሳየት እንደሆነ ፣ ... በሉዊ ቦናፓርት ቤተሰባዊ የስልጣን ቅብብሎሽ ተመሳሳይ ታሪክ በመፈፀሙ ያንን ለመግለፅ እንደሆነ አስተማረን።... በረከት በፈረንሳይ አብዬትና ካርል ማርክስ ፍልስፍናዎች ላይ የጠለቀ እውቀት አለው።... ከመፅሀፍቶቹ የሚያገኘውን ቁምነገር ከወቅታዊ ሁኔታዎች ጋር በማጣጣም ወደ ተግባር ይመነዝራቸዋል።

የአሁኑ ተረኛ አይችሎም ሆነ!

አይችሎምን ከእጩነት እንደሰረዝነው ለህዝብ መግለፅ እንደሚገባን፣... በመግለጫችን ላይ ኢህአድግ በመርህ ደረጃ የሰናፍጭ ቅንጣት የምታክል ቅሬታና የሌብነት ጥቆማ የቀረበበትን ሰው እጩ አድርጐ ለማቅረብ ፍላጐት እንደሌለው፣... የአይችሎም ውሳኔ ከዚህ የእምነት ማእቀፍ የሚነጨ እንደሆነ መግለፅ እንዳለብን አሳሰበ...

መግለጫውን እኔ እንደምሰጥ፣ ለየትኛው የሚዲያ ተቋም የሚለውን ከደቂቃዎች በኃላ እንደሚያሳውቀኝ ተነግሮ ስብሰባው ተጠናቀቀ።

በየቀኑ ጆሮ የሚሰቀጥጥ የሌብነት መረጃ የሚነሳባቸው እነ መላኩ ፋንታ ለከንቲባነት እጩ በሆኑበት ሁኔታ በመልካም ስሙ የሚታወቀውን ግለሰብ ያልሆነ ስም ለጥፌ ለመናገር መዘጋጀቴ አበሳጨኝ (በመላኩ ፋንታ ድጋፍ በእግዚአብሔር የሚባል የቅርብ ዘመዱ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከአርክቴክትነት ወደ ሚሊየነር ተቀይሯል... ልማታዊ ባለሀብት ተብሎ ከአቶ መለስ ሽልማት ያገኘ ሲሆን ፣ከሀገር ከወጣሁ በኃላ የህዳሴው ግድብ አስተባባሪ ሆኖ በድጋሚ ሽልማት ተቀብሏል።)

እነዚህ መሬት ላይ የተፃፉ ሀቆች ናቸው፣... በረከትም ሆነ ህላዌ ያውቋቸዋል።

ታዲያ ለምን እኔ ተለይቼ መግለጫውን እንድሰጥ ተደረገ ? ለምን ህላዌ? ለምን ካሚል?...?

ከደቂቃዎች በኃላ የኢህአድግ የህዝብ ግንኙነት ሀላፊ ሴኮቱሬ ጌታቸው በኢንተር - ኮም ደወለልኝ... በረከት ያዘጋጀውን የሚዲያ ተቋም እንዲነግረኝ እንዳዘዘውና ወደ ቢሮዬ እየመጣ እንደሆነ ነገረኝ።

ሴኮን እየጠበኩት በሀሳብ ሔድኩኝ... ወደ ራሱ!

***

ሴኮቱሬ አዲሳባ ተወለደ። በለጋነት ዘመኑ እንደማንኛውም የመዲናይቱ ልጅ አፈር እየፈጨ፣የጨርቅ ኳስ እየተጫወተ ፣ድንጋይ እየወረወረ አደገ።...

ለአቅመ አዳም ሲደርስ ኮትኩታ ያስተማረችው ሀገሩን ለማገልገል ባደረበት ጽኑ ፍላጐት ምክንያት በመምህርነት ሰልጥኖ ወደ ክፍለ ሀገር በመሄድ

አስተማሪ ሆነ።

ከእለታት በአንዱ ቀን በጨለማ ሲጓዝ ህውሀት የምትባል ነጻ አውጭ ከበበችው።... ህውሀት አላማዋንና ማንነቷን ገልጻ ስታበቃ ፍላጐት ካለው እንዲቀላቀላት፣ ካልተመቸችው ደግሞ በሰላም እንደምትሸኘው ነገረችው... ወጣቱ መምህር ለጥያቄው ምላሽ አላወላወለም፣...በአንድ ምሽት ወደዳት። ... ህውሀት እናት አባቱ ያወጡለትን ስም ቀይራ ሴኩቱሬ አለችው...

ሴኩቱሬ ጌታቸው!

ከጠበቀው በላይ ህውሀት ተንከባከበችው... ቋንቋዋን አስተማረችው... ሀይማኖቷ የሆነውን አብዬታዊ ዲሞክራሲ አጠመቀችው... ሙሉ በሙሉ ከእሷ ላለመነጠል ቆረበ።

አምላክ በሰጠው እጅና አፍ እስከ ድል ማግስት አገለገላት።

በ1993 አ•ም• ህውሀት ለሁለት ስትሰነጠቅ ሴኩቱሬም ተቦተረፈ።ግማሽ ጐኑን ይዞ ወደ ትልቁ ክፉይ ተቀላቀለ...የሚሆን አልነበረም... አዲሷ ህውሀት ዘር ማንዘር ቆጠረች፣ "ማነህ?" የሚል ጥያቄ አነሳችበት...የእሷ ደም እንደሌለው አረጋገጠች! አፍታም ሳትቆይ ዘርህን ፈልግ ብላ አባረረችው።

ማረፊያገኦጀ የሌለው ሆነ።...

አማራጭ ሲያጣ ወትሮ ሲንቃት ወደ ነበረችው ብአዴን ወደምትባለዋ ወይዘሮ ሐደ። ብአዴን ራሷ የማንነት ጥያቄ ችግር ስላለባት ለቅበላ አላስቸገረችውም። ይልቁንስ ራስ ምታትየሆኑበት የብአዴን ልጆች በተለይም የበኩር ልጇ የሆነው በረከት ስምኦን የሚባለው ካድሬ ነበር።

ሴኮ እንደሌሎች ካድሬዎች መደበኛ ትምህርት ልማር ብሎ ቢጠይቅይህ የብአዴን የበኩር ልጅ ከለከለው።... አጠገቡ አስቀምጦ በጫማው ረጋገጠው... ሚስጥራዊ በሆነ ድርጅት ውስጥ የህዝብ ግንኙነት የሚል ማእረግ በመስጠት ከጨዋታ ውጭ አደረገው ...ብአዴን ከምትመርጣቸው ፓሊት ቢሮዎች አስር እጥፍ ድርጅታዊ ብቃት ቢኖረውም፣ ጉባኤ በመጣ ቁጥር ከአቋም መግለጫ አንባቢነት እንዳይሸጋገር አደረገው... ኢህአድግ ውስጥ ካሉት ካድሬዎች የተሻለ የቋንቋና ኮሙዬኒኬሽን ብቃት እያለው ፣ በተቃራኒው የሚዲያ ሀ - ሁ የማይገባቸው እነ ዘርአይ አስግዶም ለእሱ የሚገባውን ቦታ ተቆጣጠሩት።

የሴኮ ልብ ቆሰለ... ይዋል ይደር እንጂ የቆሰለ ልብ ወደ ቂምና በቀል መሸጋገሩ አይቀርም።... ሴኮ ከሚታማበት መጥፎ ነገሮች ዋነኛው ደግሞ ይህ ነው።

ብአዴን የሚጠላውን ወንድም ብቻ አልሰጠችውም... ከራሷ በላይ የምትወደው እህት ሰጥታዋለች... ፍሬህይወት አያሌው ትባላለች።

ከሴኮ ጋር የሩቅ ሰው ብንሆንም በየቀኑ ውሎና አዳሩን፣ ምሳና እራቱን ፣ ሽሚዝና ከረባቱን (የውስጥ ሱሪውን አይጨምርም !) ባልፈልግ እንኳን በፍሬህይወት በኩል ይደርሰኛል... ፍሬ ስለ ሴኮ አውርታ አትጠግብም... እሱ በሌለበት የምትጠጣው ውሀ እንደ ፀበል ይወፍርባታል...ታዲያ ይህን የታዘቡ ካድሬዎች "ፍሬ የምትተነፍሰው በሴኮ ሳንባ ነው " እስከ ማለት ደርሰዋል ...

የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጾች ናቸው።

ሴኮ ከፍሬ ውጭ ወዳጅ የለውም።... የብአዴን ካድሬዎች ይጠሉታል... ህውሀቶች አይኑን ማየት አይፈልጉም... ኦህዴዶች ድምጹ ይቆረፍዳቸዋል። አሱም ይህን ያውቃል... አንድ ጊዜ ምርር ብሎት " ለምን ይጠሉኛል? ለምን ይጨቁኑኛል?" የሚል ጥያቄ አንስቶ ነበር።

ርግጥም ሴኮ ከበቀለኝነት ውጭ በሙስና የሚታማ አይደለም፣ የደሞዝ ቀን እስኪደርስ የሚጨንቀው ምስኪን ነው፣...የሚኖርበት የአራት ኪሎ አፓርትመንት ብዙ ማስፈራሪያ ደርሶብኛል ብሎ ቢያለቅስም ሰሚ አላገኘም፣... ኢህአድግ ለእሱና ስራ አጋሮቹ የመደበለት አሮጌ ሱዚኪ እየተበላሸች ብታስቸግረው ፍሬ ሹፌር ሆና ታመላልሰዋለች...የፓርቲው ባለስልጣናትን ቻይናና ደቡብ አፍሪካ ለመላክ ፓስፓርታቸውን ተሸክሞ ቪዛ ለማስመታትይሯሯጣል እንጂ እሱ እንዲሔድ አይፈቀድለትም...እኔንም ቢሆን አንድ ጊዜ ታንዛኒያ፣ ሌላ ጊዜ ቻይና ልኮኛል።

በተቃራኒው ፓርቲው ውስጥ ካሉት ስራ አስፈጻሚዎች በእውቀቱ ይልቅ ይሆን እንጂ አይተናነስም።... ከኢህአድግ ውጭ ባለው ማህበረሰብ የተሻለ መቀራረብ አለው... ቁመኝነቱ እንዳለ ሆኖ በዙሪያው ካሉ ሰወች ጋር ተግባብቶና ተዋህዶ መስራት ይችልበታል... ከመረጃ ዘመን ጋር ራሱን እያበቃና እየለወጠ የሚሄድ ሰው ነው።

ታዲያ ለምን ?... መልሱ አንድ ነው : -

አዲሳባ ራሷ ብቻ ሳትሆን ከአብራኳ የወጡት ልጆቿም ባለቤት አልባ ናቸው!!

***

ስለሴኮ አስቤ ሳልጨርስ በሬን ከፍቶ ገባ።

የማስበውን ያወቀብኝ መሰለኝ። ለማስቀየስ ፊት ለፊቴ ያለውን የድርጅት ጋዜጣ አገላበጥኩ...ያጋጣሚ ነገር ሆኖ ጋዜጣው በልዩ አትም የተዘጋጀና በብሔር ድርጅቶች የተመረጡ ማእከላዊ ኮሚቴና ፓሊት ቢሮ አባላት ዝርዝር የያዘ ነበር።

" እንደኔ ጊዜ ተርፎሀል ! ጋዜጣ ትገርባለህ?" አለኝ...

" በጋዜጣው ላይ የተዘረዘሩት ሰዎች ውስጥ ሳጣህ ገርሞኝ ነው...እነ አያሌው ጎበዜ፣ ደመቀ፣ ገዱ፣ዬሀንስ ... ፓሊት ቢሮ በሆኑበት ሁኔታ አንተን ማእካላዊ ኮሚቴ ውስጥ እንኳን እንዴት አትገባም? መመዘኛው የፓርቲውን መርሆዎች ጠንቅቆ የሚያውቅና ኪራይ ሰብሳቢ ያልሆነ ከሆነ ? "

" መመዘኛው አንተ ያልከው አይደለም ? "

" ታዲያ ምንድነው? "

" የተላኩትን እንዳታስረሳኝ! ለማንኛውም መመዘኛው ሁለት ነው:- በድርጅቱና እነ በረከትን በመሳሰሉ ካድሬዎች ይሁንታ ማግኘት፣...ሁለተኛው ደግሞ የተወለድክበት አካባቢ ያሉትን ካድሬዎች በመንደርተኝነት አደራጅተህ ወደ ጉባኤ ማስገባት ! ...አዲሳባ ደግሞ ትንሿ ኢትዬጲያ እንጂ የመንደር ጎጆ የምትቀልስባት ስላልሆነች ከጨዋታ ውጭ ትሆናለህ !"

"የማታመጣው የለም? "

" አውነቱን ነው የምልህ! ኢህአድግ ከብሔርተኝነት ወደ

መንደርተኝነት ቁልቁል ተምዘግዝጐ ወርዷል... የስርአቱ ቀጣይ አደጋ ይህ እንደሚሆን ምን አለ ሴኮ ትለኛለህ ! ... እንደውም የቤት ስራ ልስጥህ! ... እንደውም ፍርዬ ባለችበት እንከራከራለን። "

" ጥሩ ! ቀጥል "

" የኦህዴድ ጉባኤ በተደጋጋሚ ተሳትፈሀል ። አስቲ የተሳታፊው አቀማመጥ፣ ማን ማንን ለማእከላዊ ኮሚቴነት እንደሚጠቁም ፣ ምርጫው እንዴት እንደሚካሔድ ፣ ኢህአድግ ቢሮ የሚሰሩ ካድሬዎች እጣ ፋንታ ወደ ጎላ ሄደህ ለማስታወስ ሞክር?።"

መስማማቴን አንገቴን በመነቅነቅ አሳየሁት።

" ለአሁኑ ወደ ተላላኪነቱ ልመለስና ጲዬን የምትባል የአዲስ ነገር ጋዜጠኛ ትደውልልሀለች!...በደንብ ቅረባት ተብለሀል!... የድርጅት ተልእኮ ነው፣... በዚህ ጉዳይ ላይ ቅሌን ጨርቄን ማለት አይቻልም! " እየሳቀ ከቢሮዬ ወጥቶ ሔደ።

ስልክ እየጠበኩ ወደ ሰጠኝ የቤት ስራ ተመለስኩ...

የኦህዴድን ጉባኤ ለሶስት ያህል ጊዜ ተሳትፌያለሁ። የጉባኤው ተሳታፊ አቀማመጥ ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ሲሆን ሁሉም ከመንደሩ ልጆች ጋር እጅብ ብሎ ይቀመጣል። ባለስልጣናት ምርጫው እስኪደረግ የሰፈራቸው ልጆች የያዙት ሆቴል በመሄድ ይጋብዛሉ። ያደራጃሉ።

የማእከላዊ ኮሚቴ ምርጫ ሲካሔድ የሁሉም ሩጫ የቁዬውን ካድሬ ለማስመረጥ ይሆናል... የሻሸመኔ ካድሬዎች ኮሚሽነር ወርቅነህ እስከኪጠቆም ይጮሀሉ፣ አዳራሹን ይቀውጣሉ...ከተጠቆመ በኃላ አፍና እጃቸው ወደ አፎቱ ይመለሳል... የአርሲ ሙስሊም ካድሬዎች ለጁነዲን፣... ጅማዎች ለሙክታር ...

የራሳቸው መንደር የሌላቸው፣ አሊያም አስቀድመው ሳያደራጅ በችሎታና ምግባራቸው እንመረጣለን ያሉ ምስኪኖች ቀልጠው ቀርተዋል : - በቅንነቱና ሀገር ወዳድነቱ የሚታወቀው ሚኒስትር ሶፊያን አህመድ ከእነዚህ ሰወች አንዱ ነው...በነቀምት በተካሔደው ጉባኤ ጥቆማው ሊጠናቀቅ ሶስት ሰው ሲቀረው በአርባ ስባተኛ ተራ ቁጥር ተጠቁሞ ነበር። የጠቆመው አባዱላ ነበር... አቶ መለስና በረከትን በመፍራት።... ኦህዴድ አራት ኪሎ ኢህአድግ ቢሮ በስራ አስፈፃሚነት የመደባቸው እነ እሸቱና የአብዬታዊ ዲሞክራሲ ጋዜጣ የኦሮምኛ ክፍል ሀላፊው ጋቢሳ ከነጭራሹም ለውድድር አልቀረቡም... ከመንደርተኝነቱ በተጨማሪ በኦህዴድ ካድሬዎች ዘንድ ኢህአድግ ቢሮ መስራት እንደ ጠላት ያስቆጥራል።

***

ስልኬ ጮኸ።

የአዲስ ነገር ጋዜጠኛዋ ጲዬን ነበረች።

በስብሰባ የወሰነውን ቃል በቃል ነገርኳት።

" አቶ አይችሎም ከእጩነት የተቀነሰው የአያት መኖሪያ ቤት ስራ ድርጅት በሙስና አስቸግሮኛል የሚል ቅሬታ ስላቀረበ ነው የሚባለው እውነት ነወይ?" ብላ የማላውቀውን ጥያቄ ጠየቀችኝ።

ለጊዜው በግለሰብ ጉዳዩ ላይ በዝርዝር መናገር እንደማልፈልግና ተጣርቶ ለህዝብ ይፉ እንደሚሆን ገልጬ ተሰናበትኳት።

አቶ በረከት ከግል ፕሬሶች አምርሮ የሚጠላውንና ከትሮይ ፈረሶች ጦራ የቀላቀለውን አዲስ ነገር ጋዜጣ የመረጠበት ምክንያት ለረጅም ጊዜ እንቆቅልሽ ሆነብኝ... ኮሙዩንኬሽን ጽ/ ቤት የእሱ ምክትል ሆኖ ስመደብ የሚስጥሩ ቁልፍ ተገለፀልኝ።

በንጋታው ቅዳሜ አዲስ ነገር ጋዜጣ ዜናውን በፊት ገፅ ይዛ ወጣች። የአይችሎም ከኢህአድግ እጩነት መሰረዝ ምክንያት አያት ባቀረበበት ቅሬታና የሙስና ጥቆማ እንደሆነ እኔን እንደ ቃል አቀባይ በመግለፅ አቀረበች።... በወቅቱ ስለምርጫው ከተዘገቡትና ከተነበቡት ዜናዎች ትልቁ ሆነ...

በሙስና የተጨማለቁ እጩዎች በየደረጃው በቀረቡበት ሁኔታ በጥቆማ ብቻ እጩን ማግለል በር ግጥም ትልቅ ዜና ነበር... የኢህአድግ ሁሉን አሟጦ የመውሰድ ግብ የተቀየረበት ሁኔታም መኖር በተጨማሪ ሊያነጋግር የሚችል ነበር።

ጋዜጣዋ በወጣች እለት ባለው ከሰአት የመንግስት ቢሮዎች ሀላፊው ታጋይ ካህሳይና አይችሎም ቢሮዬ መጡ... ቀጠሮ ስላልነበረንና ያልጠበኩት ስለሆነ ደነገጥኩኝ።

ሁለቱም አዲስ ነገር ጋዜጣ በሁለት እጃቸው ይዘዋል። አይችሎም በጋዜጣው ላይ እሱን በተመለከተ የሰፈሩትን ቁም ነገሮች በቀይ ብእር ያሰመረበት ከርቀት ይታያል።

ከንዴቱ ብዛት እጁ ይንቀጠቀጣል፣ አይኖቹ ደም ለብሰዋል ...

ለደቂቃዎች ዝምታ ወረሰን።

አይችሎም ገነፈለ... ሲቃ እየተናነቀው ስለ እሱና አያት የመኖሪያ ቤት ስራ ድርጅት ያለመግባባት ምክንያት አስረዳኝ። ... ኢህአድግና መንግስትን እያታለለ የሚኖር ድርጅት አንደሆነ፣ ህገ መንግስቱን በመፃረር ባዶ መሬት እያጠረ እንደሚቸበችብ ፣ በሲኤምሲ እና በአየር ጤና አካባቢ ለታይታ የሚሆኑ ትናንሽ ሰርቪስ ቤቶችን እያሰራ ባዶውን ቦታ በመቶ ሺዎች እንደሚሸጥ፣ ከዛም አልፎ የግንባታ ደረጃው ለባንክ ብድር የማያበቃው ሆኖ ሳለ የተሳሳተ መረጃ እንዲሰጥ አማላጅና ጉቦ ልኮለት እንደነበር... በመሬት አስተዳደር ውስጥ ከአያት ጋር ተመሳጥረው የሚሰሩ ሙያተኞችና መሀንዲሶች መኖራቸውን በማስረጃ አስደግፎ አቀረበ።

እንባው በጉንጮቹ መስመር ሰርተው ፈሰሱ...

ሲቃ አስቸግሮት መናገር አቆመ።

ካህሳይ በበኩሉ የህውሀት/ ኢህአድግ አመራሮች በተለይም ወይዘሮ አዜብና ትግራይ ልማት ማህበር (ትልማ) በአያት ጉዳይ እንደተሳሳቱ ገለፀ። ... በፓርቲው ሰነድ ውስጥ እንደተጠቀሰው ከባለስልጣናት ጋር በመሞዳሞድ ተጨማሪ እሴት ሳይጨምሩ ሀብት ከሚያግበሰብሱት ዋነኛው ሀያት መሆኑን በተቆርቋሪነት ስሜት ውስጥ ሆኖ ተናገረ... ከጨለማው ዘመን ንጉስ አሊ አብዶ ጀምሮ አያት እንዴት ኪራይ እንደሰበሰበ አስረዳን።

ለሁለቱም የምሰጠው መልስ አልነበረኝም... አንደበቱ ተሳሰረ ። ለራስ ያላመኑበትን ነገር እንደመናገር ህሊና የሚጐዳ ነገር የለም... የአብዬታዊ ዲሞክራሲ ምሶሶ ደግሞ ይህ ነው፣ የበላይ አካል እስከወሰነ ድረስ ተጻረህ

መቆምም ሆነ የምታምንበትን መናገር አትችልም።... የት ነው ያለሁት ? አይችሎም ላይ የተሰነዘረ ዱላ ነገ ወደእኔ እንደማይዞር ምን ዋስትና አለ? ... እራሴን እያታለልኩት እንደሆነ ተሰማኝ... ቢያንስ በንግግሬ እንዳልረክስ ዝም አልኩ...

ገብቶአቸው መሰለኝ ለመሄድ ተነሱ።

አይችሎም ተሰናብቶኝ ሲወጣ የነበረው ፊት ፣ሲያገኘኝ ከነበረው ጋር ተመሳሳይ ነበር።

***

ቧልተኞቹ ታሪኮች

ከምርጫ 2000 ጋር በተያያዘ በርካታ አሿፊ ታሪኮችን ማንሳት ይቻላል። ከእነዚህ ውስጥ ኢህአድግ ብቻውን ሮጦ አሸነፈ እንዳይባል የተፈጠሩት የፓለቲካ ፓርቲዎች። ድምጽ አልባ ድምፀኞች። ዳግም ንቅል ካድሬ ጦላ ብለው ሊነሱ የሚችሉት ናቸው። እያንዳንዳቸውን በዝርዝር ወደ መመልከት እንሸጋገር።

"ባንክና ታንክ"

የ2000 የአዲሳባ ዳግም ምርጫ የመቶ ፐርሰንት የማሸነፍ ግብን ለማሳካት ከሃደቱ ይልቅ ለውጤቱ ትኩረት በመስጠት መፈፀም ተጀመረ። የምረጡኝ ዘመቻውና ውድድሩ የሚዲያ ትኩረት ተነፈገው። በውስጣቸው ምንም አባላት የሌላቸው ብቻ ሳይሆኑ የአንድ ቤተሰብ ዘመዳሞች ተሰብስበው የፓለቲካ ፓርቲ መሰረቱ።

በአቶ አርከበ እቁባይ የጥፉት ዘመን የአዲሳባ አማካሪ ምክርቤት አመራር የነበረ መስፍን መንግስቱ የሚባል በአራዳ ክፍለ ከተማ የሚኖር ግለሰብ መላዉ ኢትዬጲያ ብሔራዊ ንቅናቄ (መኢብን) የሚባል የቤተሰብ ድርጅት አቋቋመ። በ12 ወረዳዎች ላይ እህቶቹን፣አማቾቹንና ሌሎች የስጋ ዘመዶቹን በእጩነት አቀረበ። ለአስራ ሁለት የፓርላማ መቀመጫ እየተወዳደሩ ያሉትን ቤተሰቦች ዝርዝር ምርጫ ቦርድ ላከልን። ስለ ግለሰቡ ማንነት የሚያሳይ መረጃ ከደህንነትና ካድሬዎቻችን አሰባሰብን።

እንደ ጭራሮ ደርቀው የቀሩት የአየለ ጫሚሶ ቅንጅትና የልደቱ ኤዴፓ ኢህአድግ ባዘጋጀላቸው እጩ ለውድድር ተዘጋጁ። ከምርጫው በፊትና በኃላ የልደቱ ፓርቲ በድርጅቱ የወደፊት አቅጣጫ ላይ ለመወሰን በሜክሲኮ መብራት ሀይል አዳራሽ የጠራውን ስብሰባ አጀንዳ የቀረጽነው ፣ተሰብሳቢዎችን ለይተን ያስገባነው እኛና ደህንነት በመቀናጀት ነበር። ልደቱ በጠራራ ፀሀይ በመብራት ሀይል አዳራሽ በዝግ የመራውን ስብሰባ እኛ ማታ ከቃለጉባኤ እናነባለን። ተጨማሪ መረጃ ካስፈለገን ተልእኮ ተሰጥቷቸው በስብሰባው ከተሳተፉት እንወስዳለን። ይህንን ተከትሎ ኢዴፓ ብዙም ሳይቆይ በፓርቲ ደረጃ እንደማይወዳደር ግን ደግሞ ግለሰቦች እንወዳደራለን የሚሉ ከሆነ መብታቸው እንደሆነ የሚያሳይ አስቂኝ

መግለጫ አወጣ።

ከ" ባንክና ታንክ" የመቀስቀሻ ማእከላዊ መልእክት ጋር የቆረበው ህብረት እስከ መጨረሻው የምርጫ ቀናት እየተንገዳገደ ቆየ። በአስራአንደኛው ሰአት ከምርጫው ሂደት አቋርጦ እንደወጣ ይፋ መግለጫ አወጣ። በወቅቱ በከፍተኛ ጥቅም ላይ ውላ የነበረችው " ባንክና ታንክ" የፈጠራት አቶ በረከት " አደገኛ ቃላት ከመፈብረክ የማይቦዝነው የጠባቦች ንጉስ " ብሎ የሚጠራው ዶ/ ር መራራ ጉዲና ነበር። ዶክተሩ ተራ በተራ የፓርቲውን ካድሬዎች በዝህች ምትሀተኛ ቃል አደቁኖበታል። በተለይም መምህር ወንድሙ የሚባሉ የፓርላማ አባልና የህብረት ከፍተኛ አመራር በምርጫ ክርክር በቀረቡ ቁጥር አልፉና አሜጋቸው ባንክና ታንክ ሆኖ ነበር።

የአጋጣሚ ነገር ሆኖ እኔና የስራ ባልደረባዬ የነበረው ፀጋዬ ሀ/ ማርያም የአዲሳባ ኢህአድግን ወክለን፣ መምህር ወንድሙ ደግሞ ህብረትን ወክለው ለሶስት ያህል ጊዜያቶችና ቦታዎች (አፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን፣ባህል ማእከልና ማዘጋጃ ቤት) የምርጫ ክርክር አድርገን ነበር።

ታዲያ በማዘጋጃ ቤት በተካሄደው የመጨረሻ ክርክር ወቅት እኔና ፀጋዬ በመኪብኑ የቤተሰብ ፓርቲ ፕሬዝዳንት አቶ መስፍንና መምህር ወንድሙ ላይ ተንኮል አዝለን ወደ መድረክ ወጣን። የተከበሩ መምህር ወንድሙ ለመከራከሪያ ያዘጋጁት ሰነድ ቀድሞ የደረሰን በመሆኑ በጋራ ተመልክተነዋል። በእያንዳንዱ አንቀጽ ላይ ይቺ እንደ ጅብ ቆዳ ተጣብቃ የቀረችባቸው ቃል በመሸጋገሪያነት ተቀስራለች።

በክርክሩ የድልድል ሰአት የመጀመሪያ ዙር ቅድሚያውን ኢህአድግ እንዲወስድ ተስማማን። የሁሉም ፍላጐት ስለነበር በቀላሉ ተሰጠን። ፀጋዬ ንግግሩን ገና ሲጀምር በቀልደኛ አንደበቱ :

" *የተከበሩ የፓርላማ አባል መምህር ወንድሙ ባለፉት ሁለት ክርክሮች መምህርነታቸው አገርሽቶ ባንክና ታንክ 101(ባታ -101) እና ባታ -102 ኮርስ ሰጥተውን ነበር። ከሚገባው በላይ ገብቶናል። ኢህአድግ ለእሳቸውና ድርጅታቸው የኮፒ ራይት መብት ይገባቸዋል ብሎ ያምናል። ይህቺን ወደ ስልጣን የምታመጣ ምትሀተኛ ቃል ሌላው መጠቀም ከፈለገ ከኦርጅናል ባለቤቶቹ ፍቃድ መጠየቅ ይኖርበታል* " አለ።

የተከበሩ መምህር ወንድሙ የመናገር ተራቸው ደርሶ ገና "ባንክና ታንክ" የሚለውን ቃል ሳይጨርሱ በአዳራሹ የተሰበሰበው ህዝብ በሳቅና ሁካታ ግራ አጋባቸው። የሚናገሩት ጠፍቶአቸው ሲንዘባዘቡ ዋሉ።

የሞኝ ለቅሶ እንዲሉ ከአምስት አመታት በኃላ በስደት ባለሁበት ሀገር በሚተላለፈው ኢሳት የሚባል ቴሌቭዥን ላይ በእንግድነት የቀረቡት የቀድሞው ህብረት የአሁኑ መድረክ ከፍተኛ አመራር የተከበሩ አቶ ገብሩ ገ/ ማርያም ሳይበረዝና ሳይደለዝ ሌጋሲውን በጠበቀ ሁኔታ " ባንክና ታንክ " ሲሉ ሰማሁ። በመጥፎ ትዝታ ባህር ተሻገርኩ።

ለካስ ይሐሌ ሌጋሲን ሳይበረዝና ሳይቀነስ ማስቀጠል የሚለው አባባል በተቃዋሚዎቻችንም ዘንድ አለ !!

***

ወደ ማዘጋጃ ቤት ክርክር አንመለስ:

ከተከበሩ መምህር ወንድሙ ቀጥሎ እድሉን ያገኙት የመኢብኑ ፕሬዝዳንት አቶ መስፍን ነበሩ። የአቶ መስፍን መተዳደሪያ ስራ ድለላ የነበረ ሲሆን በ1995 በጊዜያዊነት በተቋቋመው የከተማው አስተዳደር አማካሪ ምክርቤት ውስጥ በመልካም አስተዳደር ቋሚ ኮሚቴ ውስጥ አገልግሏል። በሁለት ሳምንት አንድ ጊዜ በማዘጋጃ ቤት በመገኘት የሚያደርገው ስብሰባ ራሱን እንደ አስፈጻሚ እንዲቆጥር አድርጐታል። በተለይም በወቅቱ ከንቲባ የነበረውን አቶ አርከበ በማዳነቅና በማሞገስ የሚናገር ስለነበረ ሰፊ የሚዲያ ሽፋን አገኘ። ይሄ አጋጣሚ የቀድሞ ስራውን በመተው ወደ "ጉዳይ አስፈጻሚነት " አሸጋገረው። በአራዳ በሚኖርበት የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ውስጥ ጉዳይ መስፈፀሙን ቀጠለበት። አስገራሚ ማስታወቂያዎችን በየመሸታ ቤቱ መናገር ጀመረ። ከእነዚህ ውስጥ :

" ክቡር ከንቲባው ጋር ቀርቦ የሚፈፀም ጉዳይ አለዎት? እንግዲያውስ የአማካሪ ምክርቤት አመራሩን መስፍን መንግስቱን ቀርበው ያማክሩ !" የሚለው አንዱ ነበር። ግፍና መከራ ወገቡን ያጐበጠው ህዝብ ያገኛትን ቀዳዳ ሁሉ ለመጠቀም መኪተኑ አይቀርምና በርካታ ማመልከቻዎች ለአቶ መስፍን ደረሰው። በዛው ልክ ኪሱ መሙላት ጀመረ።

የግንቦት 97 ማእበል የአቶ አርከበን የነቀዘ ገዥ መደብ ጠራርጐ ከከተማዋ ሲያባርር የአቶ መስፍን ጥገኛ ጥቅም አብሮ ተቋረጠ። ወደ ሌሎች አማራጮች ተሸጋገረ። ባለአደራ አስተዳደሩ ውስጥ ለመግባት ያደረገው ጥረት ሳይሳካ ቀረ። ለገዥዎች ማደግደግና አጠገባቸው መንጐዳጐድ የሚያስገኘውን ጠቀሜታ በተግባር ያረጋገጠው የአራዳው ጨልሌ "መኢብን " የሚባል ፓርቲ መስርቻለሁ ብሎ ብቅ አለ። ለድህረ ምርጫ 97 ሁከትና ብጥብጥ ተጠያቂዎች አክራሪ ተቃዋሚዎች ናቸው የሚል መግለጫ በማውጣትና መኢብን የኢህአድግ ታማኝ ተቃዋሚ ሆኖ እንደሚቀጥል በኢቲቪ ቀርቦ መግለጫ ሰጠ።

አቶ መስፍን በማዘጋጃ ቤቱ ክርክር ሰአት ታማኝነቱን አረጋግጦ የዘንድሮ የአዲሳባ ምርጫ ብርቱ ፉክክር የሚደረገው በመኢብንና ኢህአድግ መካከል ብቻ እንደሚሆን፣ ሌሎቹ ተቃዋሚዎች ህዝቡ አንቅሮ እንደተፉቸውና እዚህ ለክርክር ከተቀመጡት ውጪ ሌላ አባል እንደሌላቸው በኩራት ተናገረ። አጠገቤ የተቀመጡት የቅንጅቱ አየለ ጫሚሶ የግንባራቸው ደም ስር ወጣ ገባ መስመር ሰራ። ከእሳቸው የተቀመጡበት ወንበር ገዘፍ ታየ።

ርግጥም አቶ መስፍን እውነቱን ነበር። የአቶ አየለ ቅንጅት በኢህአድግና ምርጫ ቦርድ አማካኝነት ከቀድሞ ቅንጅት የአልጋ ወራሽነት ያገኘው አቶ መለስ የቆረጧትን የሁለት ጣት አርማ ብቻ ነበር።

በሁለተኛው ዙር የክርክር ሰአት ኢህአድግን ወክዬ እንድናገር ለእኔ እድሉ ተሰጠኝ። ቀጣይ ትኩረት ያደረግነው አቶ መስፍንን በመሆኑ በ12 የተለያዩ ወረዳዎች መኢብን ያቀረባቸውን ሰዎች እስከ አያት አነበብኩ። መኢብን በለስ ቢቀናው የኢትዬጲያ ፓርላማ ደርዘን የሚሞሉ የአንድ ቤተሰብ አካላት በመያዝ ታሪክ ይሰራ እንደነበረ ተናገርኩኝ። ከአዳራሹ ጩኸት በላይ የአቶ አየለ እንባ ያዘለ ሳቅ ጆሮዬን ሰርስሮ ገባ። የአየለ ጫሚሶ አንጀት ቅቤ ሲጠጣ አየሁት።

አቶ መስፍን ያልጠበቀው ስለሆነ ተወራጨ። ተራው ሳይደርስና ሳይፈቀድለት :

" ኢህአድግ የራሱን ጉድ በጉያው ሸሽጐ ስለሌላ ያወራል። አቶ መለስና ሚስታቸው የተቀመጡበት የፓርላማ ዙፋን ክብደት ሁሉም የሸንጐ አባላት ተጨፍልቀው አይደርሱበትም " በማለት ጮኸ። በአንድ ግዜ ታማኝ ወዳልሆነ ተቃዋሚ ተሸጋገረ። የክርክሩን ማሳረጊያም የአቶ መለስና ሚስታቸው ዙፋን ግዘፈት ሆነ።

ማምሻውን ኢቲቪ የተካሔደውን ክርክር ሰፊ የዜና ሽፋን ሰጠው። የአዲሳባ ፕሮግራም ደግሞ በልዩ ፕሮግራም እንደሚያቀርበው ገለፀ።

በንጋታው ጠዋት የሆነው ግን ሌላ ነበር። የከተማው ኢህአድግ ስራ አስፈፃሚ በረከት ቢሮ አስቸኳይ ስብሰባ ተጠራን። እኔና ፀጋዬ ክርክሩን ወዳልሆነ አቅጣጫ መምራታችንን ተነገረን። የመኢብኑ አቶ መስፍን ኢህአድግ ቢሮ መጥቶ ቅሬታ ማቅረቡ ተነገረን። የድርጅት ጉዳዮን ለሚመራው ካሚል ደውሎ የመደራደሪያ ሀሀሳብ እንዳቀረበ ሰማን። ይህም ኢህአድግ ከዚህ ቀደም ለአቶ በድሩ አደም እንደሚያደርገው አንድ ወንበር ከለቀቀለት 11 ቤተሰቦቹን ከእጩነት እንደሚሰርዝ የሚገልፅ ነበር።

በረከት በተቃራኒው ድርጅቱ አዲስ አቅጣጫ ማስቀመጡን ነገረን። አዲሱ ስትራቴጂ በምርጫው ውጤት ላይ ለውጥ የማያመጡ ፓርቲዎች በውድድሩ እንዲሳተፉ ማበረታታት እንደሆነ ተገለፀልን። ይህም በአንድ በኩል በምርጫ ቦርድ በኩል የሚመደበውና ለፓርቲዎች የሚከፋፈለው ገንዘብ በእጩ ብዛት እንዲሆን፣ ኢህአድግ ድርሻውን ውድድር ለሚገቡ ፓርቲዎች እንደሚያከፋፍል ነገረን። በመንግስት የተያዙት የሚዲያ ውጤቶች ለተቃዋሚዎች ሰፊ ሽፋን እንዲሰጡ አቅጣጫ መቀመጡን አስረዳን።

የዚህ ሁሉ ምክንያቱ ኢህአድግ ብቻውን ሮጦ አሸናፊ ሆነ ከሚለው ወቀሳ ለመዳን መሆኑን ማብራሪያ ሰጠ። ውሳኔውን ተከትሎ በሀገር ደረጃ ለአካባቢና ማሞያ ምርጫ ከሰላሳ ፓርቲዎች በላይ ተመዝግበዋል የሚለው መልእክት የምርጫውን አብዝሀነት ማሳያና በኢትዬጲያ መድብለ ፓርቲ ስርአት የማይቀለበስበት ደረጃ መድረሱን ማሳየት የቀጣይ ቀናት ቁልፍ ስራችን ሆኖ ተቀመጠ።

ኢቲቪም በመስተዳድሩ ፕሮግራም አቀርበዋለው ያለውን የፓርቲዎች ክርክር ሰርዞ ለመወዳደር የተመዘገቡ ፓርቲ አመራሮችን በተናጠል በመጋበዝ የመድብለ ፓርቲ ስርአቱ ይበልጥ እየተጠናከረ መሄዱን አበሰረ። እኛም ጓዛችንን ጠቅልለን መድብለ ፓርቲን ማሰስ ጀመርን... ላም ባልዋለበት!!

***

ድምፅ አልባ ድምፀኞች!

የ2000 አ• ም የአዲሳባ ዳግም ምርጫ እየተካሔደ ነው። ኢህአድግ ከከተማዋ ምክር ቤት ወንበሮች ውስጥ አንዱን ለቆ መመረጥ ጀምሯል። አይችሉም የተቀነሰባት ወንበር ለአየለ ጫሚሶ ቅንጅት ተሰጥታለች፣...አለበለዚያ የታሰበው "ዳግማዊ ታሪክ "ምልዑ አይሆንም።

እናም የኢህአድግ ካድሬዎችና አባላት የአቶ አየለ ቅንጅትን ወክላ የቀረበችውን እጩ(ዶክተር ናት) እንደራሳቸው በመቁጠር ቅስቀሳ አደረጉላት...

መድረክ እያዘጋጁ አስተዋወቁት። እሷም በተጠራችበት ሁሉ በመገኘት የሞተው ቅንጅት አክራሪው እንጂ የኢህአድግ ታማኝ ተቃዋሚው ይበልጥ እየተጠናከረ መሄዱን፣ ድርጅቷ ከገዢው ፓርቲ ጋር የፕሮግራም ልዩነት እንደሌለው ፣ ለቀጣይም እጅ ለእጅ ተያይዞ እንደሚሰራ አበሰረች።

እሁድ (የድምጽ መስጫው ቀን) ሂደቱን ለመምራት ኢህአድግ ቢሮ ለሁለት ተከፈለ... በመላ ሀገሪቱ የሚካሔደውን ለማስተባበር በታደሰ ካሳ (ጥንቅሹ) ቢሮ እሱን ጨምሮ ሐይለማርያም ደሳለኝ፣እሸቱ ደሴ እና ሞፈሪያት ተመደቡ። የአዲሳባን ክንፍ ህላዌ፣ካሚል፣ፀጋዬ፣ፍሬ፣ይሳቅ ቆሪጥና እኔ ተደለደልን። ለከተማው ክትትል የካሚል ቢሮ ጊዜያዊ ማዘዣ ጣቢያችን ሆነ። ሴኩቱሬ የሁለቱ ቡድን ጆከር በመሆን በየሰአቱ መርጦ የወጣውን ብዛት እየመዘገበ ለምርጫ ቦርድ ያስተላልፋል። ምርጫ ቦርድ የእኛን ቁጥር መሰረት አድርጐ በየሁለት ሰአቱ ለኢትዩጲያ ህዝብ መግለጫ ይሰጣል...የኢህአድግና ምርጫ ቦርድ መደጋገፍ እስከዚህ ድረስ ይዘልቃል።

በአዲሳባ የዘረጋነው ኔትወርክ አንድ መራጭ ድምፅ ሰጥቶ ሲወጣ የምናውቅበት ነበር... ለዚህ እንዲረዳ ከአንድ ሚሊዬን ብር በላይ በማውጣት የሞባይል ካርድ ገዝተን አከፋፈልን። በከተማዋ ከ500 ያላነሱ ምርጫ ጣቢያዎች ሲኖሩ በእያንዳንዱ ጣቢያ 20 አባላት እንዲመደቡ ተደረገ።... አባላት በምሳ ሰበብ ጣቢያቸውን ለቀው እንዳይሔዱ ተመሳሳይ መጠን ያለው የምሳ አበል ወጪ ተደረገ። እነዚህ አባላት አንድ ሰው መርጦ በወጣ ቁጥር ቀበሌ ላይ ላለው ኮሚቴ በሞባይል SMS መልእክት ያስተላልፋል። የቀበሌው ካድሬ መቶ ሲሞሉለት ለክፍለ ከተማ ያስተላልፋል። ክፍለ ከተሞች በየ20 ደቂቃው ደምረው ለእኛ ይደውላሉ። አቶ በረከት በየግማሽ ሰአቱ ወደ እኛ እየመጣ ይወስዳል።

እስከ ረፉዱ ድረስ ምርጫ ጣቢያዎች የመራጭ እጦት አጋጠማቸው። እርቃናቸውን ቀሩ። ሁላችንም ደነገጥን። በረከት መረጋጋት አቃተው።... የተለያዩ ፈጠራዎችን አባላችን እንዲጠቀም አሳሰበን።

ይህቺ ቃል ወደ ታች ስትወርድ እንዴት እንደምትተረጐም እያወቅን "ፈጠራ ተጠቀሙ " ብለን አስተላለፍን።... አባሎቻችን እያንዳንዱን ቤት እያንኳኩ ማስፈራራት ጀመሩ..." ያልመረጠ የቀበሌ አገልግሎት አያገኝም !"፣" ኮንዶሚኒየም ለማግኘት ምረጥ ይኖርባችኃል! " ያልመረጠ የቅንጅት ደጋፊ ነው!" የሚሉ ቃላቶች በጥቅም ላይ ዋሉ። ... በእለቱ እየተካሄዱ ያሉ እድር ስብሰባዎች እንዲቋረጡ ተደረገ። አባሎቻችን ቤተክርስትያን ደጃፍ ቆመው የሚወጣውን ምእመን በቀጥታ ወደ ምርጫ ጣቢያ ወሰዱ።... ህዝቡ መፈናፈኛ ሲያጣ ወደ ምርጫ ጣቢያ መትመም ጀመረ። ሰልፎች መታየት ጀመሩ።

በረከት እፎይታ አገኘ። ፀሀይ ማዘቅዘቅ ስትጀምር ትንሽ ቆይቶ እንደሚመጣ ነግሮን ሔደ። በፉንታው ሽማግሌው ስብሀት ነጋ ተቀላቀሉን።

ሽማግሌው ጠጥቷል።

ህላዌ ትንሽ እናስቀባጥረው ብሎ ጠርሙስ ውስኪ አሰጨበጠው።...

" ስማ እስኪ ስብሀት! አንተን የከንቲባው ልዬ አማካሪ ልናደርግህ አስበናል?"

" እንኳን አርጅቼ ድሮም የሴት ቀሚስ ተከትዬና አልብሼ አላውቅም!"

" ከአረጁ አይበጁ ሆንክ እኮ!... ማሞ ሌላ መታወቂያው ሌላ! "

" ህላዌ በሚገባ ስምቸሀለሁ! አበሳጭቶኝ ነው። በምን አይነት መለኪያ አስቴር ማሞ ከንቲባ ልትሆን ትችላለች?... በል መልስልኝ?... እናንተስ ብትሆኑ የአዜብን ሀሳብ ዝም ብላችሁ ትቀበላላችሁ? መተጋገል የሚባል ነገር ጠፉ እንዴ ? እኔ ሰሞኑን በጠቅላላ ስከራከራት ነበር። የምትሆንበትን ምክንያት አሳምኝኝ አልኳት። ከሷ ውጭ የተሻለ የለም... ትሆናለች! ትሆናለች! አለችኝ።"

ህላዌ እንደ ሎጥ ሚስት ደርቆ ቀረ።... ሁላችንም እርስ በራስ ተያየን።

" ህላዌ! እውነቴን ነው የምልህ። ይህችን ሴት ወደ ከንቲባነት ማምጣት ህዝብ እንደ መናቅ ነው። እነ መላኩ ፈንታ ባሉበት እንዴት አስቴር? በደንብ ልታስቡበት ይገባል።... ባይሆን አርከበን አሳትፉት...ሊረዳችሁ ይችላል "

ሽማግሌው እንዳልሰከረና ሽፍጥ አንግቦ እንደመጣ ገባን።

ያለማቋረጥ ጠዘጠዘን።

ሽማግሌው ጥይቱን ሲጨርስ ጠባቂዎቹን ተደግፎ ወደ መጣበት ሔደ። ባልተጠበቀ ሁኔታ በይሳቅ ቆሪጥና ፀሀይቱ በሀታ መካከል ጭቅጭቅ ተነሳ። በትግርኛ ተጠዛጠዙ። ይሳቅ የአስቴርን ከንቲባ መሆን ይደግፋል፣ ፀሀይቱ ደግሞ በተቃራኒው...ይቀጥላል

ፍሬ የሰማችውን ሚስጥር ነገረችን። ከወራት በፊት በህውሀት ከፍተኛ ካድሬዎች በአጀንዳ ይዘው ተነጋግረውበታል። በሽማግሌው ስብሀት (አርከበ እቁባይ) እና በወይዘሮ አዜብ መካከል ማን ከንቲባ ይሁን በሚለው ዙሪያ ተጨቃጨቁ ። አዜብ በጉን በሉል ድጋፍ ለማግኘት ዘመቻዋን አጠናክራ ቀጠለች። የኦህዴድ ጽ/ ቤት ካድሬዎች በሷ መስመር እንዲሰለፉ አደረገች ... አስቴርን ለከንቲባነት መለስ ስለመረጠሽ ተዘጋጂ ብላ ነገረቻት።

ህላዌ " ሴትየዋ በእጅ አዙር አስተዳደሩን ሳትረከብ አንድ ነገር ማድረግ አለብን! "

ፍሬ " ጓዶች ! እንደተለመደው በተባበረ ክንዳችን እቴጌን ጉድ እንስራት ! "

ካሚልና ፀጋዬ ወደ እኔ ተመለከቱ።

ምሽቱኑ ሴራ ጠንስሰን አደርን።

***

የካሚል ቢሮ ፉታ አጥታለች። ትላልቅ ካድሬዎች እየጐበኙን ይሄዳሉ። ከምሽቱ አራት ሰአት አካባቢ በረከት ስምኦን፣ ተፈራ ዋልዋና ባለቤቱ አይኔ ጽጌ ተያይዘው መጡ።...ሞቅ እንዳላቸው በማየት የስታውቃሉ። ተፈራ ጨርቅ ሆኗል።

" ተፈ ግርግር "..."ዋልዋ " የበረሀ ጓደኞቹ እንደሚጠሩት።

ደርዘን ማርቲኒ ይዞልን መጥቷል። አይኔ ደግሞ መጠጫ ብርጭቆዎች። በረከት ፊቱ ፀሀይ ሆኗል። ለመምረጥ የወጣው ህዝብ ከገመተው በላይ ነው። የኢህአድግ የአየለ ጫሚሶ እጩዎች አብላጫ ደምፅ እንደሚያገኙ አልተጠራጠረም። እናም መጠጣትና መጫወት ብቻ ነው የፈለገው። ከኢህአድግ

ካድሬዎች ከመለስ ቀጥሎ ተጫዋችና ተራቢ በረከት ነው...ከፓለቲካ ውጭ የሚያመጣው ጨዋታ ሁለገብነቱን ያሳያል፣... ስለ ስፓርት፣መዚቃ፣ፊልም፣መጽሀፍ ቢነሳ አብሮ መጠረቅ ይችላል።... የእንግሊዙ አርሴናል ቀንደኛ ደጋፊ ነው ... ስለ አርሰን ቬንገር የአመራር ብቃትና ደፋር ውሳኔ ሲናገር በምርጫ 97 ምክንያት ያጣነውን የስፓርት ጋዜጠኛ ፍስሀ ተገኝ ያስንቃል።

የሁላችን ሞቅታ እየጨመረ ሲሄድ በረከት ዋልዋን ማብሸቅ ጀመረ... ህላዌና አይኔም ተጨመሩ። መለያው የሆነችውና ተጣብቆ የቀረባት " የዋልዋ ኮት " ተነሳች...የዋልዋ ኮት ታሪካዊ አመጣጥ ትረካ ዘበረከት እንደሚከተለው ነው:

አቶ መለስ ለኢህአድግ ስራ አስፈፃሚ የአስተሳሰብ እድገት መጥቶባቸዋል ያላቸውን ጉዳዬች ይዞ ይመጣል። ውይይቱ ሲካሔድ ነባር ታጋይ የነበሩ ካድሬዎች አልዋጥላቸው ይላል። ከሌላው በተለየ ተፈራ አዲሱን ሀሳብ ደግፎ ይናገራል።

በሌሎቻችን የተበሳጨው አቶ መለስ " ... አዳዲስ አስተሳሰብ እየፈራን እስከ መቼ እንደምንኖር አይገባኝም፣... ይህ ተፈራን አይመለከትም፣... ዋልዋ የተቸነከረችበት ኮቱ ብቻ ናት።... አሁንማ መርካቶ " የዋልዋ ኮት " የሚል ባጅ ሊጀመር እንደሆነ ሰምቻለሁ " አለ።

ሁላችን ፈገግ አለን።

በረከት ቀጠለ : -" ከመለስ ንግግር በኃላ ተፈ ግርግር የአለባበስ እድገት አመጣ።... ኮቱን እርግፍ አድርጐ በመተው አዲስ ቢጫ ቆዳ ጃኬት ለበሰ... እነሆ ላለፉት ሁለት አመታት ያቺን ጃኬት የሚያስወልቀው ተናጋሪ ታጣ!"

ህላዌ " የኢህአድግ ባህል ማእከል ተገንብቶ ሲጠናቀቅ በሚኖረው መዚየም ሁለቱንም በክብር እናሳርፋለን "

በረከት " እስከዛ ለምን ብሔራዊ መዚየም ከሳሞራ የኑስ አጠገብ አይቀመጥም?"

ተፈራ " አቤት ብአዴን ! መቼ ይሆን ቅናት የሚለቅሽ?"

***

የተፈራ ሚስት አይኔ ደርባባ ናት። የብአዴን ካድሬዎች ደግነቷን ይመሰክራሉ። ቤቷን "የአብርሀም ቤት " ይሉታል። ድስትና መሶብ የሚገለበጥበት ቤት። ...ቅዳሜ ከሰአት የዋልዋ ቤት ትደምቃለች፣ ብአዴኖች የበረሀና የስልጣን ህይወታቸውን ያወጋሉ: ... በአዘቦት ቀንም ቢሆን ምሳ መብላት የፈለገ "እየመጣሁኝ ነው" ብሎ መደወል በቂው ነው... እኔም አንዲት አርብ ከህላዌ ጋር ሔጄ ድንኳን ሰብሬያለሁ።

በደግነት የተሞላችው አይኔ የምታሳልፈው ህይወት አልጋ ባልጋ አይመስልም... የዜሮ ድምር ጨዋታ የሆነው የኢትዬጲያ ፓለቲካ በርካታ የህይወት ጠባሳ አሳርፎባታል።

ወንድሞንና የቅርብ ዘመዶቿን በቀይ ሽብር አጥታለች። የተፋራጅ ኮሚቴ ውስጥ አመራር ሆና ሰርታለች። የቀይ ሽብር ሰማእታትን ለመዘከር መስቀል

አደባባይ የተሰራው ማእከል በእሷ ያላሰለሰ ጥረት የተሰራ ነው። የሰማእታቱ አጽም በክብር የተቀመጠ እለት ባሏን ተደግፉ ያነባችው እንባ ጭንቅላቴ ላይ ተቀርጾ ቀርቷል። የኪሱን መሀረብ የሰጣት አላሙዲ ነበር።

ያ! ክፉ ዘመን አልፎም አይኔ እፎይ አላለችም። ቀድሞ በአንድ መስመር የነበሩት ባሏና ወንድሞ አንዳርጋቸው ጽጌ ከአመታት በኃላ በተቃራኒ ተሰልፈዋል።... በወንድሞ የሚመራው ግንቦት ሰባት ሁሉን አቀፍ ትግል ብለው የሚጠሩትን ፀረ ኢህአድግ ዘመቻ አጠናክሮ ቀጥሏል። ዱሩ ቤቱ ብሎ ወደ ኤርትራ ተመላልሷል።

የ70 አመት አባቷ የገዛ ባሏንና ጓደኞቹን ለመግደል በማሴር ተጠርጥረው ማዕከላዊ ወርደው ነበር።... አባቷ ላይ የደረሰውን ኢ -ሰብአዊ ድርጊት ረፍት ቢነሳት " የፍትህ ያለህ! አባቴ የደም ብዛትና ስኳር በሽተኛ ነው። መዳኒት በየሰአቱ መውሰድ አለበት " በማለት ለሚዲያ አጋለጠች...በድጋሚ አነባች።

ባለቤቷ የብአዴን ማእከላዊ ኮሚቴ ሲመረጥ አሻፈረኝ አለ። ለወጣቶቹ መልቀቅ አለብን ብሎ ተከራከረ። ካድሬው "ያለ አንተ ብአዴን ... " ብሎ ጥያቄውን ውድቅ አደረገበት... የአንድ ሳንባ ብቻ ሳይሆን የማይድን በሽታ እያሰቃየው እንደሆነ ለጉባኤው ነናገረ...ጓደኞቹ "በቃ አታስጨንቁት! " ብለው ተማፀኑ። አይኔ በስልክ ተሰብሳቢው በአዳራሽ ተላቀሰ...

ለቀበቶ አልባው..." ዋልዋ!"... "ተፈ ግርግር!"

***

እኩለ ለሊት ሲቃረብ በረከት፣ ተፈራና ሚስቱ ጥለውን ሔዱ። የመርካቶና የካ ካድሬዎች አለቃ የሆኑት ሺሰማና ፈለቀ ተቀላቀሉን። ... ሁለቱ ጓዶች በከተማዋ ተካሂዶ የነበረውን " ጉራጌ መራሽ አብዬት " ከጠነሰሱት መካከል ግንባር ቀደሞቹ ናቸው። የአብዬቱ ሴራ ከታወቀ በኃላ ሂሳባቸውን አወራርደው የቅልበሳው መሪ ተዋንያን ሆነዋል። ለዚህ ውለታቸውም የአዲሳባን ካቢኔ እንዲቀላቀሉ ተደርጓል።

እነ ሺሰማ በዛ እኩለ ለሊት ሲመጡ የምስራች ይዘው አልነበረም። ቆጠራው አስደንጋጭ ውጤት ይዞ እየመጣ መሆኑን አረዱን። የአዲሳባ ህዝብ በድጋሚ ቀለደብን አሉን።

የቆጠራ ሂደቱን በአካል ተገኝቶ ለማየት ወጣሁ። አራት ኪሎ አቅራቢያ ወደሚገኙት አምስት ምርጫ ጣቢያዎች ተራ በተራ ሔድኩኝ፣... አይንና ጆሮዬን ማመን አቃተኝ።

የምርጫ ጣቢያ ሀላፊዎች ድምፅ የተሰጠባቸውን ወረቀቶች በመፈታታት ለታዛቢዎች ተራ በተራ ያሳያሉ። ለማን እንደሚመዘገብ ይናገራሉ።... የምርጫ ታዛቢዎች ወረቀቱ ላይ የሰፈረውን ምልክት በማየት በሶስት ጮራ ይመዘግባሉ : - ኢህአድግ ፣ተቃዋሚና ድምፅ አልባ በማለት። የተቆጠሩት ወረቀቶች በሶስቱ ፈርጅ ተለይተው ይደረደራሉ።

በሄድኩባቸው ጣቢያዎች የኢህአድግ ታዛቢዎች የመዘገቡትን ውጤት ወሰድኩኝ።... በአምስቱም ጣቢያዎች የሚመራው " ድምፅ አልባ " የሚለው ነበር።... ከተቆጠሩ አንድ መቶ ወረቀቶች ውስጥ ከሀምሳ በላይ ድምፅ አልባ

ነበር።

እየገረመኝ በደምፅ አልባ ወረቀቶች ላይ የሰፈረውን ጽሁፍና ምልክት ወደ መመዘገብ ተሸጋገርኩ...

ሌላ ጉድ!!

" ኢህአድግ ሌባ!"..." ኢህአድግ ዘረኛ "..." የደም ስልጣን " ..."ሆዳም !"...

በመላ አዲሳባ ያለውን ለማወቅ ጉጉት ስላደረብኝ ወደ ቢሮ ተመለስኩ። ከሁሉም ክፍለ ከተማ እውነቱን ሊነግሩኝ ይችላሉ ብዬ የማስባቸውን ካድሬዎች አሰማራሁ።

የሚገርም ነበር። በሁሉም ጣቢያዎች እየመራ ያለው ድምፅ አልባ ቀጥሎ ኢህአድግ መሆኑን ነገሩኝ። ስድቦቹም ተመሳሳይ ናቸው ። የተጻፉትም ልቅም ባለ አማርኛ ስለነበር ፀሀፊዎቹ ወጣቶችና የተማሩ ሰዎች እንደሚሆኑ ጥርጣሬያቸውን ነገሩኝ።

ኢህአድግ ሌባ! ፣ ኢህአድግ ዘረኛ ፣የደም ስልጣን ፣...

ይህ ጥሬ ሀቅ የተደበቁ እውነቶችን ፍንትው አድርጐ ያወጣ ነበር።

በአንድ በኩል ነዋሪው በተለይም ወጣቱና የተማረው ክፍል በድጋሚ ኢህአድግን እንደማይፈልግ ያረጋገጠበት ነበር። በተጨማሪም ህዝቡ ከኢህአድግ በላይ ለምርጫ የቀረቡትን ተቃዋሚዎች እንደሚጠላ አሳይቷል።

በሌላ በኩል እኛ ኢህአድጐች ከአስር ሚሊዬን ብር በላይ አውጥተን ከዘረጋነው ኔትወርክ በላይ ውስጥ ለውስጥ የተደራጀ ህቡእ ሀይል መኖሩን ያመላክታል። ... ይህ ውስጥ ለውስጥ የተደራጀ ኔትወርክ በከተማዋ ገጠር ቀበሌዎች ሳይቀር የተዘረጋ ነበር፣ በከተማው አርሶ አደር አካባቢ " ኢህአድግ ሌባ "፣ " ሆዳም!" ተብሎ የተጻፈበት ወረቀት ማግኘት የሚስጥር አደረጃጀቱ ምን ያህል ወደ ህብረተሰቡ ዘልቆ የገባ መሆኑን የሚያሳይ ነበር።

***

ምርጫው በተካሔደ በንጋታው ሰኞ የሁሉም ምርጫ ጣቢያዎች ውጤት እጃችን ገባ። በ2000 አ• ም• የተካሄደውን ዳግም ምርጫ አሸናፊው " ድምፅ አልባ " የሆነው የከተማው ነዋሪ ሆነ። ሁለተኛ ኢህአድግና የአየለ ጫሚሶ ዶክተር ሆኑ።

በደስታ ብዛት አመሻሽ ላይ የቀበሌና ክፍለ ከተማ ካድሬዎቻችንን ኢህአድግ ቢሮ የምግብና መዚቃ ድግስ ጠራን። ግቢውን በእንኳን ደስ አላችሁና ባንዲራ አሸበረቅን።...ካድሬዎቻችን የሶስት አመት ልፋት ውጤታቸውን በጋራ ለማክበር ተጠራርተው መጡ። አራት ኪሎን የሚያንቀጠቅጡ የማጉሊያ እስፒከሮች በአራቱም አቅጣጫዎች ተተክለው መጮህ ጀመሩ።

ሁሉም መገኘቱ ሲረጋገጥ ህላዌ የደስታ መግለጫ ለማሰማት ወደ መድረክ ወጣ። ብርጭቆአችንን እንድናነሳ ጠየቀ። አነሳን።

" በምርጫ 97 ከ138 ወንበር 137 ቅንጅት አሸንፎ ነበር። አሁን ደግሞ ታሪክ ራሱን ይደገማል እንዲሉ በተቃራኒው ኢህአድግ ከ138 ወንበር 137 ሰከያሸንፍ ቅንጅት አንድ ወንበር ብቻ አገኘ።... ለዚህ ታሪክ ደጋሚ ድል ዋንጫችንን እናንሳ።" በማለት ጮክ ብሎ ተናገረ።

ብርጭቆአችንን አጋጭተን የተቀዳልንን ወይን ጨለጥን።

ደም የጠጣሁ ያህል ዘገነነኝ... የአይችሎም ያልደረቀ እንባ ፊቴ ላይ ድቅን አለ... የድምፅ አልባ ወረቀቶች ድምፅ ህሊናዬን ረፍት ነሳው...ጩኸታቸው አንዳልረጋጋ አደረገኝ።

ኢህአድግ ሌባ... ዘረኛ... የደም ስልጣን...ሆዳም!

የሙዚቃ ድግሱ ሊጀምር ሲል የከተማው ኢህአድግ ክንፍ በአስቸኳይ አቶ በረከት ቢሮ ተጠራን።

የበረከት የትላንትና ደስታ ብንን ብሎ ጠፍቷል። ጠረጴዛው ላይ የማጠቃለያ ውጤቱን የሚያሳይ ሪፓርት ብቻ ተቀምጧል። በሰንጠረዥ መልኩ አዘጋጅተን የሰጠነው እኛ ነበርን።

ሁላችንም መምጣታችንን ሲያረጋግጥ አጭር ማሳሰቢያ ሰጠን : -

" ከዛሬ ጀምሮ በክፍለ ከተማና ቀበሌ ሊካሔዱ የታሰቡ ተሀድሶዎች እንዳይካሄዱ። ያልመረጠን ህዝብ ብዙ ስለሆነ ዳንኪራ ባዘጋጀን ቁጥር የባሰ ቂም ይይዝብናል። ድምጻችንን አጥፍተን ልማታዊ መንግስት መሆናችንን እናሳያለን። ድርጅቱ ሁሉም ነገር ወደ አዲሳባ እንዲሆን ወስኗል። " አለን።

እቤቴ ስደርስ በማስታወሻዬ ላይ " ድምፅ አልባ ድምፀኞች" በሚል አሰፈርኩት።... አቶ በረከት ደግሞ ከሶስት አመት በኃላ " ታሪክ ራሱን ይደግምል፣ መጀመሪያ አሳዛኝ፣ ቀጥሎም ቧልት በሚመስል መንገድ " ብሎ በመፅሀፍ መልክ አዘጋጅቶ ለንባብ አበቃው።

***

ዳግም ንቅል ካድሬ

በኢህአድግ ከፍተኛ ካድሬነት ዘመኔ በአቶ መለስና በረከት መካከል ለሶስት ያህል ጊዜያቶች ዱላ ቀረሽ ጭቅጭቆችን አይቻለሁ። እነዚህ ልዩነቶች በድርጅቱ የወደፊት አቅጣጫዎች ላይ ትርጉም ያለው ለውጥ የሚያመጡ በመሆናቸው ምክንያት የዘወትር ትዝታዎች ናቸው።

የመጀመሪያው አለመግባባት የተፈጠረው በአዳዲስ አባላት የምልመላ መስፈርትና ብዛት ላይ ነበር። አቶ መለስ በጥራት ላይ አተኩረን ማኔጂብል አባላት ይኑረን የሚል አቅጣጫ አስቀመጠ። በረከት ደግሞ ከገበሬ እስከ ምሁር፣ ከናጠጠ ሀብታም እስከ ጉዳና ተዳዳሪ ከመምህር አስከ ተማሪ በአስር ሚሊዬኖችን በመመልመል የኢትዬጲያን ምድር በኢህአድጎች ጎርፍ እናጥለቅልቃት አለ...

በረከት አሸነፈ። መለስ የፈራው አልቀረም ድርጅቱ ቆሜለታለሁ የሚለውን ወገንተኝነትና አብዬታዊነት አጣ።

ሁለተኛው አቶ መለስ በ2001 አ•ም• ለጋዜጠኞች ጋዜጣዊ መግለጫ ሲሰጥ በድጋሚ ስልጣን እለቃለሁ ብሎ በመናገሩ ምክንያት የመጣ ነበር። የዛኑ እለት እኔና ሽመልስ ከማል በረከት ቢሮ ተቀምጠን በስልክ ከአንድ ሰአት በላይ ሲጠዛጠዙ አዳመጥን። በረከት የኢህአድግን አሰራር ጠቅሶ መርህ ጥሰሀል ብሎ ተከራከረው። የአማርኛ መነታረኩ ወደ ጠንካራ ትግርኛ ተቀየረ።

አቶ መለስ :"ህመሜን የማውቀው እኔ ነኝ እንጂ አንተ አይደለህም" ብሎ ተከራከረ።

በረከት በበኩሉ "ማን ያልታመመ አለ? አንተ የምትለቅ ከሆነ እኛም እንለቃለን " ብሎ መለስን አስፈራራው። ሳይግባቡ ስልኩ ተዘጋ። የዛኑ ማታ በረከት ለአንድ የግል ፕሬስ ደውሎ " መለስ በግሉ እለቃለሁ ብሎ መናገር አይችልም። በዚህ ጉዳይ የመወሰን ስልጣን የለውም " ብሎ መግለጫ ሰጠ። አዲስ ነገር ጋዜጣን ጨምሮ የሁሉም ፕሬሶች ሳምንታዊ ትኩረት በሁለቱ ዝሆኖች ልዩነት ላይ አነጣጠረ። ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በረከት አሸነፈ። አቶ መለስ ሀሳቡን አሻሽሎ " የግል ፍላጐቴን ነው ያነሳሁት። የመጨረሻውን ውሳኔ የሚሰጠው ድርጅቴ ነው። ድርጅቴ ይፈቅድልኛል ብዬ አስባለው " በማለት አክሮባት ሰራ። ድርጅቱ ሳይፈቅድለት ቀረ። አቶ መለስ የፈራው ግን አልቀረለትም... ሞተ።

ሶስተኛው ልዩነት የመጣው በ2000 አ• ም• የአዲሳባን ከንቲባና ካቢኔ ለማደራጀት በተደረገው እንቅስቃሴ ላይ ነበር። አቶ መለስ ከከንቲባና ምክትሉ ውጭ ሌሎቹን የካቢኔ አባላት አዲስአባ ተወልደው ያደጉ (Indigenous) መሆን እንደሚኖርባቸው አሳሰበ። በረከት በበኩሉ ትልቁ ጉዳይ ልማታዊ መንግስትነታችንን የሚያረጋግጡ ሰዎች ከየክልሉ አምጥተን እንደምንደራጅ ገለፀ። በረከት አሸነፈ። አዲሳባ ድጋሚ በንቅል ካድሬዎች ተጥለቀለቀች። ቀጥሎ የሚመጣው ጥያቄ ማን ከንቲባ ይሁን የሚለው ቧልተኛ ታሪክ ይሆናል።

***

የአዲሳባ ኢህአድግ ስራ አስፈጻሚዎች በረከት ቢሮ ለስብሰባ ተቀምጠናል። አጀንዳው በዳግም በሁለት ሺህ ምርጫ መዲናይቱን በድጋሚ በመቆጣጠራችን ከንቲባና የካቢኔ አባላትን ለመመልመል ነበር።

አሳዛኙ፣ዳግማዊውና ቧልተኛው ታሪክ የትኛው ነው ?

አያት አክሲዮን ማህበር ህገ ወጥ በሆነ መንገድ የተገኘን ገንዘብ ህጋዊ አስመስሎ በመስራት፣ በአራጣ ማበደር ፣ያልተፈቀደ የባንክ ስራ መስራት፣ የ ገቢ ግብርና ታክስ ህግ መተላለፍ፣ ከቀረጥ ነፃ እቃዎች እንዲገባ በማታለል ... አጠቃላይ በ21 ክሶች ጥፋተኛ ተባለ። ከፍተኛው ፍርድ ቤት ለጥፋቱ 176 ሚሊዬን ብር በላይና የ12 አመት እስራት ተፈረደበት። የሚገርመው ነገር በክሱ ውስጥ ህገ መንግስቱን በመጻረር የከተማዋን ሲሶ መሬት መሸጥ መለወጡ አልተነሳም። ይህ ቢነሳ ኖሮ ከማዘጋጃ ቤት እስከ ቤተመንግስት የሚደርስ ክር ይመዘዛል።..... ይቀጥላል

የከተማው ነዋሪ በሰለጠነ መንገድ በድምፅ አልባ ድምፀኞች አማካኝነት የውስጡን ፍላጐት የገለፀበት ፣ ወይንስ በአቶ በረከት የተገለፀው ? ...

ምእራፍ ፡ **ዘባተሎው መሪ !**

ወደ ኦሮሚያ ምክር ቤት ተመልሰናል።

በጨፊ እየተካሔደ ባለው ግምገማ አጠቃላይ ችግሮች ከቀረቡ በኃላ ወደ ግለሰብ አውጫጭኝ ተገባ። የመጀመሪያው አቅራቢ አሊ አብዶ ሆነ። ...ሰውየው ተደናግጦል፣... በከተማው ግንባር ቦታ የገነባው ቪላና ፎቅ እንቅልፍ ነስቶታል...

አይውጠው ነገር...!

ቢሆንም ግን አልሞት ባይ ለመሆን አይኑን በጨው አጥቦ ጥቂት ዘላበደ :- የሙስና ችግር እንደሌለበት፣ ለጥቅም የዘረጋው ኔትወርክ እ ንደሌለው፣ አዳዲስ አስተሳሰቦችን ለመቀበል ችግር እንደሌለበት አስረዳ።... ቁልፍ ችግሩ " አደራጅቶ መምራት ያለመቻል " እንደሆነ ገለፀ።

ርግጥም ተምታቶበታል... መሪ ሳይኮን መምራትን ከየት አመጣው ?

ሽሮ ቢደነፋ እንጀራ እስኪቀርብ ነው !

አባይ አለ ያላነሳው ነገር ካለ ቤቱ እንዲያሳየው እድል ሰጠ።...አባይ በአለ አቀራረብ መናደዱ ያስታውቃል... ሁለት እጆች ቀድመው ተቀሰሩ፣... ማካቬሊያኖቹ ዘርአይ አስግዶምና ኢሳያስ ... ለዘርአይ አስቀድሞ ተሰጠው።

ዘርአይ " አለ! የዝች ከተማ መበስበስና መብከት ተጠያቂው አንተ ነህ። ...ከሙስና የፀዳው ነኝ የምትለው ቦሌ የገነባኸው የሁለት ሚሊዬን ብር ቤት መሬቱንና ገንዘቡን ከየት አምጥተህ ነው?"

አለ " ... መሬቱን ህጉን በተከተለ መንገድ በካቢኔ ውይይት ተደርጐበት በአብላጫ ድምፅ ተወስኖ ነው። ... ብዙዎቻችን ወስደናል። ... ቤቱን የሰራሁት አረብ ሀገር ባሉ ዘመዶቼ እርዳታ ነው... ቤቱ የተሰራው በግማሽ ሚሊዬን ብር ነው።"

ዘርአይ " የካቢኔ አባላት አብራችሁ ነዋ የዘረፋችሁት?"

አለ " አማርኛህን አስተካክል! በካቢኔ የመወሰን ስልጣን አለን።"

ዘርአይ " ካቢኔውን ወደ አይን ያወጣ ዝርፊያ የወሰሰድከው አንተ ነህ።...ይባስ ብላችሁ መሀል ቦሌ ላይ የህዝብ ንብረት ትዘርፉላችሁ?"

አለ " ስነስርአት አድርግ!... ዘራፊ እንድትለኝ አይደለም እዚህ የተቀመጥኩት።... ሀቁን ተናገር ካልክ አንተን እንዲህ ያብገነገነህ ሌላ ነገር ነው... አንተን ጨምሮ የፌዴራል ተቋማት ኢህአድግ ኮሚቴዎች እኔ ጋር መጣችሁ ለእኛም የቤት መስሪያ ቦታ ስጠን ብላችሁ ጠየቃችሁኝ።... ደብዳቤ ፅፋችሁ አምጡና በካቢኔ እናየዋለን አልኳችሁ፣... በተለይ አንተ ወደ ኃላ ቀረት ብለህ ደብዳቤ መፃፍ አደጋ አለው ድርጅቱ ሊሰማ ይችላል አልከኝ።"...

አዳራሹ በሳቅ ተሞላ...

ለባለጌ ገድሉ ውርደቱ !

አባይ " የዘርአይን በራሱ ጊዜ እናየዋለን።... እነ አለ ቦሌ ላይ መሬት የተቆራመታችሁት ወንጀል ነው። ... እርምት ካልተወሰደበት በወንጀል ሊያስጠይቅ ይችላል።...እኔ ባለኝ መረጃ የተዘረፈው መሬት የትምህርት ቤት ቦታ ተቆርጦ ነው ፣ይህ ደግሞ የከፉ ያደርገዋል።"አለ...አጠገቤ የታመጠው ፍስሀ "አባይ መቋጠር ጀመረ " ብሎ ማስታወሻዬ ላይ ፃፈ።

ቀጥሎ ለደህንነት ሀላፊው ኢሳያስ ተሰጠው፣ ... በእብሪት የታጨቀ ስድብ ካቀረበ በኃላ በማጠቃለያው " አለ አዲሳባን የመሰለች ውስብስብ ከተማ ቀርቶ ወረዳ ለመምራት ብቃት ያንሰዋል።... በዛ ላይ ዝርክርክ ነው" አለ።

አባይ ተመሳሳይ ይዘት ያለው ትችት አቅርቦ ማሳረጊያውን " አለ ዝርክርክ ብቻ ሳይሆን ደንታ ቢስና ዘባተሎ ነው" በማለት አጠናከረ...

ዝርክርክ ! ... ዘባተሎ !!

አለ በተቀመጠበት ወንበር ተፈረካከሰ።

የእለቱ ግምገማ በዚህ የአባይ ቃል ተፈፀመ፣... ለቃል አቀባይነት የተመረጥነው እኔና ሉልሰገድ ወደ ኃላ እንድንቀር ተነግሮ ሌላው ተበተነ። ... ከኢህአድግ ቢሮ ጋዜጠኞች እየመጡ ስለሆነ የእለት ውሎውን እንድንገልፅላቸው እንደሆነ ተነገረን። ... አፍታም ሳይቆይ የአብዬታዊ ዲሞክራሲ አዘጋጆቹ ሴኮቱሬና ፍሬህይወት አያሌው ተያይዘው መጡ። ...ወሎውን በጥቅሉ

ነግረናቸው በግለሰብ ደረጃ እየተነሱ የነበሩት ማጠቃለያ ስላልተሰጣቸው በንጋታው አመሻሽ ላይ እንደምንገልፅላቸው ተስማምተን ተለያየን።

ወደ ቤቱ ገብቼ ሬዲዬ ስከፍት ሬዲዬ ፋና ሰበር ዜና እያነበበ ነው።... በዜናው መዲናይቱን የማደስ ስራ መቀጣጠሉን ያበስራል።... ይህን ተከትሎ በአመራሮቹ ላይ ግምገማ እየተካሔደ መሆኑና በእለቱ ውሎ የአዲሳባ ፕሬዝዳንቱ አለ አብዶ መገምገሙን ያትታል።...አቶ አለ ከተማዋ እንደ ግመል ሽንት ወደ ኃላ እንድትጐተት ያደረገ ደንታ ቢስና ዝርክርክ መሪ አንደሆነ መግባባት ላይ መደረሱን ከግምገማው ቃል አቀባይ መረጃ እንዳገኙ ገለፁ፣

ደንታ ቢስ!... ዝርክርክ!!

አሊን በተመለከተ ለፍሬህይወትና ሴኮ ምንም መረጃ ባልሰጠናቸው ሁኔታ እንደዛ አይነት ዜና መለቀቁ አስገራሚ ነበር።

በንጋታው ጠዋት ረፈድ ብሎ የተጀመረው ስብሰባ በአለ እንባ የታጠበ ነበር።... በእጁ የያዘው የግል ፕሬስ በርዕሰ አንቀፁ በሳለው ካርቶን ስዕል የአለ ቢሮ በዶሴ ተሞልቶ፣ የሚሰራው ግራ ገብቶትና ንፍጡ ተዝረክርኮ የሚያሳይ ነበር። ...ይህም ቢሆን አስቀድሞ የተሰራ ካልሆነ በአንድ ምሽት ተዕፎ ለህትመት አይደርስም።... አለ በሲቃ " የእኔስ ይሁን እዳው ገብስ ነው! ቢያንስ ለባለቤቴና ልጆቼ እንዴት አይታሰብም ? ... ባለቤቴ ምሽት ላይ ሀዘን ቤት ሔዳ መሳለቂያ ቢያደርጓት እያለቀሰች መጣች፣ ...ዛሬ ጠዋት ልጆቼ ትምህርት ቤት ቢያስጨንቋቸው ደውለው ደንታ ቢስና ዝርክርክ ማለት ምን እንደሆነ ጠየቁኝ "አለ።

ካድሬው በቅንብሩ አዘነ እንጂ በአለ አብዶ ላይ የቀረበበት ስድቦች የሚያንስበት እንደሆነ ያውቃል፣... አለ አብዶ በብዙ ጉዳዬች ወንጀለኛ ነው: ... ኢትዬጲያዊነት እና የጋራ ማንነት እሴቶቻችን እንዲጠፉ አድርጓል፣ ... ህዝቡ በዘር መከፋፈሉ ሳያንስ በሀይማኖት ጐራ ለይቶ እንዲጫረስ ለማድረግ ቀን ከሌት የሰራው እሱ ነው ፣ በዚህ ምክንያት ብዙ ዜጐች እርስ በራስ ተጋጭተዋል፣ በመንግስት ታጣቂዎች ተገለዋል፣... የህዝብ ንብረት የሆነው መሬት እንዲዘረፍ አድርጓል ፣...ይህም ከሁለት ቢሊዬን ብር በላይ የህዝብ ገንዘብ ቀልጧል። ... ህገመንግስት የሚንዱ መመሪያዎች እንዲወጡ በማድረግ ነዋሪው ከአካባቢው እንዲፈናቀል አድርጓል። ... የከተማው ህዝብ በማያቋርጥ የድህነትና በሽታ ኡደት ውስጥ ገብቶ እንዲማቅቅ የእሱ ድርሻ ከፍተኛ ነው፣ ...በከተማዋ የተካሔዱት የሰብአዊ መብት ጥሰቶች በሱ መሪነት አለያም አድርባይነት የተፈፀሙ ናቸው።

ስለዚህም ይህንን የሰውየውን ጥፋቶች ገለጥለጥ አድርጐ ማሳየት አሰፈላጊ መስሎ ስለተሰማኝ አስተያየት ለመስጠት የመጀመሪያው የመዲናይቱ ካድሬ ሆንኩኝ። አለ በእኔ ላይ የፈፀመውን በደል ስለሚያውቀው የእኔ እጅ በቅድሚያ ተቀስሮ ሲያይ ደነገጠ...

እንደማለቀው ገብቶታል... አንድ ቀን በሰፈረኝ ቁና እንድ ሰፍረው አምላኬን ተማፅኜ ነበር። ... የጨፈፌ ግምገማ የያዘውን ድብቅ አላማ ባልደግፈውም የሰውየውን ነውረኝነት ለመግለፅ ከዚህ የተሻለ እድል አላገኝም። ...የመናገር እድሉ ተሰጠኝ፣ ተረጋግቼ ነጥብ በነጥብ አቀረብኩ ፣አንገቱን ደፉ።

... ለጨፈው በአጭሩ የተናገርኩት፣ ለግል ማስታወሻዬ ደግሞ ዘለግ አድርጌ የፃፍኩት ወግ የሚከተለውን ይመስላል:–

***

እኔና አለ. አብዶ መጀመሪያ የተጋጨነው በውጭ ጉዳይ ፓሊሲ ስልጠና ላይ ነበር።... ስልጠናውን የሚሰጡን እሱና የወጭ ጉዳይ ምክትል ሚኒስትሩ ደ/ ር ተቀዳ አለሙ ነበሩ፣... ከዶክተሩ ገለፃ ቀጥሎ በነበረው ውይይት በፓሊሲው ላይ ያሉኝን ሁለት ልዩነቶች አንስቼ ተከራከርኩ። ... እነዚህም ፓሊሲው በኤርትራ መንግስትና በግብፅ ላይ ያስቀመጠውን የተመለከቱ ነበሩ ...

የውጭ ጉዳይ ፓሊሲው ከኤርትራ መንግስት ጋር መቼም ቢሆን ሰላማዊ ግንኙነት አይኖረንም ይላል። ግብፅን በተመለከተ ደግሞ በሚስጥር አለ.ያም በመንግስት ደረጃ መገለፅ በሌለበት መልኩ ተፅፉል፣ ግብፅ የኢትዬጲያ ስትራቴጂክ ጠላት እንደሆነችና፣ ሀገሪቷ ጫካ ሳይኖራት 50 ሺህ የሽምቅና የጫካ ተዋጊዎችን አሰልጥና ዝግጁ ያደረገችው ለማን እንደሆነ ሳይታለም የተፈታ እንደሆነ ያሳስባል። በመሆኑም ከግብፅ ጋር የሚኖረን ግንኙነት ይህን ከግምት ውስጥ ያስገባ ሊሆን እንደሚገባ ይገልፃል።...

እኔ በበኩሌ ያነሳሁት ፓሊሲ በአጭር ጊዜ እይታና ስሜታዊነት መፃፍ የለበትም ፣የኤርትራ መንግስትም ሆነ ሻዕቢያ ሊቀየሩ የሚችሉበት እድል ዝግ መደረግ የለበትም የሚል ነበር።... ግብፅንም ቢሆን ከመልካም ግንኙነትና የጋራ ጥቅምን ከማሳየት ይልቅ ሰነዱ ፀብ አጫሪነትን ያሳያል የሚል ነበር።

አለ. አብዶ ...አበደ።

...ፓሊሲው አንዳችም እንከን የማይወጣለትና ድርጅቱ ተጨንቆ ተጠቦ ያወጣው እነደሆነ በመቆጣት ገለፀ።... የኤርትራ መንግስትም ሆነ ህዝብ የጥገኛ ፍላጐታቸውን ለማሳካት የሚንቀሳቀሱ በመሆናቸው ምንም ግንኙነት እንደማይኖር አሳሰበ። ... ግብፅንም በተመለከተ በአይነ ቁራኛ እየተከታተልናቸው መሆኑንና እኛም በበረሀ የሚዋጋ ሰራዊት እንደምናዘጋጅ ሊያዉቁ ይገባል አለ... ተቆጥቶ!

አጠገቤ ተቀምጦ የነበረው የካዛንችሱ መንግስት አባል የሆነው ፍስሀ መአሲ ወደ ጆሮዬ ጠጋ ብሎ " ዶክተር ብርሀኑ ነጋ ያለው ትክክል ነው! የጠላት አስተያየት ብለን ማጣጣል አልነበረብንም ። ይሔ ሰውዬ የሚረባ አይደለም...ሻዕቢያንና የኤርትራ ህዝብን መለየት አልቻለም" አለኝ። ...

(** በዛን ሰሞን የአዲሳባን ማስተር ፕላን ከመፅደቁ በፊት ለመተቸት ኤግዚብሽን ማዕከል የምሁራን ስብሰባ ተጠርቶ ነበር። በዛ ስብሰባ ላይ የተገኘው ዶክተር ብርሀኑ ማስተር ፕላኑ ሊያሰራ የሚችል እንደሆነ ፣ ግን ደግሞ በአሊ አብዶ ብቃትና ችሎታ ይፈፀማል የሚል እምነት እንደሌለው በግልፅ ተናገረ። ... የዶ/ ሩ አስተያየት በአህዴድ ደጋፍ ቁጣን ቀሰቀሰ።... ዶክተሩን በረከት ስምኦን ልኮት እንደሆነ መነገር ተጀመረ። በወቅቱ መልካም ግንኙነት እንደነበራቸው ይወራ ስለነበር፣...

የዛሬን አያድርገውና !...

ግራም ነፈሰ ቀኝ የዶክተሩ ቃል በተግባር ተፈፅሞል።)

በዉጭ ጉዳይ ፓሊሲው ላይ አስተያየት መስጠት የጀመረው

ዶክተር ተቀመዳ እኔን ደግፎ ተናገረ። ... አንድን መንግስት መቼም ቢሆን ዘላቂ ጠላት አድርጐ ማስቀመጥ የተለመደ ፓሊሲ እንዳልሆነ ፣ ... በሚስጥር መያዝ ያለባቸው እውነቶች በተለይም ወታደራዊ መረጃዎች በመንግስት ከሚገለፁ ይልቅ በሌሎች አካላት ቢነገሩ ዲፕሎማሲያዊ በሆነ መንገድ መልዕክቱን ማስተላለፍ እንደሚቻል አስረዳ።... ከልምድ አኳያም ቢሆን ሀገሮች የመንግስት ተቃዋሚ ፓርቲዊችን ፣ መንግስታዊ ያልሆኑና ለሀገር ተቆርቋሪ የሆኑ ድርጅቶችንና የሚዲያ ተቋማትን እንደሚጠቀሙ አብራራ...

በመሆኑም የኢትዬጲያ የውጭ ጉዳይ ፓሊሲ መቀየር አለበት ብሎ እንደሚያምን፣ ግን ደግሞ ፓሊሲ ከመለወጥ አንፃር እሱ አንዳችም ሚና እንደሌለውና ለፃፉት ሰወች መልእክታችንን እንደሚያደርስ በቅንነት ገለፀ። ... የዶክተሩ ንግግር አግራሞትን የፈጠረ ነበር፣... አንድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚንስትር በራሱ ተቋም የሚፈፀመውን ፓሊሲ ችግር አለበት ግን ደግሞ የመወሰን ስልጣን የለኝም ሲል ምን ሊባል ይችላል?...

ያዉም የዶክተረ ምሁር!!

የዛኑ እለት ማታ አሊ አብዶ ቢሮው ጠራኝ ፣...ሔድኩኝ።... ለመቀመጥ እንኳን እድል ሳይሰጠኝ " ሰድበህ ለሰዳቢ አዳረከን ፣ ተቀዳ ኢህአድግ አለመሆኑን እያወክ እንዴት እንደዚህ አይነት አስተያየት ትሰጣለህ? ... በዲፕሎማሲው ዙሪያ የስዩምን ክፍተት ይሞላል ተብሎ እንጂ ፀረ _ኢህአድግ መሆኑን ጠፍቶህ ነው? " አለኝ።

ሰለ ተቀዳ እንደማላዉቅ ገለፅኩለት፣ ... ትክክልም በተባራሪ ከሚወራው ዉጭ ስለ ዶክተሩ የማውቀው ነገር የለኝም። ... የአቶ ስዩምን የብቃት ማነስ የሸፈነለት እሱ እንደሆነና ካለፈው ስርአት ጋር ንክኪ እንዳለው ሲወራ ሰምቻለሁ።... በፓሊሲው ላይ ልዩነት ያነሳሁት በትምህርት ቤት የአንድ ተቋም ራዕይ ፣ ፓሊሲና ስትራቴጂ እንዴት እንደሚቀረፅ የተማርኩትን እንደሆነ ጨምሬ ነገርኩት።

አሊ ጨሰ ፣የሰነፍ ስድቡን አዘነበብኝ...

" ፓሊሲውን ያወጡት ሰወች ያልተማሩ ይመስልሀል? ... ከልጅ አእምሮ በላይ የሆነ ጉዳይ ስለፃፉ ነው ሮኬት ሳይንስ የሆነብህ !" አለኝ።... ዝም አልኩት፣ እንዲገባው ብዬ።

" የምትሰማ ከሆነ ኢህአድግ ሆኖ በድርጅቱ መርሆዎችና ፓሊሲዎች ላይ ልዩነት ማንሳት አይቻልም። አለበለዚያ ግን ድርጅቱን ለቀህ መውጣት ይኖርብሀል" ብሎ ዛቻ አዘል ማስጠንቂያ ሰጠኝ። ...ብናደድም የመጨረሻውን ድንጋይ ሳልወረውር መው ጣት ስላልፈለኩ : " አቶ አሊ እኔ እስከሚገባኝ ፓሊሲ የሚቀረፀው ከዚህኛው አማራጭ ይሔኛው ይሻላል በሚል ስሌት መሰለኝ። ... በመሆኑም የድርጅታችንን አማራጭ ሆነ ተባራሪውን በእውቀት ላይ በመመስረት ብንገነዘበው የተሻለ ይመስለኛል" በማለት በስላቅ ተናገርኩት።

ስሜን እየጠራ " ቀስ ብለህ እደግ!... እንደ ጓደኞችህ ብትበስል ይበጅሀል!" በማለት አመናጭቆ አሰናበተኝ።

***

በንጋታው ጠዋት ዶክተር ተቀዳ በፓሊሲው ላይ

የተደረጉ ማሻሻያዎች የያዘች አንዲት ወረቀት በተነ።... ማሻሻያው በፓሊሲው ላይ የኤርትራ መንግስትን በተመለከተ የተቀመጠው ሙሉ ለሙሉ ተሰርዟል ይላል። አሊን በቆረጣ አየሁት ፣እሱም እያየኝ ነው።... ትላንትና ዝም ያለው ካድሬ ስለማሻሻያው ትክክለኝነት ለመግለፅ እጁን ችቦ አደረገ።

በምሳ እረፍት በድጋሚ ቢሮው ጠራኝ። ...ድንቁርናውን ተገንዝቦ ይቅርታ ሊጠይቀኝ እንደሆነ ገመትኩ፣ ... የሆነው ግን ሌላ ነበር•••

እኔ አሰተዳደር ዘርፍ ሆኜ በተመደብኩበት ዞን ወስጥ በሚገኘው ወረዳ 24 አስቸኳይ ስራ ስለመጣ ስልጠናውን ማቋረጥ እንዳለብኝ ነገረኝ።... ስራው እውነተኛ ኢህአድግነቱ በወሬ ሳይሆን በተግባር የሚለካበት እንደሆነ አስገነዘበኝ። ... ከሰአታት በኃላ ካሊድ ቢሮ ስብሰባ ሰለሚጀመር ምሳዬን በልቼ እንድሔድ ገለፀልኝ።

***

ካሊድ ቢሮ ተገኘሁ። ...ለእኔ ሳይነገረኝ በ ስራ ያሉት ወረዳ 24 ሊ/ መንበሯ ወይዘሮ ሙለሜ ረሺድና በዛው ወረዳ ቀበሌ 15 (አየር ጤና) ሊ/መንበሩ ዘርሙ ከማል ተገኝተዋል። ...አንድ የማላውቀው ዒሙን ያጐፈረ በጐልማሳ እድሜ ያለ ሰው የተጠቀለለ ወረቀት ይዞ ተቀምጧል፣... ግራ የሚያጋባ ነው!... ስብሰባው በካሊድ ዲስኩር ተጀመረ: ... በመዲናይቱ የክርስትናና እስልምና ተከታዬች ህዝብ ብዛት፣ ... ቤተክርስትያኖችና መስኪዶች አለመመጣጠን፣ ... ይህንን ችግር የፈጠሩት ያለፉት መንግስታት እንደሆኑ ፣... አብዬታዊ መንግስታችን የተዛባውን ለማመጣጠን በትጋት እየሰራ እንደሆነ ፣ ... ይህ ደግሞ የአብዬታዊ ዲሞክራሲ የፀና ደጋፊ የሆነውን የሙስሊሙ ማህበረሰብ የበለጠ እያስደሰተው እንደሔደ ተናገረ።

እነሱ አንገታቸውን እየነቀነቁ ፣ እኔ ደግሞ ተከታዩን ለመስማት በመጓጓት አዳመጥነው።

የተሰበሰብንበት ምክንያት በወረዳ 24 ቀበሌ 15 ሁለት የተለያዩ ቦታዎች ላይ ህጋዊ በሆነ መንገድ የመስኪድ ግንባታ ስለተፈቀደ አፈፃፀሙ ላይ ለመነጋገር እንደሆነ ገለፀልን። ... በስብሰባው አብረው ያሉት ጐልማሳ መሀመድ እንደሚባልና የመስኪድ ግንባታዉ አስተባባሪ እንደሆነ ጨምሮ ተናገረ።

በአንድ ቀበሌ ውስጥ በተመሳሳይ ጊዜያቶች መስኪድ ለመስራት አንዴት ይፈቀዳል የሚል ጥያቄ አነሳሁ። ... ሰዎቹ የመስኪድ ግንባታ የጠየቁትና የጠቆሙት በከተማው ማስተር ፕላን መሰረት ህግን ተከትለው እንደሆነ በድጋሚ ገለፀ። ... ካቢኔው በቅድሚያ ለሚመጣ ጥያቄ ፍትሀዊነቱን እየፈተሸ እንደሚፈቅድ ጭምር ቆጣ ብሎ ተናገረ... እንዳለቃው!

ሙለሜ በበኩሏ የመስኪድ ግንባታ ጥያቄው የአስተባባሪ ኮሚቴው ብቻ ሳይሆን በቀበሌው የሚኖሩ ሙስሊሞች እንደሆነ የሚያሳይ የድጋፍ ፊርማ የተሰባሰበበት ወረቀት አውጥታ አሳየች። ... ኮሚቴው በጠራው ስብሰባ በአካል ተገኝታ እንዳረጋገጠች ማስተማመኛ ሰጠች።...የቀበሌው ሊቀመንበር እሱ የሚያስተዳድረው ቀበሌ ከፍተኛ የማስፉፊያ ቦታ ስለሆነ ጥያቄውን ፍትሀዊ እንደሚያደርገው ነገረን፣... የህዝብ ስርጭቱን በጐሳና ሀይማኖት በመከፋፈል ዘረዘረ።... የሀይማኖት ተቋማት ብዛት ኢፍህታዊ በሆነ መልኩ እንደተሰራጩ

ገለፀ።

የመጨረሻው ተናጋሪ ጉልማሳው እንግዳ ሆነ።፣... ሰዉየው ፍቃዱን ለማግኘት ስድስት ወር እንደፈጀባቸው፣ አንደኛውንመስኪድ ለማሰራት ቃል የገቡት የአንድ አረብ ሀገር ልዑል እንደሆኑና ቃላቸውን ሳያጥፉ መፍጠን እንዳለባቸው ፣ ሁለተኛውን የሚያስገነቡት በአካባቢው መኖሪያ ቤት የሰሩ የቡና ነጋዴዎች እንደሆኑ ተናገረ። በእጁ ያዘውን ፕላን እየዘረጋ በተጨማሪም በአካባቢው ለህዝቡ የሚጠቅሙ መሰረተ ልማት ፣ ትምህርት ቤትና ጤና ጣቢያ አብሮ እንደሚገነባ ማብራሪያ ሰጠ።

ዝም አልኩኝ፣ ...እነሱ የተናገሩት እውነት ከሆነ ህብረተሰቡ ሀይማኖት ሳይለይ በጋራ ተረዳድቶ እንደሚሰራ የቀደሙ ልምዶች እንዳሉ ስለማውቅ።...የአዲሳባ ክርስትያንና ሙስሊሙ ማህበረሰብ ከመቻቻል አልፎ እርስ በራስ የሚረዳዳ ህዝብ ነው ፣ ... ደስታውን ፣ሀዘኑን ፣አውደ አመቱን በጋራ የሚያከብር ጨዋና የሚያስቀና ... ቤተሰቦቻችን የአመቱ ገብርኤልን ለመዘከር ድግስ ሲያዘጋጁ ሁለት ድስት ጥደው ነው፣ ... በተመሳሳይ የረመዳንን ጾም ሙስሊም ጐረቤቶቻችን ቤት ሆደን አ ብረናቸው እናፈጥራለን... እንደነሱ የጾሙን ወቅት በጉጉት እንጠብቃለን።

ካሊድ ግንባታው እንዴት እንደሚፈፀም አቀረበ : _ዙሪያውን የማጠር ስራ ለሊት እንደሚጀመር ፣ ኮሚቴዎቹ በቂ ድንጋይ ፣ አሸዋና ሲምንቶ እንዳዘጋጁ ፣ ከዞኑ የተውጣጡ 250 ፓሊሶች እንዲዘጋጁ ለፓሊስ ኮሚሽነሩ ጥብቅ መመሪያ መሰጠቱን ገለፀ። ... ፀረ ሰላም ሀይሎች ሊያደርሱ የሚችሉትን ትንኮሳ የመመከት ስራ በወረዳው ፓሊስ አዛዥ ተሰፋ ፈርሻ እና በአኔ ላይ እንደወደቀ ነገረን።

እነሱ በገለፁት መልኩ ከሆነ ለምን እንደ ሌባ በለሊት ፣ ያውም በፓሊስ ታጅበን ለመፈፀም እንፈልጋለን የሚል ጥያቄ አነሳሁ።... ካሊድ እኩልነትን የማይወዱ ጥቂት የአብዬታዊ ዲሞክራሲ ጠላቶች እንዳይረብሹ በማሰብ የታቀደ መሆኑን ነገረኝ፣... ካሊድ ስለ አብዬታዊ ዲሞክራሲ ሲናገር አወቅሽ-አወቅሽ ከተባለችው የቁሱ ሚስት ያስንቃል!!

ካሊድ አብዬታዊ ነበር።

***

የእነ ካሊድን ስብሰባ እንደጨረሰኩ በቀጥታ ጦር ሀይሎች ወደ ሚገኘው የኮማንደር ቢሮ አመራሁኝ። ... ኮማንደር መገናኛ ሬዲዬ ላይ ተተክሏል ፣...ረፍት እንዳጣ ፊቱ ያስታውቃል፣... ጭላሽት መስሏል። ጊዜ ማጥፋት አልፈለገም። ... የመጀመሪያው ኦፕሬሽን ለሊት ስምንት ሰአት ፣ ሁለተኛው በንጋታው በተመሳሳይ ጊዜ እንደሚጀመር ነገረኝ። ... ለመጀመሪያው ቀን 150 ፓሊሶች እንደተዘጋጁና አስቀድመው ለሊት ሰባት ሰአት ላይ መንገዶቹን እንደሚዘጋጉ ፣እስከዛው ድረስ ከወረዳው መከላከል ሀላፊ ውጭ ማንም ተልእኮውን እንደማያውቅ ገለፀልኝ።

ቀድሞ መንገሩ ችግሩ ምን እንደሆነ ጠየኩት።

ኮማንደር " ሚስጥሩ እንዳይወጣ ተፈርቶ ነው። ... እንደምታውቀው የሀይማኖት ነገር በጣም ስሱ ነው።... መስኪድ እንዲገነባ ትእዛዝ የተሰጠባቸው

ሁለቱም ቦታዎች በጥምቀት በአል የታቦት ማደሪያ ናቸው ፣ የሚቀጥለው ወር ደግሞ የጥምቀት በአል የሚከበርበት ስለሆነ ከፍተኛ ግጭት ሊነሳበት ይችላል የሚል ግምት አለን።"

" ታቦት ማደሪያ! ? ... ታቦት!?... " ከተቀመጥኩበት ተነሳሁ፣

" መረጃ የለህ መስሎኝ ነበር ፣ ... ሌላ ቦታ ቢሆን ምን አስጨነቀን ብለህ ነው ፣ ... ቢያንስ የጥምቀት በአል ይለፍ ብለናቸው ነበር ፣... አሊ አብዶና ካሊድ እኔንና የፓሊስ ኮሚሽነሩ በፍቃዱ ቶሌራን ጠርተው ማስፈፀም ካልቻላችሁ የስራ መልቀቂያ አስገቡ ብለው አስጠነቀቀን። " አለኝ።

***

ከኮማንደር ጋር አብረን አምሽተን ለሊት ሰባት ሰአት ሲሆን ኦረንቴሽን ወደሚሰጥበት ቦታ ሔድን። ... ቦታው በአየር ጤና ትምህርት ቤት ወደ ውስጥ አንድ ኪሎ ሜትር ያህል የሚያስገባ የተንጣለለ ሜዳ ላይ ነው። ... ከሜዳው ፊት ለፊት የማርያም ቤተክርስትያን ይታያል ፣ ቦታው ቤተክርስትያኗ በጥምቀት በአል ታቦት የምታሳድርበት ቦታ ነው።... 150 ፓሊሶች በአምስት ቡድን ተከፍለው በሜዳው ዳር ተቀምጠዋል፣... ግራ መጋባት ይታይባቸዋል ፣ በአካባቢው ህገ ወጥ ግንባታ የማፍረስ ስራ በየጊዜው ስለሚከናወን ለዛ የሚታዘዙ እንደሆነ በሹክሹክታ ይነጋገራሉ፣... አንዳንዶቹ የወታደር እጥረት ስለተከሰተ ባድመ ሊልኩን ነው ብለው ሲቀላለዱ ሰማዋቸው።

ኮማንደር ተስፉ በየቡድኑ እየዞረ አረንቴሽን ሰጠ: ... እያንዳንዱ ቡድን ወደ ሜዳው የሚያስገቡ አምስት መንገዶችን እንደሚዘጋ ፣... ሁኔታዎች ከቁጥጥር ውጭ መውጣታቸውን ከማዕከል ካልተነገረ በስተቀር አንድም ጥይት እንዳይተኮስ ፣ ...ምግብን ጨምሮ ሌሎች ሎጅስቲክ በተመደቡበት ቦታ እንደሚከፉፈልና ማንም ከምድብ ቦታ መንቀሳቀስ እንደማይቻል ትእዛዝ ሰጠ ፣... ጥያቄ የሌለው ፓሊሳዊ ትእዛዝ !

ኦፕሬሽኑ ተጀመረ።

የቡና ነጋዴዎች ከተባሉት ግለሰቦች ቤት ውስጥ ድንጋይና አሸዋ ሞልተው የቆሙ ከ20 በላይ የጭነት መኪናዎች ተግተልትለው የጫኑትን አራገፉ።... በየቤቱ ተደብቆ የነበረው ግንበኞችና ቀን ሰራተኛ ከፓሊሱ ቁጥር በላይ ሆኖ ተዘረገፈ። ... የአጥር ግንባታው በአምስቱም መንገዶች ዙሪያ ተጀመረ።... ለጠጠር መጣያ እስከሚቸግር ድረስ ሜዳው በወጣት ሙስሊሞች ተጥለቀለቀ፣... አብዛኛቹ የአካቢው ነዋሪዎች አልነበሩም።

ከንጋታው አስራ ሁለት ሰአት :

ከማርያም ቤተክርስቲያን ይሰማ የነበረው ቅዳሴ ተቋረጠ። ... ከቤተክርስትያኑ የድረሱልኝ ጥሪ ተስተጋባ፣... የድምፅ ማጉያው የኡኡታ ድምፅ ደጋግሞ አሰማ። ...የአካባቢው ነዋሪ ቤተክርስትያኒቱ ላይ አደጋ ደረሰ በማለት ሊታደጓት መሯሯጥ ጀመሩ ፣... ወጣቱ ፣አዛውንቱ ፣ክርስትያኑ ፣ ሙስሊሙ...ወደ ቤተክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ ቀረብ ብዬ ቆምኩ። ... ቄሱ በማይክራፎን ህዝቡን የሚያነሳሳ ንግግር እያደረጉ ነበር፣ ... መንግስት ፓሊስ አሰማርቶ የጥምቀት

ማደሪያውን ለባለሀብት እያከፋፈለ እንደሆነ ይናገራሉ።

አጠገቤ የዛፍ ዝንጣይ የያዙ አዛውንት ለየት ስላሉብኝ ምን እንደተፈጠረ ጠየኳቸው።

" እሳት የተነሳ መስሎኝ ነበር።... ከቁሱ እንደሰማሁት የጥምቀት ማደሪያውን መንግስት ለባለሀብት እየሸጠው ነው።... ይሔ መንግስት ግን ምን ነክቶታል?... እኔ እዚህ አካባቢ ከኖርኩ ከአስር አመት በላይ ሆኖኛል፣ ... ፓሊሶቹ አሁን የከበቡት ቦታ በየአመቱ የጥምቀት ማደሪያ እንደሆነ አውቃለሁ። ... እኔ በእምነቴ ሙስሊም ነኝ... ነገር ግን የሀይማኖት ቦታዎች መከበር አለባቸው። " አሉኝ።

" አባቴ ! እኔ እንኳን የሰማሁት ለመስኪድ ሊሰጥ እንደሆነ ሰምቻለሁ።" አልኳቸው ፣ስሜታቸውን ለማየት ፈልጌ።

" ተሳስተሀል ወንድሜ! ... ይህ በፍፅም ሊሆን የሚሆን አይደለም፣... ሙስሊሙንና ክርስትያኑን ለማቃቃር ካልታሰበ በስተቀር። ...እኔ አካባቢውን ወክዬ የወረዳው እስልምና ምክርቤት አባል ነኝ። ... የመስኪድ ግንባታ ጥያቄ ያቀረብነው ትምህርት ቤቱን ተሻግረህ ባለው ቦታ ላይ ነው፣... የክርስትያን ወንድሞቻችንን ድጋፍ አግኝተናል።

ከሰውየው ጋር እያወራሁ ሰቪል የለበሰ ፓሊስ ወደ ጆሮዬ አንሾካሾከ። ... ሁኔታዎች እየተባባሱ መምጣታቸውን ፣ ነዋሪው ስለት ያላቸው ነገሮች ይዞ መውጣት መጀመሩን ፣መንግስት መሳሪያ ያስታጠቃቸው ሚሊሻዎች ከህዝቡ ጋር እንደተሰለፉ ነገረኝ። ... የቤተክርስትያኑን መብራትና ስልክ እንደቆረጡትና ደውሉን ለጊዜው እንደተቆጣጠሩት ገለፀልኝ... በስውር ፓሊሶች ታጅቤ ወደ ግንባታ የሚካሔድበት ቦታ ሔድኩኝ።

***

ጠዋት አንድ ሰአት:

በአጥሩ እየታጠረ ባለበት ቦታ ያሉ ሰወች አምላካቸውንና መንግስትን ያመሰግናሉ ፣... ይዘምራሉ ... ግንባታውን ለማፋጠን የሚሰሰት ጉልበት የላቸውም ፣...ብዙዎቹ በደስታ ሰክረዋል። ... ጥቦቶች በየቦታው እየታረዱ ነው። ... ሴቶቹ የምጣድ ጥብስ ለቁርስ ለማድረስ ይንደፋደፋሉ።

በዙሪያው ደግሞ ኡኡታውና የድንጋይ ኡርምታው መሬቱን አንቀጥቅጧል። ... ከየመንደሩ የሚወረወሩት በአሸዋና ጋዝ የተሞሉ ላስቲክ ኮዳዎች ሲፈነዱ የሚያሰሙት ደምፅ ቦታውን የጦርነት ቀጠና አሰመስሎታል። ... ጉዳቶች መሰማት ጀምረዋል ፣ጊዜያዊ ማዘገጋ ላይ ያለችው የኮማንደር መገናኛ ሬዲዬ ፉታ አጥታለች።

" ዋልያ 24! ነብር 24 ነኝ... እኔ ባለሀብት አካባቢ ሁለት አባላት ከባድ ጉዳት ደርሶባቸዋል።"

" ዋልያ 24! አንበሳ 22 ነኝ... እኔ ባለሀብት አካባቢ አምስት አባላት ተጐድተዋል እርዳታ ይፈልጋሉ"

" ዋልያ 24! ዋልያ23 ነኝ... ከቤተክርስትያኑ መዝሙር እያሰሙ እ ንደጐርፍ እየመጡብን ነው... ሀይል ይጨመርልን" ... ኮማንደር በዋልያ 23 ተናዶ ምንም ሀይል እንደማይጨመርለት መለሰለት ፣ " ዘላለሙን እንደፈራ

ይኖራል " ብሎ ለራሱ ተናገረ። ... ማን እነደሆነ ጠየኩት።... የወረዳ 23 ፓሊስ አዛዥ የነበረው ጥሩነህ በርታ እንደሆነ ነገረኝ...

(**ጥሩነህ በዞን በሚካሔደው ግምገማ ሁልጊዜ በስንፍናው ይወቀስ ነበር።... ኢህአድግ ውስጥ ከችሎታ ይልቅ የሚዘረጋ የጥቅም ኔትወርክ ወሳኝ በመሆኑ ከደቡብ ጀምሮ ከገቢዎች ሀላፊ ከነበረው ገብረዋህድ ጋር በዘረጋው ሰንሰለት መሰረት ኮማንደርነቱን ትቶ ወደ ጉምሩክ እንዲዘዋወር አደረገው... እኔም ታታሪ ነው ብዬ የድ ጋፍ ደብዳቤ ፃፍኩለት። ... የገቢና ጉምሩክ ካድሬዎች እስር ውስጥ የገብረዋህድን ስም ስሰማ ጥሩነህ እንደሚኖሮ ለሰከንድ አልተጠራጠርኩም ነበር።... የቁራና ጮፉ ህዝብም ፊት ለፊቴ ተደቀኑ ፣ በምርጫ 97 ገብረዋህድን በእነዚህ አካባቢዎችለፓርላማ እንዲወዳደር አቅርበነው ነበር።... የአካባቢው ህዝብና ጉምሩክ የሚሰሩ ሰራተኞች ለመስማት የሚዘገንኑ ጥቆማዎችን ይዘው ወደ እኛ መጡ... በመረጃ አስደግፈን ለአለቃችን ከንቲባ አርከበ እቁባይ አቀረብንለት...አርከበ "የትግራይ ጠላት የሆነው የቅንጅት ወሬ ነው " ብሎ አጣጣለብን።

እውነት ይዘገያል እንጂ•••

ገብረዋህድ ወደ ወህኒ ወረደ...ጥሩነህንም አጀበው... ከዛ ቀን ጀምሮ ለገብረዋህድ ሀገሪቷ ወዴት እየሔደች እንደሆነ ተገለፀለት... ሁለቱም የቅርብ ሩቅ ጓደኞቼ ነበሩና ለጥፋታቸው ተመጣጣኝ ፍትህ ለነብሳቸው ደግሞ መፅናናት ይሁን !)

***

ሁለት ሰአት:-

ሁኔታዎች ከቁጥጥር ውጭ እየሆኑ ሔዱ:... እናቶች ነጠላቸውን ታጥቀው ደረት ይደልቃሉ ፣ ...ወጣት ሴቶች ከፓሊስ ጋር ከፊለክ ግደለኝ በሚል ፀጉራቸውን እየነጨ ይተናነቃሉ ፣ ብዙዎቹ ባዶ እግራቸውን ናቸው፣ ...ጮረምሳ ወጣቶች የድንጋይ ናዳ ያዘንባሉ። ...መሳሪያ ለመንጠቅ በተደረገ ትንቅንቅ አንዲት ሴት በጥይት እግሯ ላይ ተመታ ቆሰለች፣... ሁለት ፓሊሶች በከባድ ሁኔታ ተጐድተው ወደ ፓሊስ ሆስፒታል ተወሰዱ። ... ጥይት መቆላት ጀመረ።... ለሁለተኛው ግንባታ ያስቀመጥናቸውን 100 ፓሊሶች አመጣናቸው ... በየቡድኑ ተደለደሉ።... የፓሊሶቹ ሁኔታ ራሱን የቻለ ትራጂዲ ነበር፣ ...ፓሊሶቹ ከህዝቡ ጋር እያለቀሱ በሚወረወርባቸው ድንጋይ ይደበደባሉ፣ ሲብስባቸው ወደ ላይ ይተኩሳሉ። ... ብዙዎቹ በወረዳው ተወልደው ያደጉ በመሆኑ ከነዋሪው ጋር ቤተሰብና ጐረቤት ናቸው... ወንድምና እህት፣ ልጅና አባት ውስጣቸው አንድ ሆኖ የሚጨፋጨፋበት ቦታ••• አየር ጤና••• አኬልዳማ •••የደም መሬት!

***

በአየር ጤና እየሆነ ያለውን ለፍስሀ መአሲ ደውዬ ነገርኩት።... እነ አሊ አብዶ የቀረ ቡላቸው መረጃ ግብር የማይከፍል ገበሬ መሬቱን እንደሚያርሰው ፣ በአካባቢው የኢህአድግ ደጋፊ የሆኑ ሙስሊሞች በሰፊው እንደሰፈሩ መሆኑን ገለፀልኝ። ... እነ አሊ ባህታዊውን እያታለሉት እንደሆነ አስረዳኝ። ... የተጀመረው ግንባታ ማስቆሙ ችግር ስለሚያመጣ እንዲቀጥል ፣ ሁለተኛውን

ግን እሱ ምላሽ እስኪሰጠኝ ድረስ እንዳላስፈፅምና ከማንም ጋር እንዳልነጋገር አስጠነቀቀኝ።... ብዙም ሳይቆይ ካሊድ ደወለልኝ፣...በአንድ ቀን ማስፈፀም እንደማንችል ነገርኩት። ... የስድብ ውርጅብኝ አወረደ። ...አብዬታዊነት መጓደልና የሀይማኖት እኩልነትን አለመቀበል ቁልፍ ችግሬ እንደሆነ ገለፀልኝ። ... እኔም ጀርባዬን ተማምኖ ሰለነበር ለእንደዚህ አይነት ስራ አስተዳደር መሆን እንደማልፈልግና ለካዛንችሱ መንግስት መልቀቂያ አስገብቼ ወደ ቀድሞ ስራዬ እንደምመለስ ነገርኩት። ... መጨረሻዬ ከርቸሌ እንደሚሆን እየደነፉ ሲጮህ " ካሊድ! ማን ላይ እግረ መቅ እንደሚታሰር በሒደት እናየዋለን" አልኩት•••

ፍስሀ የአህያ ባል እንደማይሆንብኝ ተማምኜ !

ቃለ ምልልሳችንን ሲያዳምጥ የነበረው ኮማንደር ተስፉ ጠጋ ብሎኝ እነዚህን ሰወች እንድጠነቀቅና ስውር ተልእኮ እንዳነገቡ ገለፀልኝ።... በያዝነው አመት ብቻ በዞናችን ውስጥ ከ18 በላይ መስኪዶች መገንባታቸውን... ከዚህ ውስጥ ግማሾቹ የተሰሩት በማስፉፊያ ቦታ በተለይም ወረዳ 24 እና 23 ላይ እንደሆነ ነገረኝ።... በከተማ፣ ማስፉፊያ ወረዳና ቀበሌዎች ሊቀ መናብርት ሆነው የሚመደቡት ከእነሱ ጋር ትስስር ያላቸው ሙስሊሞች እንደሆኑ ጥርጣሬውን ገለፀልኝ...

አሊ አብዶ••• ካሊድ አብድርሀማን••• ሙለሜ ረሺድ••• ዘርሙ...

ከከተማ እስከ ቀበሌ።

***

ከረፉዱ ሶስት ሰአት:

ፓሊስ የቤተክርስትያኗን ቁሶችና የአመፅ አስተባባሪዎችን እየለየ ማሰር ጀመረ፣ የደብሩ አሰተዳደሮችና ቁሶችን በአቅራቢያው ወደ ሚገኘው ወረዳ 23 ፓሊስ ጣቢያ ተወሰዱ። ... እያስቸገሩ ያሉትን ሴቶች ወደ ዞን ፓሊስ ተጋዙ። ... አፍታም ሳንቆይ አየር ጤና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በረበሻ ተናወጠ ... መስታወቶች ፣ መቀመጫ ዴስኮች ተሰባበሩ።... ተማሪዎች ወደ ክፍል አንገባም በማለት ሜዳ ላይ ተዘረገፉ። ... ፓሊስ ዙሪያውን ከበበ። ... ይቺ የጭንቅ ሰአት እንድታጥር ተመኘሁ።

***

የመስኪዱ አጥር ግንባታ በብርሀን ፍጥነት ተጓዘ። ...በነፃ የሚያግዙት ወጣቶች የስራ ትጋት እስከ ምሽት አልቀነሰም ፣ ...መዙሙራቸው የፍንዳተውን ድምፅ ሸፍኖታል፣ ድግሱም አልበረደም። ... ከምሽቱ አምስት ሰአት አካባቢ አራት የግል ታርጋ ያላቸው ላንድክሩዘር መኪናዎች አጥሩን አልፈው ወደ ውስጥ ገቡ።... ከመጀመሪያው መኪና ውስጥ የኦሮሚያ ምክትል ፕሬዝዳንቱ ዶክተር መሀመድና በካሊድ ቢሮ አብሮን የተሰበሰበው የግንባታ አስተባባሪ ወጡ። ... ከሁለተኛው መኪና የአረብ ሀገር ዜጐች የሚመስሉና ጥምጣም ያደረጉ ሰዎች ተከታትለው ወጡ... ከሶስተኛው በኢጃብ የተሸፈኑ ሶስት ደርባባ ሴቶች...ጠባቂዎች ከኃላ ተሰልፈዋል።

በዝማሬና ለአምላካቸው በሚያቀርቡት ምስጋና ደማቅ አቀባበል ተደረገላቸው።

የመስኪድ ግንባታ አስተባባሪው እየመራቸው ወደ እኔና ኮማንደር ይዟቸው መጣ፣ ... ምክትል ፕሬዝዳንቱ ሰላምታ እየሰጠን አጠር ያለ ስብሰባ

እንድናደርግ መምጣቱን ነገረኝ። ...አጅበውት የመጡት ሰወች ከኃላው ቆመዋል። ..." ማን ልበል አላወኮትም?" አልኩት ፣ሆን ብዬ ...

" የኦሮሚያ ምክትል ፕሬዝዳንቱ የተከበሩ ዶክተር መሀመድ ናቸው? ..." ብሎ አስተባባሪው ተናገረ።

" የኦሮሚያ አስተዳደር ምን አግብቶት ለስብሰባ እንደመጣ አልገባኝም " ሁሉም እንዲሰማ ጮክ ብዬ ተናገርኩ።

" የምናግዛችሁ ነገር ካለ ብለን ነው፣ ወረዳው ከኦሮሚያ ስለሚዋሰን ድጋፍ ልንሰጣችሁ ስለፈለግን ነው።" ዶክተሩ ቀስ ብሎ ተናገረ።

" አያስፈልገንም ... ራሳችን የምንቆጣጠረው በቂ ሀይል አለን።" ኮማንደር መልስ ሰጠ።

" ኮማንደር! ለሊት ለምትጀምሩት ሁለተኛው ግንባታ ተጨማሪ ሀይል ያስፈልጋችኃል፣ የኦሮሚያ ፓሊሶች የአዲሳባ ዩኒፎርም ለብሰው ሊቀላቀሏችሁ ይችላሉ ብለን ነው... ክቡር ፕሬዝዳንቱ ሊተባበሯቹህ ፍቃደኛ ናቸው" ዶክተሩ ገለፀ።

" ሁለተኛው ግንባታ ከኢህአድግ ቢሮ መልስ እስክናገኝ አይጀመርም። ... በዚህም ላይ ቢሆን ምርመራ እየተካሔደ ነው ፣ ...ባልጠፉ ቦታ በጥምቀት ማደሪያ ላይ መስኪድ እንዲገነባ መፍቀድ ምክንያቱ መጣራት ይኖርበታል ...በውሳኔው ልዩነት ካለህ ለከተማዋ ኢህአድግ ቢሮ መደወል ትችላለህ። "... ረገጥ አድርጌ ነገርኩት... የኦህዴድ ካድሬዎች ማን ሲጠራ እንደሚያስፈራቸውና እንደሚበራገጉ ስለማውቅ።

" እዛ የሚያደርስ አይደለም ።" ተሰናብቶን ኩምሽሽ ብሎ ሔደ።

ዘግየት ብለን ባደረግነው ማጣራት ዶክተሩን የላከው በወቅቱ የኦሮሚያ ፕሬዝዳንት የነበረው ጁነዲን ሳዶ እንደነበረ አረጋገጥን።... ዶክተሩ ብዙ ጊዜውን የሚያጠፉው እንደዚህ አይነት ስራዎችን ፊት ለፊት ወጥቶ በማስተባበር አንደሆነ ደረስንበት፣ ...ሰውየው ፅንፈኛ አመለካከቱን በግላጭ የሚያቀርብ ፣ አልፎ ተርፎም ኦሮሞነትና እስልምና የአንድ ሳንቲም ግልባጭ ናቸው የሚል አግላይ ቅስቀሳ እንደሚያደርግ በክትትል ደረስንበት። ... እነ ጁነዲና አሊ አብዶ ደግሞ መኖሪያ ህንፃቸውን እያስገነቡ ያሉት በግንባታ ኮሚቴው አስፈፃሚነት ከአረብ ሀገራት በሚላክላቸው ገንዘብ መሆኑ ተረጋገጠ።...ከእለታት በአንዱ ቀን በምሰራበት ዞን የገቢዎች ምክትል ሀላፊ የነበረችውን አሰፋ ፈንቱ (የበረከት ስምኦን ሚስት) ቢሮዬ ጠርቼ በዝርዝር ነገርኳት።... አሰፋ ልታይ የማታበዛ ፣ ስልጣን የምትሸሽ ፣ጨዋና ትጉህ ሰራተኛ ነበረች።... በዚህም ምክንያት መልካም ግንኙነት ነበረን። ...ወንድሞ ገጣሚና ደራሲ መዝሙር ፉንቱም እንደሷ ነው። ... ስለ ቤተሰቦቿ መልካምነት ከብዙ ካድሬ ሰምቻለሁ።

ዶክተር መሀመድን አስመልክቼ የነገርኳትን በጥሞና ስታዳምጠኝ ቆይታ " ቆይ ዝምበል!" ብላኝ ወጣች።... ብዙም ሳይቆይ ዶክተሩ ከምክትል ፕሬዝዳንትነትና አህዴድ አባልነት ተባረረ።... በተራዬ አሰፋ ቢሮ ሔጄ እጅ በመንሳት ምስጋና አቀረብኩ።

***

በሳምንት ውስጥ የአየር ጤና መስኪድ አጥርና ጊዚያዊ የቆርቆሮ

ቤት ተገንብቶ ተጠናቀቀ።... ሁለተኛው ግንባታ እስኪጣራ ድረስ በካዛንችሱ መንግስት ትእዛዝ ተቋረጠ። ህዝቡ በበኩሉ ለጥምቀት አመፅ ቀጠሮ ይዞ አደብ ገዛ።... እኛ ደግሞ የአሊ አብዶ የጨለማ ዘመን አካል ነንና ወደ ሌላ አጥፍቶ መጥፉት ተሸጋገርን: ...

ኮሊድ ቢሮ እኔ ፣ ኮሚሽነር በፍቃዱ ቶሌራ ፣ ኮማንደር ተሰማ በጠዋት ተገኝተናል። ... የወረዳ 24 የኦርቶዶክስ ሀይማኖት ተከታዩ ህዝብ በእልህ ተነሳስቶ ሁለት ቦታዎች ላይ ህገ ወጥ ቤተክርስትያን በሶስት ቀን ገንብቶና ታቦት አስገብቶ አምልኮ ጀምሯል። ... ካሊድ ቢሮ የተሰባሰብን ባለስልጣናት ቤተክርስትያኖቹን እንዴት እንደምናፈርስ እየተነጋገርን ነው።... የተለመደው የካሊድ አብዬታዊ ደሞክራሲ ኪኒን ሽፉኑን ሳይቀይር ህገወጥነትን ለመከላከል ፍቱን መዳኒት ሆኖ ቀርቧል።

ህገ ወጥነት ላይ ጠንካራ አቋም ስለነበረኝ ከማስተር ፕላኑ ጋር ተመሳክሮ ወደ ህጋዊ መስመር የሚመመጣበት ካልሆነም የመከፈርስበት ሁኔታ መፈጠር እንዳለበት አስተያየት ሰጠሁ። ... አስቀድሞ በህዝቡ ዘንድ የፓለቲካ ስራ መስራት እንደሚገባ እና የሐይማኖቱን ክብር በማይነካ መልኩ መፈፀም እንዳለበት አሳሰብኩኝ። ... ካሊድ ተልእኮን ለመፈፀም መፍራትና ህዝበኝነት የሚል መሸከም የማልችላቸው ስሞች ጨመረልኝ... አያልቅበት!

የማፍረሱ ስራ ሃፊውኑ መሆን እንዳለበት ካቢኔው መወሰኑን ነግሮን ተለያየን።

ሌላ የጭንቀት ሳምንት...ድቅድቅ ጨለማ...

***

ኮማንደር ጋር ተያይዘን ወደ ወረዳ 24 ሔድን። ... ዝርዝር መረጃዎቹን ወሰድን። ... ቤተክርስትያኖቹ የተገነቡት ሚሊፎኒ (በተለምዶ ህዝቡ ሙስና ሰፈር) ከሚላቸው ቦታዎች አንዱ እና ቻይና ኤምባሲ ጀርባ ኮምፒንሳቶ እንጨት መሰንጠቂያ አጠገብ ነበር።... የመጀመሪያዉ ለሀይማኖት ተቋም የማይሆን ቦታ በመሆኑ ማፍረሱ አማራጭ እንደሌለው ተስማማን። ... ሁለተኛው ከማስተር ፕላኑ ጋር የማይጋጭና ጫካ ውስጥ ስለሆነ ወደ ህጋዊ መስመር የሚገቡበትን ሁኔታ ማመቻቸት እንደሚገባን ተማመንን።

የሚሊፎኒ ግንባታ ኮሚቴዎችን ጠርተን አናገርናቸው፣ ...መግባባት ላይ መድረስ አልተቻለም ... እንደምናፈርሰው በግልፅ ነገርናቸው።... ህገወጥ መሆኑን እያመኑ ፉክክራቸው እነ አሊ አብዶ ከዘረጉት ህገወጥ ኔትወርክ ጋር ሆነ ፣... እኛም ከግለሰብ እምነታችን ተነስተን እንድንደግፋቸው ያግባቡን ጀመር።... የሚሆን አልነበረም፣... የህግ የበላይነት ሌላው ስለጣሰ እኛም ማክበር የለብንም የሚባል አመክንዬ እንደማይሰራ ነገርናቸው፣ ለሚከሰተው ጥፋት ሀላፊነቱን እንደሚወስዱ አስጠነቀቅን።... እንደማያዛልቅ ስንገነዘብ እነሱ በወረዳው እገታ ተደርጉባቸው ቤተ ክርስትያኑ ፈረሰ።... አፍታም ሳይቆይ ቤተክርስትያኑ ከፈረሰበት አካባቢ የተመሙ ሰወች ወረሩን፣ ... ጣቢያው በድንጋይ ተደበደበ።...የመንግስት ታርጋ የነበረው መኪና ታገተ፣ ... ፓሊሶች ከግራ ወደ ቀኝ ፣ ከታች ወደ ላይ እየተሯሯጡ ጣቢያው እንዳይሰበር ተከላከሉ። ... ተጨማሪ ፓሊሶችን ከየወረዳው ኮሚሽነር በፍቃዱ ልኮልን የሀይል ሚዛኑ

ወደ ፓሊስ ተቀየረ። የፓሊስ መኪና በሙሉ አይናችን ለማየት እንኳን የማንደፍረውን ታቦት ተሸክሞ ወደ ጣቢያ መጣ ፣ ... ሬዲዬ ላይ የተቀመጡት ሴት ፓሊሶች ሰውነታቸው ይርዳል፣ ይጮሀሉ። ... ኮማንደር ግብታዊ በሆነ ሁኔታ መለዬውን አውልቆ ወረወረ፣...

ፀጉሩን እየነጨ ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ ።

በጥላቻና ባንዳነት ሲፈርጁን አልፎ ተርፎም በፔትሮሊየም ዶላር የተደለልን አድርገው ሲሰድቡን የነበሩት የኮሚቴው አባላት ተደናገጡ፣ ... ጭንቀታችንን ተጋሩት ፣ አብረውን አዘኑ።... የገባንበትን አጣብቂኝ በመገንዘብ ነዋሪውን ለማረጋጋት ሀላፊነ ት ወሰዱ።... አመስግነን ሸኘናቸው... ህዝባቸውን ይዘው ወደ ቄያቸው ተመለሱ።

ኮማንደር መዕናናት አቃተው።

(*** ኮማንደር ተስፉ ፈርሻ ወልቂጤ ካፈራቻቸው ቆፍጣና ወታደሮች አንዱ ነው፣ ወታደራዊ ዲስፕልን ከተሞላ ቁመና ጋር የተቸረ ሰው ነው።... የተሰጠውን ተልእኮ ሲፈፅም በልበ ሙሉነትና የሰው ልጅ ሰው በመሆኑ ያገኘውን ሰብአዊ መብቶች በማክበር ነው።... በቅርብ የምናውቀው አለቆቹ ከባድ ስራ ከመጣብን አይናችን የሚያርፈው እሱ ላይ ነበር... በከተማዋ የሚገኙ የፓሊስ አባላት በአካል ባያውቁትም በአስገምጋሚ ድምፅ ይለዩታል... ኮማንደር በመገናኛ ሬዲዬ ሲናገር ምድብ ቦታቸውን የለቀቁ የፓሊስ አባላት ይሯሯጣሉ... ላልሰሙትም " አንበሳው አጋስቷል! ዛሬ የዞኑ ተረኛ እሱ ።" የሚል የተጠንቀቅ መልእክት ያስተላልፉሉ... ይቀጥላል

***

የጥምቀት በአል ሶስት ሳምንት ቀርቶታል። ... ባለፉት ሳምንታት አንድ መስኪድ አስገንብተን ሌላውን አስቀርተን፣ ... አንድ ቤተክርስትያን አፍርሰን ሌላውን ትተን ካሊድ ቢሮ ተገኝተናል፣... ለዳግም ጥፋት...

የማያቋርጥ የደም ግብር!

የካሊድ አብዬታዊ መፈክሮችና አልባሳት አልተቀየሩም ፣...አዲሱ ነገር ምክትል ፕሬዝዳንቱ ደሳለኝ ሸሹ እና የአዲሳባ ሀገረ ስብከት ስራ አስኪያጁ አቡነ ሳሙኤል መጨመራቸው ብቻ ነበር። ... በኃላ ላይ ከደሳለኝ እንደሰማሁት እነ አሊ እንዲካተት ያደረጉት ሆን ብለው ተወልዶ ካደገበት ማህበረሰብ ለማጣላትና ለማጋጨት ነበር። ... ካሊድ ደግሞ የምክትልነቱን ቦታ ነጥቆኛል የሚለውን " በህዝበኝነት " ከሶ ቦታውን ለመንጠቅ ድብቅ ሴራ ጠንስሶ ነበር።...ካሊድ ፊት የህዝቡን ፎላጐት ማንፀባረቅ ህዝበኝነት በምትባል አብዬታዊ ቃል ያስከስሳል፣ ... በእሱ ግምገማ ወቅት ህዝብ ይጠላሀል የሚል ትችት ቀርቦበት " የህዝብ አመለካከት ተሸካሚ ስላልሆንኩ ነው " የሚል አስቂኝ ምላሽ ሰጥቷል።

በካሊድ ቢሮ የተሰበሰብንበት አጀንዳ በከተማዋ ከሚገኙት የኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን ውስጥ መሀል ከተማ ሰለምትገኘው ልደታማርያም በተመለከተ በፍርድ ቤት የተወሰነውን ለማስፈፀም የተጠራ ነበር።... ቤተክርስትየኗ ለብዙ ወራት አራት ኪሎ ከሚገኘው ሲኖዶስ አስተዳደር ራሷን

አግላና አመራር ኮሚቴ መርጣ መተዳደር ጀምራለች። ... ከተከታዬቿ የምታገኘውን ገቢ ወደ ሰኖዶሱ ቋት ሳታስገባ እዛው ትጠቀምበታለች። ...ሲኖዶሱ በየጊዜው አስተዳዳሪ እየሾመ ቢልክም በምዕመናኑ እምቢተኝነት ወደ ተግባር መለወጥ አልቻለም።...

ይህን ተከትሎ የቀድሞው ፓትሪያርክ አቡነ ማርቆሬስ (ነብሳቸውን ይማርና !) ህዝቡ ለመታረቅ ያደረጉት ጥረት ሳይሳካ ቀረ ፣... በተቃውሞ ብዛት ወደ ደብሯ መምጣት አቆሙ። ... የልደታ ምእመናን ውሳኔ አድማሱን አስፍቶ ወደ ጐፋ ገብርኤልና ሌሎች ቤተክርስትያኖች ተሸጋገረ። ... በመዲናይቱ የሚገኙ ደብራት በፀረ_ፓትርያርኩ ተቃውሞ መናጥ ጀመሩ። ... አመታዊ ንግስ በመጣ ቁጥር ፌደራል ፓሊስና ምዕመናን ትንቅንቅ መግጠም የተለመደ ሆነ።... ፌዴራል ፓሊስ ልደታን ለማንገስ የመጣ ህዝብን በያዘው ቆመጥና መሳሪያ እየወገረ የማርያም ጠላት አደረገው፣... በየጊዜው በሚነሱ ግጭቶች ምክንያት መንገዶች እየተዘጋጉ የከተማዋ የእለት ተእለት እንቅስቃሴ ተስተጓጐለ። ... እርምጃው ሰላማዊ ተቃውሞ ያላቸውንና አክራሪዎችን የማይለይ በመሆኑ ውጤቱ የበለጠ አስከፊ እየሆነ ሔደ። አጋጣሚውን ተጠቅመው የፅንፈኝነት አጀንዳቸውን ማራመድ ለሚራወጡት ሀይሎች ምቹ ሁኔታን ፈጠረ።

***

***

በልደታ ቤተክርስትያን የነበረው አለመግባባት አየተባባሰ በመሔዱ አራት ኪሎ የሚገኘው ሲኖዶሱ ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት ይዞት ሔደ።...ፍርድ ቤት የህዝቡን ፍላጐትና ተቃውሞ ወደ ጐን በመተው ቤተክርስትያኗን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በሁለት ሳምንት ውስጥ ለሲኖዶሱ እንድናሰረክብ አፈፃፀም ላከልን፣ ...ውሳኔውን ተከትሎ ለመጀመሪያ ዙር አስተዳደሩን ለሲኖዶሱ ለማስረከብ ያደረግነው ጥረት በከፍተኛ አመፅ ሳይሳካ ቀረ።...ከአራት ኪሎ የተላኩት አስተዳዳሪ በአንድ ቀን ቤተክርስትያኗን ለቀው ወጡ። ...የቀድሞዎቹን ቄስና ዳቆናት ለመተካት የመጡትም ወደ ቀድሞ ቦታቸው ተመለሱ።...ቤተክርስትያኗ እኛ ባሰማራናቸው ፓሊሶችና ደህንነቶች መጠበቅ ጀመረች።

አቡነ ሳሙኤል ከእንግሊዘኛ ቋንቋ ውጭ የምእራቡን አለም ባህልና አስተሳሰብ የኮረጁ አይደሉም።...የሰውየው ዘለፋ ትእቢት የተሞላበት ፣ዘረኛና አምባገናዊ ነበር።... ከንግግራቸው ግማሹ በእንግሊዘኛ የታጀበ ሲሆን ሀይማኖታዊ ያልሆኑ አመክንዬቶች የሚበዙበት ነበር፣ "ህዝቡን ትታችሁ

የፍርድ ቤት ውሳኔ እንድታስፈፅሙ አለበለዚያ በፓሊስ አሳስረን ፍርድ ቤት እናቀርባችኃለን "የሚል ዛቻ ከአንድ አቡን መስማት አስደንጋጭ ነበር።... ሰውየው በአውቆ አጥፊነትና በአፍቅሮ ንዋይ አንደበት እንደሚናገር ያስታዉቃል፣... ስለ ቤተክርስትያኗ እና ተከታዬቿ ህልውና ደንታ አልሰጣቸውም ... ጋግመዉ የሚናገሩት ቤተክርስትያኗ ሰበካ ጉባኤ እጅ ይገኛል ስለተባለው ሰባት ሚሊዬን ብር የሚጠጋ ጥሬ ገንዘብ ነበር።ችግሩን

አርቆ በማየት ሰላማዊ መፍትሔ ይሰጣሉ ብለን ስናስብ ይበልጥ ቤንዝን አርከፈከፉበት።...

... ይቀጥላል

... የሚገባ

¶¶¶¶ መሰረተ እምነት (ዶግማ) በአምላክ ቃል መሰረት ብቻ የቆመ ፣ የሚጨመርበትና የሚቀንስለት ወይም እንደ ሁኔታው ታይቶ የሚሻሻል ነገር የሌለበት ዘላለማዊ ነው። ቀኖና ደግሞ አምልኮተ እግዝአብሔርን ለማካሔድ ፣ ወንጌልን ለማሰራጨት ና የመሳሰሉትን መንፈሳዊ ተግባራትን ለማከናወን ሲባል የሚወጣ ስርአት ነው። ቀኖና ስርአት በመሆኑ እንደጊዜው ታይቶ መሻሻል የሚደረግበት ነው። ቢሆንም ስርአቱን የማሻሻል ስልጣን የቅዱስ ሲኖዶሱ ብቻ ነው። እዚህ ሲኖዶስ ውስጥ በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት ባለመረዳት ምክንያት የሚያደባልቁ አሉ ። ስርአት አይቀየርም ብለውበመስበክ ቤተክርስትያኗን ወደ ሌላ አቅጣጫየሚመሩ አሉ። ... እነርሱ ይህን ቢሉም ስርአት ባህርይው ቋሚነት እንደሌለው ና ከህዝቡ የኑሮ ደረጃና የአስተሳሰብ እድገት ፣ ከአለም ስልጣኔ አንፃር እየተሻሻለ ፣ አያደገና እየተለወጠ መሔዱአልቀረም። ... አለም አቀፍ ሁኔታው ተጠንቶና ከክርስትና ቀኖና ጋር ተመሳክሮ መታረም ያለበት ጉዳይ ቢስተካከል ሀይማኖቱን ማዳን ይቻላል። ¶¶¶¶¶¶¶

ምእራፍ :

የጥፉቱ ቅብብሎሽ: ከመመሪያ ቁጥር አንድ ወደ ሁለት ወደ•••

መመሪያ ቁጥር አንድ !!

" መመሪያው ህገ-ወጥ ግንባታን በማያዳግም መልኩ በቁጥጥር ስር ያውላል ! "
(ፕሬዝዳንት አሊ አብዶ : 1993 አ•ም•)

የጨለማው ዘመን መሪ አሊ አብዶ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ከተንቀሳቀሰባቸው ነገሮች ዋነኛው የተወረሩ ህገወጥ መሬቶችን ህጋዊ ከለላ መስጠት ነበር።... ለዚህም እንዲረዳ መመሪያ ቁጥር አንድ የሚባል ህግ በአስፈፃሚ አካል ለማውጣት እንቅስቃሴ ተጀመረ። ... መመሪያ ቁጥር አንድ በከተማዋ የሚገኙ ህገ ወጥ ይዞታዎችን ወደ ህጋዊ ለመለወጥ በሚል ሽፋን ተዘጋጀ። ...

በተቃራኒው መመሪያውን ለማፅደቅ አንድ ሳምንት ሲቀረው የተዘረፈው መሬት ብዛት በሁለት አመት ውስጥ ያለው በአጠቃላይ ተደምሮ በእጥፍ ይበልጥ ነበር። በወቅቱ የካቢኔ አባል የነበረው አበበ ዘልኡል ያቀረበው

ጥናት አመላክተ።... አበበ በቁጭት ተሞልቶ " መመሪያውን ማውጣት አልነበረብንም! ..... በዚህ መመሪያ ምክንያት የተዘረፈው የህዝብ ንብረት ከሁለት ቢሊዬን ብር በላይ ሲሆን ይህም ከመቶ በላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን (ቢያንስ በቀበሌ አንድ) እና አስር ደረጃውን የጠበቁ መለስተኛ ሆስፒታሎችን ይሰራ ነበር " ብሎመመሪያው በፀደቀ አንድ ወር ሳይሞላው አጋለጠ። ... ከአመክንዬ ይልቅ ስድብ የሚቀናው አሊ አብዶ : - " አበበ! በመመሪያው መውጣት ምክንያት የሚገኘው ፓለቲካ ትርፍ በቴክኖክራቶችና ድንክዬ እድሜ በሚኖራቸው ሰዎች የሚታሰብ አይደለም " የሚል ነውረኛ አስተያየት ሰጠ፣... አበበ ከፓለቲካ ብቃቱ ይልቅ በፕሮፌሽናል ሙያተኝነቱ ከፍተኛ ክብር የሚሰጠው ነበር። አበበ ዶንቦስኮ የሚገኘው የካድሬዎች ማሰልጠኛ ተቋም ከጐዳው በላይ አሊ አብዶ አንገቱን አስደፉው።

መመሪያ ቁጥር አንድ ህግ ሆኖ የወጣበት አካሔድ በራሱ ወንጀል ነበር ።... በመጀመሪያ ደረጃ ከአዋጅነትና ደንብነት ዝቅ ብሎ ለምን መመሪያ ሆነ የሚለው ከህጉ በስተጀርባ ያለውን ፍላጐት ፍንትው ብሎ የሚያሳይ ነበር።... እንደሚታወቀዉ የአዲሳባ ምክር ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ለእያንዳንዱ የስልጣን እርከን ህግ የማውጣት ስልጣን ይሰጣል። ... በዚህ መሰረት የአስተዳደሩ የህዝብ ተመራጭ ምክርቤት ከተማው ላይ ትር ጉም ያለው ፓለቲካዊ ፣ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ ጉዳዬችን በአዋጅና ደንብ መሰረት ያወጣል ፣ ካቢኔው አዋጆችን ተንተርሶ መመሪያ ያዘጋጃል።... ከዚህ አኳያ መመሪያ ቁጥር አንድ አግባብ እንዳልሆነ የሚያረጋግጠው የምክር ቤቱን ማቋቋሚያ ሆን ተብሎ ወደ ጐን በመተው በካቢኔ ደረጃ በቆረጣ መመሪያ እንዲሆን መደረጉ ነበር።

በወቅቱ በፍትህና ፀጥታ ቢሮ ውስጥ የህግ ነክ ጉዳዬች ሀላፊ የነበረው ወልደሰንበት በመመሪያ መልክ መውጣቱን በመቃወም "የጉዳዩ ባለቤት የሆነው የአዲሳባ ህዝብ መምከር ይኖርበታል ፣ ከሁለት ቢሊዬን ብር በላይ የሆነ የህዝብ ሀብት ለህገወጦች እየሰጠን መሆኑን ነዋሪው አውቆ መነጋገር አለበት።... ይህ ካልተቻለና ጉዳዩ ህግ ሆኖ መውጣት አለበት ከተባለ ቢያንስ የህዝብ ውክልና ያላቸው የምክር ቤት አባላት ተወያይተውበት በአዋጅ መልኩ መዘጋጀት ያስፈልጋል " በማለት አጥብቆ ተከራከረ።... ለዚህም ህጋዊ ጥያቄ ምላሱ በማስትሽ የተጣበቀበት አሊ ቅሌተኛ በሆነ መንገድ የህግ ጉዳዬች ሀላፊውን ስም እየጠራ " መመሪያዉ በአስቸኳይ መውጣት በከተማዋ የሚታየውን ህገወጥነት ሙሉ ለሙሉ እንደሚያስቀር ለመገንዘብ በአብዬታዊ ዲሞክራሲ አስተሳሰብ መቃኘት ብቻ ሳይሆን አይንን ገለጥለጥ አድርጐ በከተማዋ አራቱም አቅጣጫ ዞር ዞር እያሉ መመልከት ይጠይቃል " የሚል አሳፋሪ ምላሽ ሰጠ።

እነ አሊ የህግ ጭብጦችን አንስተው ምላሽ ይሰጣሉ ተብለው ባይጠበቁም ፣ ይህን ያህል ወደታች ወርደው የአምላክ ስጦታ የሆነ ን አካል ጉዳተኝነት ላይ ያላግጣሉ ተብሎ የጠበቀ አልነበረም። ይህ ማየት የተሳነው ሀላፊ " የአስተዳደሩ የህግ መሀንዲስ " በመባል የሚታወቅ ሲሆን በአሊ አብዶና አርከበ እቁባይ የሚፈፀሙ የህግ ጥሰቶችን ፊት ለፊት በመቃወም ይታወቃል።... ለግል

ፕሬሶችም የመረጃ ምንጭ በመሆን የታቀዱና ሊተገበሩ የተዘጋጁ እኩይ ተግባሮችን የሚያጋልጠው እሱ እንደሆነ በካድሬዎች ዘንድ ይጠረጠር ነበሩ።... በዚህም ምክንያት ከደረጃው ዝቅ እንዲል የተደረገ ሲሆን በምርጫ 97 የቅንጅት ቀንደኛ ደጋፊ ሆኖ አስተባብሯል በሚል መረጃ ቀርቦ ለረጅም ጊዜ እንዲንሳፈፍ ተደርጓል።

በመመሪያ ቁጥር አንድ ላይ ቀጥሎ የተነሳዉ ለምን "ቁጥር አንድ " ተባለ የሚለው ነበር። እነ አሊ የመመሪያው መውጣት በመዲናይቱ የተከሰቱ የመሬት ዝርፊያዎችን ሙሉ ለሙሉ ያስቀራል ባሉበት ሁኔታ ለምን ይህ ስያሜ ተሰጠው ።... የመሬት አስተዳደር ላይ ሙያተኛ የሆኑት እነ አበበ ዘልኡል " መመሪያው ህገ ወጥነትን የሚያበረታታና ለሌላ አዲስ ህግ ማውጣት የሚዳርገን ይሆናል... ቁጥር አንድ ማለት በቀጣይ ቁጥር ሁለት ... ሶስት..." እየተባለ እንደሚወጣ አመላካች ይሆናል በማለት ተከራከሩ።...ስያሜው በራሱ ህገ _ወጥነትን ያበረታታል የተባለውን የተቃወመው አሊ አብዶ ከተማዋን በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዴት ስርአት እንደሚያሲዛት ዝርዝር የስራ እቅድ አቀረበ። " እመኑኝ በዚህ መመሪያ ምክንያት ህገ ወጥነት በማያዳግም መልኩ በቁጥጥር ስር ይውላል " አለ።

"ዘመቻ ጨረቃ መውጣት"

የተፈራው አልቀረም መመሪያ ቁጥር አንድ ይፉ በተደረገ ምሽት መሬት ወረራውና ግንባታው በሻማና ጨረቃ ብርሀን ተጧጧፈ።... የህንፃ መሳሪያዎች ፣የሲምንቶና አሸዋ ነጋዴዎች ተቀናጅተው ወደ ጨረቃ ቤት ግንባታ ተመሙ (የጨረቃ ቤት የተባሉበት ምክንያት ቤቶቹ ጨለማን ተገን በማድረግ በጨረቃ ብርሀን ታግዘው በመሰራታቸው ምክንያት ነው)። ... መመሪያ ቁጥር አንድ በወጣ በሳምንቱ ውስጥ የቆርቆሮ ፣ ሚስማርና ድንጋይ ዋጋ ጣራ ነክሰ ።... በሀገሪቱ የሚገኙ ገልባጭ መኪኖች የመከላከያ ካሚዬኖችን ጨምሮ የግንባታ እቃዎችን በምሽት ማመላለስ ጀመሩ።... ከቀንበላ ወደ ጨረቃበላነት የተቀየረው የጉልበት ሰራተኛ እንደአሜሪካ ሀገር በሰአት የሚከፈለው ገንዘብ ከመሀንዲስ በላይ ሆነ ። ስርአት አልበኝነት ሲሰፍን ለሙያና ለሙያተኛ የሚሰጠው ዋጋ አፈር ድሜ ይበላል። ህገወጥነት ሊቀናጁ የማይችሉ ሀይሎችን በአንድ መርከብ ያሳፍራል፣... ለዚህም ነበር የህዝብ ትልቅ ሀብት የሆነው መሬት ሲዘረፍ: የመንደር ጐረምሶችና ፓሊሶች ፣ ... ለደህንነት ስጋት የሆኑ ሀይሎችና የሀገሪቷን ሰላም ለማስጠበቅ ሀላፊነት የተሰጣቸው የመከላከያ መኮንኖች ፣... የአስተዳደሩ ደንብ አስከባሪና ደላላው የጋራ ትኬት ቆርጠው መሳፈራቸው።

መመሪያውን ተከትሎ የተሰሩት የጨረቃ ቤቶች የግንባታ ሂደት አሳዛኝም፣ አስገራሚም ነበር። በኢትዬጲያ ታሪክ ውስጥ የቆርቆሮ ቤት በሁለት ምሽቶች ተሰርቶ ለአገልግሎት አሊያም ለመሸጥ ዝግጁ ሆነ ቢባል የማይታመን ይሆናል።

እውነቱ ግን ይህ ነበር ።

ከአርብ ማታ እስከ አስከ እሁድ ምሽት ያለውን የስራ ሒደት

ማንሳቱ አስገራሚነቱን ሊያሳይ ይችላል•••

እንደሚታወቀው የመንግስት ስራ ቅዳሜና እሁድ ይዘጋል።ሰራተኞች የእረፍት ቀን ይሆናል።... የፀጥታና ህገ ወጥ የሚከታተለው ክፍልም የመንግስት ሰራተኛ ስለሆነ በመስክ ላይ ተገኝቶ ግንባታዎችን አይቆጣጠርም ። ይልቁንስ በሰንበት ቀናት ተገንብተው ከተሸጡት ቤቶች ውስጥ በአብዛኛቹ ላይ እነዚህ ደንብ አስከባሪዎች ተሳታፊዎች ነበሩ።... በህገወጥነት ገንብቶ ከመቸብቸቡ በተጨማሪ ለስርአት አልበኞቹ መረጃ በማቀበል ቅድመ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ያግዛሉ።

የጨረቃ ቤቱ ግንባታ የስራ ሒደት የሚጀምረው በከተማው የመሀል ቦታዎች በሚገኙ ሰፋፊ ግቢ ያላቸው ቤቶችና የካስ መጫወቻ ሜዳዎች ላይ ነበር።... በየቦታው በከተማዋ ባዶ ቦታዎች በተለይም የዳርቻ አካባቢዎች የተደራጁ ሰዎች በትራክተር በመታገዝ አፈር እየቆፈሩ ይቆልላሉ።ገልባጭና የመከላከያ ካሚዬኖች ከሰኞ እስከ አርብ የተዘጋጀውን አፈር ወደ መሀል አዲሳባ የግለሰቦች ግቢና ሜዳዎቹ ያግዛሉ፣... ጦር ሀይሎች፣ ልደታ፣ ቂራ፣ አብነት፣መሳለሚያና ጦሩ ሰፈሮች በከፍተኛ ሁኔታ በጥቅም ላይ የዋሉ ቦታዎች ነበሩ።... የተራገፈው አፈር እርሾ ተጨምርቦት በእለቱ በመቡካት ወደ ጭቃነት ይቀየራል ፣እስከ አርብ ማታ እየተገላበጠ እንዲቆይ ይደረጋል።

በመሀል ከተማ በተለይም በጦር ሀይሎች፣ ልደታና ሳርቤት አካባቢዎች ተለጥፈው የነበሩት የጭቃ ሽያጭ ማስታወቂያዎች አዝናኝ ነበሩ።... የጭቃውን ጥንካሬ ለማሳየት " ሲምንቶ የሚያስንቅ ጭቃ እዚህ ይሸጣል!" ፣... " አንድ ወር ሙሉ ተጨንቀን ያቦካነው ጭቃ አለ ጉራ ብለው ይጠይቁ "... " በከተማችን ታዋቂ ጭቃ አቡኪዎቹ በለጠ ፣ቢሆነኝና ጆርጌ ያቦኩት ጭቃ እንዳያመልጥዎት" ይላል። ...ውበቱንና አስቸኳይነቱን ለማሳየት ደግሞ " በአድአ ጤፍ የተቦካ..." ፣ "ጊዜ የለንም ጭቃ መሸጫ " ፣..." ውጤት ተኮር ጭቃ ቤት " የሚሉ ይገኙበታል።

በእለተ አርብ ፀሀይ መጥለቅ ስትጀምር የጭነት መኪኖቹና ካሚዬኖቹ የተዘጋጀውን ጭቃ ወደ መጫን ይሸጋገራሉ።... ሌሎች ተሸከርካሪዎች በአዲሳባ ዙሪያ ከሚገኙ የኦሮሚያ ከተሞች ለጨረቃ ቤቱ መስሪያ የሚያገለግሉ ቋሚ ፣ ማገርና ፍርግርግ እንጨቶችን ተሸክመው ወደ ግንባታ ቦታ ይተማሉ።... አቅርቦቶች መሞላታቸው ሲረጋገጥ ግንባታ ይጀመራል።... ማታዉኑ የቤቱ አፅምና ቆርቆሮ ሽፋን ይጠናቀቃል ፣... ቅዳሜ ጠዋት ማገርና ጭቃ መለጠፍ ጦን ለጦን ይካሔዳሉ፣... እስከ ማታ ድረስ አዲሱን ቤት የማደላደል፣ የላስቲክ ምንጣፎች ይዘረጋሉ። ከነባር ቤቶች በአንድ አንፓል እስከ መቶ ብር በወር የሚከፈልበት መብራት ይጠለፋል። ከነባር ወደ አዲሱ ጨረቃ ቤቶች የሚዘረጋዉ የኤሌክትሪክ ገመድ በኪሎሜትሮች የሚጠጋ ሲሆን እርስ በራሱ ተጠላልፎ የኤሌክትሪክ አውቶብስ የተዘረጋበት ይመስላል...

ከቅዳሜ ማታ ጀምሮ እስከ እሁድ ረፋዱ ድረስ የጨረቃ ቤቶች ሽያጭ እጅ በእጅ ይከናወናል።... ቤቱን ሰርቶ ለማጠናቀቅ አሰር ሺህ ብር የፈጀበት ህገ _ወጥ በሁለት ቀን ውስጥ እሰከ ሀምሳ ሺህ ብር ይቀበላል ። ...ብዙዎቹ በአንድ

ጊዜ ከልለው የሚይዘው ቦታ አስከ አስራ ሁለት ቤቶች የሚያሰራ በመሆኑ በሳምንት ውስጥ ወደ ሚሊየነርነት ይቀየራሉ። የራሳቸው ጋንገስተር ቡድን ያደራጃሉ፣ ... ይህ አደገኛ ስብስብ አካባቢውን በቁጥጥር ስር በማዋል የትኛውም የመንግስትና ፀጥታ ሀይል አካባቢው እንዳይደርስ ያደርጋል።...የአስተዳደሩን ባለስልጣናት ፣ፓሊስና መከላከያ ውስጥ ያሉ ሌቦች የቡድኑ ስውር አባል በመሆን መረጃ ያቀርቡለታል።

በሌላ በኩል በቤት እጦት የሚሰቃዩ ነዋሪዎች "የጨነቀው እርጉዝ ያገባል " እንደሚባለው ያላቸውን ጥሪት ሸጠውና በጐደለው ተበድረው ቤቶቹን ይገዛሉ። የዛኑ እለት በተጠንቀቅ ከሚጠብቁት የጭነት መኪኖች ጋር በእጥፍ ዋጋ በመዋዋል እቃቸውንወደ አዲሱ ጐጆ ያጓጉዛሉ ።በትራንስፓርት ለማስጫን ካወጡት ያልተናነሰ በመክፈል በጫኝና አውራጅ እቃቸውን ያራግፋል። ለሰው ልጅ ኑሮ መሰረታዊ ነገሮች ተደርገው የሚቆጠሩት እንደ የመጠጥ ውሀ ፣የፍሳሽ አገልግሎት፣ መንገድ ፣ ትራንስፓርት ፣ ትምህርት ቤት፣ የጤና ጣቢያ... በሌለበት ሁኔታ ቤተሰቡ ተሰብስቦ በጨረቃ ቤት መኖር ይጀመራል፣ ... ህገ ወጥ በመሆን ተከትሎ የሚመጣው ውጣ ውረድ የእለት ተእለት ህይወት ይሆናል : ...ወደ ስራና ትምህርት ቤት ለመሄድና ለመምጣት መከራቸውን ይበላሉ። ለሰአታት ከጅብ ጋር እየተጋፉ በእግራቸው ይጓዛሉ። ሚስትና ልጅ እንዳይደፈሩ ይጠብቃሉ። ውሀ ወለድ በሽታ እንደ ጉንፋን ይፈራረቃል።

የጭንቀት ህይወት!

***

የጨለማው ዘመን ታሪክ የጫኝና አውራጆችም ስለነበር ጥቂት ስለእነሱም እናውጋ -:

በአዲሳባ ከተማ ነዋሪዎች ዘንድ ጫኝና አውራጅ በማለት የሚታወቁት ወጣቶች የመስፋፋት መንስኤ በከተማው ተንሰራፍቶ የነበረው ስርአት አልበኝነትና ህገ _ወጥ ግንባታ ነበር።... አስተዳደሩ በሁሉም ጉዳዬች ላይ የተኮላሸና የነቀዘ በመሆኑ በተስፋ መቁረጥ ምክንያት ያገኟትን ቀዳዳ ህጋዊና ህገ _ወጥ መንገዶችን በመጠቀም ጥቅም ለማግኘት የተደራጁ ቡድኖች ናቸው። ጫኝና አውራጆች ወደ አደገኛ ቡድን ከመቀየራቸው በፊት በአካባቢያቸው ለሚካሔዱ ህጋዊ ግንባታዎች ግብአት የሚሆኑ ቁሳቁሶችን በማውረድና በመጫን ይተዳደሩ ነበር ።በሂደትከማውረድና ማውጣቱ በተጨማሪ አፈርና ድንጋይ በመቆፈር ወደ መሸጥ ተሸጋገሩ።... ቀስ በቀስ ከመሀከላቸው የቀለም ትምህርት የቀመሱትንና ረብሻ ጠል የሆኑት ትላልቅ የጭነት መኪናዎችን ወደ መግዛትና ለግንባታ የሚያስፈልጉ ግብአቶችን ማቅረብ ጀመሩ።... አንዳንዶቹ ደግሞ እነ አሊ አብዶ ካሰማሯቸው የመንግስት አካላት ጋር በመሰማጠር ወደ መሬት ደላላነት በመቀየር በአጭር ጊዜ ውስጥ በሚሊዬን ብሮች መቁጠር የእለት ስራቸው ሆነ።

በፀብ አጫሪነትና አደገኝነት የሚታወቁት ደግሞ የበለጠ አስፈሪ በመሆን የመንደር መንግስታት አለቆች ሆኑ ፣... በቁጥጥራቸው የሚካሔዱ ማንኛውም እንቅስቃሴ የእነሱን ይሁንታ ካላገኘ መፈፀም የማይችልበት ደረጃ ተደረሰ ፣ ...ወደ ለየለት ማጅራት መቺነት ተቀየሩ።... በ600 ብር የተገዛ ወንበርና ጠረጴዛ ከመኪና ላይ ለማውረድ መቶ ብር ይጠይቃሉ። የእቃው

ባለቤት ራሱ ማውረድ ከፈለገ እስከ 25 ብር የኩቴ መክፈል ግዴታ ሆነ። ... ቁሳቁሱን ጭኖ የመጣው ሹፌርም ተመሳሳይ ግብር ይጥሉበታል።

ሌላው ቀርቶ በወቅቱ አንገብጋቢ ለነበረው የውሀ ችግር በከፍተኛ ደረጃ ጥቅም ላይ ውላ የነበረችው እንሰሳ አህያ የነበረች ሲሆን አንድ ጀሪካል ውሀ እስከ ሀያ ብር ይሸጣል፣ ከውሀ ሽያጭ ከተገኘው ገቢ ሩብ ያህሉ ለእነዚህ ለመንደር አለቆቹ ይሰጣል። የጨረቃ ቤቱን ገዝቶ የገባው ነዋሪ ሚስቱና ልጁ በሰላም ወጥተው እንዲገቡ በየቀኑ ገንዘብ ይከፍላሉ። አንዳንዶቹም ህሊና በሚጐዳ መልኩ አንዷን ልጅ ለመንደር አለቆች ገብረው ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን ይታደጋሉ።

የጫኝና አውራጆች ቡድኖች የራሳቸውን ክልል ያሰመሩ ሲሆን አንደኛው ወደ ሌላው ገብቶ መስራት አይችልም ፣...ይህንን ተላልፎ የተገኘ በስለታማ ጦር መሳሪያዎችና በድንጋይ ይወገራል፣... የአንዱ መንደር አለቃ አጉራዘለል ሆኖ የድንበር ማስፋፊያ እርምጃ ቢወስድ ሌሎች ተረባርበው አይቀጡ ቅጣት አሳርፈውበት ወደ ነበረበት ቦታ ይመለሳል።

እነዚህ የመንደር መንግስታት ራሳቸውን በማጠናከር የጦር መሳሪያ እስከመታጠቅ ደርሰው ነበር።... በአንድ ወቅት የኮልፌ ቀራንዬ ፓሊስና ደህንነት ባደረገው የተቀናጀ ኦፕሬሽን ከአንድ ቡድን ብቻ አምስት ሽጉጦችንና ሶስት "ቆመህ ጠብቀኝ " ጠመንጃዎች አግኝቷል። ... የቡድኑ አለቃዎች በቁጥጥር ስር ውለው በተደረገባቸው ምርመራ አስደንጋጭ ሚስጥሮችን አውጥተዋል፣... ከላይ እስከ ታች የተዘረጉ የሌብነት ሰንሰለቶችን አጋልጠዋል...

ከቀበሌ አስከ ከተማ ... ከዘርሙ አስከ አሊ አብዶ።

***

የመንደር መንግስታት የሆኑት ጫኝና አውራጆች እያደር ከሰሙ። የምሽት ጭፈራ ቤቶች - የባህል ሙዚቃ ቤቶች -ውስኪ ቤቶች - ራቁት ቤቶች ማደሪያቸው ሆነ። በቀን ያለልፉት የሚያገኙትን ገንዘብ ልደታ፣ ካዛንችስ፣ ዶሮ ማነቂያ የቡና ቤት ሴተኛ አዳሪዎችን በየቀኑ ቀያየሩበት። ያለ እውቀትና ግንዛቤ ባገኙትገንዘብ የማይድን በሽታ ገዙበት ። ኤች አይ ቪ ኤድስ ያዛቸው። አብዛኞቹ ያለ እድሜያቸው ተቀጩ።

ጨለማው ሳይነጋ የእነሱ ዘመን ተፈፀመ።

***

የጥፉት ቅብብሎሹ በጨረቃ መኖሪያ ቤቶች ብቻ አላበቃም።... ሌሎች ማህበረሰቡየሚጠቀምባቸው አስተምህሮና የህክምና ተቋማት ጨረቃን ተገን አድርገው ተገንብተዋል።... መዋዕለ ህፃናት ፣ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ ክሊኒክ ፣ እና የሀይማኖት ተቋማት የሚጠቀሱ ናቸው።... በተለይ ቤተክርስትያኖችን (የሁሉም ክርስትና እምነቶች) እና መስኪዶቹን ከህገ _ወጦች መሬት በመግዛት ጨለማን ተገን ተደርጐ ግንባታ ሲሰራ ማየት የስርአቱ አልበኝነት ምን ያህል ስር የሰደደ መሆኑን የሚያሳይ ነበር። ... አንደ እውነቱ ከሆነ የእምነቱ አባቶች በዚህ መልኩ የተቋቋመን ማምለኪያ ቦታ ለመንፈሳዊ

ስብከት ሲያውሉትና ለህገ _ወጦች ጠበቃ ሆነው ሲከራከሩ ማየት የተለመደ ነው።... በእርግጥ ብዙዎቹ የእምነት አባቶች በሚያገለግሉበት የእምነት ተቋም አጠገብ የጨረቃ ቤት ባለቤቶች ስለሆኑ ለህገወጥነት ጠበቃ ቢቆሙ የሚገርም አልነበረም... እነሱስ ቢሆን የጨለማው ዘመን አካል አይደሉ !

መመሪያ ቁጥር አንድን ተከትሎ የተዘረጋው የጥፋት ቅብብሎሽ በዚህ አላበቃም፣... በመንግስት ስልጣን ላይ ያለው ህገ ወጥ ሀይል የግለሰብ ቤት ኪራይና የቤት ችግር አናቱን አዙሮት የጨረቃ ቤት በመግዛት ቤተሰቡን ሰብስቦ የሚኖረውን የከተማው ነዋሪ ለሁለት ከፍለው ቀይ መስመር ያሰምራሉ ፣... ከመስመሩ ወዲህ በመመሪያ ቁጥር አንድ የሚሸፈኑ፣ ወዲያ ደግሞ በቅርብ ጊዜ የሚፈርሱ የሚል ትእዛዝ ያስተላልፋሉ ፣የማፍረሻ ማስጠንቀቂያዎች ይሻርጉደጉዳል።... ጥራቱን ሸጦ ፣ ተበድሮና ተለቅቶት የጨረቃ ቤት በመግዛት ኑሮ የጀመረውና ከመስመሩ ወዲያ ያለው ህዝብ ከፓሊስና አፍራሽ ግብረ ሀይሉ ጋር ለመፋለም በየቦታው መደራጀት ጀመሩ... የጦር መሳሪያ እስከመታጠቅ ደረሱ።

በከተማዋ በሚገኙ ማስፋፊያ ወረዳዎች የተሰሩትን የጨረቃ ቤቶች ለማፍረስ የፌዴራል እና የአዲሳባ ፓሊስ ከአፍራሽ ግብረ ሀይሉ ጋር በመቀናጀት "ዘመቻ ጨረቃ መግባት" ለማስፈፀም ተንቀሳቀሱ።... የሰው ህይወት በየቦታው መውደቅ ተከተለ... ወላጆች ከነልጆቻቸው ወደ ጎዳና ወጡ።

በወቅቱ የነበረውን እሪታና ዋይታ በታዘብኩ ቁጥር በኢትዬጲያ ቴሌቭዥን ኢህአድግ የፊውዳሉን ስርአት አስከፊነት ለማሳየት በአንዲት ገጠራማ አካባቢ የተፈፀመውን ግፍ በፊልም አስደግፎ በተደጋጋሚ ያሳየንን ያስታውሰኛል።... በፊልሙ ላይ አንድ ፊውዳል በትራክተር የገበሬውን ቤት ሲያፈርስ ያሳያል...ገበሬዎቹ ጮጆአቸው በዶዘር እየተገረሰሰ እያዩ ባላባቱን መሬት ላይ ወድቀው ይለምኑታል፣... ተማፅኖአኖአቸውን ከቁብ ሳይቆጥር ጮጆአቸውን ሲቦድሰው ወጣቱ ገበሬ ላይ የሚንቀለቀለውን የበቀል እሳት ከተሌቪዥኑ አልፎ ተመልካቹን ይለበልባል።

የገበሬው ትናጋ እሳት ፊውዳሉን እንዴት እንደጠበሰው የቅርብ ጊዜ ታሪካችን ነው ፣... ያለውን ብቻ ሳይሆን ከሰው የተበደረውን ያጣው የአዲሳባ ከርታታ፣ በህገወጥ አካባቢ በመኖሩ ሚስቱና ለአቅመ አዳም ያልደረሱ ሴት ልጆቹ የተደፈሩበት ምስኪን ...ከገበሬው ባልተናነሰ ኢህአድግን ቢጠላና በምሬት ቢሞላ ያንስበት ይሆን? ... ለሀይማኖቱ ቀናኢ የሆነ ህዝብ የሙሴ ትዕዛዝት ተዕፎበታል ብሎ በሙሉ አይኑ ለማየት የማይደፍረውን ፅላት (ታቦት) በፓሊስ መኪና ላይ እንደወንጀለኛ ተጭኖ ፣ ጣቢያ ለኤግዝቢትነት ከተቀመጠ ጦር መሳሪያ ተቀላቅሎ ሲያየው መንስኤው ምንም ይሁን ምን እንደውርደት መቁጠሩ አሌ አይባልም።

የማፍረሱ ሂደት በሁለት ቢላዋ ለሚበሉት የመንደር መንግስታት ጥሩ አጋጣሚ ነበር። በአንድ በኩል በተልእኮ ተዋጊነታቸው ገንዘብ ከህገ ወጥ ቤቱ ባለቤት ይቀበላሉ። በሌላ በኩል ቆርቆሮና እንጨት እየነቀሉ ወደ ራሳቸው ማከማቻ መጋዘን በጭነት መኪና ይወስዳሉ። መንግስት ያሰማራቸው አፍራሽ ግብረ ሀይሎች የሚታወቀው ትልቁ ደሞዛቸው የፈረሱትን ቆርቆሮ መከፋፈል

ነበር። እናም ያፈረሱትን ቆርቆሮ በመሰብሰብ በሽንኩርት ዋጋ ሲሸጡ ታሳቢ የተደረገው መመሪያ ቁጥር ሁለት እንደሚሆን የሚያጠራጥር አልነበረም።

መመሪያ ቁጥር ሁለት!!

" ከእንግዲህ ህገ -ወጥ ግንባታ ታሪክ ይሆናል!! "

(ከንቲባ አርከበ እቁባይ : 1995 አ• ም•)

የማስታወሻው ጉዞ እንደ ፔንዱለም ነውና ገመዲ ከአንደኛው ጫፍ ወደ መሀል ቀርባለች፣... የተፈፀሙት ጥፉቶች በቅብብሎሽ ስለሆነ ተያያዥነት ያላቸውን ቁም ነገሮች አስተሳስሮ መመልከቱ የተሻለ ስለሚሆን...

ወደ ወጋችን እንመለስ...

የመመሪያ ቁጥር አንድ በተግባር ላይ መዋል ህገ ወጥነቱ በተደራጀ መንገድ እንዲጧጧፍ አደረገው። በፊት መስመር የተሰለፉት የመንግስት ባለስልጣናት፣የኢህአድግ ካድሬዎች፣የፓሊስ አባላት፣ የመከላከያ መኮንኖች፣ የአስተዳደሩ የመሬት ልማት ሙያተኞ ሆኑ።... አዳዲስ ስያሜ ያላቸው ማህበራት ዶሴ እየተከፈተላቸው ተደራጁ።... በአስተዳደሩ ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩ የቅየሳ ሙያተኞችና መሀንዲሶች የመንግስት ተሽከርካሪዎችንና የቅየሳ መሳሪያዎችን በመጠቀም ወደ መሬት ሽንሸና ተሸጋገሩ። ... ክፍፍሉ እንደ ቀድሞው ጨረቃን ተገን በማድረግና በሰንበት ብቻ አልነበረም። በመደበኛ የመንግስት ስራ ሰአት በአዘቦት ቀን ጭምር የሚከናወን ሆነ።

ለዚህኛው የተደራጀ ዝርፊያ መሰረት ከጣለው መመሪያ ቁጥር አንድ በተጨማሪ ህገ _መንግስቱን በጠረባ የመታው "የሁከት ይወገድልኝ " አዋጅ የጐላ ሚና ተጫውቷል።... ከዚህ አዋጅ በፊት መሬቶቹን በባለቤትነት ይዘው ሲያርሱ የነበሩ ገበሬዎች እንዲነሱ በሚደረግ ሰአት የካሳ ጥያቄና ሌሎች ከመሬቱ ጋር ተያያዥነት የላቸውን መብቶች ለማስከበር ለፍትህ አካላት አቤቱታ ያቀርቡ ነበር። በዚህም ካልተስማሙ ህገ _መንግስታዊ መብታቸውን በመጠቀም ወደ ፍርድ ቤት በመሄድ ክስ ያቀርባሉ።... ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን በደንብ አጣርቶ ብይን እስኪሰጥ የመሬት ይዞታው ባለበት እንዲቆይ የእግድ ትእዛዝ ይሰጣል።

ከአዋጁ መውጣት በኃላ የገበሬው መብት ሙሉ በሙሉ ተገፈፈ። የአርሶ አደሩ አቤቱታ "የተሰጠኝ ካሳ ያንሰኛል "ወደሚል የወረደ ጥያቄ ተሸጋገረ።...ይህም ሆኖ የተገመተለትን ካሳ ለማግኘት ከአንድ ቢሮ ወደ ሌላ መንከራተቱና ቢሮክራሲው አማረረው።

፣ ... በዛ ላይ የተደራጀው የዝርፊያ ቡድን ለካሳ እጅ በእጅ የሚያቀርብለት ገንዘብ እጥፍ የላቀ ሆኖ አገኘው...ሳያቅማማ መሬቱን ለቀማኛ አስረክቦ ወጣ...

በዜሮ ዋጋ!

በሌላ በኩል የማፊያው ቡድን መንግስታዊ ቅርፅ የያዘ በመሆኑ በግላጭ መሬቱን ወደ መከፋፈል ገባ፣... የከተማዋ ማስተር ፕላን እየተመሳከረ መሸንሸን ተጀመረ። ...በፕላን የተደራጁ ባዶ መሬቶች ዝግጁ ሆኑ።... ሰፋፊ አውራና ውስጥ ለውስጥ መንገዶች ተቀየሱ።... የትምህርት ተቋማት ፣ጤና ኬላ ፣ አረንጓዴ ቦታዎች ለብቻቸው ተከልለው ታጠሩ።...ከአስራ ሁለት እስከ ሀያ መደቦችን አንድ ላይ በማጣመር የማህበር ስያሜ ተሰጣቸው : - መብረቅ ፣አንድነት ፣ጣምራ -ጦር ፣ሀገሬ ፣እፎይታ፣ ዞሮ መግቢያዬ...

አብዛኛቹ የማህበር ስያሜዎች በደርግ ዘመን ቤት ለመስራት ለማዘጋጃ ቤት ቀርበው የነበሩ ናቸው፣... ይህም ማህበራቱ ጥንት መደራጀታቸውን ለማሳየት ሆን ተብሎ የተደረገ ነበር። ... በመሆኑም መዝገቦቹ

አባራቸው ተራግፎ መጠሪያቸውንና የአባሎቻቸውን ስም ዝርዝር ሳይለቁ ወደ ማስፋፊያ ቦታዎቹ መጡ።... የማህበሩ አባላት በስም ይገለፅ እንጂ በአካል አልነበሩም :-ግማሾቹ ሞተዋል ፣ ከፊሉ ሀገር ጥሎ ተሰዷል ፣ ሌላው ከቀድሞ ስርአት ጋር በተያያዘ ወህኒ ተወርውሯል፣ የተቀረው ደግሞ ከደርግ ጋር አብሮ የተቀበረ ፉይል ስለመሰለው እርግፍ አድርጐ ትቶታል።

የቀድሞዎቹ ማህበሮች ነብስ እንዲዘሩ የተደረጉት በወቅቱ የመሬት አስተዳደር ባለስልጣን በነበረው አርቴክት አማረ አስግዶምና አለ አብዶ አማካኝነት ነበር፣...ሁለቱም የራሳቸው ማፊያ ቡድን ቢኖራቸውም ተቀናጅተው ማህበሩንና የተሸነሸነውን መሬት አዋደዱ።...ሁሉ ሙሉ ፣ ሁሉ ዝግጁ የሆነው መሬት አየር ባየር መቸብቸብ ተጀመረ።...እነ አማረ ቢጠሯቸው የማይሰሙበት ደረጃ ደረሱ...ነግቶ በመሸ ቁጥር ሚሊየነሮች መፈልፈል ጀመሩ።... የቤት እጦት ያማረረው የመዲናይቱ ነዋሪ ለሁለተኛው ዙር የጥፋት አዙሪት ቀበቶውን ፈታ።

ሌባ ሲሰርቅ እንጂ ... እንደሚባለው አማረና አለ አብዶ ከፍተኛ ፀብ ውስጥ ገቡ።...ይህን ተከትሎ አርትቴክቱ ለሀገሩ ልጅና ለሞክሼው የሪፓርተር ጋዜጣ ባለቤት መረጃዎችን ማሹለክ ጀመረ ። ዳጐስ ያለ ገንዘብ እንደተቀበለ የሚነገረው ሪፓርተር የአሊን ዱካ እየተከተለ ማጋለጥ ጀመረ ፣... የአስተዳደሩን መሞሸሸና መኮላሸት በሁሉም የጋዜጣው አምዶች አስተጋባ ... አልፎ በመሻገር በርዕሰ አንቀፁ:-

ወይ አዲሳባ ወይ አራዳ ሆይ ፣
አለ አለ አብዶ አላየሽም ወይ።

የሚል ስንኝ አሰፈረ።

በሌላ በኩል አለ አብዶ አርቴክቱን ለማባረር ሌሎች የሌብነት ዶሴዎችን ይዞ ብቅ አለ፣...በመዲናይቱ የተገነቡት አዳዲስ ግዙፍ ህንፃዎች ካርታና ፕላናቸውን ለማፅደቅ አማረና ቡድኖቹ እስከ ሀምሳ ሺህ ብር እንደሚጠይቁ በመረጃ አስደግፎ አቀረበ።... በዚህ ሌብነት ብቻ አርክቴክቱ ከአምስት ሚሊዬን ብር በላይ ሀብት ማካበቱን አጋለጠ።... መረጃዎቹን አለ አብዶ በስሜት ተነሳስቶ በካድሬዎች ፊት በመዘርገፉና እውነተኛ ስለነበሩ ያለደብዳቤ እንዲያባርረው ተፈቀደለት። አለ አብዶ ደስ አለው... ትልቅ ድራማ እንደተሰራበት ሳያውቅ !

የድራማው ከፊል ገቢር የሚከተለው ነበር :

አማረ አስገዶም የህውሀት ባለሀብቶችን መፍጠርና ማገዝ በሚለው ቡድን ውስጥ ተደራጅቶ ከሚንቀሳቀሱ ቁልፍ ሰወች አንዱ ነበር። ከመሬት ጋር በተያያዘ ለህውሀት ሰወች የሀብት ምንጭ ሆኗል። ለራሱም አልቦዘነም። ከእለታት በአንዱ ቀን የሚሊየነሮች መስመር ውስጥ ተሰልፎ ተገኘ... እናም በአለ አብዶ ተባረረ። ... ጊዜውን ጠብቆ የአብዶ ልጅ "ዘባተሎ... ዝርክርክ " ተብሎ ሲሰናበት የአርከበ የምህንድስና ጉዳዬች ዋና አማካሪ ሆነ።

አርቴክቱ የሰራቸው ወንጀሎች አይን ያወጡ ነበሩ። ከማዘጋጃ ቤት ውስጥ የከተማዋን ካርታ (ማስተር ፕላን) አሰርቆ አውጥቷል። ይህን ተከትሎ የከተማዋን ባዶ መሬት ሸንሽኖ ሸጠ። በኮልፌ ቀራንዬ ብቻ 26 ማህበራት በመሰየም ከአንድ ሺህ በላይ ለሆኑ ሰዎች ቸበቸበ። ይህ ዘረፋ በድዱ የሚኖረው የፀረ ሙስና ኮሚሽን ተረጋግጦ ይፉ ሆኗል። የእሱ ግብረአበሮች ከመቶ ሚሊዬን

ብር የሚጠጋ የህዝብ ንብረት ላይ ጉዳት በማድረስ ተከሰው ቃሊቲ ወረዱ። አማረ ደግሞ አርከበን ወደ ስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር አጅቦት ሄደ!

***

በፕላን የተሰሩት ህገወጥ ግንባታዎች ተጠናቀቁ። ቤቶቹን የገዛው ነዋሪም ጠቅልሎ ገባ። ቀስ በቀስ የመሰረተ ልማት ጥያቄዎች በነዋሪዎቹ መነሳት ጀመሩ... በተለይ የመብራት ጥያቄ ጊዜ የማይሰጠው ሆነ... መሬቱን የቸበቸቡላቸውን የመንግስት አስተዳደሮች ማስጨነቅ ጀመሩ። ... መመሪያ ቁጥር ሁለት ይወጣል ብላችሁ ነበር። በማይቀመስ ዋጋ ሸጣችሁልን ለምን የውሀ ሽታ ሆነ የሚል ቅሬታ መቅረብ ጀመረ ። ይህንን የነዋሪው ቅሬታ ተከትሎ ሚስጥሮች ማፈትለክ ጀመሩ። በተለይ ከ16 ማህበራት በላይ የተፈጠረባት ወረዳ 24 የተቃውሞው ማእከል ሆነች።

በወረዳ ሀያአራት ልዩ መጠሪያው ጀሞ በሚባለው አካባቢ ከተመሰረቱት ህገ -ወጥ ማህበሮች አንዱ "መብረቅ " ይባላል። ... ማህበሩ የተመሰረተበት ቦታ በከፍታ ቦታ ላይ በመሆኑ ቁልቁል አዲሳባን ለማየት ያስችላል ፣...ማታ ማታ ከከተማው መብራት ጋር ልዩ ውበት ይሰጠዋል። በዚህ ቁልፍ ቦታ የተመሰረተው የመብረቅ ማህበር ባለቤትነቱ የአሊ አብዶ፣ የወረዳው ሊቀመንበር የነበረችው ሙስሜ ረሺድና የቀበሌ 15 ካድሬ ዘርሙ በጥምረት ነበር። ...እነዚህ ካድሬዎች መሬቱን 36 ቦታ ሸንሽነው አያንዳንዱን በሀምሳ ሺህ ብር አሻገሩት።

መሬቱን ገዝተው መኖሪያ ቤት የገነቡት ነዋሪዎች ጊዜ ጠብቀው የመብራትና ውሀ ይግባልን ጥያቄ በማንሳት የወረዳዋን ሊቀመንበር መቆሚያ መቀመጫ ያሳጧታል፣... የሰዎቹን መመላለስ የከነከነው የወረዳው ደህንነት (ዘካሪያስ ይባላል) ክትትሉን አጠናክሮ ይቀጥላል።

ከእለታት በአንዱ ቀን ጠልፎ የሚያዳምጠው የሊቀመንበሯ የቢሮ ስልክ ያልጠበቀውን መረጃ አፈሰሰለት። ሴትየዋ ከአሊ አብዶ ጋር እያወራች ነበር...መብረቆች በመብራትና ውሀ ጉዳይ እንዳስጨነቋት ትነግረዋለች ። የውሀውን እሱ እንደሚጨርስ ለመብራት ሀይል ባለስልጣን ግን የድጋፍ ደብዳቤ እንድትፅፍላቸው ይነግራታል። እሷም ዋዛ አይደለችምና ዘርሙ ከቀበሌ መነሻ ፅፎ እንዲልክ ታዘዋለች፣... የቀበሌው ካድሬ የፃፈላት ላይ ተመስርታ ደብዳቤ ታዘጋጃለች።...የወረዳው ደህንነት ደብዳቤዎችንና ሌሎች ዶክመንቶችን ቢሮዋን በሚስጥር ቁልፍ በመግባት በእጁ ያስገባል...ለሙስና ክስ ማደራጀት ይጀምራል፣ ለእኛም መረጃውን ይሰጠናል።

በዚህ ሁኔታ ላይ እያለ ነበር ያልተጠበቀ ነገር የተከሰተው...

የኔዘርላንድ መንግስት ለከተማው አስፈፃሚ አካላት በመሬት መረጃ ሳይንስ የሁለተኛ ዲግሪ የትምህርት እድሎች ያመጣል... ሙስሜ ረሺድ መመዘኛውን ማሞላት ሳትችል አሊ አብዶ እሷ እንድትሄድ ይወስናል... የሚጣሩ ነገሮች ስላሉ ለተወሰነ ጊዜ አንድትቆይ ብንነግረውም አጣድፎ ወደ ኔዘርላንድ በሚስጥር ይልካታል።

በጨፌው ግምገማ የደህንነቱ ዘካርያስን የሚስጥር ስራ ሳንገልፀው ሴትየዋን

ለማሸሸ አለ አብዶ ያደረገውን ሩጫ አነሳን... ሰፊ ውይይት ተካሂዶት ጥፉቱ የእሱ እንደሆነ ተደመደመ።...ከሁለት አመት በኃላ ነገሮች ተረጋግተዋል በሚል ሴትየዋሁለተኛ ዲግሪዋን ጨርሳ ከባህር ማዶ መጣች... አርከበን ቀርባ አወያየችው... "የመብረቅ ማህበር ችግር በመመሪያ ቁጥር ሁለት ተመልሷል " በማለት የመሬት አስተዳደር ከፍተኛ ባለስልጣን አድርጐ ሾማት፣... የቀድሞውን ዶሴ እንደማስፈራሪያ አየተጠቀመ በርካታ ህገ -ወጥ ደብዳቤዎች አስፈረማት ፣... አንድ ጊዜ በሌብነት የተነካካ ባለስልጣን አፉን ለጉሞ የተባለውን እየፈፀመ እንደሚኖር ከራሱ ልምድ ያውቀዋል፣...እሷም ብትሆን "ድመት መንኩሳ... " ነበረችና የቀድሞ ወዳጇ (የቀበሌ ካድሬ ዘርሙ) ይዛ በድጋሚ ሌብነት ውስጥ ተዘፈቀች... ተያይዘው ወህኒ ወረዱ።

ኢህአድግ ቢሮ የአዲሳባ ኢህአድግ ስራ አስፈፃሚ እያለሁ ከቃሊቲ የመጣ መልእክት ደረሰኝ። ዘርሙ ነበር። ላገኝህ እፈልጋለሁ ይላል። ለስራ ባልደረቦቼ ካሚልና ፀጋዬ ነግሬያቸው ሔድኩኝ።

ዘርሙ በሀይለማርያም ደሳለኝ የተቋቋመውና እኛ አባል የሆንበት የባለስልጣናትን ንቅዘት ደረጃ በሚስጥር እያጣራ ያለው ኮሚቴ እየሰራ ያለውን ዘከዘከልኝ። ሀይለማርያም በከፊል የተሰረቀውን የከተማዋን ማስተር ፕላን ኮፒ ሊያመጣ ዱባይ እንደሔደ ነገረኝ።እኔ ደግሞ ሙስና ለማጣራት የዱከም ከንቲባ ጋር ለመሔድ መዘጋጀቴን ጨመረልኝ። ቃሊቲ ተቀምጦ።

ዘርሙ ቀይ መስመር እንዳለፍኩና በእሳት እየተጫወትኩ መሆኔን ሳይፈራ አስጠነቀቀኝ። የነገረኝን በሙሉ አመንኩት። ይህ መልእክት እንዲደርሰኝ የፈለገ ሀይል ከዘርሙ ጀርባ እንዳለ ተገነዘብኩኝ።

ከሀገር ከወጣው በኃላ ስለ ዘርሙ አሰደንጋጭ ዜና ሰማሁ ፣...ዘርሙ ከአለ አብዶ ዘመን ጀምሮ የሰራው ግፍ ፀፅቶት ለፍርድ ቤት ለመናዘዝ ፍቃደኝነቱን ባሳየ ሳምንት ሳይሞላው በድንገተኛ ህመም ወህኒ ቤት ህይወቱ አለፈች፣...

አዘንኩኝ!...

ከሞቱ በስተጀርባ ያለውን ሰው ለመገመት ግን አልተቸገርኩም።

***

አርከበ እቁባይ ወደ አዲሳባ በመጣ በቀናቶች ውስጥ እሱን ለመሸጥ ሰፋፊ መድረኮች ተከፈቱ... ከህዝብ የተውጣጣ አማካሪ ምክርቤት የሚባል ከከተማ እስከ ቀበሌ ተቋቋመ።... በአለ አብዶ ትርፍራፊ ኔትወርኮች አማካኝነት ረጃጅም ድምፅ ያላቸው ህገ -ወጦች የምክር ቤቱ አባላት ሆኑ። ... አጀንዳው በሙሉ መመሪያ ቁጥር ሁለት በአስቸኳይ መውጣት አለበት ሆነ ...

ይህን ተከትሎ አርከበ ለአማካሪ ምክርቤቱ ባቀረበው የሁለት አመት የከተማው የልማትና መልካጸም አስተዳደር እቅድ ላይ የሚከተለውን ጽፎ ቃል በቃል አነበነበ :-

" ... አስተዳደሩ ህገ -ወጥነትን በማያበረታታና ከማስተር ፕላኑ ጋር በማይጋጭ መልኩ ህገ -ወጦችን ህጋዊ የሚያደርግ መመሪያ ቁጥር ሁለት ያወጣል።...መመሪያው ከዚህ በኃላ በመዲናችን ህገ ወጥነት በቁጥጥር ስር በማዋል ልዩ ታሪክ ይሰራል።... ከእንግዲህ አስተዳደሩ ህገ ወጥ በሚገነቡ ሰወችና አስፈፃሚዎች ላይ የማያዳግም እርምጃ ይወስዳል። ... በተለይም

በማስተር ፕላኑ ላይ ተለይተው ለአረንጓዴ ቦታ የተባሉ ቦታዎች ላይ ግንባታ የሚፈፅም እስከ አስር አመት የሚፈጅ እስር ይጣልበታል። ... ይህንን በተደራጀ መንገድ ለማስፈፀም እንዲረዳ ከከተማ እስከ ቀበሌ ድረስ ጠንካራ አደረጃጀት ያለው ደንብ ማስከበር የሚባል ፅህፈት ቤት ይቋቋማል።" ብሎ ተናገረ።

መመሪያ ቁጥር ሁለት በተግባር ላይ ዋለ... አሊ አብዶ ነፃ ወጣ !

ከአመታት በኃላ ሙስሜ ረሺድ ዘብጥያ ወረደች!... ዘርሙ ወህኒ ቤት ሞተ!... አሊ አብዶ ከሱዳን ወደ ናይጀሪያ አምባሳደርነት በመሸጋገር ደረጃውን አሻሻለ።

የኢህአድግ ስልጣን የዛፍ ላይ እንቅልፍ... ከላይ ወደ ታች።

መመሪያ ቁጥር ሶስት!!

"ከእንግዲህ በመዲናችን ህገ-ወጥ ግንባታ አይኖርም!! "
(ሚኒስትር መኩሪያ ሀይሌ : 2005 አ• ም•)

መመሪያ ቁጥር ሶስት ወደ ረጅም ትረካ ይወስደናል። በኢትዬጲያ ታሪክ

ውስጥ ትልቅ ስፍራ ያለው ስለሆነ ዘለግ ተደርጐ ቢተረክ የሚያንስበት አይሆንም። ክስተቶቹ ከህሊና የሚጠፉ አይደሉም...

ምርጫ 97...

በጉዳዩ ላይ በርካታ መጽሀፎች ተጽፈዋል። በግራም በቀኝም። አንዳንዶቹ ወገንተኝነት የተጠናወታቸውና ራስን ለማዳን የተጻፉ ናቸው። ሌሎች ደግሞ በመጽሀፋቸው ላይ እውነቱን አውጥተዋል። ይህ ማስታወሻም በተቻለ መጠን ከዚህ ቀደም የተነገሩትን ላለመድገም ይሞክራል። ከውስጥ ወደ ወጭ ስለሆነ የተሸራረፉና ያልተነገሩ ታሪኮች አይጠፉበትም።

ከምርጫ 97 በኃላ የተካሄደው የመሬት ወረራ በታቀደ መልኩ በአቶ መለስ ቀጭን ትእዛዝና በአርከበ ቀጥታ መሪነት የተከናወነ ነበር። ይህ የውንብድና ስራ እኔ ከሞት ሰርዶ አይብቀል እንዳለችው አህያ የተፈጸመ መንግስታዊ ንቅዘት ነው። የከተማው ባዶ መሬት ሙሉ ለሙሉ በሚባል መልኩ ተዘርፉል፣ "እዚህ ቦታ ራቁቱን የተቀመጠ መሬት አለ" በሚል ጥቆማ የተሰረቀ... ይህን ተከትሎ አዲሳባ መሬት አልባ ሆናለች።

የአዲሳባ መሬት ወረራ የመጨረሻው ጫፍ ላይ የደረሰው አርከበ እቁባይ ስልጣኑን ለባላደራው ከማስረከቡ አስቀድሞ በነበሩት ወቅቶች ነበር። በፌደራል ፀረ ሙስና ኮሚሽን ተጠንቶ ይፉ በተደረገ ሰነድ እስከ 2003አ• ም• ድረስ ከ3•5 ሚሊዬን ካሬ ሜትር የሚደርስ የከተማዋ መሬት በወረራ ተዘርፉል። ይህም ወደ ገንዘብ ሲቀየር ከአስር ቢሊዬን ብር በላይ የህዝብ ገንዘብ ወደ ግለሰብ ኪስ ገብቷል።

ሌላው ቀርቶ ለአስር አመታት (1995 -2005 አ• ም•) ተዘጋጅቶ በትግበራ ላይ ያለው ማስተር ፕላን ላይ በፅኑ በእስራት ያስቀጣሉ ተብለው የተለዩት ተጣሱ፣... በማስተር ፕላኑ ላይ ለፓርኮችና አረንጓዴ ቦታዎች ተለይተው የተቀመጡ ቦታዎች አርከበና ቡድኖቹ ቆራርጠው ቸበቸቡ... ከእነዚህ ውስጥ በመገናኛ በሀይሌ ገ/ ስላሴ ቤትና እና ብሉ ቶፕ ሆቴል አጠገብ የሚገኘው ፣ ሲኤምሲ ስራ አመራር ኢንስትትዩት አጠገብ የሚገኙት ቦታዎች ይገኙበታል፣... በተለይ በቦሌ አካባቢ ለአረንጓዴ ብቻ ሳይሆን ለወጣቶች ማዘውተሪያ የተቀመጠ ቦታ ሳይቀር ተሸጠ።

ቀጥሎ የሚነሳው ነገር ይህንን አይን ያወጣ ወረራና ዝርፊያ በፍጥነት ሩጫ ህጋዊ በማድረግ ከተጠያቂነት መዳን ነው፣ ...ሩጫው አጭር ነው ፣ የአራት መቶ ሜትር ዱላ ቅብብሎሽ ።... ዱላዋ ደግሞ መመሪያ ናት...

መመሪያ ቁጥር አንድ!... ቁጥር ሁለት!... ቁጥር... ?

አለ አብዶ የመጀመሪያውን መቶ ሜትር በመሮጥና አዲስ ክብረወሰን በማስመዝገብ ለአርከበ አስረክቧል... አርከበ የቆየ ልምዱን አክሎበት ቀጣዩን መቶ ሜትር ክብረወሰን በማሻሻል ጭምር ለአልጋ ወራሹ ሚንስትር መኩሪያ ሀይሌ አስተላልፉል...ሚኒስትር መኩሪያ በኢህአድግ የአዲሱ አመራር ትውልድ ውስጥ ያለ ካድሬ ነው... በመተካካት ህግ መሰረት የቀጣዩን አጭር ሩጫ ከግብ ለማድረስ ተስፉ ከተጣለባቸው የለውጥ መሀንዲሶች አንዱ ነው...

ርግጥም ሩጫው ለሚኒስትር መኩሪያ ላይከብደው ይችላል...

እድሜ "ለመደገፍ መርሆ!"።

ኢህአድግ "የመተካካት መርሆ "ብቻ እንዳለው የሚቆጥሩ የዋሆች አሉ... ፓርቲው ነገሮችን አስተሳስሮ የሚያይ ነውና በተደራቢነት "የመደገፍ መርሆ "የሚባል ከሰገሌ ጀምሮ በስራ ላይ ያዋለው ውስጣዊ አሰራር አለው።... ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ካድሬው ከሚገመገምበት ቁልፍ ነጥቦች ዋነኛው " ጓዶችህን ምን ያህል ደግፈሀል ?፣ ለመደገፍ ያለህ ዝግጁነት እስከምን ደረጃ ነው?..." የሚሉ ሆነዋል።

የኢህአድግን "የመደገፍ መርሆ" እንደ "መረዳዳት" አድርጐ የሚቆጥር ካለም ለዳግም የዋህነት ተጋልጧል...በፓርቲው ቋንቋ ለመደገፍ ዝግጁ መሆን ማለት ቀይ መስመር ለዘለለ ጣልቃ -ገብነት ራስን ማሳመን ማለት ነው፣... መደገፍ ዳር ድንበርና ጣራ አያውቅም... ተጠያቂነት የለውም ።...ይህንን በተመለከተ በአቶ በረከት መፅሀፍ መቋጫ ወግ በሚለው ርእስ ስር በገፅ 312 ላይ "... ከፊት መስመር ገለል ብለን፣ከኃላና ከጐን ሆነን መደገፍ አለብን... " ተብሎ በነጠረ አማርኛ ተፅፉል...

እንደ ቭላድሚር ቭላድሚሮቪች ፑቲን !

(** እነ ግርማጺዮን አራት ኪሎ ኢህአድግ ቢሮ ተቀምጠው የአፉርን፣ ጋንቤላን፣ቤኒሻንጉልንና ሱማሊያ ክልሎችን እቅድ ያወጣሉ፣በጀት ይመድባሉ፣ ካቢኔ ይሾማሉ ፣ያባርራሉ። ... ለኢህአድግ ቢሮ የስራ አፈፃፀማቸውን ለማሳየት የሚያዘጋጁትን ሪፓርት እንደ እኔ ለማየት ያገጠመው ሰው በቀላሉ አንድ ነገር ይታዘባል : ለአብነት የሱማሊያ ክልል ሪፓርት ይህን ይመስላል:-ምዕራፍ አንድ: የሱማሊያ ክልላዊ መንግስት ከመደገፍ አኳያ ; ክፍል አንድ : የክልላዊ መንግስቱንና የሶህዴፓ ፓርቲ አመታዊ እቅድ ማውጣት ; ክፍል ሁለት : በጀት ማዘጋጀትና ማደላደል; ክፍል ሶስት : የአመራር ሀይል መመደብና ሽግሽግ ማድረግ ; ክፍል አራት : ልማታዊ ባለሀብቶችን መፍጠር ;ክፍል አምስት : ፀረ - ሰላሞችን ከመከላከል አንፃር የተሰጠ ድጋፍ ...

በግለሰብ ደረጃም የኢህአድግ መደጋገፍ አቅጣጫ ተመሳሳይ ነው... የፌዴራል ጉዳዬች ሚኒስትር ዶክተር ሽፈራው ከላይ አባይ ፀሀዬ ፣ ከጐን በሽማግሌው ስብሀት ነጋ ፣ከታች ደግሞ የህውሀት ነባር ታጋይ የነበረው መራሳ ይደግፉታል።... የመከላከያ ሚኒስትሩ ሲራጅ ፈርጌሳ ከላይ ጀነራል ሳሞራ፣ ከጐን ኩማ ደመቅሳ ይደግፉታል፣...የፍትህ ሚኒስትር የነበረው ብርሀን ሀይሉ በአቶ በረከት ስምኦን ይደገፉል...

ነገር ነገርን ይወልዳልና አንድ ጊዜ ጋዜጠኛ ሲሳይ አጌና የሚባልየግል ፕሬስ ባለቤት ለፍትህ ሚኒስቴር የጋዜጣ የፍቃድ ጥያቄ ያቀርባል፣ ሚኒስትር ብርሀን ምላሽ ከመስጠቱ በፊት ድጋፍ ፈልገ እኛ ጋር ይመጣል... አቶ በረከት እሳት ጐርሶ " ኢህአድግን ከቀበርክ በኃላ ለሾቪኒስቱ ፍቃድ መስጠት ትችላለህ ! " ይለዋል። ... ሽመልስ ከማል በበኩሉ ከቂሱ ዲያቆኑ እንደሚባለው በፕሬስ አማካኝነት ስለሚካሔድ ነውጥ (Conspiracy) ታሪክ እያጣቀሰ አስተማረን... ሽመልስ የወጣለት አንባቢ ነው፣ ከእሱ ጋር ስቀመጥ መፅሀፍ እንደማንበብ ይሰማኝ ነበር... እውቀቱ የትየለሌ ነው...

እውቀትና ምግባር ካልተገናኙ ግማሽ ሰው ያደርጋል።

የሁለቱም ምላሽ ያልተዋጠለት ሚኒስትር ብርሀን የጋዜጠኛው ጥያቄ ህገ -መንግስቱን የተከተለና ለመከልከል የሚያስችልህጋዊ መሰረት ማጣቱን በጥሞና አስረዳ... የበረከት ረጅም አፍንጫ ለብቻው ፍም መስሎ እንደ እባብ ተንቀሳቀሰ :

" ስማ! ብርሀን ! ድርጅቱ ስላንተ ብነግረው አልሰማኝም!... አንተ መደገፍ የማትፈልግና እንዳፈተተህ የምትሔድ ሰው ነህ!... ጥቂት ጊዜ ስጠኝና የማደርገውን አሳይሀለሁ " አለው። ... አቶ በረከት የጉዳዩን አንገብጋቢነት በማየት ጊዜ መስጠት አልፈለገም፣... ሁላችንም በተቀመጥንበት ለንግድ ሚኒስትሩ ግርማ ብሩ ደወለለት... ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ለአንድ ሽብርተኛ የንግድ ፍቃድ መስጠቱን ነገረው።... ሚኒስትር ግርማ ኢንፎርሜሽን ስለሌለው ይቅርታ ጠይቆ ቀጣይ ምን ማድረግ እንዳለበት ድጋፍ ጠየቀ... በረከት መሻሪያ ደብዳቤ እንዲፅፍ ቃል በቃል አዛፈው... ሚኒስትር ግርማ ለተደረገለት ድጋፍ አመስግኖ ወደ ተለመደ አድርባይ ስራው ገባ...

የአድርባዬች ንጉስ!!

ሽመልስ ደግሞ ደስታ የሚባለውን የብሮድካስቲንግ ሀላፊ በአስቸኳይ ቢሮው እንዲመጣ አዘዘ...

ድጋፍ ለመስጠት።

ሾቪኒስቱ ጋዜጠኛ ሀገር ጥሎ ወጣ... ኢሳት በሚባለው የሚዲያ ተቋም ነበልባል እሳት ሆነ !... በሀገሩ ላይ ብዕርና ወረቀት አዋዶ ጆሮ ለመሆን ሲያስብ፣ ...በሀገረ አሜሪካ አይንም፣ጆሮም፣ ልብም ፣ኩላሊትም ሆነ... በሽኩቻና እውቀት ማነስ ቁልቁል እየተምዘገዘገ ያለውን የዲያስፖራ ፓለቲካ ማረቅ የዘወትር ስራው ሆነ።

ድርጅቱ ከዚህ አለም በሞት ተለየ !... ሚኒስትር ብርሀን በብርሀን ፍጥነትሻንጣውን ሸክፎ ፍትህ ሚኒስቴርን ተሰናበተ!***)

ወደ ተነሳንበት እንመለስ...

መኩሪያ ሀይሌ ሚኒስትር ከመሆኑ በፊት የደቡብ ክልላዊ መንግስት ንግድና ኢንዱስትሪ ሀላፊ ነበር... በዛን ወቅት ከአዋሳ እየተመላለሰ አዲሳባ ላይ የሀብታሞች ጉዳይ አስፈፃሚ ይሆናል፣... በተለይም በአንድ ወቅት ቦሌ መንገድ ደንበል ሲቲ አጠገብ የሚገኝ ቦታ ላይ የይገባኛል ጭቅጭቅ ይነሳል፣ ጥያቄውን ካነሱት ግለሰብ አንደኛው ከእሱ ጋር የጥቅም ትስስር ያላቸው የሀገሩ ልጅ ነበሩ።... ሰውየው ጉዳዩን ይዞ ወደ አዋሳ ያዘግማል... አቶ መኩሪያ ከአርከበ ጋር በመነጋገር ጉዳዩን ያስፈፅማል።... በተቃራኒ ወገን ተሰልፎ የነበረው የዞን አራት ኢህአድግ የካድሬዎች አለቃ ገ/ እ (በአሁን ሰአት የከተማዋ ባህልና ቱሪዝም ሀላፊ) ለኢህአድግ ቢሮ ያስተላልፉል።...

አርከበ የክፉ ቀን መምጣቱን ሲያረጋግጥ ውለታውን ለመቀበል ለትልቅ ቦታ ያጨዋል... ለአዲሳባ ስራ አስኪያጅነት... ወደ ላይ ድጋፍ መስጠት በሚለው መርህ መሰረት መንግስታዊ አለቃው ለሆነው ዶክተር ካሱ ኢላላ ትእዛዝ ያስተላልፉል (ዶክተር ካሱ ለህውሀት ሁለተኛ ሰው አለቃ ሲሆን?... ቢልት!!)

... ጉራጌው ካሱ ፣ጉራጌው መኩሪያን ወደ አዲሳባ እንዲያመጣ ለሀይለማርያምና ለድርጅቱ ፕሮፓጋዛል ያቀርባል... የተፈራው በረከት

ነው...እንደተጠበቀው የስምኦን ልጅ የብርጭቆ ማእበል አስነሳ፣..." ለዚህ አይን ያወጣ ሌባ ዝረፍ ብለን አዲሳባ አንሰጠውም " ብሎ ደነፉ ...

የቁራ ጩኸት!

(*** በረከት ስምኦን መኩሪያ ሀይሌንና ግርማ ብሩን " ውስጣቸው ኢህአድግ ሳይሆን ድርጅቱን የሚያታልሉ ሞላጫ ሳሙናዎች " እያለ ይጠራቸዋል።)

በመርህ መመራት ያቆመው ድርጅት የመኩሪያን የትላንት ውለታ መርሳት አልፈለገም... መኩሪያ ለድርጅቱ ከፍተኛ ጭንቀት ፈጥሮ የነበረውን የጉራጌ መራሽ አብዬት እንዲቀለበስ አድርጓል።

መኩሪያ ስራ አስኪያጅ ሆነ!!

(*** የአዲሳባ ስራ አስኪያጅነት ሙያ ተኮር በመሆኑ አለም አቀፍ ማስታወቂያ ወጥቶ ከፍተኛ ፕሮፌሽናሎችን በማወዳደር ይፈፀም የሚል አስተያየት አቶ መለስ ጋር እስኪደርስ ድረስ ተቀባይነት አግኝቶ ነበር። ... አቶ መለስ ይህን አስተያየት እንደሰማ በቁጣ " የአዲሳባን ስራ አስኪያጅነትን አሳልፎ መስጠት ማለት ወደ ጥልቅ ጉድጓድ ኢህአድግን ከመወርወር አይተናነስም " አለ።...

ርግጥም አቶ መለስ እንዳለው የአዲሳባ ስራ አስኪያጅነት ስልጣን ከከንቲባው በላይ ነው።... የከተማዋ የዝርፊያ ማእከል የሆኑት እንደ መሬት፣ መንገድ፣ውሀ... በቁጥጥር ስር የሚውሉት በስራ አስኪያጁ ነው።...ኢህአድግ ቢሮ ከንቲባ ማን ይሁን ከሚለው በላይ የሚያጨቃጭቀው ስራ አስከያጅ መምረጥ ላይ ነበር።... አቶ አርከበ በለስ ቀንቶት በእሱ ዘመን የህውሀት ካድሬውን_____ አስመደበ፣ ቀጥሎ መኩሪያ ሀይሌን፣ በመጨረሻም የቅርብ ዘመዱን ሀይሌ ፍስሀ !

በዳግም ምርጫ 2000 አ• ም• ኢህአድግ መዲናይቱን በተቆጣጠረ ወቅት አቶ በረከት ቢሮ ውስጥ እኔ፣ህላዌ፣ካሚል፣ፀጋዬና ፍሬህይወት ተሰብስበን ከንቲባ፣ ስራ አስኪያጅ ፣የካቢኔ አባል አየመለመልን ነበር... ስብሰባው ሳይጠናቀቅ ከቤተ መንግስት የአቶ መለስ ስልክ ተንጫረረ... አርከበ ለስራ አስኪያጅ የሚሆን ይዞ እየመጣ ስለሆነ ተቀበሉት የሚል አጭር ትእዛዝ ሰጠን።... ስልኩ ሲዘጋ: -

ህላዌ " Well come! ሀይሌ ፍስሀ፣...Well come !! መኩሪያ ሀይሌ " ብሎ በዜማ ቅላጼው ዘፈነ...

ካሚል ከጣራ በላይ ሳቀ!...

ፀጋዬ አንገቱን ነቀነቀ ...

እኔና ፍሬህይወት በአይናችን አወራን... ስብሰባውን ጨርሰን ስንወጣ ፍሬህይወት የምትፅፈውን ግጥም ለማንበብ ጓጓሁ!

በረከት እንደተለመደው " ሀይሌም ሆነ መኩሪያ ወደ አዲሳባ የሚመጡት እኔና አርከበ ቦታ ስንቀያየር ነው " በማለት ጥርሱን ነከሰ... አፍንጫውን ፈተገ።

ወቅቱ ለአርከበ ወሳኝ ነውና በድል አድራጊነት ሰሜት የምንግዜም ባላንጣው ቢሮ ተገኘ፣...ጊዜ ሳያጠፉ " መለስ ስራ አስኪያጅ የሚሆኑ ሰወች መልምል ባለኝ መሰረት ሁለት ጠንካራ ካድሬዎች ይዜ መጥቻለሁ... የመጀመሪያ ምርጫዬ መኩሪያ ሀይሌ ነው... የደኢህዴን ሊቀመንበሩ ሀይለማርያምን አስተያየት ጠይቄው ደቡብን ባዶ ተደርግብናለህ እንጂ ሁነኛ ሰው

መርጠሀል ብሎኛል ፣...በሁለተኛ ደረጃ ሀይሌ ፍስሀ ቢሆን የሚል አስተያየት አለኝ... የህውሀት ቢሮ ለመስጠት አንገራግረው ነበር ግን አዲሳባ ላይ ጠንካራ ሰው መመደብ ወሳኝ መሆኑን ነግሬያቸው ፍቃደኛ ሆነዋል።... እናም መኩሪያ የመጀመሪያ ምርጫዬ ቢሆንም ደኢህዴን ካለበት የሰው ሀይል እጥረት አኳያ ሀይሌ ፍስሀ ቢሆን ይሻላል..." አለ።

የፍርዬ ቁንጥጫ አጥንቴን ዘልቆ ተሰማኝ።

መኩሪያ ሀይሌ ስራ አስከአያጅ ሆነ!...

በረከትና አርከበ ቦታ ሳይቀያየሩ ቀረ።

መኩሪያ ሚኒስትር ሲሆን ደግሞ በቅብብሎሽ ህግ መሰረት ለሀይሌ ፍስሀ አወረሰው !***)

***

ሚኒስትር መኩሪያና ሀይሌ ፍስሀ የቀድሞውን ምድብ ከንቲባ አርከበን ለመታደግ መመሪያ ቁጥር ሶስት እንደሚያወጡ የሚያጠራጥር አልነበረም...መመሪያ ቁጥር ሶስት መውጣት ብቻውን ግን አቶ አርከበን ከተጠያቂነት አይድንም...በከተማዋ ማስተር ፕላን ላይ በምንም መልኩ ድርድር የማይካሔድባቸውና በወንጀል የሚያስቀጡ አረንጓዴ ቦታዎችበእሱ ቀጥተኛ ትእዛዝ ተወረዋል። በመሆኑም መመሪያ ቁጥር ሶስት ብቻ ሳይሆን የማስተር ፕላን ክለሳ ተቀናጅተው መፈፀም ይኖርባቸዋል... መመሪያው ወጥቶ ማስተር ፕላኑ ባይሻሻል ከወንጀለኝነት አያድንም።

ሚኒስትር መኩሪያና ስራ አስኪያጅ ሀይሌ ፍስሀ ተቀናጅተው ህገ ወጦችን ህጋዊ የሚያደርግ መመሪያ በ2003 አ• ም• አወጡ... በመመሪያው መሰረት እስከ ህዳር 2004 አ• ም• ድረስ መሬት በህገ ወጥ መንገድ የያዙ ባለይዞታዎች ህጋዊ እንደሚሆኑ ፣በአምስት አመት ውስጥ ህገ ወጦችን ህጋዊ አድርገው በማጠናቀቅ የህገወጥነት አጀንዳ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንደሚዘጋ ... በአዋጅ 47/67 መሰረት የይዞታ ማረጋገጫ ሳይሰጣቸው የነበሩትን በሙሉ እንደሚያገኙ አበሰሩ። ...በተደራቢነት የማስተር ፕላን ማሻሻያ እንደሚደረግ ይፋ አደረጉ።

ሚኒስትር መኩሪያ በወርሀ የካቲት 2005 አ• ም• ከሪፓርተር ጋዜጣ ጋር ባደረገው ቆይታ የሚከተለውን ገለፀ : -

" ... በ*2005 አ• ም• ለአስር አመታት የተተገበረው ማስተር ፕላን ይጠናቀቃል። ከሚቀጥለው አመት ጀምሮ አየተሰራ ያለው ማስተር ፕላን ተግባራዊ ይደረጋል። በዚህ ረገድ ለአረንጓዴ አካባቢዎች አዲሱ ፕላን ልዩ ትኩረት ይሰጣል። ከዚህ ጋር በተያያዘ በ2003 አ• ም• የወጣው ህገ ወጦችን ህጋዊ የማድረግ ስራ በአምስት አመት ውስጥ ይጠናቀቃል። ከዚህ በኃላ ህገ ወጥ ግንባታ ከተካሄደ አካባቢውን የሚያስተዳድረውም ህገ ወጥ የገነባውም ተጠያቂ የሚሆኑበት ሰርአት ይዘረጋል። በመሆኑም ይህንን ለማስፈፀም በክህሎቱና አቅሙ የፓሊስ ቁመና ያለው ደንብ ማስከበር ጽ/ ቤት እንዲደራጅ ይደረጋል።*"

በፕሬዝዳንት አሊ ፣ በከንቲባ አርከበ እና ሚኒስትር መኩሪያ መግለጫዎች መካከል ልዩነት የለም።... ልዩነቱ እንደ ኢትዩጲያ ድርቅ ዘመኑ መለዋወጡ ብቻ ነው።... ርግጥ ሚኒስትር መኩሪያ በመግለጫው ማጠናቀቂያ ላይ ከኢኮኖሚስቱነቱ በላይ ሳይኮሎጂስትነቱ አገርሽቶበት :

"... በህገ ወጥ መንገድ መሬት ያገኙ ሰወች በመንግስት በኩል ተጠቅመዋል የሚል እምነት የለንም። ህገ ወጥነት የሞራል ቅጣት አለው። ህገ ወጥነት የስብእና መጓደል ነው። ሀፍረት ነው። አጥፍተው ህብረተሰቡና መንግስት ይቅርታ እያደረገላቸው ነው " የሚል አስቂኝ ምላሽ ሰጥቷል።

ግራም ነፈሰ ቀኝ መመሪያ ቁጥር ሶስትና ማስተር ፕላን ማሻሻያው ከንቲባ አርከበን ነፃ አውጥተዋል... ከእንግዲህ ራሱን ከፊት ለፊት መስመር አግልሎ ከጮንና ከኃላ ይደግፉል።

***

ከዚህ ቀጥሎ ሊነሳ የሚችለው መመሪያ ቁጥር አራት ሊወጣ ይችላል ወይ የሚለው ይሆናል።... መመሪያ ቁጥር አራት የመታወጅ እድሉ ጠባብ ነው...የማይሆንበት ምክንያት የአስተዳደሩ የሌብነት ቅብብሎሽ ሰለተበጣጠሰ ሳይሆን የአዲሳባ ባዶ መሬት ሙሉ ለሙሉ በሚባል መልኩ በመዘረፉ ነው።

በመሆኑም የጥፉቱ ቅብብሎሹ መልኩን በመቀየር በሌላ መልኩ የሚገለፅ ይሆናል...ፍንጮችም እየታዩ ነው..."ከተማዋን መልሶ ማልማት" የሚል ስያሜ ተሰጥቷቸዋል...

የበሰበሰች ከተማ !

አዲሳባ ከአቅሞ በላይ 800 ሺህ ቤቶችን ተሸክማለች ፣ከእነዚህ ውስጥ 80 በመቶ የበሰበሰ ነው።... እነዚህ ቤቶች አንደሚፈርሱ ሚኒስትር መኩሪያ የመደገፍ መርሆን ተጠቅሞ ይፉ አድርጓል።... በመሆኑም የዝርፊያ ቅብብሎሹ በአዲስ መሬት ላይ የሚፈፀም ሳይሆን ነባር ቦታዎችን በማስነሳት ሒደት በሚፈፀም ሌብነት ይሆናል።... ለተነሺዎች ከአቅም በላይ ካሳ ለመክፈል ከመንግስት ካዝና በሚወጣ ገንዘብና አካባቢ በመለየት የማልማት ጥያቄ ከሚያቀርቡ ሰወች የሚገኝ ምልጃ ዋነኞቹ ይሆናሉ።

በተጨማሪም በጨረታ ቤትነት የተሰሩት አብዛኞቹ ቤቶች ደረጃቸውን ያልጠበቁ ናቸው... መፍረሳቸው አይቀርም።... ቤቶቹ ህጋዊነት ስለተሰጣቸው ሲፈርሱ ዳጮስ ያለ የህዝብ ገንዘብ ይወስደሉ... ከፊሉን ለአፍራሾቹ ይሰጣሉ...

አዙሪቱ ይቀጥላል...

***

ክፍል ሁለት : የሐማውያን ዘመን

"... ታሪክ ያሳየን ምስለኔ ሲዘርፍና ሲበዘብዝ ነው ! "

ዶክተር ሀይሉ አርአያ

(ዘመን መፅሔት)

ምእራፍ አንድ : ከተማ ቀመስ

ምእራፍ ሁለት : ቆርኪው ሲላጥ

ምእራፍ ሶስት : ጉንጭ አልፉው ግምገማ

ምእራፍ አራት : የጉብልስ ትእዛዛት ማጠንጠኛ "The Big Lie theory"

*የዛፍ ላይ እባብ (Boomslang)

ምእራፍ :

የጉብልስ ትእዛዛት ማጠንጠኛ: "The Big Lie Theory "

" Make the lie big,make it simple,keep saying it, and eventually they will believe it "

Joseph Goebbeles

"ከተማ ቀመስ"

በረከት ስምኦን በሁለት ምርጫዎች ወግ መጽሀፍ በገጽ 44 ላይ የሚከተለውን

ጽፎ እናገኛለን ፡

"... የከተሞችን አመራር የመቀየር ሰራ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሞከረው በአዲስ አበባ ከተማ ነበር። ከተማውን ሲያስተዳድር የቆየው አመራር እንዲቀየር ከተደረገ በኃላ ከየክልሉ ከተማ ቀመስ ሰው እየተፈለገ ተመልምሎ አዲስ አበባ እንዲገባ ተደረገ... እነዚህ ሰዎች የአገሪቱን ርዕሰ ከተማ እንዲመሩ የተመደቡት ከተሞችን እንደገጠር ሳይሆን አንደ ከተማ ለመምራት ይቻል ዘንድ ነበር።" ይላል።

የበረከት ከተማ ቀመሶች ምን እንደሚመስሉ ለማረጋገጥ አንዳንዶቹን በጨረፍታ እናንሳና እንመልከት:

***

ከአርከበ ካቢኔ አባላት እንጀምር።

ሲቪል ሰርቪሱን ፣ትምህርት ቢሮንና አጠቃላይ አቅም ግንባታን እንዲመራ የተመደበው ካድሬ ተክለብርሀን ይባላል። አርከበ ከትግራይ ይዞ ከመጣቸው የህውሀት ቁልፍ ካድሬዎች አንዱ ነው። ይህ ካድሬ በትምህርት ዝግጅቱ ከሁለተኛ ደረጃ አልዘለለም። ለረጅም አመታት የሰራው በትግራይ ገጠራማ አካባቢዎች አባላት የማደራጀት ስራ ሲሆን አዲሳባን በጣት ለሚቆጠሩ ቀናት ለህክምና ከመምጣት ውጪ አያውቃትም። በትግራይም ቢሆን የትኛውንም ከተማ መርቶ አያውቅም። በእንቅርት ላይ እንዲሉ በትጥቅ ትግሉ ወቅት ጉዳት ደርሶበታል። በዚህም ምክንያት ጀሮው ሙሉ ለሙሉ አይሰማም። ይህን ተከትሎ ከተክለብርሀን ጋር አንድ አይነት ነገር ማውራት በፍጹም አይቻልም። ግምገማው ስለ ትምህርት ጥራት ችግሮች ሆኖ እሱ ስለ አነስተኛና ጥቃቅን ሊያወራ ይችላል።

ከእለታት በአንዱ ቀን የሀገሩ ልጅና የትምህርት ቢሮን የለውጥ ኮሚቴ የመራው ገ/ ተንሳይ አፍ አውጥቶ " ተ/ ብርሀን አንተ እኮ ደንቆሮ ነህ! ከአንተ ጋር እንዴት እንደምሰራ አይገባኝም? " ብሎ ተናገረ። ተክለብርሀን በበኩሉ ምን አንዳለው ሳይገባው " ገ/ ተንሳይ ልክ ነው። ለመምህራን ስልጠና መስጠት አለብን " የሚል ምላሽ ሰጠ። ገብረተንሳይ ከማዘጋጃ ቤት ጣራ በላይ ሳቀበት። እንደሌሎቻችን መናደዱን መቆጣጠር ያቃተው ታደሰ የሚባል የአዲስ ከተማ ካድሬ " ገብረተንሳይ! እንዳንተ ቆዳውን እየቀያየረ ሁለት ስርአት አላገለገለም። መስማት የተሳነው አንተ ስትመራው የነበረውን አስከፊ ስርአት ሲታገል ነው።" የሚል ብሽቀት ያዘለ መልስ ሰጠው..... ብአዴኑ ታደሰ።

የተክለብርሀንን ክፍተት ለመሙላት አርከበ መላ ዘየደ። አማረ ሺበሺ የሚባል የተጨበጨበለት ምሁር በምክትል ቢሮ ሀላፊነት መደበለት። አማረ ነባር የአስተዳደሩ ሰራተኛ ሲሆን ቀንደኛ የኢሰፓ ካድሬ የነበረ። አማረ ለኢህአድግ ጫፍ የወጣ ንቀት የለውና አርከበን " ያልተገራ ፈረስ " ብሎ ይጠራው ነበር። እናም የመዲናይቱ ሲቪል ሰርቪስና የትምህርት ተቋማት የተመሩት በረከት ከተማ ቀመስ ባላቸው መጤዎች ሳይሆን ለኢህአድግ የመረረ ጥላቻ በነበራቸው የኢሰፓ ካድሬ በሆኑት አማረ ሺበሺና አበባየሁ (የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽነር) ነበር። እነዚህ ምሁራን ሲቻላቸው በሀገሪቱ ህግ መሰረት ትክክለኛ ስራ ሲሰሩ፣ ጫናውን መቋቋም ሲያቅታቸው ደግሞ በግል ፕሬሶች ኢህአድግንና አርከበን

ሲያጋልጡ ሰነበቱ። ምርጫ 97 ደረሰና ከነዋሪው ጋር ኢህአድግን ገለባበጡት።

በአንድ ነገር ላይ ስለተክለብርሀን ምስክር ሰጥቼ ልሰናበተው። ተክለብርሀን ጨዋ ነበር። ወደ አዲሳባ ሲመጣ ባዶ እጁን ነበር። ወደ ትግራይ ሲመለስም ቅያሪ ኮት እንኳን አልነበረውም። መቀሌ ችግሩን ተረድታ የድርጅት ስራ ብቻ እንዲሰራ አድርጋዋለች። ውሎው ቀያዬቹ የመቀሌ አዳራሾች ሆነዋል።

***

ወደ ጨፌ የኦሮሚያ ምክር ቤት አዳራሽ ተመልሰናል። የጨለማው ዘመን መሪ ወደ ነበረው አሊ አብዶ ግምገማ። ሀብቱ የሚባል የአዲሳባ የትምህርት ቢሮ ሀላፊና የካቢኔ አባል አሊን አንድ ጥያቄ ጠየቀው :

" ከፉይናንስና ኢኮኖሚ ቢሮ ሀላፊዋ ገነት አበራ ጋር ያለህ ግንኙነት እስከምን ድረስ ነው ? " በማለት

የአሊ አንቱና ተነካ። ያልተጠየቀውን ዘባረቀ:

" ከወይዘሮ ገነት ጋር ምንም ግንኙነት የለንም። ባይሆን ተፈራ ዋልዋን ጠይቁት። እኔም የተረከብኳት ከእሱ ነው " ብሎ ተናገረ። ሴትየዋ የኢህአድግ አባል ስላልነበረች በግምገማው አልተገኘችም። ስጋዋ ከመቦጨቅ ግን አልዳነም። የከተማውን ፉይናንስ በተለይም የበጀት ዝግጅትና ገቢ መቀመቅ የከተተችው እሷ መሆኗ መግባባት ላይ ተደረሰ። ግን ደግሞ እንደዚህ ከፍተኛ የብቃት ማነስ ችግር እንዳለባት እየታወቀ እንዴት ከተፈራ ዘመን አስከ አሊ አብዶ አገለገለች የሚለው የካድሬው ያልተገለፀ ሀሜት ሆነ።

በኢህአድግ ቤት መኖር ሁሌም ከኃላ እንደ ጅራት የሚጐተት ጉድ አለውና ቀኑን ጠብቆ ብቅ አለ። ወይዘሮ ገነት አበራ የአዲሱ ከንቲባ አርከበ እቁባይ የፉይናንስና ኢኮኖሚ ቢሮ ሀላፊ ሆና ካቢኔውን ተቀላቀለች። ታሪክም ራሱን ደገመ። መጀመሪያ አሳዛኝ ቀጥሎ ቧልት በሚመስል መንገድ።

ብዙዎች በአርከበ ጊዜ የነበረውን ማዘጋጃ ቤት ባለ ሶስት በር ያለው "አዳራሽ "(ስያሜው ተቀይሯል) አድርገው ይቆጥሩት ነበር። ታዲያ ወደ እልፍኙ ለመግባት የበሩን ቁልፎች የያዙት ሰዎች ሶስት ነበሩ። ያለእነሱ የሚሞከር አልነበረም :- አማረ ሺበሺ፣ አበባየሁና ገነት አበራ።

አርከበ መቼም ከኃላ የሚሰሩ ሞተሮችን መምረጥ ይችልበታል። እናም ለወይዘሮ ገነት ሞክሼዋን (ገነት ትንሿ) የምትባል ምክትልና ሁለት ኤፍሬም የሚባሉ ወጣት ምሁራን በገቢዎች ኤጀንሲ ሀላፊነት መደበ።

ገነት ትንሿ ትልቅ እንዝርት ነበረች። ስለእውነትም ክብር የሚገባትና አርአያ የሆነች የጽናት ተምሳሌት። ትንሿ ወይዘሮ ገነት በጽዳት ሰራተኝነት ተቀጥራ አስተዳደሩን ተቀላቀለች። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን እንዳጠናቀቀች ወደ ተላላኪነት አደገች። ቤተሰብ እየመራች ወደ ኮሌጅ ሄደች... እነሆ ትምህርቷን አጠናቃ የኢኮኖሚና ፉይናንስ ቢሮ ጭንቅላት ሆነች። ከእሷ ጋር በቅርብ የሰሩ ሰዎች "ትንሿ ሰርቨር"(" Mini Server")ብለው ይጠሯታል።

የገቢዎች ሀላፊ የነበሩት ወጣቶቹ ኤፍሬሞች ደግሞ ለወይዘሮ ገነት አበራ አንደኛው የደም ስር ሌላኛው ደግሞ ደም ነበሩ። ... ለነገሩ ጭንቅላት፣ የደም ስርና ደም የተቀጠለላት ወ/ሮ ገነት ብቻ ሳትሆን አርከበና አዲስ አበባ ጭምር ነበሩ።

እንግዲህ በእነዚህ ሰዎች ውስጥ በረከት " ከየክልሉ ከተማ ቀመስ ፊልገን አመጣን " ብሎ ያላቸው ካድሬዎች እንደሌሉ ልብ ይሏል። ይህ ቦታ የፓርቲ ታጊላን ሳይሆን የከተማን ፓለቲካል ኢኮኖሚን መረዳትና መተንተን ይጠይቃልና ሞፈር ዘመቶቹ ካድሬዎች አለመኖራቸው የሚጠበቅ ነበር።

ምርጫ 97 መጣና እነ ኤፍሬም አሰላለፉቸውን አስተካከሉ። ትልቁ ኤፍሬም ከምርጫው ጋር ተያይዞ ክትትል አየተደረገበት እንደሆነ ከውስጥ መረጃ እንዳገኘ ይታመናል...አገር ጥሎ ወደ አሜሪካን ሀገር ተሰደደ።

ከእለታት በአንዱ ቀን በሜሪላንድ ግዛት በምትገኝ ሲልቨር ስፕሪንግ ከተማ ስታር ባክስ ውስጥ ቡና ሲጠጣ ከርቀት አየሁት። የተስማማው አይመስልም። እንኳን እሱ አዲሳባም ቅር ብሏታል... ተስፉ ያደረገችውን የደም ስሯን አጥታለች።

***

አባዱላና ጁነዲን...

ሁለቱ የኦህዴድ ዝሆኖች አንድ ሰሞን ፍቅራቸው ጣራ ነክሶ ነበር። የኦህዴድ ካድሬም የተቀናጁበትን ሁኔታ " አርሰናል" በሚል አንዲት ቃል ገለፀው። ወቅቱ በእንግሊዝ ፕሪምየር ሊግ የአርሰን ቬንገሩ አርሰናል ኮከብነቱን የተቆናጠጠበት ነበር። ታዲያ ይሄ ከአባዱላና ጁነዲን ጋር ምን አያያዘው ? ነገሩ እንዲህ ነው :

የኦህዴድ ካድሬዎች አንድ ሰው ለትልቅ ስልጣን ታጭቶ ከሆነ " አርሴናል ነው እንዴ ? " ብለው ይጠይቃሉ። ሌላ እንዳይመስላችሁ " የአርሲ ልጅ ነወይ ? " ብለው እየጠየቁ ነው። ትግራይ ላይ የአድዋ ልጆች እንደሚባለው። ልምድ በመውሰድ ተወዳዳሪ የሌላቸው አባዱላና ጁነዲን አድዋን ጦትተው ኦሮሚያ ላይ አመጧት። የአርሲ ልጆች ሰልጣኑን ተቆጣጠሩት። አርሲ አድዋና አርሴናል ሆነች።

በዚህ ምክንያት ነበር እነ ድሪባ በአርከበ ካቢኔ ውስጥ ለመቀላቀል ከአርሲ የመጡት። ድሪባ ከአንዲት የአርሲ ወረዳ አመራርነት ተነስቶ የከተማ ልማት ጥልቅ እውቀት የሚጠይቀው የንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ሀላፊ ሆነ። የሚይዘው የሚጨብጠው ጠፉው። የከተማው ጥቃቅንና አነስተኛ ልማት ወደ ኃላ ሲጦተት የተመለከተው አቶ መለስ አርከበንና ካቢኔውን ጠርቶ :

" *አርከበ! ጣድ ያልተባልከውን ዘጠኝ ድስት ጣድክ። ትክክለኛ አማሳይና ማመሲያ ሳታዘጋጅ አጦረናኸው* " ብሎ ተቆጣው።

ከአማሳዬቹ አንዱ ድሪባ ነበር።

የአቶ መለስ መልእክት የገባው አርከበ እንደ ሌሎቹ ሁሉ ለንግድና ኢንዱስትሪ ከጀርባ ታኮ ማስቀመጥ ጊዜ የማይሰጠው መሆኑን ተገነዘበ። በከፍተኛ ሙያተኝነቱ የሚታወቀው ግን ደግሞ የቀድሞ ስርአት ንክኪና ለኢህአድግ ጥላቻ እንዳለው በየጊዜው የሚነገርለት አቶ ዩሀንስ የሚባል ትልቅ ሰው ተገኘ። በምክትልነት ተመደበ። ከክፍለ ከተማ እየተተወረወረ እንዲያግዘው ደግሞ ትንታግ የሆነና የፓለቲካ ብቃቱ የት ያደርሰዋል የተባለ ሚፍታህ አብዶ የሚባል ካድሬ ተጨመረለት። የድሪባ ስራ መቀስ እየተሰጠው ሪባን ወደ መቁረጥ ተሸጋገረ።

የበረከት ከተማ ቀመሶች ከላይ ባለው ካቢኔ ደረጃ ይህን ይመስላሉ። ወደ ክፍለ ከተማ ሲወረድ ደግሞ ለመጻፍ እንኳን ይዘገንናል። ታሪክ ነውና ምን ይደረጋል። ተዛብቶ በተጻፈበት ሁኔታ እውነቱን አለመግለጽ ደግሞ ስህተቱ እየተደጋገመ ተነግሮ እንደ እውነት ይቆጠራል... ሀገሪቷ እየተመራች ያለችው በጆሴፍ ጐብልስ ሀልዩት ስለሆነ።

***

አዲሳባ በአስር ክፍለ ከተማ የተከፈለች ሲሆን የአራቱ ክፍለ ከተማ ከንቲባዎች አርከበ ከትግራይ ይዞአቸው የመጣው የህውሀት ካድሬዎች ነበሩ ...ቂርቆስ አተይ (በአሁን ሰአት የኤፈርት ማርኬቲንግ ዴሬክተር) ፣ የካ ግርማጺዮን (በአሁን ሰአት የአፋር፣ጋምቤላ፣ቤኒሻንጉል፣ሱማሌ የበላይ ጠባቂ) ፣ ላፍቶ ሀይሌ ፍስሀ (በአሁን ሰአት የአዲሳባ ስራ አስኪያጅ) ፣ ቦሌ ሀ/ ስላሴ(የትግራይ ዞን አስተዳዳሪ) ። ከንቲባ ባልሆኑባቸው ክ/ ተሞች ደግሞ ምክትል ነበሩ... ኮልፌ ነጋ በርሄ (የኢህአድግ ስልጠና ማእከል)፣አራዳ መውጫ (ስራና ከተማ ልማት) ፣አዲስ ከተማ ታደለ(ፓስታ ድርጅት ስራ አስኪያጅ) ፣ቦሌ ገ/ ተንሳይ (ስራና ከተማ ልማት)፣ ጉለሌ ከበደ ብሩ(ስራና ከተማ ልማት) ...

ሁሉም የራሳቸው አሳፋሪ ታሪክ አላቸውና ጊዜውን ጠብቀው ይመጣሉ።

እንደ እውነቱ ከሆነ የኦህዴድ ከተማ ቀመሶችን ለመግለጽ ያሳፍራል...

ከአርሲ ገጠር መጥቶ የላፍቶ ክ/ ከተማ አፍና ጆሮ እንዲሆን የተመደበው ካድሬ በመጣ በሁለት ወሩ ስራውን አልቻልኩትም በማለት ወደ መጣበት ተመለሰ። ልደታ ሲቪል ሰርቪሱንና መምህራንን ይመራል ተብሎ ከአርሲ የተመደበው ካድሬ (ከበደ ይባላል) አንድም ቀን ሰራተኛና መምህራን ሳይሰበስብ ዘመኑ አለቀ... "ገና ሳያቸው ያስፈሩኛ "ብሎ።

ብአዴንም ተመሳሳይ ነበር... " ጋንጃ ጋንጃውን " የሚለው ወግ ከገጠራማው የአማራ ክልል የመጣው ታረቀኝ ታሪክ ነው። ህላዌ "ፈላስፉው " ብሎ የሚጠራው የአቃቂ ምክትል ከንቲባ ጫኔ ይባላል ... ርግጥም ጫኔ የታላቁ ፈላስፉ ሲስሮ ደቀመዝሙር ነበር... ምንም እንኳን ደግና ጥሩ ሰው ቢሆንም።

ቆርኪው ሲላጥ

አቶ በረከት በሁለት ምርጫዎች ወግ መጽሀፉ ምእራፍ አንድ ማሚሻ ወግ በሚለው ረእስ ስር :

"... **አዲሱ የአዲሳባ አመራር በከፍተኛ ተነሳሽነት ስራ በጀመረ ማግስት በብዙ መስኮች የቆየውን አዝጋሚ አካሄድና አመራር የሚቀይር በኢትዬጲያ አዲስ የከተሞች እድገት ምእራፍ መከፈቱን የሚያበስር ሰፊ እንቅስቃሴ አቀጣጠለ። ነባሩን የሰው ሀይል በተለይ ሲቪል ሰርቪሱን በአጭር ጊዜ ገምግሞ ግልብጥብጡን አወጣው። በአዲስ አበባ የለውጥ መንፈስ ብቻ ሳይሆን ተጨባጭ የለውጥ መስፉፉት ታየ። በዚህም የአዲስ አበባ ትንሳኤ ተበሰረ።**" በማለት ይገልጻል።

አቶ በረከት በዚህ ጽሁፉ የአዲሳባን ቢሮክራሲ በመገምገምና በማስተካከል የተጀመረው ለውጥ ለትንሳኤ ብስራት መነሻ እንደሆነ ይነግረናል። ማን ያርዳ የቀበረ ነውና በወቅቱ የነበረውን እውነታ ከውስጥ ሆነን ስለምናውቀው ገለጥለጥ

አድርጐ ማሳየት ተገቢ ይሆናል። ከታሪክ ተወቃሽነትም ያድናል።

የከተማው ነዋሪና ሲቪል ሰርቪሱ አርከበ በሚባል የደስታ በሽታ ተረፈረፍን፣ " የለውጥ ኮሚቴ" ተብሎ የተሰየመው አካል በጐሰኝነት፣ በጥቅማ ጥቅምና ዘመደ አዝማድ የተቆላለፈ ነበር። ግምገማው በዝጉብኝ የተከናወነ ሲሆን ለወራት ተራዝሞ ነበር። ቢሮክራሲው ጭንቅ አርግዞ ቀንና ለሊቱን በፀሎት ያገጣጠመበት ነበር። በመሆኑም ይህ የሺዎች እንባ የፈሰሰበትን አጋጣሚ ሰፉ አድርጐ ማየት ያስፈልጋል። የከተማው ሲቪል ሰርቪስና የኢህአድግ አባላት የተገላበጡበት ሂደት ቆርኪው ሲላጥ የሚከተለውን ይመስላል :

***

" አርከበ የደስታ በሽታ "

በአንድ ወቅት በከተማችን ውስጥ " አርከበ የደስታ በሽታ" የሚባል በሽታ ይነሳል። በሽታው በጅምላ ጠራርጐ የሚገል ወረርሽኝ ነበር። ይህ ወረርሽኝ አርከበ እቀ-ባይ ከንቲባነት በተመደበ በወራት ጊዜ ውስጥ የተከሰተ ሲሆን እያሳደደ የገደለው ከ5 ሺህ በላይ የሚሆነውን የአስተዳደሩ ሰራተኞንና የኢህአድግን ካድሬዎች ነበር።

የአርከበ የተሳሳተ ትርጉምና ጠባብ አስተሳሰብ በፈጠረው በሽታ በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ቤቱ ያልተንኳኳበት የከተማው ነዋሪ አልነበረም። አራትና አምስት የልጅ ልጆች የሚያሳድጉ እናቶች ሰለባ ሆነዋል። አስተዳደሩ ከፍተኛ ወጪ አውጥቶ ውጭ ሀገር ድረስ ያስተማራቸው ከፍተኛ ሙያተኞች ሳይቀር በወረርሽኙ ተጠቅተዋል።

የወረርሽኙ መንስኤ ክቡር ከንቲባው አቶ መለስ የሰጠውን ትእዛዝ ስላልተገነዘበና በተሳሳተ መንገድ ስለተረጐመ ነበር። ከአቶ መለስ አስተዳደሩ በተቻለ መጠን አዲስ አስተሳሰብ ሊቀበሉ በሚችሉ የተማሩ ሰዎች እንዲመራ ትእዛዝ ያስተላልፉል። ሁልጊዜም ቁንጽሉን ወስዶና የራሱ ፈጠራ አድርጐ የሚሮጠው አርከበ የቢሮክራሲውን ውስብስብ ያለ ችግርና ብሶት ሳይገባው ወደ ሰራ ይገባል። የሲቪል ሰርቪሱን ህግ ባልተከተለ መንገድ " የለውጥ ኮሚቴ " የሚል ከላይ እስከ ታች ያደራጃል። የለውጥ ኮሚቴዎቹን ተጠሪነት ለእሱና ይዞአቸው ለመጣው ምስለኔዎች ያደርጋል።

በወቅቱ አርከበ በአውደ አመት ልዩ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ላይ ቀርቦ ስለ በሽታው ተጠይቆ ነበር። እሱም ተኮፍሶና ፈገግ ብሎ " በከተማው ከዚህ ውጭ ሌላ ወሬ ያለ አይመስለኝም " የሚል ምላሽ ሰጥቷል። ይህቺ ንግግሩ ሰውየው ምን ያህል ነገሮችን አዙሮ ማየት እንደማይችልና ሁሌም የብአዴን ቁንጮዎች " የፓለቲካ ደሀ" ብለው የሚጠሩትን ያረጋገጠ ነበር።

ሲጀመር ህዝቡ እየተናገረ ያለው ስሚያስደስተው ነገር ሳይሆን ስለ በሽታ ነው። ያውም በኢትዬጲያ ታሪክ ውስጥ በመግደል ተወዳዳሪ የሌለውና ማንንም ሳይለይ የጨረሰ ወረርሽኝ። በመቀጠል በሽታው ያጠቃው ኢህአድግ ማህበራዊ መሰረቶቹ ናቸው ያላቸውን በዝቅተኛ ስራ ላይ የተሰማሩ እናቶችንና ብልጣ ብልጥ ያልሆኑ ሙያተኞችን ነበር። በመጨረሻም አብዬት ልጆቿን ትበላለች በሚለው እሳቤ መሰረት የገዛ አባሉንና ካድሬው የተረፈረፈበት ነበር።

ራሱን የለወጠው የለውጥ ኮሚቴ

አዲሶቹን ምስለኔዎች የተጠጉ ፣በመጣው ስርአት ቆዳቸውን እየቀያየሩ ሰራተኛውን ደም እምባ ሲያስለቅሱ የነበሩትን " የለውጥ ኮሚቴ " የሚል ስያሜ ተሰጣቸው። ኮሚቴው በከተማ፣ ወረዳና ቀበሌ ደረጃ እንዲዋቀር ተደረገ። በተመሳሳይ መልኩ በተቋማት ደረጃም ተቋቋመ።

በአንዳንድ ቢሮዎች የተመሰረቱት የለውጥ ኮሚቴዎች ስብጥር አስደንጋጭ ነበር። መረጃ የደረሳቸው የግል ፕሬሶች ኢህአድግ አይንና ጆሮ የለውም የሚሉ ሰፋፊ ጽሁፎችን በመፃፍ ሂደቱን አጋልጠዋል። ርግጥም የአርከበ ዘረኝነት ከመጀመሪያው ፍንትው ብሎ የወጣበት ነበር። ለአብነት የትምህርት ቢሮ የለውጥ ኮሚቴ ከነበሩት ሰባት አባላት ውስጥ ስድስቱ የህውሀት ካድሬዎች ነበሩ። ከዚህ በመነሳት የትምህርት ቢሮ ምደባ ምን ሊመስል እንደሚችል መገመት ይቻላል።

የለውጥ ኮሚቴው በኢህአድግ የተለመደው ዝጉብኝ ስብሰባ ስራውን ጀመረ። ሰራተኛውን " የለውጥ ሀይል " ፣" የለውጥ ሀይል ያልሆነ " በሚል ሁለት ጐራ ከፈለ። ይህ አሰራር ህገ መንግስቱንና የሀገሪቱን ሲቪል ሰርቪስ ህግ ባልተከተለ መንገድ ሰራተኛውን መፈረጅ ጀመረ። የሀገሪቱ ሲቪል ሰርቪስ ህግና የአስተዳደሩ ደንቦች አንድ ሰራተኛ ሲመዘን፣ ሲቀጣና ከስራ ሲሰናበት በምን አግባብ ሊሆን እንደሚችል በግልጽ አስቀምጧል። ሰራተኛው የሚወሰድበት እርምጃ በምን ምክንያት እንደሆነና የቅጣቱ ደረጃ የት ላይ ማረፍ እንደመገባው ተዘርዝሮ ተቀምጧል። ሰራተኛውም በየጊዜው ስልጠና ወስዶበት የስራው መመሪያ አድርጐታል። በየደረጃው ከሰራተኛው የተመረጡ ዲስፕልን ኮሚቴዎች ተቋቁመው መመሪያውን ያስፈጽማሉ።

ለህግ የበላይነት ቁብ የማይሰጠው አርከበ ስራውን ሲጀምር መጀመሪያ የደረመሰው ይህንን ህግ ነበር። የአስተዳደሩን ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ከጨዋታ ውጭ አደረገ። በየደረጃው በሰራተኛው ምርጫ የተቋቋሙትን የዲሲፕሊን ኮሚቴ አፈረሰ። በወቅቱ ህግ ተጥሷል በማለት የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ኮሚሽነር አበባየሁ በመናገሩ ለጊዜው እንዲንሳፈፍ አደረገው። ቂም የቋጠረበት አርከበ "በምርጫ 97 ቅንጅትን ደግፉል ፣ ቀንደኛ ኢሰፓ ነበረ " በማለት ከኮሚሽነርነት አውርዶ የውሀና ፍሳሽ ባለስልጣን በተራ ሰራተኝነት እንዲመደብ አደረገው።

ቀን ቀን በሩን ዘግቶ የለውጥ የሆነና ያልሆነ በሚል የሚፈርጀው የለውጥ ኮሚቴ ነውረኛ ተግባሩ መሸት ሲል በየመሸታ ቤቱ ይገለጻል። በጭንቀት ላይ ያለው ሰራተኛ እንደ እንቁራሪት ተወጥረው ሊፈነዱ ወደደረሱት የኮሚቴ አባላት ምሽቱን ጠብቆ ይሄዳል። ለክፉ ቀን ያስቀመጣትን ገንዘብ በማውጣት እስከ አፍንጫቸው ይጋብዛል። ዘመነኞቹ ስክር ሲሉ የቀን ሚስጥራቸው ይዘከገክሉ። ይህም የበለጠ ሽብር መፍጠር ጀመሩ።

በሂደትም የለውጥ ኮሚቴው ወደሚያስፈራ ሀይል ተቀየረ። በወራት ውስጥ አስተዳደሩ እጅ ያሉ ጉዳዬችን አስፈጽመው ኪሳቸውን አደለቡ። መሬት መስጠት በታገደበት ሁኔታ የሞቱ ፉይሎችን ህይወት እየዘሩ የከተማዋን መሬት ተቆራመቱ። ወትሮ በዘር ስልቻ ውስጥ ራሱን ከቶ የማያውቀው የከተማው ሲቪል ሰርቪስ በለውጥ ኮሚቴዎቹ ወሬ ምክንያት ዘሩን መቁጠር

ጀመረ።አማራነት፣ ጉራጌነት የሚያስጠቃ ሆነ።

ከዘር ጋር በተያያዘ በኮሚቴው አባላት የተነዙት ወሬዎች ከእውነት የራቁ አልነበሩም። አርከበ በውስጠ ድርጅት ስብሰባ ላይ " ከአዲሳባ ቢሮክራሲ ውስጥ 65% አማራ በመሆኑ የትምክህት ጫካ ነው። ይህንንም መስበር ይኖርብናል " በማለት በተደጋጋሚ ሲገልጽ ነበር። የእሱን ንግግር ተከትሎ በአቅም ግንባታ ቢሮ በተዘጋጀው የስልጠና ሰነድ ላይ 65% ያህሉ ሲቪል ሰርቪስ አማራ መሆኑ ፍትሀዊ እንዳልሆነና በተራዘመ ጊዜያቶች ቢሮው የማመጣጠን ስራ እንደሚሰራ አስታወቋል።

ከጉራጌ ተወላጆች ጋር ተያይዞ የተወሰነው በተቻለ መጠን ወደ ቢሮክራሲውም ሆነ ፓርቲ አመራር እንዳይመጡ መከላከል ነበር ። በዚህ ጉዳይ የመጀመሪያው ተጠያቂ አቶ መለስ ሲሆን አርከበ የማስፈፀም ሚና ብቻ ነበረው። በመሆኑም በአርከበ የከተማ ካቢኔ ውስጥ የጉራጌ ተወላጅ የሆነ ካድሬ አልነበረም። ከክፍለ ከተማ ከነበረው 70 ስራ አስፈጻሚ ውስጥ ሁለት ካድሬዎች ብቻ ነበሩ። የላፍቶው ሚፍታህ አብዶና የጉለሌው ዳንኤላ አርጋው። ከአመታት በኃላ ሚፍታህ ወደ ቃሊቲ ሲወረወር ፣ዳንኤል ከስራና ከድርጅት ካድሬነት ተባሯል።

የለውጥ ኮሚቴ አባላት ስራቸውን አጠናቀቁ። ይህንን በማስመልከት አርከበ በቴሌቪዥን ቀርቦ መግለጫ ሰጠ። የአስተዳደሩ ሰራተኞች በየወረዳው በሚገኙ አዳራሾች በመሰብሰብ ምደባቸውን እንዲሰሙ ጥሪ አስተላለፈ። በከተማው የምንገኝ ካድሬዎች በየወረዳው እየተዘዋወርን ሂደቱን እንድንመለከት ተነገረን። መድረኮቹን የሚመሩት እነ አርከበ ይዘዋቸው የመጡት ምስለኔዎች እንደሆነ በጥብቅ ተገለፀልን።

ወደ 50ሺህ የሚጠጋው ሰራተኛ በየእምነቱ ፀሎቱን አድርሶ፣ ከዚህ ክፉ ቀን እንዲያወጣው ስለቱን ተስሎ ወደ አዳራሾቹ ተመመ። በረከት በመፅሀፉ ላይ "ግልብጥብጡን አወጣነው " ያለው ቢሮክራሲ አጀማመሩ ይህን ይመስላል። ወደ ውስጥ ሲገባ ደግሞ ሽግሽጉ ከየት ወደ የት እንደሆነ በግልጽ ስለሚያሳይ እጅግ በጣም ጥቂቶቹን በማንሳት እንመልከት።

***

" ቢሮ ሀበሬታ ትምህርቲ !"

የአርከበ ግልጽ ዘረኝነት ከተገለጸባቸው ቦታዎች አንዱ ትምህርት ቢሮ ነበር። ይህ በታሪክ ተወቃሽ የሚያደርግ ስራ የተመራው ከበደ ብሩና ገ/ ንሳይ (ከቤና ገሬ) በሚባሉ የአርከበ ቀኝ እጅ የህውሀት ካድሬዎች ነበር። እነዚህ ካድሬዎች ከከተማ እስከ ትምህርት ቤት ያሉትን የለውጥ ኮሚቴዎች በህውሀት ካድሬዎች ጠቀጠቁት።

የትምህርት ቢሮ የዝጉብኝ ግምገማውን አጠናቆ ውጤቱ ይፉ ሲደረግ ያልደነገጠ አልነበረም። ቢሮው የለውጥ ሀይል አይደሉም ብሎ ካባረራቸው 80% የአማራ ተወላጆች ነበሩ። በተቃራኒ በመላው አዲስ አበባ በሚገኙ ኮሌጆች፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቤቶችና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተመደቡት ዲኖችና ርእሰ መምህራን አብዛኛው የትግራይ ተወላጆች ሆኑ።

የዝርፊያ ዋነኛ ማእከል የሆነው ትምህርት ቢሮ አመራሩ በህውሀት

ካድሬዎች ተዋጠ። ከሌላ ብሔረሰብ የመጡት ካፊቾው ዶክተር ዘሪሁንና አማራው ወርቅዬ ብቻ ሆኑ (በከፍተኛ የትምህርት ሙያተኝነቱ የተጨበጨበለት ወርቅዬ በተመደበ በስድስት ወሩ ከህሊናዬ ጋር እየተጣላሁ እስከ መቼ ብሎ ስራውን ለቀቀ) ።

የአቶ መለስ ታናሽ እህትን ጨምሮ ሌላው ቢሮክራሲና ድጋፍ ሰጪ ከአመራሩ ጋር ቀጥተኛ ትስስር ያለው ሆነ። የቢሮው የስራ ቋንቋ በይፋ ባልተገለፀ ሁኔታ ወደ ትግርኛ ተለወጠ።

በክፍለ ከተማም ተመሳሳይ ነበር። የቂርቆስ፣ የካ፣ጉለሌ፣ ላፎቶ፣ልደታ፣ኮልፌ፣አራዳ፣ቦሌ ክፍለ ከተማ ትምህርት መምሪያ ሀላፊዎች የህውሀት ካድሬዎች ሆኑ። ሁለት ክፍለ ከተማ ብቻ አዲስ ከተማ (ወ/ሮ አበዜ) እና አቃቂ (አቶ ግርማ ጀርመን) ከሌላ ተቀላቀሏቸው። አንድ ከአማራ፣ አንድ ከኦሮሞ።

በጥሬው የሚበላባቸው በከተማው ስር የሚገኙ ኮሌጆች ፕሬዝዳንቶችና የትምህርት አመራሮች ውስጥ ከ80% በላይ የህውሀት ካድሬዎች ሆኑ። የሁለተኛ ደረጃ ርእሰ መምህራንም ተመሳሳይ ነበር። ይህ አይን ያወጣ ብልግና በመምህራን ዘንድ በመድረሱ የየትምህርት ቤቱ መነጋገሪያ ሆነ። የመምህራን ማህበር በሂደቱ ባለመሳተፉችና ባይተዋር በመደረጋችን የመጣ ችግር በማለት የተቃውሞ መግለጫ አወጣ። መምህራን ቂም አዝለው እስከ ምርጫ 97 ድምጻቸውን አጠፉ።

የምሁራን መናኸሪያ የሆነ ቦታ ላይ እንዲህ አይነት እርምጃ መውሰድ የህዝብ ንቀትና በዘር ላይ የተመሰረተ ሌብነት ካልሆነ በስተቀር ሌላ ምን ሊሆን ይችላል ? ርግጥምበመጨረሻ የተረጋገጠውም ይህ ነው። የለውጥ ኮሚቴውን የመሩት ከቤና ገሬ በከፍተኛ ሌብነት ውስጥ ተዘፍቀው ተገኙ።

***

" ጋንጃ ጋንጃውን "

የሰራተኛውን ምደባና አረንቴሽን እየተሟገርን እንድንመለከት በተነገረን መሰረት ወረዳዎችን ተከፋፈልን። ለእኔ ወረዳ 21 (ቂርቆስ) እና ወረዳ 20 (ጉራ ገብርኤል) ደረሰኝ። በቅድሚያ ወደ ወረዳ 21 ቀበሌ 09 አዳራሽ ሄድኩኝ።

ብዙዎቹን ሰራተኞች አውቃቸዋለሁ። በሶስት ወር ውስጥ ባደረባቸው ስጋት ምክንያት ፊታቸው ገርጥቶ አመድ የተነሰነሰባቸው መስለዋል። የታመቀው ጩኸታቸው ስጋ ሰርስሮ ይገባል። የአንዳንድ እናቶች ድምፅ ግን መታመቅ አልቻለም። ሳያስቡት ይፈነዳል:-

" የጭንቅ አማላጅቷ እንግዲህ አንቺ ታውቂያለሽ "

" ገብርኤል ! አንተ እያለህ መቼም ለምግብ እንጂ ለአቅመ አዳም ያልደረሱ ሁለት የሙት ልጆችን ባዶ ሜዳ ላይ አትጥል " ይላሉ።

ብአዴን ካመጣቻቸው አንዱ የሆነውና የቂርቆስ ምክትል ከንቲባ ሆኖ የተመደበ ታረቀኝ የሚባለው ካድሬ ስብሰባውን እየመራ ነው። ሰራተኛው አይቶ ስለማያውቃቸው አንዱ ለሌላኛው "ደሞ እነዚህ እነማን ናቸው ? ፣ አይ!

ይሄኛው ደግሞ እንደወረደ ነው። " ይላል። ሌላኛው ደግሞ " አልሰማህም እንዴ በድፍን ከተማ እየተወራ ያለውን። የጠገበው ሄዶ የራበው ጅብ መጣ የተባሉት እነዚህ ናቸው " በማለት በተባረር የሰማውን ይናገራል።

የመድረክ መሪው ታረቀኝ በበኩሉ የፈረደበትን የቀድሞ ካድሬ መኮነን ጀመረ " ከዚህ ቀደም የነበረው አመራር የከተማዋን ህዝብ ጋንጃ ጋንጃውን ሲመታ ነበር ፣ እኛ ግን አዲሳባን የቤጂንግ ታናሽ እህት ለማድረግ ቆርጠን ተነስተናል " አለ። ብዙዎቹ በቴሌቭዥቦን እንኳን የቻይናን ከተማ አይተዋት የሚያውቁ አይደሉም።

ከተሜን በለመዱት የአርሶ አደር ቅኝት ለመሰብሰብ የፈለጉት ካድሬዎች ከልቡ የሚያዳምጣቸው ጠፉ። ከምንም በላይ ሰራተኛው እንደ ዝንጀሮዋ መቀመጫዬን ብሏል። የታረቀኝ ገጠር ቀመስ ዲስኩር ማቆሚያ ሲያጣ ሰራተኛው ተሰላቸ። ማጉተምተም ጀመረ። አንድ ተሰብሳቢ ሳይፈቀድለት ፡ -

" ስማ ወንድሜ ! ጋንጃ ጋንጃውን ስትል አልገባኝም? ኢህአዴግ ግን መቼ ይሆን ትላንትናን አመሰግኖ መናገር የሚጀምረው። አዲሳባን ከተቆጣጠራችሁ ስንት ዘመን አለፋችሁ? ደርግ ጠላታችሁ ስለሆነ ሀጢያት ብታበዙበትም አይገርምም። የሚገርመው ትላንትና ኢህአዴግ የመደባቸውን ባለስልጣናት ድክመት በማጉላት ዛሬን ልትሻገሩ መፈለጋችሁ ነው። ... የአዲሳባ ከንቲባ የነበሩት አቶ ተፈራ ዋልዋ ጥሩ ሰርተዋል ተብሎ መሰለን የአቅም ግንባታ ሚኒስትር የሆኑት፣ አቶ አሊ አብዶ 4 ሚሊዬን ከሚሆነው የአዲሳባ ነዋሪ ወደ 30 ሚሊዬን በላይ የሆነው የኦሮሚያ ክልልን ለማስተዳደር መስሎን የኦሮሚያን ካቢኔ የተቀላቀሉት ። አይ አይደለም የምትሉንና የተለየ ግምገማ ካላችሁ ንገሩንና አብረን እንኮንናቸው። " ብሎ ተነገረ።

አዳራሹ በጭብጨባ ተናወጠ። ከየቦታው ስድቦች ተወረወሩ...

" ምድባችንን እንድትነግሩን ነው የመጣነው ! "

" ስብከቱን ለነገ አቆዩልን!"

" እሳት ካየው ምን ለየው? ሁላችሁም አንድ ናችሁ ! "

ስብሰባው ተቋረጠ። አፍታም ሳይቆይ ሞባይሎች መንጫረር ጀመሩ። አጠገቤ የተቀመጠው ጐልማሳ ስልክ የሚያናግረው እንባውን እያፈሰሰ ነበር። ለምን እንደሚያለቅስ ጠየኩት። ወረዳ 20 ስብሰባው ተጠናቆ የሰራተኛው ምደባ ግድግዳ ላይ መለጠፉንና ታላቅ እህቱ የለውጥ ሀይል አይደለሽም ተብላ እንደተባረረች ነገረኝ። ሶስት የሙት ልጆች የምታሳድገው ለብቻዋ እንደሆነ ገለፀልኝ።

ስብሰባው መቀጠል ስላልቻለ ምደባ ወደ ተነገረበት ወረዳ 20 ሄድኩኝ። በመንገዴ ላይ የታረቀኝ " ጋንጃ ጋንጃውን " ማንን እንደመታ ማሰብ ጀመርኩ። የትምህርት ደረጃቸው ከ9ኛ ክፍል በታች የሆኑት በሙሉ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ከምደባ ውጭ ሆነዋል። አዲስ የተሰራው መዋቅር ጽዳትና ተላላኪነትን፣ ጥበቃና አትክልተኛን ወደ አንድ መደብ ስለጨፈለቀ በዚህ ስራ ላይ ከተሰማሩት ግማሽ ያህሉ መቀነሳቸው ግልፅ ነበር።

እነዚህን ብቻ ለአብነት ወስደን ከስራ እየተባረረ ያለው ማነው ? ወደ ጐዳና እንዲወጣ እየተገፋ ያለው ማነው ? የአርከበ ጋንጃ የቆራረጠው እንደዚህ አይነት

ሰወችን ነበር።

በነገራችን ላይ ታረቀኝ በጨፌ ኦሮሚያ በተደረገው የካድሬዎች ግምገማ ላይ ይህቺ ኪሱ ይሏት የሚዞረውን " ጋንጃ ጋንጃውን " የምትል ቃል በተደጋጋሚ ተጠቅሞባት ነበር። ለእኔም ስም የማውጣት ተራ ደረሰኝና ታረቀኝን " ጋንጃ ጋንጃውን" ብዬ የዳቦ ስም አወጣሁለት።

ቀኖች አለፉና የምርጫ 97 ማግስት ላይ ለምን ተሸነፍን በሚለው ጥያቄ ላይ ህላዌ ዬሴፍ አረንቴሽን ሊሰጥ ጠራን። በስብሰባው ላይ የተገኘው ታረቀኝ እጁን አውጥቶ " ህላዌ ! የአዲሳባ ህዝብ ጋንጃ ጋንጃችንን ለምን እንደመታን አልገባኝም ? " ብሎ ጠየቀው። ህላዊ ቆጣ ብሎ " ታረቀኝ! ዛሬም አልከተምክም?" ብሎ ገሰፀው።

***

ወረዳ 20 ቀበሌ 46 አዳራሽ ስደርስ መድረኩን እንዲመራ ሀላፊነት ተሰጥቶት የነበረው አዲሱ የቂርቆስ ከንቲባ አተይ በቦታው የለም። ከሁሉም መድረኮች ቀድሞ የሚበተነው የእሱ እንደሚሆን አስቀድሜ መገመቴ ትክክል ነበር። አተይ ቃላቶችን አሳክቶ ለ5 ደቂቃ በተከታታይ መናገር አይችልም። የአማርኛ እጥረት ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ የብቃት ማነስ ችግር አለበት። ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ ገብቶ ዲግሪውን የወሰደው ከስምንተኛ ክፍል እንደሆነ የኮልፌው ነጋ በርሄ በአደባባይ ነግሮናል... ነጋ ከንቲባነት ለእኔ ነው የሚገባው ብሎ አርከበን ይከራከራል። አርከበ ተበሳጭቶ " ነጋ መጀመሪያ ማትሪክ ተፈተን ይለዋል። በምላሹ የተናደደው ነጋ " አእምሮአችን አልፈቅድ ብሎ አንጂ እንደ አተይ በሚኒስትሪ ካርድ ኮሌጅ መግባት የሚከለክለን አልነበረም" ብሎ ምላሽ ይሰጣል። አተይ በዲግሪ ሳይወሰን ህንድ አገር ሄዶ ማስተርሱን ይዞ መጥቷል።

ሰለ አተይ እያሰላሰልኩ ወረዳ 20 ደረስኩ። ሰራተኛው ከአዳራሽ ወጥቶ ፊት ለፊት ባለው የእግር ኳስ ሜዳ ላይ በቡድን ተሰብስቧል። በዋናው መንገድ ጠርዝ በኩል ከ20 የማያንሱ እናቶች ነጠላቸውን አዘቅዝቀው ደረታቸውን ይደልቃሉ። ስም የተለጠፈበት ግርግዳ አጠገብ ወጣቶች " እንኳን ደስ አለህ " በመባባል ይተቃቀፉሉ...ከ30 በላይ የቀበሌ ነባር ካድሬዎች ከአዳራሹ በር አጠገብ ፈዘው ቆመዋል። የካድሬዎቹ ተራ ገና አልደረሰም።

አልቃሽና ዘፋኝ።

ማንንም መቀላቀል አልፈለኩም። የመጣሁበትን ፒካፕ ተደግፌ በትምህርት ዝግጅታቸው ማነስ ምክንያት ሰለተባረሩት እናቶች ማሰብ ጀመርኩ። ይህን ተከትሎ ስሚከሰተው ከተማ አቀፍ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ አሳሰበኝ። በአንድ ወቅት ሐይለልኡል የሚባል የአስተዳደሩ ማህበራዊ ጉዳዬች ከፍተኛ ሙያተኛ በመንግስት ሰራተኛ እናቶች ላይ የደረገውን ጥናት ሲያቀርብ ተሳትፌ ነበር። ከጥናቱ ውጤቶች አንዱ ከ30% በላይ የሚሆኑት የመንግስት ሰራተኛ ሴቶች እማወራ (single mam) ናቸው። እነዚህ አናቶች በአማካይ ሶስት ልጆች ያሳድጋሉ። የአርከበ ግልብጥብጦሽ ቆርኪው ሲላጥ እነዚህን ህጻናት ወደ ጐዳና ለመስደድ የተዘጋጀ ነበር።

የቀበሌ 46 ካድሬዋ ዬርዳኖስ አጠገቤ መጥታ ቆመች። ከማልቀሷ ብዛት አይኗ ቀልቷል። አፍታም ሳትቆይ ሲቃ እየተናነቃት " ወይኔ ጉዴ። ከማን ጋር ልኖር

ነው። ይሄ ሁሉ ቤት እንዴት በአንድ ቀን ይፈርሳል?" በማለት ሯሷን እየጠየቀች ተነፉረቀች።

አንዲት ጥቁር ሴትዬ ደረታቸውን ገልብጠው ከሚያለቅሱት መሀከል እየሮጠች መጥታ እግሬ ላይ ተደፉች። በቁራ በሚገኘው ቀበሌ በተላለኪነት የምትሰራ የኢህአድግ አባል ናት። ስሜን እየጠራች " ልጆቼን ተረከበኝ" እያለች ጮኸች። ቀስ በቀስ ሌሎቹም ከበቡኝ።ከዬርዳኖስ የቢሮዋን ቁልፍ ተቀበልኳት። በሩን ዘግቼ በተራዬ አስነካሁት። በሆቴል ሩዋንዳ ፊልም ላይ መሪ ተዋንያኑ ፓል ሪሴባጊና የተረፈረፈውን የቱትሲ ሬሳ በመኪና ሲዞር በመመልከቱ ምክንያት ያነባውን የደም እምባ ብቻዬን ደገምኩት።

***

"ጨነቀን ያየ..."

የአዲሳባ ማዘጋጃ ቤት በአስቸኳይ ስብሰባ በመጡ ከአንድ ሺህ በላይ ካድሬዎች ተጨናንቋል። ካድሬዎቹ የክፍለ ከተማና ቀበሌ ናቸው። ስብሰባውን የሚመሩት አርከበና ህላዌ አስቀድመው ወደ መድረክ ወጥተዋል። አርከበ ጉሮሮውን ስሎ የተሰበሰብንበትን ምክንያት መግለጽ ጀመረ። የከተማው ነዋሪ በአገልግሎት አሰጣጣችን ላይ ላይ ምሬት እያሰማ እንደሆነ... ምክንያቱ ደግሞ ብዙዎች ትምህርት ቤት መሄድ በመጀመራቸው እንደሆነ አስረዳ። ቀጣዩን ሳይናገር ቤቱ በተቃውሞ አጉተመተመ። አጠገቤ የተቀመጠው ሺሰማ (በወቅቱ በኮልፌ የአንዲት ቀበሌ የካድሬዎች አለቃ ነበር፣ በአሁን ሰአት የአዲሳባ ካቢኔ አባል ነው) ወደ ጆሮዬ ጠጋ ብሎ " ይሄ ሰውዬ አሁንስ ይበልጥ ግራ ተጋብቷል። ትላንትና ሰው የሀገሪቱ እምብርት ላይ ተቀምጦ እንዴት መሀይም ይሆናል ባለ አንደበቱ ለምን ትምህርት ቤት ሄዳችሁ ይለናል?" ብሎ ጠየቀኝ።

አርከበ ንግግሩን አቋርጦ ካድሬው ለምን እንዳጉተመተመ ጠየቀ። ከብዙ ፀጥታ በኃላ አንድ ካድሬ ከጫፍ አካባቢ እጁን አወጣ። ማይክራፎን ተሰጠው።

" ጨነቀን ያየ በፊደል አይቀልድም!!" የሚል መፈክር አሰምቶ ተቀመጠ።

አዳራሹ በሳቅ ተናወጠ። ቀጥሎ ሞቅ ያለ ጭብጨባ።

አርከበ ካድሬው የተናገረው እንዳልገባውና እንዲደግምለት አሳሰበው።

" ጨነቀን ያየ በፊደል አይቀልድም !!" ደገመለት።

አርከበ እኔና በጣም ጥቂቶች አልገባንም። አጠገቤ የተቀመጠው ሺሰማ በሳቅ ይንተከተካል። ጨነቀ የሚባለው ታታሪ ካድሬ እሱ በሚሰራበት ወረዳ ሲሰራ እንደነበር ስለማውቅ ምን እንደሆነ ጠየኩት። ምንም አለመስማቱ ገርሞት በዝርዝር አጫወተኝ።

***

አርከበ ሲቪል ሰርቪሱን እያገላበጠ ጐን ለጐን ዘመቻውን በነባሩ ካድሬና አባላት ላይ ሆነ። ለዚህ ደግሞ የአባይ ፀሀዬ " የከተማው የድርጅት ማሽን ጥሬ ከቶ ጥሬ የሚያወጣ " ብሎ የገለፀውና አቶ መለስ " ይህንን ጌቶ (getto) መዋቅር ከህዝብ ጫንቃ ላይ አውርደን ፊደል የቆጠረ ሰው ከተማውን መምራት

ይኖርበታል " የሚለው አባባል ለአርከበ ጅምላ ጠረጋ ጠቅሞት ነበር።

የአቶ መለስም ሆነ አባይ ንግግር ትክክል ነበር። የአዲሳባ ኢህአድግ መዋቅር እንኳን የመሪነት ሚና ሊጫወት ቀርቶ ለህዝብ ጭራነት ብቁ አልነበረም። ካድሬውና አባላቱ በተግባር ኢህአድግ አልነበሩም። ዘባተሎውን አሊ አብዶ ጨምሮ የአብዬታዊ ዲሞክራሲ ምንነትና ግብ ምን እንደሆነ የማያውቁ ነበሩ። አቶ መለስ ይሄንን ክፍተት በማየት የተማረ ሰው ፈልጉ ያለው።

በዚህም ምክንያት ለነባሩ ካድሬ በስራ መቀጠልና መባረር ትልቁ መመዘኛ የትምህርት ደረጃ ሆኖ ብቅ አለ። ቀድሞ የነበሩት የመገምገሚያ ነጥቦች (አብዬታዊነት፣ የአላማ ጽናት፣ ወገንተኝነት፣ ህዝባዊነት...) ገደል ገቡ። መዋቅሩ ተደናገጠ። የለመደው ቀረበት።

ከግምገማው በኃላ የነበረው የምደባ ሂደት የጨነቀን ስም በማይረሳ መልኩ እንዲተከል አደረገ።

ጨነቀ ካድሬ ነው። መርካቶ ውስጥ በሚገኝ ወረዳ ለረጅም ጊዜ የአስተዳደር ዘርፍ ሀላፊ ሆኖ ሰርቷል። ጨነቀ በአብዬታዊነቱ፣ በታማኝነቱና የአላማ ጽናቱ ተወዳዳሪ አልነበረውም። የመንግስት ሰራተኞችን፣ መምህራንን ሰብስቦ ስለ አብዬታዊ ዲሞክራሲ ስልጠና ይሰጣል። የአገሪቷን የልማት አቅጣጫ በየመድረኩ የብራራል። ኢትዬጲያ አጋጥሞት የነበረውን መስቀለኛ መንገድ፣ አንቀጽ 39 የአንድነታችን መሰረት እንደሆነ ሳይታክት ባገኘው አጋጣሚ ያስተምራል።

ጨነቀ ትጉህ ነበር...

ለውስጥ ለውስጥ መንገድ በእሱ ወረዳ በአመቱ ውስጥ አንድ ሚሊዬን ብር ከህዝብ መዋጣት አለበት ተብሎ እቅድ ይላክለታል። በአመቱ መጨረሻ ከራሱ ቤትና ቤተሰብ ጀምሮ የእያንዳንዱን በር በየቀኑ አንኳክቶ ሁለት ሚሊዬን ብር ሰብስቦ ገቢ ያደርጋል። ይህንን ብር ለማሰባሰብ የማይቆፍረው ጉድጓድ የለም። የአካባቢው ነዋሪዎች በራቸው ያለማቋረጥ ከተንኳኳ " ጨነቀ ነው መሰለኝ!! የተጣለብንን መዋጮ ከከፈልን ወር ሞላ እንዴ ? በሉ በር እንዳትከፍቱ" እስኪባል ድረስ እግሩ እስኪነቃ ይመላለሳል። ህገ ወጥ ንግድ መርካቶን አስቸገረ ከተባለ ጨነቀ ይላካል። ድምጥማጡን አጥፍቶ ይመለሳል። ... ለኢህአድግ ማጠናከሪያ ሩብ ሚሊዬን ሰብስብ ተብሎ ኮታ ከተጣለበት ግማሽ ሚሊዬን ሰብስቦ የሌሎቹን ይሸፍናል።

ጨነቀ ጀግና ነበር...

ጨነቀ ወንጀለኞችን፣ጉልበተኞችንና ሴሰኞችን ልክ በማስገባት ተወዳዳሪ አልነበረውም። በአንድ ወቅት በትምህርት ቤቶች ዙሪያ " ሹገር ዳዲ" የሚባሉ አዛውንቶች ላይ የተቀናጀ ዘመቻ ተጀመሮ ነበር። ታዲያ በፈጠራ ማንም የማይደርስበት ጨነቀ አድብቶ በመጠበቅ አንዱን የሸማግሌ ቀላል እጅ ከፍንጅ አልቤርጉ ውስጥ ይይዘዋል። እናም " እኔ ሹገር ዳዲ ነኝ። እኔን ያየ ይቀጣ " የሚል ወረቀት ለጥፎበት በወረዳው ፒካፕ ላይ አስጭኖ አዞረው። ሹገር ዳዲዎች ለጊዜው ደብዛቸው ጠፋ።

ጨነቀ ጨዋ ነበር...

መሀል መርካቶ እያስተዳደረና አማላይ ጉቦዎች እየተላኩለት ሰጪውን

እየተከታተለ የሚቀጣ። ልጆቹን ሽራ ጫማ አልብሶ ትምህርት ቤት የሚልክ። ሚስቱ የቋጠረችለትን ሽሮ በቧንቧ ውሀ አያወራረደ የሚሰለቅጥ ምስኪን።

የትምህርት ሰርተፍኬትን እንደ መመዘኛ ይዞ ብቅ ያለው የአርከበ አዲሱ ምደባ ጨነቀን የመጀመሪያ ተጠቂ አደረገው። የቀለም ትምህርትን ከ8ኛ ክፍል አልዘለለም። በግምገማ ወቅት ለምን አልተማርክም ተብሎ ተጠየቀ። ጨነቀ ጠንካራ መከራከሪያ ከተጠያቂነት ጋር አያይዞ አቀረበ። እንዲህ በማለት:-

" ያዘናጋኝ የድርጅታችን ሊቀመንበር አቶ መለስ ዜናዊ ነው። በፓርላማ ቀርቦ ለኢህአድግ ካድሬነት መመዘኛችን የትምህር ደረጃ አይደለም። አብዬታዊ መሆን በቂ ነው ብሎ ተናገረ። እኔም ልማር ያሰብኩትን እሱን በማመን እርግፍ አድርጌ ትቼ አብዬታዊነቴን ስጠብቅ ኖርኩኝ።"

ጨነቀ እውነትም ወደ ላይ የሚታገል አብዬታዊ ነበር። ቱባ ካድሬዎችን እየጠራ ሞገተ :-

" *እነ ሀላዊ፣ አባዱላ፣ የዞናችን ሊ/ መንበር ሱልሰገድ ይፍሩ መቼ ሰርተፍኬት አላቸው ? ... ተፈራ ዋልዋ የተግባረድ ዲፕሎማ አይደል የያዘው?...አርከበ ከመቀሌ ይዞአቸው የመጡት እነ ነጋ በርሄ፣ ግርማ ጸዬን ፣ጣይቱ ባእታ፣ሀይለስላሴ ዘጠነኛ ሲደመር ጭጭ እንደሆኑ ሰምቻለሁ* " ብሎ ተከራከረ።

የጨነቀ አብዬታዊ መከራከሪያ ነጥቦች አልጠቀሙትም። ከካድሬ ምደባ ውጭ ሆነ። ምንም አይነት አማራጭ ሲጠፉ ወደ ቢሮክራሲው መዋቅር እንዲመደብ ስሙ ተላለፈ። እዛም ቢሆን መደብ አልተገኘለትም። በመለስ ቀጭን ትእዛዝ አዲስ የተፈጠረው የደንብ ማስከበር መደብ እንኳን ትንሹ መመዘኛ አሱ ካለው ደረጃ ከፍ ይላል። ይህም ሆኖ የካድሬነት ዘመኑ እንደ አገልግሎት ተቆጥሮለት ደንብ ማስከበር ተመደበ። ቆመጥ ተሰጥቶት ሰልባጅ ነጋዴንና ሱቅ በደረቴን ማባረር ቁልፍ ስራው ሆነ።

ጨነቀ ከፍተኛ የሞራል ውድቀት ደረሰበት። ራሱን ከማህበራዊ ተሳትፎዎች ሳይቀር አገለለ።

ጨነቀን ...ጨነቀው!

የቢሮክራሶውን፣ የመምህራንና የነዋሪውን አይን ፈራ። በቀናቶች ውስጥ ራሱን ጠላና አረቄ ውስጥ ደበቆ አገኘው።

በሌላ በኩል ጨነቀና እሱን መሰል ካድሬዎች የተቀጡትን አይቀጡ ቅጣት ያየ የከተማው ካድሬ " ዘመቻ - ጨነቀ" አውጆ ወደ አስኳላ ተመመ። የካድሬው ወሬ በሙሉ ትምህርት ሆነ። ይህንን ተከትሎ የመንግስት ጽ/ ቤቶች ከቀኑ ዘጠኝ ሰአት መዘጋት ጀመሩ። አገልግሎት ፈልጎ የሚመጣው ነዋሪ ሀላፊዎች ባለመኖራቸው በንጋታው እንዲመለሱ መነገር ተጀመረ። ህዝቡ አርከበ በሚዲያ የሚያወራውና መሬት ላይ ያለው ነገር ተለያየበት።

እንግዲህ በማዘጋጃ ቤት የተጠራው ስብሰባ ይህን የህዝቡን ቅሬታ ለማስተንፈስ ያለመ ነበር። " ጨነቀን ያየ በፊደል አይቀልድም!!" የምትለዋ መፈክር የተነሳችው በዚህ ሁኔታ ነበር።

በስብሰባው ማጠቃለያ አርከበ ማስጠንቀቂያ ሰጠ "እማራለሁ የሚል ከዛሬ

ጀምሮ ከካድሬነት ተሰናብቷል... መንገዱን ጨርቅ ያድርግለት" በማለት።

የውሳኔው አፈጻጸም የኢህአድግ ልጅና የእንጀራ ልጅ ማን እንደሆነ አጋልጦአል። አብዛኛው ሊመረቁ አንድ ሴሚስተር የቀራቸው ነባር ካድሬዎች ትምህርታቸውን አቋረጡ። መጨረስ አለብን ያሉ ከስራ ተባረሩ። ብዙ ካድሬዎችን በማባረር ሪከርድ የሰበሩት የላፍቶ ክፍለ ከተማ ከንቲባው ሀይሌ ፍስሀና የአዲስ ከተማው ሉልሰገድ ነበሩ። ሉልሰገድ የተማረ የማይወድና ትምህርት አላርጂክ የሆነበት ነባር ካድሬ ነበር።

ሀይሌ ፍስሀ ሌላውን ፎርም አስሞልቶ እያባረረ ለራሱ ግን ሁለት ማስተርስ ይሰራ ነበር። አንደኛውን በአራት ኪሎ ዩንቨርስቲ ጂኦሎጂ ዲፓርትመንት የሙሉ ጊዜ ተማሪ በመሆን፣ ሌላኛውን ከእኛ ጋር በለደርሺፕ ይማራል። ሀይሌ ሲያጠና እንኳን ሁለት እግሩን የቢሮው ጠረጴዛ ላይ ሰቅሎ ነበር...የኮልፌና የካ ክንቲባ የነበሩት ነጋ በርሄና ግርማጺዮን ለተራዘመ ወራት መቀሌ በመሄድ እየተማሩ ይመጡ ነበር... የአራዳ ድርጅት ሀላፊ የነበረው ሀይላይ ሲቪል ሰርቪስ የቀን ገብቶ አየተማረ በሳምንት ሶስት ቀን ይሰራ ነበር።

ከዚህ በተቃራኒ ከአርከበና ከትምህርት ጠሎች ከሆኑ ካድሬዎች የሚደርስባቸውን ጫና በመቋቋም ከስራቸው ያለው ካድሬ የጀመረውን እንዲያጠናቅቅ ያገዙ ነበሩ። ምስጋና የሚገባቸው ናቸው... በተለይም የአቃቂ ክንቲባ የነበረው ተክለ ጳዲቅ፣ የጉለሌው ኤቢሳ፣ የኮልፌው አባተ ስጦታውና የየካው ግርማጺዮን ለአርከበ ሪፓርት ሳያደርጉ ካድሬዎቹ እንዲማሩ ሽፋን ሰጥተዋል። ዛሬ በአዲሳባ አስተዳደር ካቢኔ ውስጥ የምናገኛቸው እነ ሺሰማ፣ ኢንተርናሽናል አልቢትር ተስፉዬ ኦሜጋ በሚስጥር እንዲማሩ ስለተደረገ ነው።

***

ምእራፍ ጉንጭ አልፉው ግምገማ

"... እኔን ከድርጅቱ ለማጣላት አስበህ ከሆነ ለዘላለም አይሳካልህም!!"

በረከት ስምኦን

" ... የእኔና የአንተ ችግር የዛሬ ሳይሆን ከበረሀ ጀምሮ ነው !!"

አርከበ እቁባይ

" ውሻ በቀደደው•••"

ይህ በረከት የመራው በኢህአድግ ቢሮ ትነሿ አዳራሽ የተካሄደ ጉንጭ አልፉ ግምገማ ነው። ለምን ጉንጭ አልፉ ሆነ የሚለው መጨረሻ ላይ ያገኙታል።

ከምርጫ 97 በኃላ የተካሔደው የመሬት ወረራ የጠቅላይ ሚኒስትርና ከንቲባ ጽህፈት ቤት የተቀናጀበት ነበር። ወረራው ከተጠናቀቀ በኃላ በበረከት ስምኦን መሪነት ኢህአድግ ቢሮ ግምገማ ተቀመጥን። ግምገማው እየጠነከረ ሲሄድ በበረከትና አርከበ መካከል ጭቅጭቅ ይነሳል። ልብ የሞላውን አፍ ያወጣዋል እንዲሉ በረከት ስምኦን ባልተጠበቀ አፍ ወለምታ ይመታል። እናም " ውሻ በቀደደው ጅብ ይገባል " ብሎ ይናገራል።

አርከበ እቁባይ የጋለ ብረት ነክሶ :-

" በረከት! ማንን ነው ውሻ ያልከው? ማንን ነው ጅብ እያልክ ያለኸው? ግልጽ እንድታደርግልኝ እፈልጋለሁ " ይላል።

አቶ በረከት ወደ ዝርዝር ሳይገባ:-

" ድርጅቱ ባስቀመጠልህ አቅጣጫ አልሄድክም። እኔን ከድርጅቱ ለማጣላት አስበህ ከሆነ ለዘላለም አይሳካልህም! " የሚልየአፀፉ ምላሽ ይሰጣል።

በግምገማው ላይ የነበርን ካድሬዎች የበረከትን አባባል ለመረዳት ወራት የዘለቀውን ግምገማ ማጋመስ ነበረብን። መልሱንም አገኘነው።

ታሪኩ ረዘም ተደርጐ ሲተረክ ይህን ይመስላል:-

***

"ማነው ውሻ ?"

የምርጫ 97 ውጤት እንደታወቀ አቶ መለስ ከመከላከያ ጀነራሎች ጋር በየቀኑ ስብሰባ ይቀመጣል። ወቅቱ ለአቶ መለስ ከየትኛውም ጊዜ በላይ አስቸጋሪ ነበር። በመዲናይቱ የሚካሄዱት ተቃውሞዎች ረፍት ነስተውታል። የድርጅት መዋቅሩ ሙሉ ለሙሉ ተበትኗል። ያለው አማራጭ አንድ ብቻ ነበር። የፀጥታና ወታደራዊ ሀይሉን ማጠናከር። ፓለቲካዊ ጤንነቱን መጠበቅ። እናም የወታደራዊ ሀይሉን ወገንተኝነት የሚያረጋግጥበት ሁኔታ መፈጠር ነበረበት። ጀነራሎቹም ይህንን ጠንቅቀው ያውቃሉ...

ሰጥቶ የመቀበል ዘመን።

በመሆኑም ጀነራሎቹ በቀኝ እጃቸው የታማኝነት ማህተም፣ በግራ እጃቸው ደግሞ ማመልከቻ ይዘው መጡ። ማመልከቻው አዲሳባ በቅንጅት እጅ ከመውደቋ በፊት በቋሚነት ጉናችንን የምናሳርፍበት መሬት ይሰጠን የሚል ነበር።

አቶ መለስ ሳያቅማማ ጥያቄያቸውን በመቀበል ለከተማው ከንቲባ አርከበ እቁባይ መሬት እየቆረሰ እንዲሰጣቸው ትእዛዝ ይሰጣል። መመዘኛውን ደግሞ ከ1978 አ•ም በፊት በትግል ውስጥ የነበሩና ማእረጋቸው ከሻለቃ በላይ የሆኑት እንዲሆን ይነግረዋል።

የበረከት ውሻ በቀደደው ታሪክ አጀማመሩ ይህን ይመስላል።

የአቶ መለስን ቀዳዳና አረንጓዴ መብራት ያገኘው አርከበ ግዜ ማጥፋት አልፈለገም። በእሱ የሚመራውን የፓለቲካ ክንፍ አስቸኳይ ስብሰባ ይጠራል።

በወቅቱ አዲሳባ ከላይ እስከ ታች ያለውን መንግስታዊ መዋቅር በማፍረስ በሰባት ማዘጋጃ ጣቢያ(ኮማንድ ፓስት) ተከፍላ ነበር። ኮማንድ ፓስቱ

የፓለቲካና የፀጥታ ክንፍ በማለት ለሁለት ተከፈለ።

የፓለቲካ ክንፍን አርከበ እንዲመራው ተደረገ። ከመቀሌ ይዞአቸው የመጡት የህውሀት ካድሬዎች ሰባቱን ጣቢያዎች በፊት መስመር ተመደቡ : - ዶክተር አብርሀም (የከንቲባ ጽ/ ቤት ሀላፊ) ፣ሀይሌ ፍስሀ (የላፍቶ ክንቲባ) ፣ ግርማጺዮን (የየካ ክንቲባ) ፣ አተይ (የቂርቆስ ክንቲባ) ፣ወ/ ስላሴ (የቦሌ ክንቲባ) ፣ ነጋ በርሄ (የኮልፌ ም/ ከንቲባ) ፣ዘሩግርማይ (የልደታ ም/ ከንቲባ) ፣ታደለ ግደይ(የአዲስ ከተማ ም/ ከንቲባ) ነበሩ።

የከተማዋን የፀጥታና ወታደራዊ ክንፍ ከአዲሳባና ፌዴራል ፓሊስ፣ ከደህንነትና መከላከያ መኮንኖች ተመደቡ: -ተስፉዬ መራሳ (የአዲሳባ ፓሊስ አዛዥ) ፣ግርማይ (ፌደራል ፓሊስ ሀላፊ) ፣መውጫ (አድማ ብተና ሀላፊ) ፣ወልደስላሴ (ደህንነት ሹም) ፣ኢሳያስ ወልደጊዮርጊስ (ደህንነት ሹም) ፣ጀነራል ታደሰ ወረደ ነበሩ።

የፓለቲካና ፀጥታ ኮሚቴው የጋራ ጥምር ኮሚቴ በመፍጠር በየቀኑ ማታ ማታ የከተማዋን አዳርና ውሎ ይገመግማል። በህዝቡ ውስጥ ያሉ እንቅስቃሴዎችን መረጃ ያሰባስባል። የተቃዋሚ መሪዎችን የእለት ንግግርና ውሎ እንድምታ ይተነትናል። በበቅሎ ቤት የቅንጅት መሪዎች ያደረጉት ስብሰባ ቃለ ጉባኤ ምሽት በንባብ ያዳምጣል። ለኢፍትን ጋዜጣ የሚላከውን በመለየት ለእነ ኢሳያስ ያስተላልፉል።

በወቅቱ የተቃዋሚውን ጐራ ከመጉዳት አኳያ ትልቅ ሚና የተጫወተችው ኢፍትን የምትባል ጋዜጣ ነበረች። ይቺ በዘሪሁን (የጋዜጠኛ ሚሚ ስብሀቱ ባለቤት) እና ጋዜጠኛ ሰለሞን አስመላሽ የምትመራው ልሳን በሚዲያ ስነ ምግባር ያልታነፀችና በደህንነት መረጃ ላይ የተንጠለጠለች መደዴ ነበረች። የጋዜጣዋ ቋሚ አምደኞች ራሳቸውን የሀሳብ አፍላቂው ቡድን (Opinion Leaders) ብለው የደራጁ ሰዎች ሲሆኑ: ሽመልስ ከማል (ብሮድካስቲንግ ሀላፊ) ፣ሚሊዬን አሰፉ (የቱዲ አፍሮ ጠበቃ)፣ ገነነው አሰፉ (የገነት ዘውዴ ወንድም) ፣ ጋዜጠኛ ሚሚ ስብሀቱ በዋናነት ይገኙበታል። ሀሳብ በማፍለቅና መረጃ በማምጣት ዙሪያ የእነ ሽመልስ ከማል የጫት ቤት ጓደኛ ሙሼ ሰሙ (የኢዴፓ ሊቀመንበር) ይሳተፍ ነበር።

በነገራችን ላይ የቅንጅት አመራሮች በታሰሩ ወቅት ልደቱ አያሌው ባለመታሰሩ ከፍተኛ ቅሬታ ያሰማው ሙሼ ሰሙ ነበር። ኢህአድግ ልደቱን ባለማሰሩ ተሳስቷል በማለት በግልፅ ከእነ ሽመልስ ጋር ተከራክሯል። የሙሼን ሀሳብ ሽመልስ ይጋራል። የአቃቤ ህግነቱን ስራ ውሽልሽሉ እንዲወጣ ያደረገው የልደቱ አለመታሰር እንደሆነ በቁጭት ነግሮኛል። ምክንያቱ ደግሞ እነ ሽመልስ አቃቤ ህግ በነበሩ ሰአት ለመከራከሪያነት ይዘው ከቀረቡት የጽሁፍና ቪዲዬ ማስረጃዎች ከ80% በላይ የልደቱ ውጤቶች ናቸው።

ልደቱ የክሱ ጭብጦች በጐን በኩል እንዲደርሰው በመደረጉ አይኑን በጨው አጥቦ ፓርላማ ገባ። የኢህአድግ ብትር እንደማይለቀው ሽዋ ሮቢት አሳይቶታል። እናም እሱ ሽንጐውን ሲቀላቀል፣የእሱ ጽሁፎችና ዲስኩሮች አቃቂ በተሰየመ ችሎት ሰላማዊነቷ በሚነገርላት ብርቱካን ሚደቅሳ ላይ መሰማት ጀመረ። እውነት ለመናገር ከማናቸውም ሰው በላይ የክሱ ሂደት ለሽመልስም እና

ብርቱካን ከባድ ነበር...የኢትዬጲያ ፓለቲካ የተሳሰረ ክር እስማባጠስ የሚሄድ ክፉት በማዘሉ። በተቃራኒው ደግሞ ባላንጠዎችን ያቀናጃል... ለዚህ ደግሞ ምሳሌ የሚሆኑ በሁሉም ጐራ አሉ። ሙሼ የልደቱ ጠላት ነው...በረከትና አርከበ ተመሳሳይ ናቸው...በረከት አርከበን "የዛፍ ላይ እባብ" (" Boomslang") ብሎ ይጠራዋል።ይህ የእባብ ዝርያ በምስራቅ አፍሪካ የሚገኝ ሲሆን በውበቱና ገዳይነቱ ተወዳዳሪ የለውም።... ሙሼ ደግሞ ልደቱን " የቱማታ አቅማዳ " ይለዋል...የኢትዬጲያ ፓለቲካ ፓርቲዎች እንዲህ ናቸው...በሬ ካራጁ!!

***

በአርከበና ጀነራል ታደሰ ወረደ የሚመራው የፓለቲካና ፀጥታ ጥምር ኮሚቴ በአንድ በኩል የአቶ መለስ ዙፋንን እየጠበቀ በሌላ በኩል የአዲሳባን መሬት መዝረፍ ጀመረ። ከ1978 በፊት ታጋይ የነበሩና ማእረጋቸው ከኮረኔል በላይ የሆኑት ቦሌ ላይ መሬት ተሰጣቸው። በተለየ ሁኔታ ቦሌ እንዲወስዱ የተደረገበት ሶስት ምክንያቶች ነበሩ... ቦሌ መሬት ማግኘት ወረቅ እንደመዝገን ስለሚቆጠር፣ ከአየር መንገዱ ጋር ተያይዞ አለም አቀፍ ትኩረት የሚሰጠው ቦታ በመሆኑና የአካባቢውን ህዝብ የሀይል ሚዛን ለማዛባት የታሰበ ነበር። የቦሌ ነዋሪ ፀረ አብዬታዊ ዲሞክራሲ ተደርጐ የተፈረጀ ሲሆን ኢህአድግ ተፈራ ዋልዋን የሚያካክሉ ካድሬዎቹን ለምርጫ አቅርቦ ከአንዱም ሁለቱ ሀፍረት የተከናነበበት ነበር። እናም ይህን የሀይል ሚዛን መቀየር እንደ አንድ ታሳቢ መውሰድ አስፈላጊ ሆኗል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የአዲሳባ ህዝብ ቦሌ አካባቢን " ትንሿ ትግራይ" ያለበት ምክንያት ይህ ነው። ርግጥም አቶ መለስ እንደገመተውም የሀይል ሚዛኑ ተዛብቷል። በተጭበረበረ የድምጽ ቆጠራ እንኳን ኢህአድግ አሸንፎባት የማያውቃት ወረዳ 18 ቦታዋን ለመርካቶ ለቃለች... ለተከበሩ ግርማ ሰይፉ!...የመርካቶ መልሶ ማልማት እስኪጠናቀቅ ድረስ።

ከሙሉ ኮረኔል በታች ያሉት ወታደሮች በሌሎች ማስፉፊያ ክፍለ ከተሞች ተደለደሉ። ወሬው ባድመና ጾረና ጦር ግንባር ድረስ ተዳረሰ። ወታደራዊ መኮንኖቹ ምሽጋቸውን አየለቀቁ በጦር ኢሊኮፍተሮች ጭምር እየተሳፈሩ አዲሳባን ወረሯት። በየክፍለ ከተማው ጽ/ ቤት ግቢ አሏራ የጠጣ የኮከብ፣ ጋሻና ጦር ክምር የተሸከመ ካኪ ተጥለቀለቀ።

ከቀናት በኃላ አዲስ አበባ አጥንቷ ተግጦ እርቃኗን ታየች። አዱገነትና ልጆቿ አለቀሱ። እንባዋን ባያብሱላትም የነቀዘውን ታሪክ በዚህ መልኩ መክተቡ አስፈላጊ መስሎ ስለታያቸው በዝርዝር ወደ ማሳየት ተሸጋገሩ።

በመሆኑም ይህን የዝርፊያ ሂደት በትክክል ለመገንዘብ ይቻል ዘንድ ይበልጥ ጐላ ብለው ስለተፈፀሙት ሌብነቶችና ግለሰቦች እያነሳን እንመልከተው። ወደ ዝርዝር ከመግባታችን በፊት ለንጽጽር እንዲረዳ በረከት ስምኦን በመጽሀፉ ላይ ያስቀመጠውን እናስቀድም:

አቶ በረከት በመጽሀፉ የመቋጫ ወግ በሚለው ርእስ ስር የኢህአድግ ካድሬዎች ከብዙ መሰል ሀይሎች የሚለዩባቸው ብሎ ከገለጻቸው አራት ባህሪያት ውስጥ ሁለተኛው ይህን ይላል :

" ሁለተኛውና ምንአልባትም የኢህአድግ መሪዎችና ታጋዬችን ከብዙ መሰል ሀይሎች ለየት ባለ ደረጃ እንዲታዩ የሚያደርጋቸው ፣እንደ ቡድን ስልጣንን ለህዝብ ጥቅም እንጂ ለራስ ጥቅም ማካበቻ ማድረግ የለብንም ብለው ማመናቸውና ይህንንም በተግባር ለማዋል ያለመሰልቸት መስራታቸው ነው።... ሀብት መፍጠር እንጂ የተፈጠረን ሀብት መቀራመት ከድህነት አያላቅቅም ብለው ያመኑት ኢህአድጎች ፣ እነሆ ስልጣንን የሀብት መቀራመቻ ሳይሆን አገር የመለወጫ መሳሪያ አደረጉት። አገር በመለወጥና ራስን በመጥቀም መካከል ያለውን ልዩነት ለአፍታም ሳይዘነጉ በመስራታቸው ፣ በአገራችን እጅግ በጣም ፍትሀዊ ሊባል የሚችል ፈጣን እድገት እንዲመጣ ለማድረግ በቁ..."

በአራት ኪሎ ኢህአድግ ቢሮ በረከት በመራው ግምገማ ይህንን አባባል የሚጣሉ ግኝቶች ተደምጠዋል... ምንም እንኳን በመጽሀፉ የትኛውም ገጽ ላይ ባይጠቀሱም። በረከት አንድ ጊዜ ፓናዶል ፣ሌላ ጊዜ ኖባልጅን እየዋጠና ቁና ቁና እየተነፈሰ ያዳመጣቸው ወጮች የሚከተለውን ይመስላሉ።

***

የሚጨመሩ

- አቃቂ አባዱላ ገመዳ vs ጣይቱ (ገሬ ባለቤቷ)
- ቀራንዬ፣አቃቂ ሰጥቷል የሚባል ካድሬ። ፍቃዱ፣ዘላለም
- የሐይለማርያም ጉዞ : የሊማሊሞ መንገድ
  - አርከበና ሰብሀት ነጋ
  - የአባዱላ ቪላዎች
  - የአዲሳባ ማስተር ፕላን

***

ከቤና ገሬ

ከበደ ብሩና ገ/ ተንሳይ የትምህርት ቢሮን የለውጥ ኮሚቴ የመሩ የህውሀት ካድሬዎች ናቸው። ከበደ የህዝብ ንብረት የሆነ ትምህርት ቤት ለግለሰብ ሸጠ። አርከበ ቦሌ ላይ መሬት ሰጠው። መቀሌ ላይ የሙስና መንደር ተብሎ በሚታወቀው ገረቡቡ በሚባል ቦታ ቪላ ሰራ።

የገ/ተንሳይ የሚገርም ነው...

የምረጫ 97 ማግስት የተካሄደውን የመሬት ወረራ አስመልክቶ በረከት ስምኦን በመራው ግምገማ ላይ ወደ ሚሊኒየርነት መሸጋገሩን በራሱ አንደበት አረጋገጠ።

ገ/ ተንሳይ ከብዙ አውጫጭኝ በኃላ የገለፀው ተጠቃሎ ሲታይ የሚከተለውን ይመስላል :-

መጀመሪያ የሚኖርበትን የቀበሌ ቤት በሀምሳ ሺህ ብር ሸጠ። ቀጥሎ አሊ አብዶን አስፈራርቶ ቦሌ ላይ አይን መሬት ወሰደ። የትምህርት ቢሮ ቁሳቁስና ማቴሪያል በመጠቀም ቪላ ቤት ሰራ። ምርጫ ዘጠና ሰባትን ተከትሎ በተካሔደው መሬት ወረራ በራሱ ስም ሁለት፣ በልጁ ስም ሁለት መሬት ወስዶ ሸጠ። ቦሌ የገነባውን ቪላ በግማሽ ሚሊዬን ብር አሻገረ። አርከበ በሲኤምሲ ከተገነቡት የአስተዳደሩ ቤቶች ውስጥ ሩብ ሚሊዬን የጨረታ ዋጋ የተሰጠፈበትን ቤት ያለጨረታ በሰባ ሺህ ብር ያውም በሀያ አመት ተከፍሎ በሚያልቅ ዱቤ ሰጠው። አንድ የቀድሞ ጓደኛው በእግርህ ስትሔድ ማየት አልፈልግም ብሎ የ200 ሺህ ብር መኪና በስጦታ መልክ ሰጠው።

ገሬ ቀልደኛ ነው...

በንዬት ተንተክትኮና አይኑ ቀልቶ የሚያዳምጠውን በረከት ስምኦን መምከር ጀመረ። እንዲህ በማለት :

" *በረከት ዘመኑ ካፒታሊዝም ነው። ከማንም በላይ ይህ ማለት ምን እንደሆነ አንተ ይገባሀል። በጅማሪ ካፒታሊዝም ግንባታ ውስጥ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ካፒታል ማከማቸት ግድ የሚልበት ወቅት ነው። ከታች ወደ ላይ በሚደረገው የሀብት ጉዞ ሽግሽግ ውስጥ የኢህአድግ አባላትን ይዞ መገኘት ለፓርቲው ህልውና ወሳኝ ነው...በዛ ላይ ኦዲሳባን ከእንግዲህ ወደ እኛ የመመለሳችን ሁኔታ የማይቻልበት ...*"

በረከት አልአስጨረሰውም ። ቁጣው ገንፍሎ መጨረሻ ደረጃ ሲደርስ እንደሚያደርገው አፍንጫውን እየጐተተ:-

" ገ/ ተንሳይ ይህንን ጠንጋራ ትንታኔ ቃሊቲ እስር ቤት ውስጥ ጊዜ ስለምታገኝ ቁጭ ብለህ ትጽፈዋለህ " አለው።

ገሬ ፈገግ አለ... እኛ ደነገጥን።

ከዛሬ ነገ ወደ ቃሊቲ ይወርዳል ብለን ስንጠብቅ አቶ አርከበን አጅቦ ከጓደኛው ከቤ ጋር ወደ ስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ሔደ። ከሚኒስትር በላይ በሆነ ደሞዝ የሰው ሀይል ልማት ዋና ዲያሬክቶሬት ሆኖ ተሾመ። ከቤ ደግሞ ምክትሉ።

ይህ ማንም ፍላጐት ያደረበት ተቆርቋሪ ወርዶ ሊያረጋግጠው የሚችል ነውረኛ ታሪክ ነው። ምንም እንኳን ለኢህአድግ አመራሮች አዲስ ባይሆንም። በረከት የታሪኩ ባለቤት ነው። በዝዋይ ህጻናት አምባ ጠቅላይ ሚኒስትር ሀይለማርያም በቁጭት ሲያነሳ ሰምቻለሁ። ከሚኒስትር ሬድዋን ጋር ደግሞ የአርከበን ስጋ በቦጨቅን ቁጥር የገሬ ታሪክ ፊታችን ትደቀናለች።

በረከት በመራው ግምገማ ገ/ ተንሳይ የወንጀሉ ጥፋት በመግዘፉ ፣ግን ደግሞ ለእናት ድርጅቱ ህውሀት ታማኝ በመሆኑ በሹመት ላይ ሹመት ተሰጥቶታል። በተቃራኒው ዳንኤል አርጋው የሚባለው የደኢህዴን ካድሬ የአርከበ ግምገማ ሲቀርብ ብዙ መገለጫዎችን በማንሳት " አርከበ ሌባ ነው! ለሌቦችም ከለላ ይሰጣል፣... አርከበ ዘረኛና አምባገነን(Totaliterian) ነው።" የሚል ማሳመኛ ያቀርባል። ዳንኤል ራሱን አስመልክቶ ሁለት ቦታ መሬት መዝረፉን እያለቀሰ በፀፀት ተናገረ። መሬቶቹን ለመመለስ ፍቃደኛ እንደሆነ ገለፀ።

የዳንኤል ግምገማ የምርጫ 97 ጥፋቶች ሳይሆኑ የተቀለበሰው

የጉራጌ መራሹ አብዬት ላይ የነበረው ሚናን እንዲዘከገዘክ ይገደዳል። እንደሌለበት ደጋግሞ ያስረዳል። ርግጥም ዳንኤል አልነበረበትም። የእምነት ቃሉ አልጠቀመውም። ከድርጅትና ማንኛውም የመንግስት ስራ እንዳይመደብ ይደረጋል። በተመረኩበት የማቲማቲክስ ሙያ የማስተማር ስራ ልመደብ ብሎ ቢጠይቅ በድጋሚ ይከለከላል። ቅሬታውን ይዞ የጉራጌ ካድሬዎች አለቃ ወደ ሆነው ዶክተር ካሱ ኢላላ ጋር ይሄዳል። ዶክተር ካሱ ዳንኤል የሚያቀርበው ቅሬታ ትክክል መሆኑን እንደሚያምንበት ግን ደግሞ እነ አርከበን የሚያካክሉ ዝሆኖች መጋፋት እንደማይችል በግልጽ ይነግረዋል። በወቅቱ ዶክተሩ የስራና ከተማ ልማት ሚኒስትር የነበረ ሲሆን አርከበ ደግሞ የዶክተሩ ምክትል ነበር።

ዳንኤል ለሶስት አመታት ስራ አጥቶ ተንከራተተ። ቅሬታዉን ለማሰማት ያልረገጠበት ቦታ የለም። በመጨረሻም ለአቶ መለስ " የጉራጌ መራሹ አብዬት እንዲቀለበስ ግንባር ቀደም ሚና እንደነበረኝ ከአንተ በላይ ምስክር የለኝም" የሚል ደብዳቤ ላከ። የአቶ መለስ ቅርጫት ውጦ አስቀረው።

ሀገር ጥዬ ከወጣው ከአመታት በኃላ ጓደኛዬ ዳንኤል እቤቱ ድረስ በቴሌቭዥን መስኮት ብቅ አለ። ያውም ቤተመንግስት ግቢ ውስጥ። ወቅቱ ደግሞ የአቶ መለስ ዜና እረፍትን አስመልክቶ ህዝቡ ለቅሶ የሚደርስበት ነበር። እናም ዳንኤል የአልቃሽ ሰራዊት አሰልፎ አንዴ ከፊት ሌላ ጊዜ ከኃላ ይመራል። የድሮ የዩንቨርስቲ ዶርምተሪ ወዳጄ ለአቶ መለስ አለቀሰ ወይስ አስለቀሰ ? ... እንደው ስገምት እንደ ጐዳና ተዳዳሪው ወጣት " አንተን ተማምኜ አርከበን ሌባና ዘረኛ በማለቴ አይቀጡ ቅጣት ተቀጣው" ያለ ይመስለኛል።

***

" ምቴና መውጫ"

የብአዴን ቁንጮዎቹ ተናደዋል...በረከት፣ ህላዌና ፍሬህይወት...

ከንቲባ አርከበን እየተከታተለ መረጃ ይሰጠናል ብለው ከባህርዳር ያስመጡት የብአዴን ካድሬ ከድቷቸዋል።

ቀውላላው ምትኩ ሀበነ ።

ምትኩ በአማራ ክልል የምትገኝ አንዲት ዞን የሲቪል ሰርቪስ ጽ/ ቤት ሀላፊ ነበር። አዲሳባ በመዋጮ እንድትተዳደር በተወሰነው መሰረት ዞኑን ለቆ ወደ መዲናይቱ መጣ። የአራዳ ክፍለ ከተማ ከንቲባ ሆኖ ተመደበ። ከተማው ግር እንዳይለውና የቅርብ ድጋፍ እንድታደርግለት ፍሬህይወትአያሌው ተመደበችለት። መኖሪያ ቤቱና የሚሰራበት ህንጻ እሷ የምትኖርበት አራት ኪሎ ፊት ለፊት ከሚገኙት መንታ ህንጻዎች ሆነ።

ከባህርዳር ሲመጣ መለመሉን እንደሆነ የተገነዘበችው ፍሬ ከኪሷ አውጥታ የቤት ቁሳቁስ ሳይቀር ገዛችለት። አሮጌ ሞዝቦልድ አልጋዋን በስጦታ መልክ ሰጠችው። ቤተሰቦቹን እንዲያመጣ ድጋፍ አደረገችለት።

ምትኩ በተሰጠው ኦረንቴሽን መሰረት ስራውን ጀመረ። ከህላዌ ጋር እየተደረበ አርከበን መቃወም ስራው አደረገው። ታማኝነቱን በተግባር አሳየ። ሁኔታው አላምር ያለው አርከበ ከትግራይ አምጥቶ ምክትል ከንቲባ አድርጐ

የሾመውን መውጫየሚባል የህውሀት ካድሬ አስታጥቆ ላከው... መውጫ የቤት ስራውን በአግባቡ ሰራ።

ምትኩ የቅርብ ድጋፍ እንድታደርግለት ከተመደበችለት ፍሬህይወት ደብዛውን አጠፉ። ከእለታት በአንዱ ቀን ወደ መኖሪያ ቤቱ ሄደች። ያየችውን ማመን አቃታት...

60 ሺህ ብር ወጪ የተደረገበት ቆዳ ሶፉ እንደ ዘንዶ ተዘርግቷል...ለቢሮው ከተገዛለት ጋር ተመሳሳይ ነበር። በወቅቱ የክላስ መለያ ተደርጐ የሚቆጠረው ጠፍጣፉ ቴሌቭዥን ግርግዳውን አድምቆታል። ተመሳሳይ ዋጋ የወጣባቸው ምንጣፎችና መደርደሪያዎች መኖሪያ ቤቱን የአርከበ እቁባይ ቢሮ አስመስለውታል።ወደ ውስጥ ሲገባ ደግሞ የሚኒሊክ አልጋን የሚያስንቅ ሞዝቮልድ የመኝታ ቤቱ ግርማ ሞገስ ሆኗል። የልጆቹ የትምህርት ቤት ወርሀዊ ክፍያ እሱ ወር ጠብቆ ከሚያገኘው ደሞዝ ይበልጣል።

አርከበ ስኳር ካላሰው በኃላ እንደ ሻንጣው ይዞት ይዞር ጀመር። በየመድረኩ ከግራ ጐኑ መቀመጥ ጀመረ። ውጭ ሀገር ህላዌን ተክቶ እስከመሄድ ደረሰ። አርከበ አፍ አውጥቶ "ብአዴን ስራ የማይወደውን ህላዌ ከሚመድብልኝ አንተን ቢያደርግ ኖሮ የት በደረስን ነበር!" በማለት አሞካሸው።

ጨዋራቸው የቆሰለው እነ ህላዌ እሾህን በእሾህ በሚለው ፈሊጥ መሰረት ይሳቅ ቆሪጥ የሚባል የህውሀት ነባር ታጋይ የአራዳ የድርጅት ጉዳይ ሀላፊ አድርገው መደቡ።

ይሳቅ ቆሪጥ በአንድ ስርአት ውስጥ ከሚፈጠሩ ልዩ ሰዎች አንዱ ነው። ይሳቅ ብዙ ሰው ነው:-አለቃ ገብርሀና ፣ቆምጬ አምባው ፣ ወልደስላሴ(የደህንነት ሹም የነበረው)፣ ኢኮኖሚስቱ ንዋይ ገብርአብ አጣምሮ የያዘ ካድሬ ...

አቶ መለስና ሚስታቸውን፣በረከትን ፣ ሽማግሌው ስብሀትን ፣ኢህአድግን ከገቡበት ማጥ አውጥቷል፣ ጉድ ሰርቷል።...ዛሬ ኢህአድግ " ሊግ " እያለ የሚመጻደቅበት አደረጃጀት ባልተጠበቀ ሁኔታ ወደ ተግባር የቀየረ የቁርጥ ቀን ታጋይ ነው።

ይሳቅ ቆሪጥ የአብዬታዊ ዲሞክራሲ ደቀ መዝሙር ነው: እነ አርቲስት አረጋሽኝ ወራሽ፣ ላፎንቴኖች፣ኢዩብ(ነብሱን ይማረውና)፣ ሀመልማል አባተን ኢህአድግ ቢሮ በመጥራት ሊያጠምቃቸው ተግቷል... ይሳቅ ለእመቤቱ ታዛዥ ነበር።

ይሳቅ የፍትህዊነት ንጉስ ነው : ኢንተርናሽናል አልቢትር የሚመራበት እግር ኳስ ውድድር ላይ በክብር እንግድነት ተገኝቶ የገባ ጐል የሚሸር-:" በአብዬታውያን መካከል መሸናነፍ የለም" በማለት :: ... ይሳቅ ቆሪጥ የሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ ፕሬዝዳንት ዶክተር ሀ/ ሚካኤል ያጐናፀፈው ኢኮኖሚስት ነው : የፍላጐትና አቅርቦትን ተዛምዶ የማያውቅ የምጣኔ ሀብት ምሁር...ይሳቅ ቁልፍ ባለስልጣን ነው : ትላንትና የአዲሳባ ኢህአደግ ክንፍ ስራ አሰፈጻሚ ፣ዛሬ ደግሞ የኢትዬጲያ መድን ፈንድ ስራ አስኪያጅ። ይሳቅ ቆሪጥ ራሱን የቻለ መጽሀፍ ነው : " ዘመን ተሻጋሪ ካድሬ " በሚል ርእስ ተጽፎ አልቋል... ተራው ሲደርስ ይነበባል።)

እናም እነ ህላዌ ይሳቅን መምረጣቸው ትክክል ነበር። በአጭር ጊዜ ምትኩ፣መውጫና የትምህርት ቢሮን የለውጥ ኮሚቴ የመራው ከበደ ብሩ የተቀናጁበትን ሌብነት ይፉ አወጣ። ታሪኩ እንዲህ ነው:

አምስት ኪሎ ከሚገኘው ሲኖዶስ ጀርባ አንድ በህዝብ የሚተዳደር አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነበር። ይህ የከተማዋ አይን ቦታ ላይ የተቋቋመ ትምህርት ቤት ከ40 አመት በላይ ያስቆጠረ ሲሆን ባለቤቱ የአካባቢው ህዝብ ነው። ነዋሪው እንደ ማንኛውም የህዝብ ትምህርት ቤት ከመንግስት ድጋፍ አየተደረገለት ልጆቹን ያስተምርበት ነበር።

እናም እነዚህ ካድሬዎች መምህራኑንና ህጻናቱን አባረው ለአንድ ከአሜሪካ ለመጣ ፓስተር ባደግ ለሚባል አጭበርባሪ በዜሮ ዋጋ ይሰጡታል። ፓስተሩም ኢንተርናሽናል ሊደርሺፕ ኢንስቲትዮት የሚል ማስልጠኛ ተቋም ያቋቁማል። እኔን ጨምሮ በረከት፣ሀይለማርያም፣ኩማ፣ሬድዋን፣ሽፈራው ሽጉጤ፣ጁነዲን፣ደግፌ ቡላ፣አስቴር ማሞ፣ጀነራሎቻችን፣የአማራ፣ኦሮሚያና ደቡብ ካቢኔ አባላት... ሸረ ስንቱ ማስተርሳችንን የሰራነው በዚህ የሌብነት ተምሳሌት በሆነ ለዲፕሎማ ማስተማር እንኳን ብቁ ባልሆነ የአየር ባየር ተቋም ነው። የተከበረው ፓርላማ ሚኒስትር በሾመ ቁጥር " በተቋማዊ አመራር " አየተባለ የሚቀርበው የትምህርት ደረጃ የፓስተር ባደግ ልዩ ስጦታ ነው።

በሌላ በኩል ይሳቅ ቆሪጥ ክትትሉን አጠናክሮ ይቀጥላል። ከ200 በላይ የአካባቢውን ነዋሪዎች ፒቲሽን ያሰባስባል። ህዝቡን በአዳራሽ ስብሰባ በመጥራት የተፈፀመውን ሌብነት በካሜራ እንዲቀረጽ ያደርጋል። ለእማኝነትም በአካባቢው የሚኖረውንና የህዝቡ አቤቱታ አልአስቀምጥ ያለውን የኢህአድግ ቢሮ ካድሬው ካሚል አብድርሀማን እንዲሳተፍ ያደርጋል። መረጃዎቹን ከካሚል ጋር አጠናቅሮ ወደ ፀረ ሙስና ሊልከው መዘጋጀቱን ለእመቤቱ በሚስጥር ሹክ ይላል። ሴትየዋም ለባለቤታ አቶ መለስ ታቀብላለች። ነገሮችን አስተሳስሮ የማየት ብቃት ያለው አቶ መለስ ችግሩን ከስር መሰረቱ ለማወቅ የኢህአድግና የብሄር ድርጅቶች ግምገማ እንዲካሄድ ያዛል።

ይህ ግምገማ የተደበቁ ሚስጥሮችን አወጣ። የህገ መንግስቱንና ኢህአድግን ህልውና አደጋ ገጠመው። የሀሪፌ ክልላዊ መንግስት ጥያቄ ውስጥ ገባ። የብአዴን አጣብቂኝ (paradox) በይፉ ተገለፀ። የኢህአድግ ካድሬዎች ባለቤት የሆኑባቸው ሼሮችና አክሲዬኖች ይፉ ወጡ ፣ሽፈራው ሽጉጤ እቤት የተቀመጡ የ80 አመት አባቱን ስራ አስኪያጅ በማስደረግ በወር 10 ሺህ ብር እንዳስቀጠረ ተጋለጠ፣ አባዱላ ምርጫ ተሰጠው (በ5 ሚሊዬን ብር የገነባውን ቤት እንዲያስረክብ አሊያም ከእነ ታምራትና ስዬ ጋር መቀላቀል... ለአህዴድ በስጦታ መልክ አስረከበ: የተዘረፈው ህዝብ የሚወርሰው ድርጅት!!)።

ይህ ሁሉ የተንዛዛ ንቅዘት ይሳቅ የጎተተው ነው። " ዘመን ተሻጋሪው ካድሬ " በሚለው መጽሀፍ ላይ " የፓስተሩ መዘዝ " በሚል ርእስ ሰፊ ቦታ ተሰጥቶታል። ለአሁኑ ወጋችን ይሳቅን ያመጣነው ስለ አዲሳባ እንቁዎች ምትኩና መውጫ ሊተርክልን ስለሆነ ወደዛው እንሻገር።

በምርጫ 97 ማግስት ደግሞ ይህ ሆነ :

ምትኩና መውጫ ለህዝብ ጥቅም ሲባል በዶሮ ማነቂያ የገነቡትን የጥቃቅንና አነስተኛ ሼድ ለባለሀብትና ገንዘብ አዋጥተው ለሰጧቸው ወጣቶች በመቶ ሺዎች ሸጡ። የተስፋ ቃል ሲመገቡ የነበሩ ከ50 በላይ ወጣቶች በይሳቅ ፊትአውራሪነት ሌብነቱን የሚያሳይ ፒቲሽን ተፈራርመው ለኢህአድግ ቢሮ አስገቡ። በረከት በመራው ጉንጭ አልፋ ግምገማ ላይ በዝርዝር ቀረበ። ተሰብሳቢውም ምትኩና መውጫ በግምገማው ላይ እንዲገኙ ጥያቄ አቀረበ።

በረከት ለምትኩ ስልክ ደወለ። መልስ አልሰጠውም። ለአርከበ በንጋታው ይዞት እንዲመጣ ትእዛዝ አስተላለፈ።

በሚቀጥለው ቀን አርከበ ብቻውን መጣ። ምትኩና መውጫ በአፋር ክልል ያለውን የቤት ግንባታ ለመመልከት ወደዛው መሄዳቸውን አስረዳ። በምላሹ የተበሳጨት የብአዴን ዝሆኖች ምትኩን ከድርጅት ማገዳቸውን ይፉ አደረጉ። ከአፋር ሲመለስም ወደ አማራ ክልል በመመለስ የቀድሞውን ሲቪል ሰርቪስ ሰራተኝነቱን እንዲሰራ ወሰኑ።

የሆነው ግን ሌላ ነበር። ምትኩና መውጫ አርከበን አጅበው ወደ ስራና ክተማ ልማት ሚኒስቴር ሄዱ። ምትኩ በቢሊዬን ብር የሚፈስበት የአፋር ቤት ልማት ፕሮጀክት ዋና ዴሬክተር በመሆን በወር 15ሺህ ብር የሚከፈለው ባለስልጣን ሆነ። ያለ ጨረታ በመቶ ሚሊዬኖች እየወጣ ሲምንቶና ብረት የሚገዛበት ተቋም በንብረትነት ተሰጠው... ከተገዛው ውስጥ ምን ያህሉ አፋር እንደሚደርስ እግዜር ይወቀው!...

በመጨረሻው ውጤት የተበሳጨው ይሳቅ ቆሪጥ መላ ዘየደ። የክስ ዶሴዎችን ይዞ ፓስተሩ ጋር ሔደ። እየገላለጠ አሳየው... አፍታም ሳይቆይ በተቋማዊ አመራር ማስተርስ በማግኘት እኛን ተቀላቀለ... የልጆቹን ስም አስተካክሎ መጻፍ የማይችለው ይሳቅ በኢኮኖሚክስ ባችለር፣ በሊደርሺፕ ማስተርስ አለው።

***

ሮምና ሉሌ

ሉልሰገድ ይፍሩ...

የዛሬዎቹ የአዲሳባ ካቢኔ አባላት ፀጋዬና ሺሰማ " ኮረኔል ! የቁረጠው ፍለጠው ጌታ " ይሉታል። አገዛዙ ወታደራዊ አምባገነን መሆኑን ለማሳየት። በተለይ ሺሰማ ሰለ ሉልሰገድ ባህሪ ሲገልጽ:

" *መጀመሪያ እንደ ዶሮ አንገትህን ጠምዝዞ ይገልህል... ቀጥሎ ቢሮው ወስጥ ጥልቅ ጉድጓድ በመቆፈር ይቀብርሀል... ጠዋት ሰራ ከመጀመሩ በፊት ወንበሮቹን እያነሳሳ አለመነሳትህን ያረጋግጣል* " ይለዋል።

ሉልሰገድ (ሉሌ) ማለት ይህ ነው። እንደስያሜው ከእንቅልፉ በተነሳ ቁጥር አንድ ሰው ያባርራል። ስራውን በአባረራቸው ሰዎች ቁጥር ይለካል። ደብዛቸውን ለማጥፉት ያሰባቸውን ካድሬዎችና የመንግስት ሰራተኞች የማይገረስስ ስም አስቀድሞ ይለጥፉል : - " የምሁር ትምክህት አለበት" ፣ " የኦነግ ባንዲራ እቤቱ ተገኘ"፣ " የህገመንግስቱን አንቀጽ 39 አይቀበልም"፣ "በመአድ ስብሰባ ላይ ተገኝቶ ነበር"...

ይህ ጭካኔው በአብዬታዊ ታጋይነት እንዲቆጠር አደረገው። የአሊ አብዶ ቀኝ እጅ ሆነ...የአሊን የብቃት ማነስና የፈፀማቸውን ወንጀሎች ያጋለጡ ካድሬዎችን እያሳደደ ደፈጠጠ። የምርጫ ኮሮጆ ግልብጥብጡን በማውጣት አሊን ከመሸነፍ ታደገው።

አሊ አብዶም ቢሆን የሉሌን ውለታ መርሳት አልፈለገም። ራሱን የማልረባ ፣ዝርክርክ ፣ ዘባተሎ ባለ በወሩ የተካሄደ ምደባ ላይ አውራ ሆኖ ተገኘ። ለነባሩ የአዲሳባ ካድሬ በክፍለ ከተማ ለመመደብ የመጀመሪያ ዲግሪ እንደ ቅድመ ሁኔታ ቢወሰድም፣ ለሉሌ እንደ ህውሀት ካድሬዎች 12 ኛ ክፍል በቂው ተደርጐ እንዲያዝለት አደረገ። በዘመነ አርከበ የአዲስ ከተማ ከንቲባ እንዲሆን አደረገ።

በአፍሪካ ትልቁ ገበያ የሆነችውን ውስብስቧን መርካቶ መምራት በሉሌ አቅም የሚሆን አልነበረም። የታቀዱ ስራዎች ዘጭ ብለው ወደቁ። በተለይ ከፍተኛ ግብር ይሰበሰብበታል ተብሎ ተስፉ የተጣለበት የንግዱ ዘርፍ ነጠፈ። አርከበና ሉሌ ግብግብ ገጠሙ። አፍታም ሳይቆይ አርከበ ከትግራይ ሮማን ተስፉይ የምትባል ካድሬ አምጥቶ ስራ አስኪያጅ ሾመ... ሮማን ወፍ ከሰማይ የምታረግፍ፣ በንግግሯ አራት ነጥብ የማታውቅ የመቀሌ ጨልሌ ናት።

ሉሌ የማይጋፉው ባላጋራ ስለገጠመው የሀይል አሰላለፍ ቀየረ...ለህላዌና በረከት ገበረ። ይህን ያወቀው አርከበ ሉሌን ለማባረር የሚያስችሉ ጥፉቶችን የከተማው ካድሬዎች በተሰበሰቡበት ዘረገፈ። እንዲባረር አሊያም ከደረጃው ዝቅ እንዲል የውሳኔ ሀሳብ አቀረበ። ህውሀቶች የድጋፍ አስተያየት አቀረቡ።

ከበረከት ጋር ተማክሮ የመጣው ህላዌ ካድሬው በተሰበሰበበት" ብአዴን ስላልፈቀደች የሉልሰገድን ጫፍ እንዳትነካ!" በማለት አርከበንና የህውሀት ካድሬዎችን አስጠነቀቀ።

በነገራችን ላይ " ብአዴን አልፈቀደችም" ፣" ህውሀት እያየችው ነው" ... " አህዴድ አላመነበትም "የሚሉ ቃላቶች በኢህአድግ ደጃፍ የተለመዱ ናቸው። ኢህአድግ የግለሰቦች ስብስብ ስላልሆነ የማባረር ስልጣን የለውም የሚል ምክንያት ይቀርባል። የብሄር ድርጅቶቹ የሌባ ጫካ ፣ሙሰኛ ካድሬዎች ደግሞ አፍቅሮ ብሄር የሆኑባቸው አንዱ ምክንያት ይህ ነው። ኢህአድግ ያባርራል... ህውሀት ይሾማል!... ኢህአድግ ሌባ ይላል... አህዴድ ለአምባሳደርነት እጩ አድርጐ ይመጣል።

የማባረሩ አማራጭ እንደማይሰራ የተገነዘበው አርከበ ከሉሌ ጋር ያለውን ግንኙነት ሙሉ ለሙሉ አቋረጠ... ስብሰባ አይጠራውም። ስራውን አይገመግምም። ሉሌ ችግሮት እንኳን ለአርከበ ቢደውል " ከሮማን ጋር ተነጋግረናል እሷ ትሰራዋለች" ይለዋል።

የሉሌ የመርካቶ ከንቲባነት የስም ብቻ ሆነ። የመንግስት ሀላፊነቱ ባዶ ሲቀርበት ወደ ፓለቲካ ስራ አዘነበለ። ይህም የሚሆን አልነበረም : የህውሀት ካድሬዎች ሉልሰገድ አይመራንም በማለት ተገንጥለው ወጡ። ሀይሌ ፍስሀና ፀሀይቱ ባህታ ከላፍቶ መርካቶ እየተወረወሩ ህውሀትን መምራት ጀመሩ። በዚህም ምክንያት የአዲስ ከተማ ኢህአድግ ለሁለት አመት ያህል (እስከ ምርጫ

97) ድረስ የሶስት ብሄር ድርጅቶች ጥምረት ነበር... ብአዴን፣ኦህዴድና ደኢህዴን።

ሮማን በበኩሏ አዲስከተማን ነገሰችበት።መርካቶን አሳርሳ ለአዲሶቹ የህውሀት ባለሀብቶች ቸበቸበች።አርከበ ከባላንጣዎቹ እነ ተወልደና አለምሰገድ ተረክቦ ያስቀጠለውን የህውሀት ባለሀብቶች መፍጠር አላማ ዋነኛ አስፈጻሚ ሆነች...የህውሀት ነጋዴዎችን የመፍጠር ስትራቴጂ አዛው ሳለ የጉራጌ ነጋዴዎችንና ባለሀብቶችን ማዳከም የሚል አላማ ነበረው። ኢኮኖሚውን የሚቆጣጠር ሀይል በሒደት ፓለቲካል ኢኮኖሚው ላይ የበላይነት ማሳረፉ ስለማይቀር ጉራጌን ከንግዱ አለም ማስወጣት ለጥያቄ የሚቀርብ አይደለም። ሮማን የጉራጌ ነጋዴዎችን እንዳያንሰራሩ የምትቀጣበት ምክንያት ይህ ነበር።

እነ አባዱላና ግርማ ብሩ ይህንን ስትራቴጂ በመከረጅ ናዝሬትን ጨምሮ በኦሮሚያ ትላልቅ ከተሞች የኦህዴድ ባለሀብቶችን ለመፍጠር ተንቀሳቅሰዋል።

እነ ሮማን በፈጠሩት ልዩነት ጉራማይሌዋ መርካቶ ይበልጥ ተዘበራረቀች።ተመሳሳይ እቃዎች በነባሮቹና አዲሶቹ ነጋዴዎች መካከል የዋጋ ልዩነት አሳየ።የግብርና ሊዝ እፎይታ ያገኙት አዲሶቹ ነጋዴዎች ዋጋቸውን አወረዱ...ሽማቹ ሚስጥሩ ሳይገባው ቅናሽ ወዳገኘበት አዲሶቹ ፊቱን አዞረ።ቀስ በቀስ ነባሩ ነጋዴ ከገበያ ወጣ።

የማፊያ ባህሪ ያላቸው አዲሶቹ ነጋዴዎች ሰው ሰራሽ እጥረት በማስከሰትም ተወዳዳሪ አልነበራቸውም።በሰአታት ውስጥ የአንድ ኪሎ ጨው ዋጋ ከአንድ ብር 50 ብር የተሸጠበትን አጋጣሚ ልብ ይሏል።

ነባሩ ነጋዴ ከገበያ መውጣቱ እልህ የተጋቡት የጉራጌ ካድሬዎቹ እነ ሺሰማ ክትትል ማድረግ ይጀምራሉ።ከብዙ ጥረት በኃላ ሽፍጥ የሚሰራበትን ቦታ ይደርሱበታል።...ሮማንና ወዳጆቿ ፉይል የሚሰርዙና የሚደልዙት፣ግብር የሚጨምሩትና የሚቀንሱት፣ሱቅ የሚሰጡትና የሚቀሙት አምባሳደር ፊልም ቤት የሚገኘው ካፍቴሪያና ሆቴል ነበር። ይህ በህውሀት ነባር ታጋይ ባለቤትነት የተያዘ ካፍቴሪያ የህገወጥነቱ ማእከል ነበር።

ከምርጫ 97 በኃላ የጉራጌ አብዬትን ለመቀልበስ በስብሰባ ማእከል በተጠራ የመጀመሪያው ዙር ማጠቃለያ ኮንፍረንስ ላይ ተገኝቼ ነበር።በጉባኤው የተሳተፉት የጉራጌ ነጋዴዎችና ባለሀብቶች ነበሩ። ይህን ለአንድ ሳምንት የዘለቀ ጉባኤ የመራው ዶክተር ካሱ ኢላላና ሚኒስትር መኩሪያ ነበሩ። ነጋዴዎቹ በሲቃ ስለ ሮማንና ሉሌ የሚያነሱት ወንጀል ጨንራ የሚልጥ ነበር።በተለይ የክፍለ ከተማው የገቢዎች ኤጀንሲ ሙያተኛ የሆነ የጉራጌ ተወላጅ ስራዬን ለመልቀቅ ብዙ ተሟግቻለው በማለት የገለፀው ታሪክ ዶክተር ካሱ አንገቱን አቀርቅሮእንዲቀር አድርጐታል። ከመቀመጫው ተነስቶ የኮንፍረንሱን ተሳታፊ እንባ እየተናነቀው ይቅርታ ጠይቋል።

ሉሌና ሮማን ከቢሮአቸው ሳይወጡ ከአስር እጥፍ በላይ ግብር እንዲጥሉ ሙያተኞቹን አስገድደዋል። ከስረው ለመዘጋት አፋፍ ላይ ያሉ ነጋዴዎችን ከግብር ህጉ በተቃራኒ ታክስ አስከፍለዋል። በድርጊቱ የተበሳጨ አንድ ነጋዴ ራሱን በገመድ አንጠልጥሏል...ተመሳሳይ ሱቅና የንግድ አይነት ያላቸውን ጉረቤት ነጋዴዎች አንዱን በዜሮ ፣ሌላውን በአስር ሺዎች ታክስ

እንዲከፍል አድርገዋል።ይህ በዘር ላይ የተመሰረተ እርምጃ ቀድሞ በነጋዴዎች ዘንድ የነበረን መደጋገፍ እንዲቀር በማድረግ አርስ በራስ በጥላቻ እንዲተያዩ አድርጓል። በዚህ ምክንያት መሳሪያ የተማዘዙ፣በገጀራ ተፈነካክተው ወህኒ የወረዱ ነጋዴዎች ይገኛሉ።

ሉሌና ሮማን ሲሰሩ የከረሙት ይህንን ነው። በረከት በመጽሀፉ ገጽ 310 ላይ ደግሞ :-

" *...የኢህአዴግ አመራርና ኮትኩቶ ያሳደጋቸው ታጋይች፣እጅግ ወሳኝ የሆነው ጥንካሬያቸው ለህዝብ የተለየ ፍቅር፣ አክብሮትና የፀና ወገናዊነት የነበራቸውና ያላቸው መሆኑ ነው ።አመራሩና ታጋይቹ ህዝብ ሲበደል አይወዱም። በህዝብ ላይ የሚፈጸም ግፍና በደል አምርረው ይጠላሉ ።የሚጠሉትን ግፍና በደል በፅናት ይታገላሉም።ከባድ መስዋዕት ቢጠይቅም ባይጠይቅም። የኢህአዴግ አመራርና በትግል እሳት ተፈትነው ያለፉት የድርጅቱ አባላት ህዝብ እንዳይጐዳ፣ይልቁንም መብቱና ጥቅሙ ተከብሮለት ይኖር ዘንድ ፣ ብዙዎች ሊከፍሉት ቀርቶ ሊያስቡትም የማይቻላቸውን መስዋዕት እድሜ ልካቸውን እየከፈሉ የዘለቁት ፣በእርግጥም ለህዝብ ሲሉ የመሰየፍን ዕዋ ሊጐነጩ የተዘጋጁ በመሆናቸው ነው።* " ይላል።

ለዚህ የበረከት መልእክት ቀላል ጥያቄ እናንሳ:-" አቶ በረከት ስለእነማን አያወራነው ? ":-...አዲሳባ ከንቲባ እንዲሆን ፈልገ የነበረውን መላኩ ፋንታ፣... የጉምሩክ ሹሙን ገ/ ዋህድ፣...የኤርትራውያን ንብረት የዘረፈውን የደህንነት ሀላፊ ወልደስላሴን፣...በሚሊዬን ብር ምልጃ ልጆቻቸውን ቻይና ያስተማሩት ሽማግሌው ስብሀት ነጋና አርከበ ፣የስብሀት ነጋ የአጐት ልጅ የሆነውና በሚሊዬን ዶላር የኤፈርት ገንዘብ ይዞ የተሰወረውን ጌታቸው በላይ፣... የሁለት ቪላ ቤት ባለቤቱን አባዱላ፣... ሞላጫ ሳሙና እያለ የሚጠራቸውን አምባሳደር ግርማ ብሩና ሚኒስትር መኩሪያ፣ ... አቶ ሽጉጤን በስተርጅና የቡና ልማት ስራ አስኪያጅ ስላደረገው ሽፈራው ሽጉጤ፣... የዛፍ ላይ እባብ ብሎ የሚጠራውን አርከበ፣... የጨለማው ዘመን ንጉስ አሊ አብዶን፣ ቪላቸውን በዶላር አከራይተው ግብር የማይከፍሉትን አምባሳደር ተሾመ ቶጋንና አምባሳደር ገነት ዘውዴን፣ የደሀ አጥንት የጋጠውን አምባሳደር ቶፊቅ አብድላዚን...፣ጀነራል ፣ገ/ ተንሳይን፣ዶክተር አብርሀምን፣ ሀይሌ ፍስሀን፣አዜብ መስፍንን፣ምትኩ ሀበነን፣ ሮማን ተስፋይን ...

እናም አቶ በረከት ከራስ ተሻግሮ ስሌላ በጥቅሉ መናገር ውጤቱ አስከፊ ይሆናል። ስለ በረከት የግል ንጽህና ተናገር ቢሉኝ ለአመታት ከአካባቢው እንደሰራ ሰው በሙሉ ልቤ ልመሰክር እችላለሁ። ሌላው ቀርቶ የወገቡ ቅማል አድርጐ የሚቆጥረው ጋዜጠኛ ተስፉዬ ገብርአብ ጨዋነቱን መስክሮ አንብቤያለሁ። ከእሱ በተጨማሪ ስለ ሐይለማርያም፣ አዲሱ ለገሰ፣ተፈራ ዋልዋ፣አባይ ጸሀዬ ፣ሴኩቱሬ፣ፍሬህይወት፣ሶፊያን አህመድ፣ዶ/ ር ቴዎድሮስ አድሀኖም፣ሙክታር ከድር፣አለማየሁ አቶምሳ፣ሽመልስ ከማል ብጠየቅ የተለየ መልስ የለኝም። ቁም ነገሩ ይህ አይደለም። የኢትዬጲያ ህዝብ እናንተን የሚመዝናችሁ ባሰፈናችሁት ተቋማዊ ስርአት ነው:- በተቋም ደረጃ ሌብነት አለመፈፀም፣አድልኦ አለማድረግ...

***

ሮማን የመርካቶ ንግስናዋን ምርጫ 97 አደናቀፈው። የጡት አባቷ የሆነውን አርከበ እቁባይ አጅባ ወደ ስራና ከተማ ልማት ሄደች።ባላንጣዋ ሉሌ ደግሞ ወደ ኢህአድግ ቢሮ የአዲሳባ ክንፍ በመመደብ ወደ ህላዌ መጣ።

በኢህአድግ ቢሮ የካድሬነት ዘመኔ የሮማን ስም በተነሳ ቁጥር አብሮ የሚደመጥ አስደማሚ ታሪክ አላት። አማተር ሌብነቷን ያሳበቀችበት ነበር። ሚስጥሩን ፈልፍሎ ያወጣው ይሳቅ ቆሪጥ በመሆኑ " ዘመን ተሻጋሪው ካድሬ " በሚለው ማስታወሻ ላይ እንዲካተት ተደርጐ ነበር። ይሳቅ ተዝቆ የማያልቅ ባህርነውና በጭልፋ ብንወስድበት አይጐዳም። እናም ስለሮማን ትንሽ እናውጋ... የመቀሌዋ ጨልሌ:-

ነጋና አባተ

አርጌው አውሮፕላን ማረፊያ አገልግሎት መስጠት ካቆመ ቆይቷል። ይህ ከጦር ሀይሎች እስከ ሳርቤትና ልደታ የተለጠጠ ሜዳ ተጉዘውበት የማያልቅ ነው። ኢህአድግ አዲሳባን ከተቆጣጠረ በኃላ አገልግሎት መስጠት በማቋረጡ እንደ ጥቁር ዘንዶ የተጥመዘመዘው የኢሊኮፍተር ማረፊያ የተቦዳደፈና ከቁመት በላይ በሆነ ሰንበሌጥ የተሸፈነ ሆኗል። ይህ ደረቱን ገልብጦ ያለ ስራ የተቀመጠ ቦታ ለብዙ ነዋሪዎች ጥያቄ የፈጠረ ነበር። እርግጥ በሳር ቤት በኩል ከፊሉ ተቆርሶ ለሼህ አልአሙዲ ተሰጥቷል። ሼሁ መለስተኛ ህንጻዎችንና " መቻሬ ሜዳ" በመባል የተሰየመ የእግር ኳስ መጫወቻ ስታዲዬም ገንብተውበታል።

ርግጥ የክፉ ቀን በመጣ ቁጥር በጥቅም ላይ በመዋሉ የኢህአድግ ባለውለታ ነው። በኢትዬ ኤርትራ ጦርነት ስንቅና ትጥቅ የሚያመላልሱ ኢሊኮፍተሮች አጨናንቀውት ነበር። የህውሀት ክፍፍል ወቅት አቶ መለስ ወደ መቀሌ የተመላለሱበት መነሻ ከዚህ ቦታ ነበር። በምርጫ 97 ማግስት የሆነውም ተመሳሳይ ነበር...

በምርጫ 97 ማግስት በዋለ አንዲት ጠዋት አራት ኢሊኮፕተሮች ተከታትለው በአሮጌው አውሮፕላን ማረፊያ ሜዳ ላይ አረፉ። የአካባቢው ነዋሪ የኢትዬ ኤርትራ ጦርነት የተቀሰቀሰ መስሎት በሀዘን ተዋጠ። እኛ ካድሬዎች ደግሞ አቶ መለስ ያቋቋመውን ሰባት ማዘጋጥ ጣቢያ ለማጠናከር የመደባቸው ተጨማሪ ወታደራዊ መኮንኖች እንደሆኑ ጠረጠርን። እኛም ሆነ ነዋሪው የገመትነው ልክ አልነበረም...

ከኢሊኮፕተሯ ውስጥ የወጡት ስምንት የኮረኔል ማእረግ የለበሱ ወታደሮች ነበሩ። መኮንኖቹ በቀጥታ ፊትለፊታቸው ወደሚገኘው የኮልፌ ቀራንዬ ክፍለ ከተማ ሄዱ። የከንቲባ አባተ ስጦታው ቢሮ ወረሩት። መሬት እንደሚሰጥ መረጃ ደርሶአቸው ከጦር ግንባር እንደመጡ ነገሩት። እያንዳንዳቸው የማህበር ስም የተሰጣቸው የአስራ ሁለት መኮንኖች ስምዝርዝርና ፊርማ የያዘ ወረቀት ሰጡት... " ዘመቻ ፀሀይ ግባት የቤት ማህበር" ፣ " ሀየሎም አርአያ የቤት ማህበር" ፣ " ዛላአንበሳ ቤት ማህበር"፣...

አባተ ደነገጠ። የተሰጠው መመሪያ ስለሌለ እንደማይፈርም ተናገረ። መንግስታዊ አሰራርን አስረድቶ ሳይጨርስ ግንባሩ ላይ ከተደቀነ ሽጉጥ

ጋር ተጋፈጠ። ማስፈራሪያዎች ተሻገሯደጉዱ :-" የቅንጅት ተላላኪ መሆንህን ደርሰንበታል" ፣ "ኢህአ ድግ እንዲሸነፍ ያደረጋችሁት እንዳንተ ያሉ ሰርጐ ገቦች ናቸው"፣ "እዚሁ ደፍተንህ እንሄዳለን "...

በዚህ አሰጨናቂ ሰአት ነበር ምክትል ከንቲባው ነጋ በርሔ የአባተን ቢሮ በርግዶ የገባው። አባተ ላይ ከተነጣጠረው ሽጉጥ አንዱ ወደ እሱ ዞረ። ነጋ የዶሮ ላባ የተደቀነበት እንኳን አልመሰለውም። መሳደብ ጀመረ:-

" ነፍጥ ከእናንተ በፊት አንግበን ተራራ ደርምሰናል። የምታስፈራሩትን ሂዱና ሌላ ቦታ አስፈራሩ " ይላቸዋል። ተደናግጠው መሳሪያዎች ወደ አፎታቸው ይመልሳሉ። ሙልጭ አድርጐ ከሰደባቸው በኃላ ከንቲባውን ይቅርታ እንዲጠይቁ ያዛቸዋል። ወታደራዊ ይቅርታ ጠየቁ። ነጋ የመጨረሻውን ተግሳጽ ተናገረ:-

" ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ጥያቄያችሁን ብታቀርቡ ኖሮ አባተ እንኳን ቤተሰባችሁን ጥላችሁ ግንባራችሁን ለጥይት ለምትሰጡት ቀርቶ ለሌላውም አይጨክንም። ያውም አቀናት በኃላ ጠላት ተረክቦ ለሚዘርፉት አዲሳባ ! "

አባተ መሬቱን ፈቀደ።

መኮንኖቹ የተሰጣቸውን መሬት እንኳን ማየት አልፈለጉም። እያንዳንዳቸው ከግማሽ ሚሊዬን ብር አየር ባየር ተቀበሉ። ለሊቱን ሙሉ ከበረሀ ትግል ጓዳቸው ነጋ በርሔ ጋር የጥንቱን እያወጉና እየጨፈሩ አሳለፉ። ወፍ ሳይንጫጫ አመስግነውት ወደ ግንባር ተመለሱ።

ነጋ ተልእኮውን በማጠናቀቁ አቶ መለስ በብርሀን ፍጥነት መቀሌ ላከው። የህውሀት ማእከላዊ ኮሚቴና የትግራይ ክልል ካቢኔ ውስጥ ተቀላቀለ። በረከት በመራው ጉንጭ አልፉ ግምገማ በአስቸኳይ እንዲመጣ ቢጠየቅ " አትቀልዱ!በድሮ በሬ ያረሰ የለም ! " በማለት ቀረ። ዘመን አለፈና አዲሱ ለገሰን ለማገዝ ኢህአድግ ቢሮ የስልጠና ማእከል ተመደበ።

የአዲሳባ ልጆች የሆኑ ፀጋዬ ፈለቀና ፀጋ የሚባሉ የላፍቶና የቦሌ ካድሬዎች አንድ መሬት ወስዳችኃል ተብለው ከካድሬነትና የመንግስት ስራ ተባረዋል፣በተቃራኒው ቀራንዬ ላይ የተንጣለለ የመንግስት ቤት የወሰደውና ቦሌ ላይ መሬት የወሰደው ነጋ በርሔ በሳይናሳዊ መተካካት ማእቀፍ ውስጥ ተካቶ አዲሱ ለገሰን ለመተካት እየተዘጋጀ ነው።

ምስኪኑ አባተ ድራማውን የተገነዘበው ውሎ ካደረ በኃላ ነበር። በምደባ ወቅት የአዲሳባ ኢህአድግ ቢሮ አባል እንዲሆን ተደረገ። በአሁን ሰአት በስራ ትጋቱ የአዲሳባ ምክትል ከንቲባ ሆኗል...በግል እውቀቱ ንጽህናውንና ታታሪነቱን መመስከር እችላለሁ። ይገባልም። ምንም እንኳን ከእንክርዳድ ክምር ውስጥ የተወሸቀ ስንዴ ቢሆንም።

***

ዶክተር አብርሀምና ሀ/ ስላሴ

ከምርጫ 97 በኃላ የነበረው ጊዜ ለከንቲባ ጽ/ ቤት ሀላፊው ዶክተር

አብርሀም ምቹ አጋጣሚ ነበር። አዲሳባን ለማጥፋት ቆርጦ የተነሳው አርከበ ብዙዎቹ የፈፀማቸው ወንጀሎች በዶክተር አብርሀም አማካኝነት ነበር።

ከአሊ አብዶ ዘመን ጀምሮ የአዲሳባ አስተዳደር በተለያዩ ቦታዎች ዘመናዊ አፓርትመንቶችንና ቁጠባ ቤቶችን አስገንብቷል...በፈረንሳይ ፣ ቃሊቲ ፣ ሲኤምሲና አቃቂ። አነዚህ ቤቶች በተለያየ ጊዜ ለጨረታ ቀርበው መነሻ ዋጋቸው ከፍተኛ በመሆኑ ለብዙ አመታት ሳይሸጡ ቆይተው ነበር።

በምርጫ 97 ማግስት እነዚህን ቤቶች የማጥፋት ሀላፊነት ለዶክተር አብርሀም፣ ለአርከበ ጠባቂዎችና ሹፌሮች ተሰጠ። ለአመታት የጨረታ መነሻ ዋጋው 150 ሺህ ብር የነበረ ቤት በ50 ሺህ ብር አሻገሩት። በአንድ ሳምንት ውስጥ ከ200 ቤቶች በላይ ሸጠው ከሀያ ሚሊዬን ብር በላይ የህዝብ ገንዘብ ወደ ኪሳቸው አስገቡ።

ቀጥሎ ዶክተር አብርሀም የቦሌ ክንቲባ የሆነውን ሀ/ ስላሴ እንዲያግዝ ተመደበ። እስቲ ቦሌ ላይ የተደረገውን ጆሮአችንን ደፍነን እናንብብ:-

የቦሌን የመሬት ዝርፊያ የመሩት ሶስት የህውሀት ካድሬዎች ናቸው :- የክንቲባ ጽ/ ቤት ሀላፊው ዶክተር አብርሀም፣ የቦሌ ክንቲባው ሀ/ስላሴና ትምህርት ቢሮን ያገላበጠው ገ/ ተንሳይ ናቸው። ሶስቱ ጓዶች በመጀመሪያ ያደረጉት በፌዴራል ተቋማትና አዲሳባ ተመድበው ለሚሰሩ ካድሬዎችና ባለስልጣናት መሬት መስጠት ነበር። የሀገሪቱ ደህንነት፣የፌዴራል ፓሊስ፣ ኢህአድግ ቢሮ፣አጋዚ ክፍለ ጦር፣የመከላከያ ጀነራሎች፣ ኤፈርት፣ ዋልታ፣ሬዲዬ ፋና፣የአዲሳባ ከተማና ክ/ ከተማ ካድሬዎችና ባለስልጣናት ሙሉ ለሙሉ በሚባል መልኩ መሬት የወሰዱት በዚህ ክፍለ ከተማ ነው።

ሶስቱ ካድሬዎች ወሳኝ የሆኑ አካላትን አፍ የማዘጋት ስራ በዚህ መልኩ ካከናወኑ በኃላ ፊታቸውን ወደራሳቸው አዞሩ።

ዶክተር አብርሀምና ሀ/ ስላሴ ከመከላከያ ሚኒስቴር ፋይል ውስጥ የትግል ዘመናቸው ከ1978 በፊት የነበሩት ባለማእረጐች ዝርዝር በማስመጣት አስራ ሁለት ሰዎች የያዘ ሁለት ማህበር ፈጠሩ። መሬቱን ከወሰዱ በኃላ በዛው ሳምንት ስም አዘዋውረው ሸጡ።

ገ/ ተንሳይ የመጀመሪያ ልጁን አሰማራ። ይህ የአባቱ ልጅ በህይወት የሌሉ ሰዎችን ጨምሮ አንድ ማህበር መስርቶ መሬት ወሰደ። በጥሩ ዋጋ አሻግሮት የሚሊኒየሮች ጉራ ተቀላቀለ።

በጉንጭ አልፋው የበረከት ግምገማ ይህ ሀቅ በዝርዝር ቀረበ። በግምገማው ላይ ዶክተሩ እንዲገኝ ግፊት ቢደረግም አርከበ ለአስቸኳይ ስራ ወደ ክልል ሄዷል በሚል እንዳይገኝ አደረገ።

አቶ በረከት " ስልጣንን ለህዝብ ጥቅም እንጂ ለራስ ጥቅም ማካበቻ አላደረግንም" በሚለው ስሌት መሰረት ዶክተር አብርሀም አርከበን አጅቦ ወደ ስራና ከተማ ልማት ነጐደ። ቀጥሎም የዘመናዊ አመራር መተካካት ውስጥ የቀጣዩ ጉዞ መሀንዲስ በሚለው እንዲካተት ተደርጐ የኢኮኖሚና ፋይናንስ ምክትል ሚኒስትር ሆነ። በሚቀጥለው የኢህአድግ ዘመን ሶፊያን አህመድ አምባሳደር ሲሆን በሙሉ ሚኒስትርነት ዶክተር አብርሀምን እናገኛለን... ከፊት መስመር ገለል ያለው አርከበ ከኃላና ከጐን ሆኖ የመደገፍ ስራ እንደሚሰራ

ይጠበቃል።

የቦሌ ክንቲባው ሀ/ ስላሴም ቢሆን በጉንጭ አልፉው ግምገማ አልተገኘም። አርክበ አስቀድሞ አርቆታል: የትግራይ አንዲት ዞባ አስተዳዳሪ በማድረግ።

የቀረው ገ/ ተንሳይ ነው። ገሬ ደግሞ የዘመነ ካፒታሊዝም ምክሩንና ቀልዱን አልጨረሰም...የህውሀት የምንግዜም ባላንጣ ተደርገው የተፈረጁት የአዲስ ከተማ ክንቲባ ሉልሰገድ እና የቦሌ ምክትል ክንቲባ ሊሻን እየተቀባበሉ አስጨነቁት:-

" ገ/ ተንሳይ ልጅህ በወሰደው መሬት ተጠያቂ ነህ!"

ገሬ መልስ ሰጠ:-

" እናንተ የህውሀት ጠላት እንደሆናችሁ ፀሀይ የሞቀው ነው። ቅንጅት አዲሳባን መረከብ አለበት ብላችሁ ስትከራከሩ ነበር።"

በረከት ጣልቃ ገብቶ " ገ/ ተንሳይ ያልበላህን አትከክ! የተጠየቅከውን ብቻ መልስ።" አለው።

ገሬ አሳማኝ መከራከሪያ አቀረበ:-

" እነ ተወልደና ስዬ የድርጅታችንን ሊቀመንበር ለማባረር ስለ ወንድሙ ኒቆዲሞስ ዜናዊ ጠይቀውት ነበር። አሱም ኒቆዲሞስ ከ18 አመት በላይ ስለሆነ እና በእኔ ቁጥጥር ስር ስላይደለ የፈለጋችሁትን ልታደርጉት ትችላላችሁ አላቸው። እኔም ከዚህ ውጭ መልስ የለኝም።" ብሎ ወደ ኃላ በመሄድ ታሪክ አጣቅሶ ተናገረ።

ግምገማው ገሬን ወደ ስራና ከተማ ልማት ከመሄድ አልአገደውም። ልጁንም የጠየቀ የለም። በተቃራኒው የክፍለ ከተማው ምክትል ክንቲባና ነባር ካድሬ ሊሻን ሁለት መሬት ወስጃለሁ፣ አንዱን ሸጨዋለሁ የተቀረውን ለመመለስ ፍቃደኛ ነኝ ቢልም ከድርጅትና መንግስት ስራ ከመባረር አልአመለጠም።

***

ግርማጲዬንና ሚደቅሳ

የሁሉ ደነቀውና ሚደቅሳ ጓደኛሞች ናቸው። የሁሉ ከባህርዳር የመጣ የብአዴን ጓድ ሲሆን ሚደቅሳ ደግሞ አባዱላ የላከው ነው።ሁለቱ ካድሬዎች የካ ክፍለ ከተማ በመመደባቸው ምክንያት ከካድሬነት ያለፈ ጥብቅ ቁርኝት ፈጥረዋል። ብዙ ሚስጥሮች አብረው ሰርተዋል... ብአዴኑ የሁሉና ቁመተ ሎጋው ሚደቅሳ...

ከእለታት በአንዱ ቀን በክፍለከተማቸው እየተካሄደ ያለ ወንጀል ጥቆማ ይደርሳቸዋል...ሰዎች አሰማርተው መከታተል ይጀምራሉ። የእነሱ ፍላጐት ከወንጀሉ በስተጀርባ ያሉትን ማወቅ ነበር። ታሪኩ እንዲህ ነው:

ከምርጫ 97 ማግስት እራሷን " ገነት" ብላ የምትጠራ ግለሰብ እንደ ድሮ ባላባት ባዶ መሬት እየመተረች አየሽጠች እንደሆነ መረጃ ይደርሳቸዋል። ከብዙ ጥረት በኃላ ሞባይል ስልኳ እጃቸው ላይ ይገባል። እናም ይደውሉናአራት ቪላ ቤቶች ለመስራት የሚያስችል መሬት እንደሚፈልጉ ይነግሯታል። እሷም አስተዳደሩ ባስቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት የመገንባት አቅም ካላቸው በካሬ ሜትር መንግስት ከሚሸጥበት ሩብ ዋጋ (75% ቅናሽ) እንደምትሸጥላቸው ትገልጻለች። እናም ቀጠሮ ይይዛሉ።

በወቅቱ አዲሳባ በሰባት ማዘጋጥ ጣቢያ የተከፈለች ሲሆን ያንን ጣቢያ የሚመራው የክፍለ ከተማው ከንቲባ የነበረው ግርማጲዬን ነበር። ግርማጲዬን በህውሀት ክፍፍል ወቅት አቶ መለስን የታደገ ሲሆን ፣ አቶ መለስ " የህውሀት የቁርጥ ቀን ልጅ" እያለ ከሚያሞካሻቸው ታጋዬች አንዱ ነው።

(የአቶ መለስን ሞት ተከትሎ ህውሀት በለቀቀው ሚስጥራዊ ቪዲዬ ላይ እነ ተወልደ መድረክ ረግጠው ሲወጡ " በስጋ ስውአት ይዘናችኃል አትውጡ!" እያለ ሲጮሁ ከነበሩት አንዱ እሱ ነበር። የድሮዎቹ ዝሆኖች መድረክ ረግጠው ከወጡ በኃላ እያለቀሰ የተናገረው ንግግር የእነ ተወልደን ፓለቲካዊ ግብአተ መሬት እንዳፋጠነ ይታመናል።

አቶ መለስ ግርማጲዬንን፣ የኮልፌው ነጋ በርሔንና የአቅም ግንባታ ቢሮ ሀላፊው ተክለብርሀንን ወደ አዲሳባ ያመጣው አርከበን እንዲቆጣጠሩት በማሰብ ነበር። ሶስቱም ካድሬዎች ከአርከበ ጋር ተስማምተው አያውቁም። ተክለ ብርሀን ጊዜና ቦታ ሳይመርጥ አርከበን ይሞልጨዋል። ነጋ በበኩሉ በውስጠ ድርጅት ስብሰባ ከቱክናክራትነትና ልታይ ባይነት አልወጠሀም በማለት ዘልፎታል።)

ከዚህ ነባራዊ ሀቅ በመነሳት እነ የሁሉና ሚደቅሳ በእንጥልጥል ላይ ያለውን ክትትል ለግርማጲዬን ያጫውቱታል። ከሰአታት በኃላ ሌላ አካል እየተከታተለው ስለሆነ በአስቸኳይ እንድታቋርጡ ታዛችኃል ይላቸዋል። የተባሉትን ያደርጋሉ።

በረከት በሚመራው ጉንጭ አልፉ ግምገማ የአርከበ ሂስና ግለሂስ እየተሰማ ነው።

ሎግላጋው ሚደቅሳ አርከበ እስኪጨርስ መታገስ አቅቶታል። ይህን የተመለከተው በረከት ቅድሚያ ይሰጠዋል። ... ሚደቅሳ ቋጥሮ የከረማትንና በእንጭጩ የተቀጨውን የክትትል ታሪክ ያነሳል።

በጥያቄው የተደናገጠው አርከበ መጀመሪያ " አንድ ሰው በሊዝ የወሰደውን መሬት መሸጥ ይችላል " የሚል ከህገመንግስቱ ጋር የሚጋጭ አስተያየት ይሰጣል። ከግራ ቀኝ "ባዶ መሬት መሸጥ መለወጥ አይቻልም" በሚሉ አስተያየቶች ተዋከበ። መልሱ እንደማያዋጣው የተገነዘበው አርከበ አክሮባት በመስራት " እኔ አጠቃላይ በሆነ ነገር አስተያየት ሰጠሁ እንጂ ሚደቅሳ ስለሚያነሳው ጉዳይ የማውቀው ነገር የለም።" ብሎ ይሸመጥጣል።

የታሪኩ ባለቤት ግርማጲዬን ደግሞ በጉንጭ አልፉው ግምገማ እንዳይሳተፍ አስቀድሞ የአራት ክልሎች ፕሬዝዳንቶችን እንዲቆጣጠር በመሾሙ ወደ ቤኒሻንጉል ክልል ሄዷል። እናም የማጣራቱ ስራ በይደር እንዲቆይ ተወሰነ... ሳይጣራ ቀረ።

ሚደቅሳ የዱከም ከንቲባ ሆነ። በአመቱ በድንገተኛ ህመም ህይወቱ አለፈ። ጓደኛው የሁሉ ደነቀው የኢትዬጲያ መዳኒትና ቁጥጥር ስራ አስኪያጅ ሆነ።

***

"ህላዌ ነብሴ!"

ህላዌ ዬሴፍ አንድ መሬት በራሱ ወስዷል። ሚስቱ የመከላከያ ሰራተኛ ስለሆነች በጅምላ መሬት ሲታደል ደርሷታል። በግለ ሂሱ ላይ አርከበ ጉድ እንደሰራው ጨምሮ ገልጿል። አንዱን መሬት ለመመለስ ፎርም ከሞሉት ካድሬዎች

የመጀመሪያው እሱ ነበር። እንዲያም ሆኖ የበረከት ዘለፋና ስድብ ከማንም ካድሬ በላይ ጠንክሮ የነበረው አሱ ላይ ነበር። ዘወትር " ህላዌ ነብሴ!" እያለ የሚጠራው በረከት ለምን እንደጨከነበትና ሙልጭ አድርጐ ለመስደብ የተነሳሳበት ምክንያት ለብዙዎቻችን ግልጽ ነበር። ህላዌም ይህን በመገንዘብ ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ... እኔንና አጠገቤ ተቀምጣ የነበረችውን አኸዛ የምትባል የህውሀት ካድሬ አጀብነው። ህላዌ ያሳዝነኛል... ምክንያቱን አላውቀውም።

ህላዌን በቅርብ አውቀዋለሁ። ቢያንስ በወር አንዲት ቅዳሜ እኔን፣ፀጋዬንና ካሚልን እቤቱ ምሳ ይጋብዘናል።እስከ ምሽት የቆጥ የባጡን እናወራለን። ሚስቱ በልተን የማንጠግብ የሚመስላት ደግ ናት... ስሟም ደጊቱ ነው።

ህላዌን እስከማውቀው ድረስ በግለሰብ ደረጃ ይህ ነው የሚባል ንብረት የለውም። የውጭ ህክምና ወጪውን የሚሸፍንለት ሼህ አላሙዲ ነው። ልጁን አሜሪካ ለእረፍት የወሰዱለት ጓደኞቹ ናቸው። ሙሉ ልብስ እየገዛ የሚያመጣለት ሰለሞን ተቀባ ነው። ባለኮከብ ሆቴሎች እየወሰደ የሚጋብዘው ጨልሌው አርቲስት ቴድሮስ ተሾመና ጋዜጠኛ ሳምሶን ማሞ ነው።

ህላዌ እንደ "ዋልዋ "ሁሉ የዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት እስረኛ ነው። ህላዌ ኢህአድግ አይደለም... ሆኖም አያውቅም። የደርግን ግፍ መቅመስና አስከፊው ስርአት እንዲወገድ ግንባርን ለጥይት ሰጥቶ መታገል በራሱ ኢህአድግ አያደርግም። ኢህአድግነት ርእዬተ አለም ነው ... ሀይል አሰላለፍና ወገንተኝነት የሚጠይቅ... የህላዌ ህይወት ይህን አያሳይም።... ኢህአድግነት በዘር ማሰብ ይጠይቃል... ህላዌ ለይቶ የቆመለት ዘር የለውም። በዚህ ስሌት ከተሰላ ምንአልባትም ከህላዌ ይልቅ ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ ለኢህአድግ ቅርብ ነው፣ ለዶክተር መራራ ደግሞ የቅርብ ሩቅ...

የህላዌ ውሎ ኢህአድግ ማህበራዊ መሰረቶቹ አይደሉም ብሎ ከሚያስባቸው ጋር ከሆነ ውሎ አድሯል። ህላዌ ውስጡ የማያምንበትን መንገድ እየተጓዘ ያለው ይህን መለየት አቅቶት ነው። ሲያዪት የተምታታበት የሚመስለው በዚህ ምክንያት ይመስለኛል።

ይህ ባይሆን ኖሮ እሱን የምናገኘው ሌላ ቦታ ነበር። ምንአልባትም ትላልቅ የስነ ጽሁፍ ሰዎቻችን ብለን የምንዘክራቸው ኢትዬጲያውያን ጐራ ይሰለፍ ነበር... ምንአልባትም "ቀይ ስህተት - የቴዎድሮስ ተሾመ ፊልም" በሚለው ፉንታ "የህላዌ ዬሴፍ" የሚል ተጽፎ እናይ ነበር። በዘረኛ የኢህአድግ ካድሬዎች ነቀፌታ የደረሰበት " የአጼ ቴድሮስ መዚቃ አዘል ተውኔት" ድርሰት የህላዌ ዬሴፍ ተብሎ ይጻፍ ነበር። ...እቤቱ መሳቢያ ውስጥ የቆለፉቸው የግጥም መድብሎች ከአንድ መጽሀፍ በላይ ሆነው ህዝብ ያነባቸው ነበር።

ህላዌን ጊዜውን ማሳለፍ የሚፈልገው ከአርቲስቶች ጋር ነው። ከኢህአድግ ካድሬዎች በተለየ ሁኔታ የተሻለ ግንኙነት ፈጥሯል። ስራቸውን ለህዝብ ከማቅረባቸው በፊት እንዲገመግም ያሳዪታል። እነ ደጋረገና ሀመልማል አባተ " ጋሼ ! ታላቅ ወንድማችን!" ብለው ይጠሩታል። አርቲስቶቹ ማንያዘዋል እንደሻው፣ ቶማስ ቶራ ተማካሪዎቹ ናቸው።

አንዳንድ አርቲስቶች በተለያየ ጊዜ ወደ ቢሮው እየመጡ ያለባቸውን

ችግር ያወያዩታል። አንድ ጊዜ የሀገር ፍቅር ስራ አስኪያጇ አርቲስት መንበረ ታደሰ ቢሮው መጣች። እንባዋን እየዘራች" መስራት አልቻልኩም... አላሰራም አሉኝ " በማለት የውስጧን ብሶት ዘረገፈችለት። በሁኔታው የተበሳጨው ህላዌ ከወራት በኃላ የኢትዬጲያን ፓርላማ ቀላቀላት... ከአስፈጻሚነት ወደ ህግ አውጭነት ተመነጠቀች...ጠላቶቿን ቁልቁል አየቻቸው... አፍታም ሳትቆይ ፀጥ ያለው ሸንጎ ሳይመቻት ቀርቶ ይሆን ፣የወይዘሮ አዜብ ጡጫ በዝቶባት ሀገር ጥላ ተሰደደች።

በረከት የቦርድ ሰብሳቢ የሆነበት የኢትዬጲያ ቴሌቭዥን መለወጥ እንዳለበት በማመኑ ህላዌን በስራ አስኪያጅነት ለመሾም አዘጋጀው። በኢህአድግ ደጃፍ የህላዌ ወደ ኢቲቪ መሄድ ብዙ ተወራ። ትልቅ ተስፋ ተጣለበት። በተባረር የሰሙ የግል ፕሬሶች መረጃውን አወጡ። እኛም የሸኘት ፕሮግራም አዘጋጅተን ለሊቱን ሙሉ አብረነው ስንጨፍር አደርን። መልካም የስራ ዘመን ተመኘንለት።

የሴጣን ጆሮ ሰማ።

እንደሚታወቀው በሚዲያው አካባቢ የበላይነቱን ተቆጣጥረው የነበሩት የህውሀት ካድሬዎች ናቸው። የዜና አገልግሎት(ኢዜአ) ዋና ስራአስኪያጅ ታጋይ ሀዱሽ፣ የሬዲዬ ፋናው ታጋይ ወልዱ ይመስል፣ የዋልታው ታጋይ ብርሀነ ማእረት...እነዚህ ካድሬዎች ወደ እመቤታቸው ወ/ ሮ አዜብ በመሄድ " ብአዴን ኢህአድግ ቢሮን ሙሉ ለሙሉ ከተቆጣጠረ በኃላ ፊቱን ወደ ሚዲያ ተቋማት አዙሯል" የሚል ቅሬታ አቀረቡ። ወይዘሮ አዜብ በእኔ ጣሉት ብላ ብርታት ሆነቻቸው።

ከቀናቶች በኃላ አቶ መለስ የሰጣቸው ሁለት ትላልቅ ሹመቶች በኢቲቪና ሬዲዬ ተደመጡ። የኢትዬጲያ ሬዲዬና ቴሌቭዥን ዋና ስራ አስኪያጅ ዘርአይ አስግዶም... ምክትሉ ደግሞ ህላዌ ዬሴፍ... አዜብ ሁልግዜም አሸናፊ ናት።

ከተማ ቀመሱ ህላዌ አዘነ። አንገቱን ደፉ... "ህላዌ ነብሴ!" አያለ የሚጠራው የድርጅቱ እስትራቴጂስት መሸነፉን አመነ።

***

" ተወዳጁ አርከበ ! "

በጉንጭ አልፋው ግምገማ ላይ በረከት አርከበን እንዲህ ሲል ጠየቀው :

" በአዲሳባ ታቅደው የተሰሩ ስራዎች ላይ አንዲት የድርጅቱ ሳይሆን የእኔ ፈጠራ ናት የምትላትን እንድትነግረን እፈልጋለሁ ? "

አርከበ በበኩሉ :

" በዚህ ጉዳይ ላይ ሁለታችንም የምንለያይ አይመስለኝም።" የሚል ምላሽ ሰጠ። ግምገማውን ከዛሬ ነገ መታሰሬ አይቀርም በሚል ተስፋ መቁረጥ የታደመው ገ/ ተንሳይ በረከትን እየተመለከተ ከት ብሎ ሳቀ።

በረከት ጥርሶቹን እያንቀጫቀጨ:

" እሱን የእኔ ግምገማ ሲቀርብ ትናገራለህ። አንተ ግን ድርጅቱ ቃል በቃል ነግሮህ እንኳን በአግባቡ መፈፀም አትችልም ነበር። የሚያሳዝነው የድርጅቱን ውጥኖች የራስህ ፈጠራ አስመስለህ ግለሰባዊ ስብእናህን ስትገነባ መክረምህ

ነው።" በማለት እቅጩን ተናገረ።

አርከበ ምላሽ አልነበረውም።

ከአመታት በኃላ ይህንን ድምዳሜ ለታሪክ ማስቀመጥ አስፈላጊ በመሆኑ በሁለት ምርጫዎች ወግ መጽሀፍ " ማሟሻ ወግ "በሚለው ርእስ ስር:

"... አዲሱ አመራር ኢህአድግ ያስቀመጠለትን አቅጣጫ ተከትሎ በከፍተኛ ተነሳሽነት ስራ በጀመረ ማግስት በብዙ መስኮች የቆየውን አዝጋሚ አካሔድና አሰራር የሚቀይር በኢትዬጲያ አዲስ የከተሞች እድገት ምእራፍ መክፈቱን የሚያበስር ሰፊ እንቅስቃሴ ተቀጣጠለ።" በማለት የፈጠራውን ባለቤት ለኢህአድግ (አቶ መለስ) ይሰጣል።

የውስጠ ድርጅቱ ግምገማ ግልጽ ነው። ለህዝቡ በሁለት ምርጫዎች ወግ የተገለፀበት አግባብ ደግሞ ውስጠ ወይራ...አርከበን በተመለከተ የድርጅቱ ከፍተኛ ካድሬዎች ያላቸው አመለካከትና ለህዝቡ እንዲሰርጽ ያደረጉት አስተሳሰብ ተቃራኒ ናቸው።

ከአቶ መለስ ጀምሮ ሌሎቹ ዝሆን ካድሬዎች በውስጠ ድርጅት ስብሰባ የአርከበን የፓለቲካ ድህነት፣ መርህ የሌለው መሆኑን፣ ውግንናው ኢህአድግ ቆሜለታለሁ ከሚለው ማህበተሰብ በተቃራኒ እንደሆነ፣ የራሱን ገጽ ሲገነባ መክረሙን በግልጽ ይናገራሉ።

አቶ መለስ የአዲሳባ ካቢኔ አባላትና ካድሬዎች በተሰበሰቡበት " ቀለም ቀቢ!" ብሎ ሰድቦታል። ባለቤቱ ወይዘሮ አዜብ ይህን ውርጅብኝ ህዝቡ እንዲሰማ ስለፈለገች ለሪፓርተር ጋዜጣ ባለቤት አሳልፋ ሰጥታዋለች። በዛው ሳምንት ሪፓርተር በርእሰ አንቀጹ " ከቀለም መቀባት ስራ እንላቀቅ " በማለት ጽፏል።...በተጨማሪም ወይዘሮ አዜብ በፒያሳ የተሰቀለውን ታጌላ አይታ "የሳሎን ውሻ!" በማለት መሳለቂያ አድርጋዋለች።

በ97 ምርጫ ዋዜማ አርከበ ጥሩ የሰራ መስሎት የታክሲ ሹፌሮችን ሰብስቦ የቅጣት ምህረት አደረገ። የነጋዴዎችን ውዝፍ ግብር በተመሳሳይ እንዲነሳ አደረገ።ይህን ድርጊቱን የአዲሳባ ምርጫ የምናስተባብር ካድሬዎች ኢህአድግ ቢሮ በሚኖረን የምሽት ስብሰባ ላይ ተናገረ። አጠገቤ የነበረው ተፈራ ዋልዋ ከመቀመጫው ተቆናጥሮ በመነሳት:-

" አርከበ! እድሜ ልክህን የፓለቲካ ደሀ ሆነህ ትኖራለህ። መሸነፋችንን አስቀድመህ ባወጅክበት ስብሰባ መሳተፍ አልፈልግም።" በማለት ስብሰባውን በጠበጠው።

የኢህአድግ ቁልፍ ካደሬዎች በውስጠ ድርጅት ይህን ይበሉ እንጂ ወደ ህዝብ ሲወርዱ በተቃራኒው ይናገራሉ። ይጽፋሉ። አርከበን የለውጥ ሀዋርያ በማድረግ ለህዝብ ይሰብካሉ። የአዲሳባን ትንሳኤ ያበሰረ መሪ በማለት ስሙን ከጫፍ ጫፍ ያስተጋባሉ። ይህ አባባል በተደጋጋሚ በመነገሩ ምክንያት የሰውየው ስም ትርጉም ባለው መልኩ በህዝቡ ዘንድ እንዲተከል አድርጐታል።... በምርጫ 97 ወቅት የአዲሳባ ዩንቨርስቲ ተማሪዎች " አርከበ ! ኢህአድግን ትተህ ቅንጅትን ተቀላቀል!" የሚል መፈክር አሰምተዋል። ...ዶክተር ብርሀኑ ነጋ በነጻነት ጐህ

ሲቀድ መጽሀፉ ላይ አርከበን በማድነቅ ጽፎታል (*የደኢህዴን ጉራጌ ካድሬዎች አርከበ በመርካቶ የጉራጌ ነጋዴዎችን በመለየት ያደረሰውን በደል ዶክተሩ እያወቀ እንደዛ ማለቱ አበሳጭቷቸው እንደነበር አስታውሳለሁ*) ... የኢሳት ቴሌቪዥን ጋዜጠኞች የሆኑት ደረጀ ደስታና ተወልደ በየነ " ተወዳጁ ከንቲባ" ብለው ሲናገሩ ሰምቻለሁ።

እውን አርከበ "ተወዳጅ" መባል የሚገባው መሪ ነበር ? የፈፀማቸው ተግባራት ይህንን ዘመን ተሻጋሪ ማእረግ የሚያጐናጽፉት ናቸው ? የአርከበ አመራር (Leadership) ጥራትና ስብእና በዚህ ደረጃ ሊያስፈርጀው የሚችል ነው?... ለእነዚህ ልብ ኮርኳሪ ጥያቄዎች መልስ ሳይሰጥ ማለፍ የማስታወሻውን ግማሽ ገጽ ቀዶ እንደመጣል ይቆጠራል።

በመሆኑም የኢህአድግ ካድሬዎች አርከበን በተመለከተ ያላቸው የውስጥ እይታ፣ ዝናውን ለማግዘፍ የተቀየሱ እስትራቴጂዎችና ያስገኙትን ውጤት ወደ መመልከት እንግባ።

-የአዲሳባ ለውጦች... ክንዴ የአካባቢ ልማት ሀላፊ

1ሁሉም ነገር ወደ አዲሳባ(ኢኮኖሚ)... ሽራተን ከአለ አብዶ ጋር

2የጐብልስ ቲዎሪ(ፕሮፓጋንዳው) " ጐብልስ በአዲሳባ"

3ታጌላው

4ዘጠኝ ድስት

5የፓለቲካ ደሀ

ሐይለማርያም የሚመልሳቸው ቀላል ጥያቄዎች

- ዝዋይ ንግግር

የአዲሳባ ለውጦች

አዲሳባን የለውጥ ምክንያቶች በማስታወሻው የመጀመሪያው ክፍል ለመግለጽ ተሞክሯል : የአርከበን ቡድን ከትግራይ ማስወጣት፣ የአዲሳባ ህዝብ በምርጫ 92 የወሰደው እርምጃ አገራዊ አደጋን እያስከተለ መሄዱና እነ ጋዳፊን በመሰሉ የአፍሪካ መሪዎች አዲሳባ እየደረሰባት ያለው ጫና በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው።

እነዚህ ምክንያቶች በምንም መልኩ የኢህአድግን " ከተማን በገጠር ስሌት መምራትና የነፍጠኛ ከተሞችን ማዳከም" የሚለውን እቅድ የቀየሩ አይደሉም። በተመሳሳይ የአዲሳባ ህዝብ ራሱን በራሱ የማስተዳደር ሉአላዊ መብቶችን ያጐናፀፉ አይደሉም። ተደጋግሞ እንደተገለፀው ከ5 ሚሊዬን በላይ የሚሆነው ህዝብ የመረጠውን ምክርቤት ፓርላማው ፀጥታ ማስከበር አቅቶሀል ብሎ የመበተን ስልጣን አለው ። የአዲሳባ አስተዳደር የራሱ የሆነ ፓሊስ ሀይል በሌለው ሁኔታ።

በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱት መሰረታዊ የህዝብ መብቶች ሳይከበሩ አዲሳባን ለመቀየር መነሳት ከጊዜያዊ አደጋዎች ለመዳን ከማሰብ እንጂ ዘለቄታዊ ፋይዳ የሚያመጣ አይደሉም።

ግራም ነፈሰ ቀኝ አዲሳባ መለወጥ አለባት !

ይህንን ገቢራዊ ለማድረግ የልማትና ፕሮፓጋንዳ ስራ ተቀናጅተው ሊፈፀሙበት የሚያስችል ስትራቴጂዎች ተቀየሱ። የልማት ስራው በረከት በመጽሀፉ እንደገለፀው ናዳን ለመግታት የሚካሄድ ሩጫ አይነት ሆነ። " ሁሉም ነገር ወደ አዲሳባ " የሚል አዋጅ ታወጀ። በፕሮፓጋንዳው መስክ የጀርመናዊው የጐብልስ ትእዛዝት ማጠንጠኛ "The Big Lie theory" ተቀይሶ ተግባራዊ ሆነ።

***

" ሁሉም ነገር ወደ አዲሳባ"

አቶ መለስ በጽ/ ቤቱ የሀገሪቱን ዋነኛ የኢኮኖሚ ነክ ዘርፎችን ሰብስቦ " ሁሉም ነገር ወደ አዲሳባ " ነጋሪት ጐሰመ። የመገርና ሞሶቦ ሲምንቶ ፋብሪካ የአዲሳባን ፍላጐት ሳያሟሉ ለሌላ መሸጥ እንደማይችሉ አስጠነቀቀ። የመንግስት የብረታ ብረት ፋብሪካዎች
በልዩ ትእዛዝ ለአዲሳባ እንዲያቀርብ ተወሰነ።

በአቶ መለስ ልዩ ትእዛዝ ከሁለት ቢሊዬን ብር በላይ ከፌደራል መንግስት በመመደብ ብረትና ሲምንቶ ለአስተዳደሩ ከውጭ ሀገር እንዲገዛ ተወሰነ። የመንገዶች ባለስልጣን ፣ቴሌና መብራት የጥምር ግብረሀይል እንዲያቋቁሙ ተደረገ። በተለይ መብራት ሀይል አዲሳባ ላይ ለሚቋቋሙ የጥቃቅንና አነስተኛ ማምረቻ ተቋማትና ሼዶች ልዩ ሪዘርቭ እንዲይዝና ለሚቀርቡ ጥያቄዎች በቀናት ውስጥ ምላሽ እንዲሰጥ ታዘዘ።

***

ሽራተን አዲስ ...

የጨለማው ዘመን ነጉስ ከነበረው አለ. አብዶ ጋር እራት እየበላን ነው። ከአለ. ጋር የተገናኘነው ከአምስት አመታት በኃላ ነበር። እሱ የሱዳን አምባሳደር ሆኗል፣ እኔ ደግሞ የበረከት ስምኦን ምክትል። ያገናኘን ምክንያት ደግሞ የኢትዬ - ሱዳን የጋራ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ ኢትዬጲያን ወክዬ በሚዲያና ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዬች ላይ እንድደራደር በመወከሌ ነበር።

አለ. ቀኑን ሙሉ በነበረው ድርድር አንገቱን አቀርቅሮ ዋለ። በሙሉ አይኑ ሊያየኝም አቅም አነሰው። ሌላው ቀርቶ በስብሰባው ወቅት በሚኖረው የሻይ ሰአት ደጋግሞ ሲሸሸኝ ተመለከትኩት። በየጊዜው የወረወረብኝ ጦሮች ያደረሱትን ጉዳት እንዳልረሳው ያስታውቃል። እኔም ብሆን ለእሱ ያለኝን ዝቅተኛ አመለካከት አመታት አልፈውም መቅረፍ አልቻልኩም። በዚህ ስሜት ውስጥ እያለን ነበር ለፕሮቶኮልየተዘጋጀ የእራት ጠረጴዛ ያገናኘን።

አጠገባችን ተቀምጠው የነበሩትን በኢትዬጲያ የሱዳን አምባሳደር ጥቂት ካወራናቸው በኃላ እኔና አለ. ተፋጠጥን።

ከረጅም ዝምታ በኃላ ስሜን እየጠራ እንዲህ ሲል ተናገረ:

" ይገርምሀል እንደዚህ አይነት አጋጣሚ ይፈጠራል ብዬ አስቤ አላውቅም። በአንዳንድ ነገሮች ቅር እንደተሰኘህብኝ አውቃለሁ። በወቅቱ አብረውኝ የነበሩት ሰዎች የማያሰሩ እንደሆነ ታውቃለህ?"

" እውነቱን ንገረኝ ካልክ በህይወቴ ካዘንኩባቸው ሰዎች አንዱ አንተ ነህ። እስከዛሬም በተለየ ጊዜ እየተከታተልክ ለምን እንዳጠቃኸኝ አይገባኝም " አልኩት።

ዘመን ተገልብጧል...

ትላንትና እሱ አበሻቅጦ " ቀስ ብለህ እደግ!" በማለት ከቢሮው አስወጥቶኛል፣ ተወዳድሬ ያገኘሁትን የውጭ ሀገር የትምህርት እድል ለሌላ አሳልፎ ሰጥቷል፣ ከስብሰባ ውሰጥ አንተን አይመለከትም ብሎ አባሮኛል፣ሶስት ቀንና ለሊት መስኪድ አሳድሮኛል፣ በአርከበ ዘመን ምደባ ሲካሄድ አህዴድ

እንድታውቅ የምፈልገው ግን የኔዘርላንዱን የትምህርት አድል ከአንተ ነጥቆ ለሙለሜ ረሺድ እንዲሰጥ ያደረጉት ሌሎች ሰዎች ናቸው።"

" እነማን?"

" ጉዳዩ ከእኔና ከአንተ አይለፍ እንጂ ካሊድ፣የመከላከያ ሚኒስትሩ ሲራጅ ፈርጌሳና ሬድዋን ሁሴን ናቸው።"

" ለምን? ከካሊድ ውጭ ሌሎቹ አያውቁኝ፣ አላውቃቸው ? "

" ታስታውስ እንደሆነ በዛን ሰሞን ሙለሜ የደኢህዴን ማእከላዊ ኮሚቴ ተመርጣ ነበር። እናም የማእከላዊ ኮሚቴ የተመረጠ ሰው እያለ ከዛ በታች ያለ ካድሬ መሄድ አይችልም ብለው ተከራከሩ። " በከፊል አመንኩት። ሴትየዋ በእያንዳንዱ ንግግሯ የደኢህዴን ማእከላዊ ኮሚቴ እና የስልጤ ፓሊት ቢሮ መሆኗን ለማሳየት ትጥር ነበር። በተለይ ሬድዋንና ሲራጅ የወሬ ማጣፈጫዋ ነበሩ።

ከግለሰብ እሰጣ ገባ መዉጣት ስለፈለኩ " አንተ ከለቀቅክ በኃላ የአዲሳባን ለውጥ እንዴት አየኸው ? "ብዬ ጠየኩት።

" እሱንማ አንተ ልትነግረኝ ነው የሚገባው። በሁለቱም ዘመን የነበርከው አንተ ነህ ? "

" በአሸዋ ላይ የተሰራ ቤት ነበር። ግለሰቦች ከድርጅቱ በላይ ራሳቸውን የሸጡበት ይመስለኛል" አልኩት።

" እውነትህን ነው። መለስና ፌዴራል መንግስት ለአርከበ ያደረገለትን ድጋፍ ለእኔም ቢያደርግ ኖሮ የእሱን ያህል መስራት አያቅትም ነበር።" ዝም ብዬ አዳመጥኩት።

አሊ ቀጠለ...

" አርከበ እንዲፈጽም የተሰጠውን እቅድ ሙሉ ለሙሉ የጻፈው መለስ ነበር። የእቅዱ ማስፈፀሚያ ገንዘብ የተመደበው ከፌደራል መንግስት በመለስ ልዩ ትእዛዝ ነበር።... ታስታውስ እንደሆነ እኔ ፕሬዝዳንት በሆንኩበት እያንዳንዱ አመታት የምንሰበስበው ገቢ ከ2 ቢሊዬን አይበልጥም። ፌዴራል መንግስት ምንም ድጉማ አያደርግልንም። እንደውም ብዙ የገቢ ምንጮችን ይወስዱብን ነበር። ለሰራተኛ ደሞዝ ከፍለን የምተርፈን ገንዘብ በጣት የሚቆጠሩ ፕሮጀክቶችን ለመስራት ብቻ የሚያስችል ነበር። በተቃራኒው ፌደራል መንግስት ለአዲሳባ ብረትና ሲምንቶ መግዣ ብቻ ሁለት ቢሊዬን ብር ድጋፍ አድርጓል።"

ትንፋሽ ወስዶ በቁጭት እንዲህ ሲል አጫወተኝ :

" የአርከበ አስተዳደር የሰበሰበው ገቢ አነስተኛ ነበር። በተለይ መርካቶ ከፍተኛ አጣብቂኝ ውስጥ በመገባቱ የተሰራው ወንጀል የሚዘገንን ነው። በእኔ ዘመን ለአካባቢ ልማት ስራዎች ህዝቡ የተሻለ ያዋጣ ነበር። የውስጥ ለውስጥ

መንገዶችና መፀዳጃ ቤቶች በህዝብ ገንዘብ የተሰሩ ናቸው። በአርከበ ዘመን ይህ ተግባር ተዳክሞ ሁሉንም ነገር የሚሰራው መንግስት ሆኖ ነበር።

ፊንፊኔ

ከምርጫ 97 ሁለት አመት በፊት ኦህዴድ የተመሰረተበትን ቀን በየአመቱ በአዲሳባ ባከበረ ቁጥር ግልጽ ተቃውሞዎች መቅረብ ጀምረዋል። የታሰሩ የሜጫና ቱለማ መረዳጃ ማህበር አመራሮች መንግስት ይፈቱና ካሳ ይከፈላቸው የሚል ሆኗል። እነዚህ ሰዎች የታሰሩበት ምክንያት የኦሮሚያ ክልል ዋና ከተማ ከአዲሳባ ወደ ናዝሬት (አዳማ) መዘዋወሩን በመቃወማቸው ምክንያት በ1996 አ• ም• በመስቀል አደባባይ ሰላማዊ ሰልፍ በማድረጋቸው ነበር። በወቅቱ " ፊንፊኔ የኦሮሚያ ዋና ከተማ ናት፣ የኦሮሞ ህዝብ በፊንፊኔ ላይ ያለውን የባለቤትነት መብት መነጠቅ የለበትም " የሚሉ መፈክሮችን አንግበው ነበር።

የሜጫና ቱለማ ማህበር ከ50 አመት በላይ ያሳለፈ አንጋፋ ተቋም ነበር። ይህ ማህበር ፓለቲካ ይዘት ያላቸውን የመብትና እኩልነት ጥያቄዎች ፊት ለፊት በማንሳቱ ግንቦት በ1996 አ• ም• የድርጅቱ አመራሮች ሽብርተኝነት ተከሰሱ፣በአንድ ወር ውስጥ ፍቃዱ ተነጥቆ ተዘጋ። የማህበሩን ንብረቶች እነ አባዱላ ኦህዴድ እንዲወርሰው አደረጉ።

ዋና ከተማው ወደ አዳማ (ናዝሬት) መዘዋወሩን ተከትሎ ሰራተኛውና ቢሮዎች አብረው ተሟሟሩ።

ምእራፍ: ጨለማና ተስፉ

1• **ህገ መንግስቱ ያልቋጨው የፊንፊኔ አጀንዳ**

1• የመዲናይቱ ወኪሎች

2• የቆሰለው ጅብ ተረት vs የተቃውሞ ድምጽ (protesting vote)

3• ኢህአድግን ያባረረው የኢህአድግ ጉባኤ

4• የትእማር ደብዳቤ

የመዲናይቱ ወኪሎች

ከምርጫ 97 ግርግር ረገብ ማለት በኃላ የአዲሳባን ህዝብ ሙቀት መለካት ያስችላሉ የተባሉ ውይይቶች እንዲጀመሩ ከአቶ መለስ ጋ ር በሚኖረን ሳምንታዊ ስብሰባ ተወሰነ። ውይይቱ ነዋሪዎች ፣ሴቶችና ወጣቶች በሚል አንዲከፉፈልና ሶስት መድረኮች እንዲሆኑ አቶመለስ አሳሰበን።

የተወያዬች ዋነኛ መመዘኛ በግልጽ ተመዝግበው ከሚንቀሳቀሱ የተቃዋሚ አባላት ውጪ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል የሚወክሉና ነዋሪው "ወኪሎቼ ናቸው "ብሎ ከሚያምንባቸው ጋር ብቻ እንዲሆን አቅጣጫ ተቀመጠ። ይህም ከዚህ በፊት ሲሰራበት የነበረው ሰዎችን በብሔር ማንነታቸው የመከፉፈልና ማወያየት ስራ አዲሳባ ላይ እንዲቋረጥ፣ በምትኩ በማህበራዊና እድሜ አደረጃጀታቸው ብቻ እንዲሆን ተደረገ።

ከአቶ መለስ ጋር በተሰበሰብን ወቅት የብሄር አዘል ስብሰባ ይሻላል የሚል አስተያየት ቀርቦ የነበረ ሲሆን ፣አቶ መለስ ንዴት በተቀላቀለበት ሁኔታ " ወደድንም ጠላንም የብሔር ፓለቲካ አዲሳባ ላይ አፈር ልሶ የማይነሳበት ደረጃ ላይ ደርሷል" የሚል አስገራሚና ያልተጠበቀ አስተያየት ሰጠ።

በስብሰባው ማጠቃለያ ለማወያያ የሚሆኑ ሰነዶችን የከተማው ኢህአድግ ክንፍ እንዲያዘጋጅ፣መድረኮቹን በብቃት ሊመሩ የሚችሉ ሚኒስትሮችንና ከፍተኛ ባለስልጣናትን የመለየት ስራ በተመሳሳይ እንድንፈጽም ተሰማምተን ስብሰባው ተፈጸመ።

ውሳኔውን ተከትሎ የነዋሪዎችን ማወያያ ህላዌ፣የወጣቶችን ፀጋዬ፣የሴቶችን ደግሞ እኔ እንድናዘጋጅ ተስማማን። ሊያወያዩ የሚችሉ ሚኒስትርና ባለስልጣናትን ካሚል ለይቶ እንዲያመጣ ተደረገ። ስራው ተቀናጅቶ እንዲፈፀም በማሰብ የዞን ቋሚ ምድብተኛ ካድሬዎችን ጠርተን አዲሱን የኢህአድግ አቅጣጫ ኦረንቴሽን ሰጠን። ብዙዎቹ ካድሬዎች የብሄር ፓለቲካ በአዲሳባ በመቅረቱ ደስተኞች ሆኑ።

የከተማው ኢህአድግ ክንፍ ሰነድ ከማዘጋጀት በተጨማሪ ቀበሌዎች በምን መልኩ ምልመላ እያካሄዱ እንደሆነ ለማወቅ እንዲያስችለን ተከፉፍለን ወደ ታች ወረድን። እኔ የካ ክፍለ ከተማ የምትገኝ አንዲት ቀበሌ ሄድኩኝ። ያጋጣሚ ነገር ሆኖ የቀበሌው ምድብተኛ ካድሬ (ቢኒያም ይባላል) ጋር በመከላከያ ሚኒስቴር ውስጥ የሚገኙትን ወታደራዊ መኮንኖች አስተምረናል። ቢኒያም በባህሪው ሰዎችን ቶሎ የመፈረጅና በተለይም ኢህአድግን ከተቀላቀለ በኃላ ድርጅቱን እንዳይጠጉት የማድረግ ባህሪ እንዳለው አውቃለሁ። ሆኖም ከምርጫ 97 በኃላ ብዙዎቹ ካድሬዎች መሻሻል ስለታየባቸው የቢኒያምንም ተስፉ አድርጌ ነበር።

ቀበሌው አዳራሽ ስደርስ አባላትን ሰብስቦ ጠብቆኛል። እያንዳንዱ አባል አስር አስር ነዋሪዎች፣ ወጣቶችና ሴቶችን ለይተው እንዲመጡ አድርጓል።

ስብሰባው ተጀመረ።

ማስታወሻ ደብተሬን ገልጬ መጻፍ ጀመርኩ። አባላት ህብረተሰቡን ይወክላሉ የሚሏቸውን ገለፀ...

እንድ አባል:" ከነዋሪዎች ውስጥ አቶ አያሌው መልምያለሁ።በአካባቢያችን የሚገኘው ትልቁ እድር ሊ/ መንበር ናቸው።"

ካድሬ ቢኒያም :"መአድ መልምለህ ና አልተባልክም!"

ሌላ አባል : " ከወጣቶች ያሬድ ተፈራ... ወጣቱ በፖለቲካል ሳይንስ ከአዲሳባ ዩንቨርስቲ የመጀመሪያ ዲግሪውን አግኝቷል። በአካባቢው ወጣቶች ዘንድ ከፍተኛ ተሰሚነት ያለው ሲሆን በአንድ የግል ትምህርት ቤት የስነ ዜጋ አስተማሪ ነው።"

ካድሬ ቢኒያም : " ሲቪክስ የሚያስተምር ሁሉ ጤነኛ ያደረገው ማነው? በአሁን ሰአት ቅንጅት መልምለህ መጥተህ ተሰሚነት የለውም ብትለኝ ኖሮ ይገርመኝ ነበር።"

ሌላ አባል : " ከሴቶች ወይዘሮ አረጋሽ ጋዲሳ... ሴቶች ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት እንዲደራጁ ከፍተኛ የቅስቀሳ ስራ ሰርተዋል። ኢህአድግ በሚጠራቸው ስብሰባዎች ሁሉ አይቀሩም።"

ካድሬ ቢኒያም : " አኢሴማና ኢሰፓ እንደነበረች አታውቂምና ነው?"

ሌላ አባል : " ከነዋሪዎች ዶክተር ዋቅቶላ ... በአካባቢያችን በከፈተው ክሊኒክ ገንዘብ የሌላቸውን ነዋሪዎችን የነጻ ህክምና ይሰጣል። በጤና ዘርፍ በምናደርገው እንቅስቃሴ በየመድረኩ በመገኘት የጤና መከላከል ፓሊሲውን ያስተምርናል።"

ካድሬ ቢኒያም : " ሰዎችን እንደሚረዱ አውቃለሁ... ግን ደግሞ መርዳትና ኦነግነት የተለያዩ ናቸው።"

ሌላ አባል : " መምህር ተክላይን መልምያለሁ። በመከላከያ ሚኒስቴር ውስጥ ሰራዊቱንና ታጋዬችን በማስተማር የዜግነት ግዴታውን ተወጥቷል።"

ቢኒያም ፈገግ አለ።ዞር ብሎ በኩራት አጠገቡ የተቀመጥኩትን የቀድሞ ስራ ባልደረባው ገልመጥ አደረገኝ። አፍታም ሳይቆይ እጅን ወደ እኔ እየጠቆመ :

" እኔም ሆንኩኝ እሱ የመከላከያ መምህር ነበርን።ሰራዊቱን የማብቃት ሰራ አመለካከትና ስነ - ምግባር ጥሩ ካልሆነ የሚቻል አይደለም። ተክላይም ቢሆን ተመሳሳይ ባህሪ የነበረው ነው። ዛሬም ቢሆን ይህ አብዬታዊነቱ የአላማ ጽናቱ አልተቀየረም። እንዲወያይ መልምላችሁ መምጣታችሁ የሚያስመሰግን ነው።"

ተመልምለው ከመጡት ሀምሳ ሰዎች አምስት ብቻ በቢኒያም ይሁንታ አለፉ። የቀበሌው ህዝብ በሙሉ በዚህ መልኩ የሚፈረጅ ከሆነ መጨረሻውን ማወቅ አያዳግትም። የቀበሌው አባላት ይዘው የመጧቸው በሙሉ በሾኬ እየተመቱ ሲያስቸግራቸው ተስፉ ቆረጡ። እኔም መጨረሻውን ማወቅ ስለፈለኩ ምንም አስተያየት ሳልሰጥ መመዝገቤን ቀጠልኩ።በመጨረሻ አንድ የእኔ ቅርብ ጓደኛ ኮሌጅ የሚያስተምረው አባል እጁን አውጥቶ:

" ከምሁራን ውስጥ ወጣት አያሌው ይሁን።በኮሌጅ ውስጥ መምህር ነው።ከተማሪዎች ጋር ያለው ግንኙነት በአርአያነት የሚነሳ ነው። በቀበሌያችን ውስጥ ተከራይቶ ለረጅም ጊዜ ኖሯል።"

እጁን አውጥቼ :

" አሁን የጠራኸው ወጣት ምሁር የቅርብ ጓደኛዬ ነው።ለብዙ አመታት አብረን በአንድ ቤት ኖረናል...ቢኒያምም ይህን ያውቃል። ስለዚህ እኔ ባለሁበት ስትወስኑ ተጽእኖ ከማሳድርባችሁ በኃላ ላይ ወስኑ።" አልኳቸው።

ቢኒያም ከአፉ ተቀብሎ " ይሻላል! ጥሩ አስተያየት ነው። ሌላ ጊዜ በደንብ አጣርተን እንወስናለን።" አለ

***

የከተማው ኢህአድግ ክንፍ አባል የሆነው ካሚል ደግሞ ወደ ኮልፌ ቀራንዬ የቀድሞ ወረዳ 24 ቀበሌ 14 በመሄድ ሪፓርቱን ይዞ መጣ። በኢህአድግ ቢሮ ሳገኘው ከአግርሞት አልወጣም። ህብረተሰቡ ይወክሉኛል ብሎ የሚያስባቸው ተብለው በየቀበሌው ካድሬና አባላት የተመረጡት ሰዎች ማንነትና የኃላ ታሪክ አስደንግጦታል። ካሚልና ኢህአድግ ብረት አንስተው የታገሏቸው ናቸው። ብዙዎቹን ኢህአድግ "ህዝቡን በድላችኃል " ብሎ ተሀድሶ ለመስጠት ጦላይ አጉሯቸው የነበሩ ናቸው። እነዚህ ከድል በኃላ በደል የተፈፀመባቸውና ፓርቲው ያራቃቸው ዜጐች በተቃራኒው ነዋሪው እኔን የሚወክሉኝና ከማንም በላይ ያሉትን የማዳምጠው እነሱን ብሎ ማቅረብ እንቆቅልሽ ሆኖበታል። ካሚል የሄደባት ቀበሌ በቅርብ አውቃታለሁ።ብዙዎችን ነዋሪዎች አውቃቸዋል።ግንባር ቀደም ወኪሎች በሚል የ50 ሰዎች ስምዝርዝር ሰፍሯል። ሙሉ ነጥብ ያገኙትን የመጀመሪያዎቹ ሁለት ሰዎች አነበብኩ።

" **ኮረኔል ሞረዳ ዳዲ**: የቀድሞ አብዬታዊት ኢትዬጲያ ሰራዊት ከፍተኛ መኮንን የነበሩ። በጠላት ወረራ ወቅት ለሀገራቸው ከፍተኛ መስዋዕትነት የከፈሉ። የሀገርና የህዝብ ፍቅር ያላቸው። አጥፊ ወጣቶችን መካሪና የሀገር ሽማግሌ።"

" **ማስተር ቴክኒሻን አበራ ጆቴ** : የቀድሞ ኢትዬጲያ አየር ሀይል ከፍተኛ ሙያተኛ። በደርግ ዘመን የቀበሌው ሊ/ መንበር በመሆን በቅንነት ያገለገሉ።በአሁኑ ሰአት ለህብረተሰቡ ቀድሞ ደራሽና በሀዘን ጊዜ አጽናኝ።የእድር አመራር።በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚያስተባብር።"

በአጠቃላይ " ግንባር ቀደም" ተብለው ከተጠቀሱት ውስጥ 70% የሚሆኑት የቀድሞ ሰራዊት አሊያም የደርግ ካድሬ ሆነው ያገለገሉ እንደሆነ ይገልጻል። በጉጉት ሲጠባበቀኝ ለነበረው ካሚል የቀበሌው ካድሬና አባላት የሰጡት መረጃ ትክክል መሆኑን አረጋገጥኩት። የተጠቀሱት ሰዎች በትክክልም ህብረተሰቡ የሚወዳቸው ፣ወጣቶች የሚሰሞቸውና የማስተባበር አቅማቸውን ከፍተኛ መሆኑን በእርግጠኝነት ነገርኩት።ሌሎች አካባቢዎችም በተለይ በጦር ሀይሎች ፣ ልደታ፣ ቶሎሳ ሰፈር ... እንደ ካሚል የሄደባት ቀበሌ ቢሰራ ውጤቱ ተመሳሳይ እንደሚሆን ደግሜ አሳወኩት።

" ኢህአድግ የሰበሰበው የህዝብ ጭራዎችን መሆኑን ዛሬ በሚገባ አረጋግጫለሁ።" ብሎ ተጨማሪ ሳይናገር ጥሎኝ ሄደ... ደርግን ለመጣል ብረት አንስቶ የታገለው ታጋይ ካሚል!!

***

ከቀናቶች በኃላ የተመለመሉ ነዋሪዎች ስምዝርዝር ከሁሉም ቀበሌዎች ወደ ኢህአድግ ማእከል ደረሰ። የቀድሞ የስራ ባልደረባዬ ካድሬ ቢኒያም የሚመራትን ቀበሌ መዝገቤ አወጣሁት። ማጠቃለያ ሰንጠረዡን ማንበብ ጀመርኩ። ከተመለመሉት ነዋሪዎች ውስጥ 50 ትግራይ፣22 አማራ፣15 ኦሮሞ፣ 23 የተቀሩት ብሔር ብሔረሰቦች ይላል። ከኦሮሚያና ከከተማው ገጠር ቀበሌዎች ከፊል ያለባት ቀበሌ ፣እንዲሁም ከአጠቃላይ ነዋሪው ከአስር ፐርሰንት በታች የትግራይ ተወላጆች ባሉበት ሁኔታ እንደዚህ መልምሎ መምጣት ምን የሚሉት አድርባይነት እንደሆነ ግራ ገባኝ። አንደኛውን አቶ መለስ ይቅር ያለው የብሄር

መመዘኛ ወደነበረበት ቢመለስ ይሻል ይሆን ወይ? የሚል ጥያቄ ለራሴ አነሳሁ።

ከቢኒያም ማጠቃላያ ሪፓርት ወጥቼ ስም ዝርዝሩን ማንበብ ጀመርኩ።ከተጠቀሱት 22 የአማራ ተወላጆች ውስጥ የኮሌጅ መምህር ጓደኛዬን አለመ· ይሁን ስም ፈለኩ ... የለም።

***

የተቃውሞ ድምጽ(Protesting Vote)

በአንድ ወቅት ለኢህአድግ ከፍተኛ ካድሬዎች ስልጠና " የቆሰለው ጅብ ተረት" የሚል ሰነድ በአቶ መለስ ተዘጋጅቶ ነበር። የሰነዱ ፍሬ ሀሳብ አብዬታዊ ዲሞክራሲ በመጥፎ መልኩ ሞቶ ግብአተ መሬቱ የሚፈጸምበት እድል ሊኖር እንደሚችል የሚያብራራ ነበር። ይህ የባለ መቶ ገጽ ጽሁፍ ይዘቱ ያልገባቸው እነ አባዱላ ርዕሱ ላይ ተንጠልጥለው : " ማነው ጅብ ? " ፣" ማነው የቆሰለው?" በማለት ሲዘላብዱ ተፈራ ዋልዋ የሳቀባቸው ሳቅና የፓለቲካ አላዋቂነታቸውን ለማሳየት በምፀት የተናገረው ንግግር በኢህአድግ ቢሮ ኦዶቪዥዋል ክፍል ለታሪክ ተቀምጧል።

እውነት ይሁን ተረት ባይታወቅም ጅብ በሚቆስል ሰአት ራሱን ያከመና ስቃዩን ያስታገሰ እየመሰለው ቁስሉን ይበላል። ቀስ በቀስም ራሱን እየበላ በመጨረስ ይሞታል።

በአቶ መለስ በተጻፈው ሰነድ የቆሰለው ጅብ ተረት ወደ ኢህአድግ ሲገለበጥ እውነትነትን የሚያሳይ እንደሆነ የሚያመላክት ነበር: ከቁጥጥር ውጭ ወጥቶ ኢህአድግን ብሎም ሀገሪቱን አደጋ ላይ ጥሎ የነበረው የ93 ክፍፍል፣ አደባባይ ሳይወጣ በውስጠ ድርጅት የታፈነውየ1995 አ• ም• የኢህአድግና የብሄር ድርጅቶቹ ግምገማ ከፓርቲው አንጻር ሊነሱ የሚችሉ ናቸው።

ክፍል ሶስት:

የተገላባጠው ድርጅትና አገራዊ አደጋው!

ከመታወጁ ስድስት ወራት በፊት በኢህአድግ ቢሮ ምርጫውን ለማሸነፍ የሚያስችሉ ዝግጅቶች ተደረጉ። እነዚህ ቅድመ ዝግጅቶች ሁለት የተሳሰሩ ግቦች ነበራቸው :-የምርጫ 97 አይነት መጥፎ ታሪክ እንዳይደገም ማድረግና በመቶ ፐርሰንት ማሸነፍ ። ግቦቹን ለማሳክት የሚያስችሉ ስትራቴጂዎችን ነድፈው እንዲመጡ ሁለት ቡድኖች ተቋቋሙ።

የመጀመሪያው ቡድን በአቶ ካሚል የሚመራ ሆኖ በአባልነት እኔና ፀጋዬ ተጨመርን።... ቡድኑ ምርጫ 97 በፓርቲው ላይ ያሳረፉትውን መጥፎ አሻራዎች ለማስቀረት ምን መደረግ አለበት የሚለውን እንዲያጠና ተደረገ። ባለፈው ምርጫ በኢህአድግና በመንግስት ተከስተዋል የተባሉ ድክመቶችን በመለየት ይዘን እንድንመጣ ተነገረን። የጥናቱ ዳራ ከቅድመ እስከ ድህረ ምርጫ እለት እንዲሆን ተደረገ።

ሁሉን አሟጦ የሚወስደውን ስትራቴጂ የሚቀይሰው ደግሟ በህላዌ የሚመራ ሆኖ የኢህአድግ ቢሮ ፕሮፐጋንዳ ካድሬዎችን የሚያቅፍ እንዲሆን ተደረገ። ... ጥናቱን በአንድ ወር አጠናቀን ለአቶ መለስ ከማቅረባችን በፊት ከበረከት ጋር ለመገምገም የሁለት ሳምንት ቀጠሮ ያዝን።

ቀኑ ደረሶ አቶ በረከት ቢሮ ሄድን።

በዚህ ስብሰባ የተወሰኑት ውሳኔዎች በመዲናይቱ ብቻ ሳይሆን በመላ ኢትዬጲያ የሚካሔደውን የዲሞክራሲ ስርአት ግንባታ የማይሞከርበት ደረጃ አደረሱት። የመድብለ ፓርቲ ስርአት ያበቃለት የሞኝ ለቅሶ ሆነ። የሲቪል ሰርቪሱ ገለልተኝነት የወረቀት አንበሳ ሆኖ ቀረ ። መንግስትና ድርጅት የማይነጣጠሉበት ሁኔታ ተፈጠረ።

ውሳኔዎቹ በፓርቲ ደረጃም ኢህአድግ የይዘት ለውጥ እንዲያመጣ አድርገውታል። ፓርቲው የመርህና የአስተሳሰብ ቀውስ አጋጥሞታል። የድርጅቱ ምሶሶ የሆነው "አብዬታዊነት " ንዙን ጠቅልሎ ከኢህአድግ ተሰናብቷል። የድርጅቱ ርእዬት ለሶስተኛ ጊዜ መሰረታዊ በሆነ መንገድ ተገላብጧል። የፓርቲው የፓለቲካና ፕሮፐጋንዳ ስራ በ180 ° ቀኝ ወደ ኃላ ዞሯል። የኢህአድግ ጉዞ ፣አላማና የመጨረሻ ግብ እንኳን ለካድሬው ለፈጣሪዎቹም ግራ የሚያጋባ ሆኗል።

ወደ አባላት ከተወረደ ደግሞ ሁኔታው እየከፉ ይሔዳል። በአንድ ፓርቲ ውስጥ እርስ በራሱ የሚጣረሱ ሶስት አይነት አባላት ተፈጥረዋል። የአባላት ተልእኮ ፀረ ኢህአድግ ሰዎችን ከመከታተልና ገነዘብ ከማሰባሰብ የማይዘልበት ደረጃ ደርሷል። በእነዚህ አባላት አማካኝነት ድርጅቱ በተዘዋዋሪ መንገድ በየአመቱ ከሶስት ቢሊዬን ያላነሰ ገንዘብ ከመንግስትና ህዝብ የሚወስድበት ስርአት እንዲገነባ አድርጓል።ኢህአድግ በአለም ውስጥ ካሉ ሀብታም የፓለቲካ ድርጅቶች በመጀመሪያዎቹ ረድፍ እንዲሰለፍ ሆኗል።

ይህ ሁኔታ በኢህአድግና በተቃዋሚዎች መካከል ያለውን የሰው ሀይል የውቅያኖስና የኩሬ ያህል ልዩነት እንዲኖረው አድርጓል።ገዥው ፓርቲ ከ6.1ሚሊዬን በላይ አባላት በመያዝ በአለም ተወዳዳሪ የሌለው ድርጅት ሆኗል። ልምድ የተወሰደባት የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ ለ – – – – ቢሊዬን ህዝብ ያለው

አባል ብዛት 4 ሚሊዬን ያህል ነው። ከገንዘብም አንጻር ኢህአድግና ተቃዋሚ ፓርቲዎች ልዩነታቸው የትየለሌ ሆኗል። ኢህአድግ በቢሊዬን የሚጠጋ ብር አውጥቶ የስልጠና፣ባህልና መዚየም ሊያስገነባ እየተጋ ባለበት ሁኔታ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ለጽህፈት ቤታቸው ኪራይ መክፈል አቅቷቸው ይንገታገታሉ። አንዳንዶቹ መስመራቸውን "ታማኝ ተቃዋሚ " በሚል አስተካክለው ከኢህአድግ በሚወረወርላቸው መና ይግተረተራሉ። ኢህአድግ ምርጫ ቦርድ የሚሰጠውን ገንዘብ አምቢ በማለት ለታማኝ ተቃዋሚዎቹ ያከፋፍላል። በምርጫ 2002 ምርጫ ቦርድ ከመደበው አስር ሚሊዬን ውስጥ ዘጠኝ ሚሊዬኑ ለኢህአድግ ደርሶታል።

አርቆ ለተመለከተው ከላይ የተጠቀሱት ውጤቶች የኢህአድግን የማይቀረውን የተፈጥሮ ሞት እያፋጠኑት መሆኑን ይሆናል። ድርጊቶቹና ውጤታቸው ፓርቲው ወደመቃብር በፍጥነት እየተወረወረ መሆኑን የሚያመላክቱ ናቸው። በማግበስበሱ ምክንያት ወደ ማሰሮ ሆድነት የተቀየረው የኢህአድግ መዋቅር ትንሽ ሽንቁር ሲያጋጥመው የሚከሰተው አደጋ አስከፊ ሊሆን ይችላል ። እንደ ፀሀፊው እምነት አደጋውም ከውስጥ ወደ ውጭ ይፈሳል። ከድርጅት አልፎ የሀገሪቱ ህልውና ላይ የሚያንጎበብ ይሆናል። በተግባርም እየታየ ያለው ይህ ነው።

ወደዚህ ሀገራዊ አደጋ የሚያመጣ የኢህአድግ ነጫጭ ዝሆኖች ታሪክ ከመግባታችን በፊት በአቶ ካሚል መራሹ ቡድን የጥናት ውጤትና በአቶ በረከት በተጻፈው የሁለት ምርጫዎች ወግ መጽሀፍ መካከል ያለውን ተቃርኖ ወደ መመልከት እንሸጋገር።

ተገላቢጦሽ

የህላዌና የካሚል ቡድን አባላት የጥናት ውጤታችንን ይዘን አቶ በረከት ቢሮ ተገኝተናል። ቅድሚያ የተሰጠው በካሚል ለተመራው የእኛ ቡድን ነበር። ጥናቱን የሰራነው ለአባላት መጠይቆችን በማውረድ፣ በየቀበሌው የቡድን ውይይቶችን በመክፈት፣ ልማታዊ ምሁራንና ባለሀብቶችን በማሳተፍ እንደሆነ ገለጽን። ከቀረቡት አስተያየቶች በመነሳት ኢህአድግ በምርጫ 97 የፈፀማቸውን ጥፋቶች በሶስት በመክፈል አቀረብን። በምረጡኝ ዘመቻ ፣በምርጫ ምልክትና ሌሎች ቴክኒካል ጉዳዬች በሚል።

በምርጫ ክርክር ወቅት ኢህአድግ ባልተዘጋጀበት ሁኔታ በሩን መበርገድ አልነበረበትም። ግንቦት ለሚካሔድ ምርጫ መስከረም ጀምሮ የሚዲያ ክርክር መካሔዱ ጥፋት ነበር። በክርክሩ ወቅት ኢህአድግን ወክለው የቀረቡ ካድሬዎች ደካማ የፓለቲካ ብቃት ማሳየታቸው ሳያንስ ሊጠቀሙባቸው የነበሩት አደገኛ ቃላት ("ኢንተርሀምዊይ" ልብ ይሏል!) የምርጫው ውጤት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አሳድረዋል። በምረጡኝ ዘመቻ ወቅት ኢህአድግን ምረጡ ብሎ በሙሉ ወኔና ፍላጐት የተንቀሳቀሰ አጨና አባል አልነበረም። በምርጫው ዋዜማ ሚያዝያ 30 የተካሔደው የተቃዋሚዎች የድጋፍ ሰልፍ መፈቀድ አልነበረበትም... የሚሉ ቁምነገሮች ላይ መነሻ ሀሳብ አቀረብን።

አቶ በረከት ጥናቱ ትክክል መሆኑን ለማሳየት በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ አሰደማሚ መገለጫዎችን አቀረበ።

አፋችንን አስከፈተን!...

ጉድ ሳይሰማ... እንዲሉ ግምገማው የተጻፈበት ብእር ሳይደርቅ ተገላብጦ " የሁለት ምርጫዎች ወግ" በሚል በመፅሀፍ መልክ ተዘጋጀ። ለህዝብም ይፉ ሆነ። ከአቶ በረከት ጋር አብረን የነበርን ካድሬዎች ይህንን ሲፅፍ ምን ያህል ከራሱ ህሊና ጋር እንደተጣላ ለመገመት አንቸገርም። በታሪኩ ውስጥ ያለፉና አብረውት ያሉ ሰዎችም ቢሆኑ " ኧረ እዚህ ጋር ያለው ሀቅ ተዛብቶ ቀርቧል " አለማለታቸው አስገራሚ ነው።

ህዝብ እውነትን የማወቅ መብት እንዳለው መገንዘብን ለጊዜው እንተወው። ነገር ግን የትላንትና ታሪካችን ውስጥ ይህ ድክመት ነበረብን ብሎ መናገር ምን ያህል የህዝብ ከበሬታን እንደሚያስገኝ አለመረዳት እንዴት ያቅታል? በታሪኩ ውስጥ አብረውን ያሳለፉ ሰዎች አንድ ቀን እውነቱን ሊያወጡብን ይችሉ ይሆናል ብሎ አለማሰብስ ምን የሚሉት ንቀት ነው? በዝምታ ውስጥ መኖር አላዋቂነት አይደለም። እንደዚህ አይነት አርምሞን የሚነካ ሀሳብ ተጽፎ ዝም ማለት ደግሞ ሌላ የህሊና ሸክም ይፈጥራል። እውነትን እስከ መቼ ሸሽተናት እንኖራለን የሚል ጥያቄ ያስነሳል።ያውም አንዳንዶቹ ፀሀይ የሞቃቸው ሆነው።

እናም ዝምታ ተሰበረ። ከግለሰብ አልፎ ሀገር የሚንድ እውነታ ተክዶ ሳይ ማን ያርዳ የቀበረ እንዲሉ ሆንኩ። ጊዜ ስታገኝ ተናገር አይደል አባባሉ። ስለዚህም የቀጣይ ወጋችን በአቶ በረከት መጽሀፍና ፣ እሱ በመራው ስብሰባ የቀረቡ ድምዳሜዎች ላይ ያለውን ተቃርኖ ወደ መመልከት እንሸጋገር።

ፍርዱን ለአንባቢ ትተን...

***

አቶ በረከት በመራው ግምገማ ቅድሚያ ትኩረት ያገኘው የምርጫ ክርክሩ ነበር። በክርክሩ ወቅት በሚያስደነግጥ ሁኔታ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ስዩም መስፍን " ኢንተርሀምዌይ " የምትል መርዘኛ ቃላት ወጣች። ይህ ሀገር የሚያጫርስ ቃላት ያውም ከአንድ የውጭ ጉዳይ የበላይ ካድሬ መመንጨቱ ሆን ተብሎ የታሰበበት መሆኑ መነገር ተጀመረ።በዚህም ህዝቡ ቁጣውን ገልጸ። የኢህአድግ ቱባ ባለስልጣናት ገመና ተዘረገፈ። በተከታታይ ፓለቲካዊ ክርክር ሳይሆን በስድብ የታጨቁ ዛቻዎችን በማሰማታቸው ህዝቡ ናቃን። ሁኔታው ከህዝቡ አልፎ የድርጅቱ ደጋፊዎችን ሳይቀር የሚያሸሽ ሆነ።

አቶ በረከት በግምገማው ወቅት " እንደዚህ አይነት ህዝብን የሚያስኮርፉ አላስፈላጊ ቃላት መጠቀም አልነበረብንም ። ኢህአድግን ከሚደግፉ ዲፕሎማቶች ሳይቀር መሳሳታችንን ነግረውናል ። የምርጫ 97 የመሸነፍ አንዱ ምክንያትም ራሳችንን መሸጥ አቅቶን የማይረባ የቃላት ጨዋታ መጫወታችን ነው።" ብሎ ተናገረ።

ከአመታት በኃላ የወጣችው "የሁለት ምርጫዎች ወግ " ይህንን ሀቅ መቀበል አልፈለገችም። እንደተለመደው የማላከክ አመክንዬ ተጠቅማለች። እንዲህ በማለት: -

" ... የአቶ በድሩ ንግግር እንደተላለፈ ኢህአድግ ወደኃላ ተመልሶ የቅንጅት መሪዎችን አስተሳሰብ ለማሳየት የተጠቀመበት አገላለፅ ትክክል

እንደነበር ለማመላከት ሞክረ። ኢህአድግ በምረጡኝ ቅስቀሳ ሂደት ይህን አስተሳሰብ በሚወክሉ አገላለጾች በመጠቀም ጉዳዩን ለማስገንዘብ ጥረት አድርጐ የነበረ ቢሆንም የሚሰማው ግን አላገኝም ነበር።"ይላል።

በዚህ አርፍተ ነገር ውስጥ ብዙ የታጨቁ ቁምነገሮች አሉ። በመጀመሪያ የሚታየው አቶ በረከት ስህተትን በስህተት በማረም ራስን ነጻ የማውጣት አካሔድ መከተሉን ይሆናል። የገሎ መዳን ስትራቴጂ... አቶ በድሩን ገሎ ፣ኢህአድግን ነፃ ማውጣት።

አቶ በድሩ አደም ቀድሞ ከኢህአድግ ጋር ያላቸውን ቅርርብ የአደባባይ ሚስጥር ነው። ሰውየው በኦሮሚያ ዞኖች ለምርጫ ሲወዳደሩ በአቶ መለስ ቀጥተኛ ትእዛዝ ወንበር ይለቀቅላቸዋል። ያለ ኢህአድግ ተወዳዳሪ አሊያም በደካማ ተፎካካሪ ይቀርባሉ። በምርጫ ጣቢያው ያሉ የኢህአድግ አባላት እሳቸውን ለማስመረጥ ይሰራሉ። ፓርላማ በግል እጩነት ከገቡም በኃላ ከጐን ድግፍ ይደረግላቸዋል። ሽንጐውን ያሞቁታል። በእሳቸው ሊቀርቡ የሚገባቸው የአፈጻጸም ግድፈቶችና መመታት ያለባቸው የኢህአድግ ባለስልጣናት ዶሴ እንዲደርሳቸው ይደረጋል። እሳቸውም የግለሰብ አጀንዳና ቅሬታ ሳይቀር የተከበረው ፓርላማ ድረስ ይዘው ይገባሉ...አቶ በድሩ በፓርላማ ዘመናቸው ወደ ግለሰብ ጉዳይ አስፈጻሚነት ተንሸራተው ነበር። በወቅቱ እኔ በነበርኩበት ዞን ከአንዱም ሁለቱ የግለሰብ ፉይል ይዘው መጥተው ተጨቃጭቀናል።

በምርጫ 97 ዋዜማ ኢህአድግ መወዳደሪያ ወንበር እንደማይለቅ የተገነዘቡት የተከበሩ አቶ በድሩ አደም ወደ ተቃዋሚ ጐራ ይቀላቀላሉ። ህዝቡ በጥርጣሬ እንዳይመለከታቸውና በእርግጥም ከኢህአድግ መፋታታቸውን ለማረጋገጥ ቀን ይጠብቃሉ...ሚያዝያ 30 ትመጣለች። እሳቸውም ከዚህ የተሻለ አጋጣሚ እንደማይመጣ በመረዳት "ግንቦት ሰባት ቀን ኢህአድጐችን ወደ መጡበት እንመልሳለን!" በማለት ሌላ መርዛማ ንግግር አደረጉ። ይህ ሾላ በድፍኑ የሆነ ቃል ምንም አይነት ምክንያት ሊቀርብለት የማይችልና እልቂት ሊያስከትል የሚችል አባባል ነበር።

እኔ ኢህአድግ ነበርኩ። ያውም በእምነት የምተጋ ካድሬ። ከራሴ አልፌ በአስር ሺዎች የሚጠጉ የዩንቨርስቲ ተማሪዎችን በአብዬታዊ ዲሞክራሲ በማጥመቅ ኢህአድግ አድርጌያለሁ። ብዙዎቹ ካድሬዎች ሆነው በመንግስትና ድርጅት ስልጣን ላይ ተቀምጠዋል። እነዚህ ሺዎች የአቶ በድሩ ልጆች አሊያም የልጅ ልጆች ናቸው። እናስ ወዴት ይሂዱ? የተፈጠሩት እሳቸው ከተፈጠሩባት ኢትዬጲያ ከምትባል ሀገር ነው። የኔ ቢጤዎቹ ደግሞ እትብታችን የተቀበረው በዝች መከራዋ በማያልቅ ባለቤት የሌላት ከተማ ነው... ወዴት እንሂድ?...

የአቶ በድሩ ያልተገራ ንግግር በተደመጠ ምሽት ዶክተር ብርሀኑ ነጋ ለበረከት እንደደወለለት አጫውቶኛል። የበድሩ ንግግር በተናጠል ራሱን እንደ ቡድን ደግሞ ቅንጅትን አይመለከትም ብሎ እንደነገረው። እንግዲያውስ መግለጫ አውጡ እንዳለውና እስቲ እንነጋገርበታለን የሚል ምላሽ እንደሰጠው ነግሮናል። በሂደትም ለማረጋገጥ እንደተቻለው በአንዳንድ የተቃዋሚ አመራሮች ዘንድየሰውየው ንግግር ትችት ገጥሞት ነበር።

አቶ በድሩ ከአፍ ወለምታ በዘለለ ተሳስተዋል። የአንድ ፓለቲካ መሪ

ብቃት ከሚለካበት ነገር ዋነኛው ሰውንና አመለካከትን የመለየት ባህሪው ነው። ርግጥ የኢትዬጲያ ፓለቲካ ጨፍልቆ የሚያይ ስለሆነ እሳቸው ተለይተው ላይፈረድባቸው ይችላል። ይህም ሆኖ የግለሰቡ ስህተት በምንም መልኩ ኢህአድግ " ኢንተርሀምዌይ " ብሎ የገለፀውን ቃል ትክክለኛነት የሚያሳይ አይደለም። በኢህአድግ ውስጠ ድርጅት ግምገማ "ልክ አልነበረንም! ይህ አባባላችን የሩዋንዳውን እልቂት አንደመጮተት ይቆጠራል" በማለት ድምዳሜ ላይ ተደርሷል። ውሳኔው ለኢትዬጲያ ህዝብ በይፋ ቀርቦ ይቅርታ መጠየቅ ነበረበት።

በነገራችን ላይ አቶ በረከት ሀሊናው ያላመነበት ነገር እንደፃፈ የሚያስታውቀ ነገርከመጽሀፉ ለማየት ይቻላል : - ይህቺን "ኢንተርሀምዌይ " የምትል መርዘኛ ቃል በመፅሀፉ ላይ አንድም ቦታ አልአሰፈረም። በደምሳሳው " የተቃዋሚን አስተሳሰብ በሚወክሉ..." የሚል ቃላትን ለመጠቀም ተገዷል። የኢንተርሀምዌይ መዘዝ ብዙ ነው። በተለይ ታሪካዊ አመጣጡን ዞር ብሎ ለተመለከተው እጅ የሚቀሰረው ማን ላይ እንደሚሆን ግልጽ ነው።

በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ቀጥሎ የምናገኘው ቁምነገር አቶ በረከት ህዝቡ መሳሳቱን በተዘዋዋሪ የተናገረበትን ሁኔታ ነው። ህዝቡ ትክክል እንዳልነበረና " ብንነግራችሁ አልሰማን አላችሁ " በማለት የገለፀበትን ሁኔታ እናገኛለን። ሁሉም እንደሚያስታውሰው የኢትዬጲያ ህዝብ ሰላማዊ የምርጫ ውድድር ማየት እንደሚፈልግ ደጋግሞ ተናግሯል። በሁሉም ወገኖች የምርጫ ክርክሩን ወደ አስደንጋጭና አስፈሪ መድረክነት የሚገለብጡ ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ አሳስቧል። የእምነት ተቋማት ሳይቀሩ የትምህርታቸውን ማሳረጊያ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ከቃላት ጦርነትና መገፋተር ወጥተው ለሀገር በሚበጅ መልኩ እንዲፎካከሩ ተማጽነዋል። የሀይማኖት አባቶች " ኢንተርሀምዌይም " ሆነ " ወደ መጡበት እንመልሳለን " የሚሉት ቃላት በጋራ መስራትንና መከባበርን ስለማያመጡ ህዝቡ እንዲያወግዛቸው ጥሪ አስተላልፈዋል። አቶ በረከት ይህንን እውነት እንዳላለፈበት ሁሉ የኢህአድግን የሁልጊዜም ትክክለኛነት ለማሳየት " ሰሚ ጆሮ አላገኘንም" በማለት ህዝቡን ይወቅሳል።

***

ሌላው በቡድኑ ጥናትም ሆነ በአቶ በረከት አስተያየት የቀረበው የኢህአድግ ከፍተኛ ካድሬዎች በክርክር ወቅት ያሳዩት ደካማ ብቃት ነበር። በሚዲያ ክርክር ወቅት ኢህአድግን ወክለው የቀረቡ ባለስልጣናት ያሳዩት አሳፋሪ የፓለቲካ ብቃት ምርጫውን በዝረራ እንድንወጣ አስተዋጽኦ አበርክቷል የሚል ነበር። አቶ በረከት ካድሬዎች የብቃት ማነስ ብቻ ሳይሆን በአቀራረብ ደረጃ በጣም አሰልቺና የህዝብን ፍላጐት ማእከል ያላደረጉ በመሆኑ መራጩ ህዝብ ፊቱን ከኢህአድግ እንዲያዞር አስተዋጽኦ አድርጓል በማለት የወቅቱን ሁኔታ በሰፊው አብራርቷል። በመሆኑም በምርጫ ክርክሩ መሸነፋችን የቅድሚያ ውጤቱን የሚያመላክቱ ነበር ብሏል።

በተቃራኒው ከሶስት አመት በኃላ በሁለት ምርጫዎች ወግ መጽሀፍ ላይ የክርክሮቹን ፉይዳ በማሳነስ እንደሚከተለው ሰፍሮ እናገኛለን :

"... በአገራችን የሚካሄዱ የምርጫ ክርክሮች ነገር ከሚሚቅ ባለፈ

የምርጫ ውጤትን የሚወስኑበት ደረጃ ላይ የደረሱ አይደሉም። በመሆኑም በምርጫ 97 የክርክሮች ፉይዳ የምርጫውን ውጤት እስከመወሰን የደረሰ ነበር ሊባል አይችልም። "

***

የአቶ ካሚል መራሹ ቡድን በመጨረሻ ያቀረበው የውሳኔ ሀሳብ ኢህአድግ ለረጅም አመታት ሲጠቀምባት የነበረችውን የምርጫ ምልክት "ንብ " የተመለከተ ነበር። በምርጫ 97 ቅስቀሳ ወቅት ህዝቡ የኢህአድግ አባላትና እጩዎችን በተመለከተ ቁጥር " ዝንቦቹ መጡ !" በማለት በግልፅ ተናግሯል። በሚያዝያ 30 በተደረገው ሰላማዊ ሰልፍ " ዝንብ! ዝንብ! ዝንብ! " የሚሉ በዜማ የታጀቡ የተቃውሞ ድምጾች ጐልተው ተሰምተዋል። ከምርጫው ውጤት በኃላ ለምን ተሸነፍን የሚለውን በተደራጀ መንገድ ለማወቅ በመላ ሀገሪቱ የአባላትና ካድሬ ስብሰባ ተደርጐ ነበር። እናም ታታሪዋ ንብ እጅ ተቀሰረባት።

አቶ በረከት የምልክት አመራረጣችን ችግር እንደነበረበት አረጋገጠ። ለቀጣይ ምርጫዎች ኢህአድግ በሌላ ምልክት እንደሚቀርብ ተናገረ። ውሳኔውን ተከትሎ በሚሚያ ፣ አካባቢና አዲሳባ ዳግም ምርጫ የኢህአድግ የምርጫ ምልክት ወደ "ችቦ " ተቀየረ። ለችቦ ምልክትም የተለየ ትርጉም ተሰጠው። ይህም ሀገራችን ወደ አዲሱ ሚሊኒየም በታላቅ መንፈስ እየገባች ያለችው በመሪ ድርጅቱ ኢህአድግ አማካኝነት እንደሆነና የህዳሴው ችቦ በማይጠፉ መልኩ መለኮሱን ለማብሰር የሚል ነበር። የተለኮሰው ችቦ እንደ ኦሎምፒክ ሁሉ በቅብብሎሽ ለዘላለም ይበራል በማለት የፓርቲው ምልክት ችቦ ሆኖ ለሚቀጥሉት ረጅም አመታት ይቀጥላል የሚል ውሳኔ ተላለፈ።

በምርጫ ውድድሩም ኢህአድግ ችቦን ይዞ ብቅ አለ። በመንግስት ሚዲያዎችና የግል ፕሬሶች የኢህአድግ የመወዳደሪያ ምልክት መቀየሩ የተለያዩ መላምቶች ተሰጠውበት ተዘገበ። አንዳንድ የተቃዋሚ አመራሮች " ምልክት በመቀየር ውስጣዊ ባህሪ አይቀየርም ! " የሚሉ አስተያየቶችን ሰጡ። ምንም እንኳን ተቃዋሚዎች ራሳቸው በጐንዬሽ የቀድሞው ቅንጅት ምልክት የሆነችውን የጣት አርማ እንዲሰጣቸው ለኢህአድግ ተማጽኖ ቢያቀርቡም።

አቶ በረከት ይህንን ወደ ተግባር የተለወጠ እውነት እያወቀ በመጽሀፉ ላይ የ2000 ምርጫ በገለፀበት " ታሪክ ራሱን ደገመ ወይስ ... ?" በሚለው ርእስ ስር የሚከተለውን አስፍሮ እናገኛለን :

"... ኢህአድግ ለፈረንጆቹ በተናዳፊነት ፣ ለኢትዬጲያውያን ደግሞ በታታሪነት የምትታወቀውን ንብ ይዞ ፣ተቃዋሚዎች ደግሞ መልኩ ቢለያይም የተለመደችውን ጣት ይዘው ቀርበዋል።... ንብም ሆነ ጣት፣ ፈረስም ሆነ መጽሀፍ የምርጫ 97 ተፎካካሪዎች የተጠቀሙባቸውን አልባሳት እንዳልቀየሩ አመላካች ነበር።" ይላል።

መቼም የአዲሳባ ህዝብ ኢህአድግ ላይ መቀለድ አያቆምና በአዲስቷ ምልክት "ችቦ "ላይም ተፊዘባታል። እስቲ አንዷን ብቻ ላንሳ :

ለአባሎቻችን የኢህአድግ ምልክት ከእንግዲህ በኃላ "ችቦ " መሆኑን በመንገር የተለያዩ ፈጠራዎችን ተጠቅማችሁ አስተዋውቁ ብለን ስምሪት ሰጠን። የአጋጣሚ

ነገር ሆኖ ምርጫ ቦርድ አሰርቶ የሰጠን ችቦ የአይስክሬም ቅርጽ የሚመስል ነበር። እናም ለፈጠራ የተፈጠሩት አባሎቻችን የምርጫው እለት ቅስቀሳቸው " አይስክሬሚን ልሳችሁ ውጡ!" የሚል ሆነ። በቂርቆስ የሚቀሰቅስ አንድ እሳት የላሰ ካድሬ በየቤቱ እያንኳኳ " የምርጫ ሰአት እያለፈ ነው። ወጥታችሁ ኢህአድግን ምረጡ!" እያለ ይቀሰቅሳል። አንድ እናት በአጠገቡ ሲያልፉ ጠጋ ብሎ " ማዘር ! እንዳይረሱ አይስክሬሚን ነው ልሰው የሚወጡት " ይላቸዋል። ማዘርም ዋዛ አይደሉምና " አይ ልጄ! በባዶ ሆድ አይስክሬም ? ቀኑን ሙሉ ከሚያስመልሰኝ እንደለመድኩት ጦሜን ብውል ይሻለኛል" አሉት። ጦም ውላ ያደረች የምርጫ ወረቀት ሳጥኑ ውስጥ አኑረው ሄዱ።ይህ ተግባር የአስር ሺህ እናቶች ሆኖ ዋለ።

የኃልዬሽ ጉዞ ወደ ግሪክ አቴንስ

በህላዌ ዬሴፍ የተመራው ሁለተኛ ቡድን የከተማው ብሎም የሀገሪቷን ምርጫ የሚመራበትን ስትራቴጂ በመንደፍ ለውይይት አቀረበ። ቡድኑ ለእንግዲህ የሚካሄዱ ምርጫዎችን ሙሉ ለሙሉ አሸንፎ ለመውጣት የሚያስችል ግብ አስቀመጠ። ይህን ለማሳካት እንዲረዳ ሁለት የተቀናጁ አቅጣጫዎችን ቀረፀ። እነዚህም የህዝብ ቀጥተኛ ተሳትፎ ማስፋት ፣ በህብረተሰቡ ዘንድ ተሰሚነትና ተቀባይነት ያላቸውን አጨዎች መመልመልና ከምርጫው ሂደት ይልቅ ውጤቱ ላይ ማተኮር የሚሉ ነበሩ። እነዚህን አቅጣጫዎችና አፈጻጸማቸውን ጠለቅ ብሎ ለመረመራቸው የኢትጲያ ዲሞክራሲ ጉዞ በብዙ ሺህ አመታት የኃሊት እንደተንሸራተተ መመልከት ይችላል። ኢህአድግም ቢሆን ማንነቱን ያጣበት ሁኔታ የፈጠረ ነበር።

የኢህአድግ ዲሞክራሲ ግንባታ በቅርጽ ሲታይ የታዋቂው ሳይኮሎጂስት አብርሀም ማስሎ የፍላጐት መሰላልን ይመስላል። በታችኛው ትሪያንግል ቀጥተኛ ዲሞክራሲን የሚያሰፉ ሆኖ ወደ ላይ በተወጣ ቁጥር የግለሰቦችን ዘላለማዊነት የሚያረጋግጥ ይሆናል። የአንድ ፓርቲ የበላይነት በሰፈነበት ሁኔታ እንዲህ አይነት ስርአት መዘርጋት በህዝብ ቀጥተኛ ተሳትፎ ስም በታችኛው መዋቅር የህዝብ ጩኸት የሚታፈንበት ይሆናል። ይህንን እንደ መደላድል በመውሰድ የፒራሚዱ ጫፍ ላይ ያሉት ሰዎች ራሳቸውን ወደ ገዥ መደብ በመቀየር ፈላጭ ቆራጭ የሚሆኑበት ሁኔታ ይፈጥራሉ።

የህላዌ ቡድን "የህዝቦች ቀጥተኛ ተሳትፎ " የሚለውን ህገ መንግስታዊ ድንጋጌ በማጣቀስ በመካከለኛና ዝቅተኛ እርከን ያሉትን የምክር ቤቶች አባላት ብዛት ለማሳደግ የሚያስችል ፕሮፓዛል አዘጋጀ። ፕሮፓዛሉ የወረዳ ምክርቤት አባላት ከ50 ወደ 200 ፣ የቀበሌ ደግሞ ከ50 ወደ 500 እንዲሆን ሀሳብ አቀረበ። የሚገርመው ነገር በመነሻ ሀሳቡ ላይ ረቡዕ በኢህአድግ ቢሮ ውይይት ተደርጐበት ሀሙስ ጠዋት በፓርላማ በአስቸኳይ አጀንዳነት ቀርቦ እንዲፀድቅ ተደረገ።

እድሜ ለአባይ ነብሶ : የሸንጐው ቁልፍ ካድሬ !

የፓርላማው አዋጅ የአዲሳባ ምክርቤት አባላትን የሚወስን ብቻ ሳይሆን በከተማዋ ምርጫ የሚካሄድበትን ቀን በታቀደና በተጠና መንገድ የቀየረ

ሆነ። ወትሮ የከተማዋ ምክርቤት ምርጫ ከፌደራልና ክልሎች ጋር አብሮ የሚካሄድ ነበር። በቡድኑ ጥናት መሰረት እነዚህ ውድድሮች በተመሳሳይ ጊዜ በመካሄዳቸው ምክንያት የአዲሳባ ምርጫ የፓርላማው ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አሳድሯል የሚል ነበር። የፌደራሉን አስቀድሞ በሁለት አመቱ የአዲሳባ ቢሆን የከተማው ህዝብ በፌዴራል ደረጃ ኢህአድግ መንግስት ሆኖ እያየ ከተማዋን እንዲያስተዳድሩ ተቃዋሚዎችን የመምረጥ ፍላጐት አያድርበትም። በመዲናይቱ የሚኖሩ የኢህአድግ አባላትም በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት " የፌዴራል መንግስት ኢህአድግ በሆነበት ሁኔታ ለከተማዋ መስተዳድር ተቃዋሚዎችን ብትመርጡ ልማቱ ወደኃላ ይቀለበሳል። አዲሳባ የሁከትና ብጥብጥ ከተማ ትሆናለች " የሚሉ ቃላቶችን በመጠቀም የህዝቡ አሰላለፍ ከኢህአድግ ጋር እንዲሆን ያደርጋሉ የሚል ነበር። እንደተገመተው በምርጫ 2000 አ• ም• ይህ ቃል ገዥ መቀስቀሻ ሆኖ ከረመ።

የዛሬይቱ ኢትዬጲያ ከ4•2 ሚሊዬን በላይ ፣ መዲናይቱ ደግሞ ወደ 55ሺህ ያህል የምክር ቤት አባላት ይገኙባታል። ይህ ለማመን የሚያስቸግር ቁጥር የሚያመላክተን ነገር አለ። የህዝቦች ቀጥተኛ ተሳትፎ በማለት በህገመንግስቱ የተቀመጠውና በፓርላማ የፀደቀው ፀረ ዲሞክራሲ አዋጅ እስካለ ድረስ በመላ ሀገሪቱ የሚካሔዱ የአካባቢ፣ የአዲሳባና ድሬደዋ የምክር ቤት ምርጫዎች የተበሉ እቁቦች እንደሆኑ ይቀጥላሉ። የሚገርመው የኢትዬጲያ የምክር ቤት አባላት እንደ አንድ ሀገር ህዝብ ቢቆጠሩ በአፍሪካ እነ ላይቤሪያ፣ ጋቦን፣ ናሚቢያንና ቦትስዋናን በመቅደም ከአፍሪካ ሀገሮች 39 ኛ ደረጃ ላይ ይቀመጡ ነበር።

የቁጥሩን አስደንጋጭነት ወደ ጐን ትተን በህገ መንግስቱና በአቶ መለስ የዲሞክራሲ ስርአት ግንባታ በኢትዬጲያ የሚለውን መጽሀፍ ላይ እንደሰፈረው እነዚህ የምክር ቤት አባላት እውን የህዝብን ቀጥተኛ ተሳትፎ ያረጋግጣሉ ወይ? የሚለውን ጥያቄ ማንሳቱ ተገቢ ይሆናል።

መነሻችን አዲሳባ በመሆኑ በመዲናይቱ ስለሚገኙት ከ55 ሺህ በላይ የቀበሌ ምክር ቤት አባላት ስልጣንና ተልእኮዎች በማንሳት እንጀምር። እነዚህ የገዝቀተኛ ምክር ቤት አባላት የአንድ ፓርቲ የበላይነት በሰፈነበት ሁኔታ የዲሞክራሲ ማፈኛ ተቋማት ሆነው በማገልገል ደረጃ የጐላ ሚና ይጫወታሉ። ዋነኛ ስራቸውም የአካባቢያቸውን ፀጥታ በመጠበቅ ስም የነዋሪውን ኮቴ መከታተል ነው። በአንዲት ቀበሌ ውስጥ ከ500 ያላነሱ የምክር ቤት ካባ ያጠለቁ አባላትና ካድሬዎችን ማሰማራት ነዋሪው ውስጥ ምን ያህል መረበሽና በነጻነት ያለመናገር ሁኔታ ሊፈጥር እንደሚችል መገመት ይቻላል። በእንቅርት ላይ እንዲሉ በእነዚህ እርከኖች በብዛት የሚሰማራው ካድሬ ህገ መንግስቱን እንኳን በአግባቡ ያላነበበና የንቃተ ህሊና ችግር ያለበት በመሆኑ እያንዳንዷን የተቃውሞ ቃላት " በፀረ - ህዝበኝነት " የመፈረጅ ባህሪው የተለመደ ነው። አንድ የምክር ቤት አባል በሚኖርበት ሰፈር ውስጥ በእድር አሊያም በለቅሶ ቤት ከኢህአድግ የተለየ አቋም ከያዘ መጀመሪያ ጠላት፣ ለተከታታይ ቀናት ካራመደ ደግሞ በሽብርተኝነት ጐራ ይሰለፋል።

በአጠቃላይ ሲታይ ኢህአድግ ለ80 ሚሊዬን ህዝብ ከ6ሚሊዬን በላይ

አባላትና የምክር ቤት ካድሬዎችን በማሰማራት በአባላት ብዛት በአለም ተወዳዳሪ የሌለው ፓርቲ ሆኗል። በሌላ በኩል ኢህአድግ ልምድ የወሰደበት የቻይና ኮሙዩኒስት ፓርቲ ለ1•4 ቢሊዬን ህዝብ ያሰማራው የአባል ብዛት 4 ሚሊዬን አካባቢ ነው። በመሆኑም ከዚህ በኃላ የልምድ ልውውጡ ተገልብጦ ጓድ Xi Jinping ወደ አዲሳባ በመምጣት ከጓድ በረከት ጋር ይመክራሉ።

***

" አብዬታዊነት ድሮ ቀረ! "

በህላዌ የተመራው ቡድን በሁለተኛ ደረጃ ለውይይት አቅርቦት የፀደቀው የእጩ ምልመላ መስፈርት መለወጥ በተመለከተ ነበር። ከዚህ በፊት ኢህአድግ ለምርጫ ውድድር የሚመለምላቸው እጩዎች በድርጅቱ መርሆዎች ላይ በመመስረትና የፓርቲው ማህበራዊ መሰረቶች ከሚባሉት ላይ ነበር። መስፈርቶቹም : አብዬታዊነት (ወገንተኝነት) ፣ የአላማ ጽናትና የብሔር መብቶችን እስከመገንጠል በእምነት የሚቀበል የሚል ነበር። ከእነዚህ ውስጥ አብዬታዊነት 60% ያህል ድርሻ ይኖረዋል። በመሆኑም የኢህአድግ ማህበራዊ መሰረት ያልሆኑት ከፍተኛ ምሁራን ፣ባለሀብቶችና ከቀድሞ ስርአት ጋር ንክኪ ያላቸው ሰዎች በእጩነት እንዳይመለመሉ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚያደርግ ነበር።

የኢህአድግ የውስጠ ድርጅት መመሪያ ከፍተኛ ምሁራንን በሁለት ጐኑ የተሳሉ ቢላዋ በማለት በንኡስ ከበርቴነት ጐራ ይመድባል። በጀማሪ ካፒታሊዝም ውስጥ የምሁራን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መሰረት ለጥገኛ ዝቅጠት የተመቸ እንደሆነና ከፍተኛ መደላድል እንደሚፈጥር ያሳስባል። በመሆኑም የምሁራን አሰላለፍ በንኡስ ከበርቴ ደረጃ በመሆኑ በህዝብ ውስጥ የሚካሔደው ትግል ሲፋፋም በመጀመሪያው የንቅናቄ መስመር በማሰለፍ ግንባራቸውን ለጥይት እንደሚሰጡ፣ ትግሉ ሲቀዛቀዝ ደግሞ ከሌላው የበለጠ ተስፉ የሚቆርጡና የሚያስቆርጡ፣ ይባስ ብሎም ለግል ጥቅማቸው የሚሯሯጡ ሆዳሞች ይሆናሉ የላል። በመሆኑም ድርጅቱን የሚቀላቀሉ ምሁራን አብዬቱን የመምራት ሀላፊነት ስለሚሸከሙ በመርፌ ቀዳዳ ማለፍ የሚችሉ ሆነው ከአጠቃላይ ተመልማዬች ከ2% መብለጥ እንደሌለባቸው ያብራራል።

የውስጠ ድርጅት ምልመላ መመሪያው ባለሀብቶችን በተመለከተ ምሁራን ላይ ከተቀመጠው መመዘኛ በከበደ ሁኔታ እንዲሰፍር ተደርጓል። በተቻለ መጠን ባለሀብቶች ድርጅቱን እንዳይቀላቀሉና ድጋፍ እንዳያደርጉ መከላከል ይኖርብናል ይላል። ኢህአድግ ከባለሀብቶች ራቅ በማለት ነጻነቱን ጠብቆ መኖር እንዳለበት በማስገንዘብ።

ከምርጫ 97 በኃላ በምሁራንና ባለሀብቶች ላይ የተቀመጠው ጥብቅ መመዘኛ ባልተጻፈ መልኩ የተቀየረ ቢሆንም የእነ ህላዌ ቡድን ይዞ የመጣው መደበኛ አሰራር ሆኖ እንዲፀድቅ በማሰብ ነበር። ቡድኑ አብዬታዊነትን ከቁልፍ መመዘኛ በማስናበት በፉንታው በህብረተሰቡ ዘንድ ታዋቂነት ያላቸውን ምሁራንና ባለሀብቶችን በእጩነት መመልመል ጊዜው የሚጠይቀው እንደሆነ አመላክተ።

ቡድኑ የምርጫ 97 ሽንፈትን ተከትሎ ባለአደራ አስተዳደሩ ስልጣኑን በተረከበ ወቅት ኢህአድግ በከተማዋ ላሰማራቸው ከ150 በላይ የሙሉ ጊዜ ምድብተኛ ካድሬዎች ደሞዝ የከፈሉትን ባለሀብቶች በምሳሌነት በማንሳት የድርጅቱ የጀርባ አጥንት እንደሆኑ አስታወሰ። በተለይም የሼህ መሀመድ አልአሙዲ ሸሪክ የሆኑት አቶ አብነት ገ/ መስቀል ለዞን ሶስት ኢህአድግ ጽ/ ቤት ግማሽ ሚሊዬን ብር በመስጠት ከ30 በላይ ለሚሆኑ ካድሬዎች ለአንድ አመት ያህል ወርሀዊ ደሞዛቸውን በመቻላቸው የድርጅቱ የቁርጥ ቀን ተደርገው መወሰድ እንዳለባቸው በምሳሌነት ተነስተዋል። አቶ አብነት ከዚህ በተጨማሪም ዞኑ በሸራተን አዲስ ባዘጋጀው ገቢ ማሰባሰቢያ ሙሉ ወጪውን በመሸፈን ከ200 ሺህ በላይ ኢህአድግን መታደጋቸው ተገለፀ።

" አብዬታዊነትን" አሰናብቶ በምትኩ ታዋቂነትን የተካው አዲሱ የምልመላ መስፈርት ኢህአድግን በቅርጽና አደረጃጀት ባይቀይረውም ይዘቱን ሙሉ በሙሉ በሚባል መልኩ ቀይሮታል። የቀድሞ ወታደር የከፍተኛ ማእረግ መኮንኖች፣ ለኢህአድግ ከፍተኛ ጥላቻ ያላቸው የእድር አመራሮች፣ የሀይማኖት መሪዎች ፓርቲውን ወክለው በየደረጃው በሚገኙ ምክር ቤቶች ውስጥ መሪ ተሳታፊ ሆነዋል። አንዳንዶቹ በከፍተኛ አመራርነት ሳይቀር ተሹመው እያገለገሉ ነው። ለአብነትም ያህል ቀድሞ በኢህአድግ ካድሬዎች በአክራሪነት ሲፈረጅ የነበረው የአዲሳባ እስልምና ምክር ቤት ፀሀፊ ሼህ ኤሊያስ ሰይድ የከተማው ምክትል አፈ ጉባኤ በመሆን ተሹሞ ነበር። ሼሁ የተመለመለበት ዋነኛ ምክንያት በወጣት ሙስሊሞች ዘንድ ተቀባይነት አለው ከሚል መነሻ ነበር። ከዛው ሳንወጣ የአፈ ጉባኤ ፅ/ ቤት ዋና ሀላፊ እንድትሆን በምክር ቤቱ የተሾመችው ወይዘሮ ነገደ ለማ የኢትዬጲያ ሰራተኛ ማህበር ኮሚሽን ከፍተኛ አመራር የነበረችና በቀይ ሽብር ዘመን ተባባሪ በመሆን የገዛ ወንድሞን በማስገደል የወቅቱ የደርግ " አብዬት ልጇን ትበላለች " መፈክር በተግባር ያረጋገጠች እንደሆነ ተጨባጭ መረጃ ቀርቦ ነበር። ይህ ሴትየዋ ፈፀመችው የተባለ ግፍ በአንድ የግል ፕሬስ ሙሉ ገጽ ሽፋን አግኝቶ ነበር። የግል ፕሬሱ የኢህአድግ ጠላት ስለሆነ ሆን ብሎ ሊከፋፍለን ነው በማለት ሳይጣራ እንዲቀር ተደረገ።

የኢህአድግ የይዘት ለውጥ በአዲሳባ ደረጃ ብቻ የተወሰነ አይደለም። በመላ ሀገሪቱ የድርጅቱ አፅም (Skeleton) ሳይለወጥ በየቀኑ እየመነመነ በሄደ አጥንቱ ላይ የሚለጠፍበት ስጋ ከሸክም በላይ ሆኗል። ይህንን ከአቅም በላይ የሆነ ስጋ የተሸከመ አጥንት በጋንግሪን እየተጠቃ መሄዱን ላስተዋለ ደግሞ ድርጅቱ እንደ ጉማ ሲጠቀለል በሀገሪቱ ሊከሰት የሚችለውን አደጋ ለመገመት ያስቸግራል።

"ባንክና ታንክ"

የ2000 የአዲሳባ ዳግም ምርጫ የመቶ ፐርሰንት የማሸነፍ ግብን ለማሳካት ከሂደቱ ይልቅ

ለውጤቱ ትኩረት በመስጠት መፈፀም ተጀመረ። የምረጡኝ ዘመቻውና ውድድሩ የሚዲያ ትኩረት ተነፈገው። በውስጣቸው ምንም አባላት የሌላቸው ብቻ ሳይሆኑ የአንድ ቤተሰብ ዘመዳሞች ተሰብስበው የፓለቲካ ፓርቲ መሰረቱ።

በአቶ አርከበ እቁባይ የጥፋት ዘመን የአዲሳባ አማካሪ ምክርቤት አመራር የነበረ መስፍን መንግስቱ የሚባል በአራዳ ክፍለ ከተማ የሚኖር ግለሰብ መላዉ ኢትዬጲያ ብሔራዊ ንቅናቄ (መኢብን) የሚባል የቤተሰብ ድርጅት አቋቋመ። በ12 ወረዳዎች ላይ እህቶቹን፣አማቾቹንና ሌሎች የስጋ ዘመዶቹን በእጩነት አቀረበ። ለአስራ ሁለት የፓርላማ መቀመጫ እየተወዳደሩ ያሉትን ቤተሰቦች ዝርዝር ምርጫ ቦርድ ላከልን። ስለ ግለሰቡ ማንነት የሚያሳይ መረጃ ከደህንነትና ካድሬዎቻችን አሰባሰብን።

እንደ ጭራሮ ደርቀው የቀሩት የአየለ ጫሚሶ ቅንጅትና የልደቱ ኤዴፓ ኢህአድግ ባዘጋጀላቸው እጩ ለውድድር ተዘጋጁ። ከምርጫው በፊትና በኃላ የልደቱ ፓርቲ በድርጅቱ የወደፊት አቅጣጫ ላይ ለመወሰን በሜክሲኮ መብራት ሀይል አዳራሽ የጠራውን ስብሰባ አጀንዳ የቀረጽነው ፣ተሰብሳቢዎችን ለይተን ያስገባነው እኛና ደህንነት በመቀናጀት ነበር። ልደቱ በጠራራ ፀሀይ በመብራት ሀይል አዳራሽ በዝግ የመራውን ስብሰባ እኛ ማታ ከቃለጉባኤ እናነባለን። ተጨማሪ መረጃ ካስፈለገን ተልእኮ ተሰጥቷቸው በስብሰባው ከተሳተፉት እንወስዳለን። ይህንን ተከትሎ ኢዴፓ ብዙም ሳይቆይ በፓርቲ ደረጃ እንደማይወዳደር ግን ደግሞ ግለሰቦች እንወዳደራለን የሚሉ ከሆነ መብታቸው እንደሆነ የሚያሳይ አስቂኝ መግለጫ አወጣ።

ከ" ባንክና ታንክ" የመቀስቀሻ ማእከላዊ መልእክት ጋር የቆረበው ህብረት እስከ መጨረሻው የምርጫ ቀናት እየተንገዳገደ ቆየ። በአስራአንደኛው ሰአት ከምርጫው ሂደት አቋርጦ እንደወጣ ይፋ መግለጫ አወጣ። በወቅቱ በከፍተኛ ጥቅም ላይ ውላ የነበረችው " ባንክና ታንክ" የፈጠራት አቶ በረከት " አደገኛ ቃላት ከመፈብረክ የማይቦዝነው የጠባቦች ንጉስ " ብሎ የሚጠራው ዶ/ ር መራራ ጉዲና ነበር። ዶክተሩ ተራ በተራ የፓርቲውን ካድሬዎች በዝህች ምትሀተኛ ቃል አደቁኖበታል። በተለይም መምህር ወንድሙ የሚባሉ የፓርላማ አባልና የህብረት ከፍተኛ አመራር በምርጫ ክርክር በቀረቡ ቁጥር አልፉና ኦሜጋቸው ባንክና ታንክ ሆኖ ነበር።

የአጋጣሚ ነገር ሆኖ እኔና የስራ ባልደረባዬ የነበረው ፀጋዬ ሀ/ ማርያም የአዲሳባ ኢህአድግን ወክለን፣ መምህር ወንድሙ ደግሞ ህብረትን ወክለው ለሶስት ያህል ጊዜያቶችና ቦታዎች (አፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን፣ባህል ማእከልና ማዘጋጃ ቤት) የምርጫ ክርክር አድርገን ነበር።

ታዲያ በማዘጋጃ ቤት በተካሄደው የመጨረሻ ክርክር ወቅት እኔና ፀጋዬ በመኢብኑ የቤተሰብ ፓርቲ ፕሬዝዳንት አቶ መስፍንና መምህር ወንድሙ ላይ ተንኮል አዝለን ወደ መድረክ ወጣን። የተከበሩ መምህር ወንድሙ ለመከራከሪያ ያዘጋጁት ሰነድ ቀድሞ የደረሰን በመሆኑ በጋራ ተመልክተነዋል። በእያንዳንዱ አንቀጽ ላይ ይቺ እንደ ጅብ ቆዳ ተጣብቃ የቀረችባቸው ቃል በመሸጋገሪያነት ተቀስራለች።

በክርክሩ የድልድል ሰአት የመጀመሪያ ዙር ቅድሚያውን ኢህአድግ እንዲወስድ ተስማማን። የሁሉም ፍላጐት ስለነበር በቀላሉ ተሰጠን። ፀጋዬ ንግግሩን ገና ሲጀምር በቀልደኛ አንደበቱ :

" *የተከበሩ የፓርላማ አባል መምህር ወንድሙ ባለፉት ሁለት ክርክሮች መምህርነታቸው አገርሽቶ ባንክና ታንክ 101(ባታ -101) እና ባታ -102 ኮርስ ሰጥተውን ነበር። ከሚገባው በላይ ገብቶናል። ኢህአድግ ለእሳቸውና ድርጅታቸው የኮፒ ራይት መብት ይገባቸዋል ብሎ ያምናል። ይህቺን ወደ ስልጣን የምታመጣ ምትሀተኛ ቃል ሌላው መጠቀም ከፈለገ ከኦርጅናል ባለቤቶቹ ፍቃድ መጠየቅ ይኖርበታል* " አለ።

የተከበሩ መምህር ወንድሙ የመናገር ተራቸው ደርሶ ገና "ባንክና ታንክ" የሚለውን ቃል ሳይጨርሱ በአዳራሹ የተሰበሰበው ህዝብ በሳቅና ሁካታ ግራ አጋባቸው። የሚናገሩት

ጠፍቶአቸው ሲንዘባዘቡ ዋሉ።

የሞኝ ለቅሶ እንዲሉ ከአምስት አመታት በኃላ በስደት ባለሁበት ሀገር በሚተላለፈው ኢሳት የሚባል ቴሌቭዥን ላይ በእንግድነት የቀረቡት የቀድሞው ህብረት የአሁኑ መድረክ ከፍተኛ አመራር የተከበሩ አቶ ገብሩ ገ/ ማርያም ሳይበረዝና ሳይደለዝ ሌጋሲውን በጠበቀ ሁኔታ " ባንክና ታንክ " ሲሉ ሰማሁ። በመጥፎ ትዝታ ባህር ተሻገርኩ።

እናንተዬ ! ለካስ ይሔ ሌጋሲን ሳይበረዝና ሳይቀነስ ማስቀጠል የሚለው አባባል በተቃዋሚዎቻችንም ዘንድ አለ !!

***

ወደ ማዘጋጃ ቤት ክርክር አንመለስ:

ከተከበሩ መምህር ወንድሙ ቀጥሎ እድሉን ያገኙት የመኢብኑ ፕሬዝዳንት አቶ መስፍን ነበሩ። የአቶ መስፍን መተዳደሪያ ስራ ድለላ የነበረ ሲሆን በ1995 በጊዜያዊነት በተቋቋመው የከተማው አስተዳደር አማካሪ ምክርቤት ውስጥ በመልካም አስተዳደር ቋሚ ኮሚቴ ውስጥ አገልግሏል። በሁለት ሳምንት አንድ ጊዜ በማዘጋጃ ቤት በመገኘት የሚያደርገው ስብሰባ ራሱን እንደ አስፈጻሚ እንዲቆጥር አድርጐታል። በተለይም በወቅቱ ከንቲባ የነበረውን አቶ አርከበ በማዳነቅና በማሞገስ የሚናገር ስለነበረ ሰፊ የሚዲያ ሽፋን አገኘ። ይሄ አጋጣሚ የቀድሞ ስራውን በመተው ወደ "ጉዳይ አስፈጻሚነት " አሸጋገረው። በአራዳ በሚኖርበት የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ውስጥ ጉዳይ መስፈፀሙን ቀጠለበት። አስገራሚ ማስታወቂያዎችን በየመሸታ ቤቱ መናገር ጀመረ። ከእነዚህ ውስጥ :

" ክቡር ከንቲባው ጋር ቀርቦ የሚፈፀም ጉዳይ አለዎት? እንግዲያውስ የአማካሪ ምክርቤት አመራሩን መስፍን መንግስቱን ቀርበው ያማክሩ !" የሚለው አንዱ ነበር። ግፍና መከራ ወገቡን ያጐበጠው ህዝብ ያገኛትን ቀዳዳ ሁሉ ለመጠቀም መኪተኑ አይቀርምና በርካታ ማመልከቻዎች ለአቶ መስፍን ደረሰው። በዛው ልጓክ ኪሱ መሙላት ጀመረ።

የግንቦት 97 ማእበል የአቶ አርከበን የነቀዘ ገዥ መደብ ጠራርጐ ከከተማዋ ሲያባርር የአቶ መስፍን ጥገኛ ጥቅም አብሮ ተቋረጠ። ወደ ሌሎች አማራጮች ተሸጋገረ። ባለአደራ አስተዳደሩ ውስጥ ለመግባት ያደረገው ጥረት ሳይሳካ ቀረ። ለገዥዎች ማደግደግና አጠገባቸው መንጐዳጐድ የሚያስገኘውን ጠቀሜታ በተግባር ያረጋገጠው የአራዳው ጨልሌ "መኢብን " የሚባል ፓርቲ መስርቻለሁ ብሎ ብቅ አለ። ለድህረ ምርጫ 97 ሁከትና ብጥብጥ ተጠያቂዎች አክራሪ ተቃዋሚዎች ናቸው የሚል መግለጫ በማውጣትና መኢብን የኢህአድግ ታማኝ ተቃዋሚ ሆኖ እንደሚቀጥል በኢቲቪ ቀርቦ መግለጫ ሰጠ።

አቶ መስፍን በማዘጋጃ ቤቱ ክርክር ሰአት ታማኝነቱን አረጋግጦ የዘንድሮ የአዲሳባ ምርጫ ብርቱ ፉክክር የሚደረገው በመኢብንና ኢህአድግ መካከል ብቻ እንደሚሆን፣ ሌሎቹ ተቃዋሚዎች ህዝቡ አንቅሮ እንደተፉቸውና እዚህ ለክርክር ከተቀመጡት ውጪ ሌላ አባል እንደሌላቸው በኩራት ተናገረ። አጠገቤ የተቀመጡት የቅንጅቱ አየለ ጫሚሶ የግንባራቸው ደም ስር ወጣ ገባ መስመር ሰራ። ከእሳቸው የተቀመጡበት ወንበር ገዝፎ ታየ።

ርግጥም አቶ መስፍን እውነቱን ነበር። የአቶ አየለ ቅንጅት በኢህአድግና ምርጫ ቦርድ አማካኝነት ከቀድሞ ቅንጅት የአልጋ ወራሽነት ያገኘው አቶ መለስ የቆረጧትን የሁለት ጣት አርማ ብቻ ነበር።

በሁለተኛው ዙር የክርክር ሰአት ኢህአድግን ወክዬ እንድናገር ለእኔ እድሉ ተሰጠኝ። ቀጣይ ትኩረት ያደረግነው አቶ መስፍንን በመሆኑ በ12 የተለያዩ ወረዳዎች መኢብን ያቀረባቸውን ሰዎች እስከ አያት አነበብኩ። መኢብን በለስ ቢቀናው የኢትዬጲያ ፓርላማ ደርዘን የሚሞሉ የአንድ ቤተሰብ አካላት በመያዝ ታሪክ ይሰራ እንደነበረ ተናገርኩኝ። ከአዳራሹ ጩኸት በላይ የአቶ አየለ እንባ ያዘለ ሳቅ ጆሮዬን ሰርስሮ ገባ። የአየለ ጫሚሶ አንጀት ቅቤ ሲጠጣ አየሁት።

አቶ መስፍን ያልጠበቀው ስለሆነ ተወራጨ። ተራው ሳይደርስና ሳይፈቀድለት :

" *ኢህአድግ የራሱን ጉድ በጉያው ሸሽጐ ስለሌላ ያወራል። አቶ መለስና ሚስታቸው*

የተቀመጡበት የፓርላማ ዙራን ክብደት ሁሉም የሸንጐ አባላት ተጨፍልቀው አይደርሰብትም " በማለት ጮኸ። በአንድ ግዜ ታማኝ ወዳልሆነ ተቃዋሚ ተሸጋገረ። የክርክሩን ማሳረጊያም የአቶ መለስና ሚስታቸው ዙራን ግዘፈት ሆነ።

ማምሻውን ኢቲቪ የተካሔደውን ክርክር ሰፊ የዜና ሽፋን ሰጠው። የአዲሳባ ፕሮግራም ደግሞ በልዩ ፕሮግራም እንደሚያቀርበው ገለፀ።

በንጋታው ጠዋት የሆነው ግን ሌላ ነበር። የከተማው ኢህአድግ ስራ አስፈፃሚ በረከት ቢሮ አስቸኳይ ስብሰባ ተጠራን። እኔና ፀጋዬ ክርክሩን ወዳልሆነ አቅጣጫ መምራታችንን ተነገረን። የመኢብኑ አቶ መስፍን ኢህአድግ ቢሮ መጥቶ ቅሬታ ማቅረቡ ተነገረን። የድርጅት ጉዳዮን ለሚመራው ካሚል ደውሎ የመደራደሪያ ሀሀሳብ እንዳቀረበ ሰማን። ይህም ኢህአድግ ከዚህ ቀደም ለአቶ በድሩ አደም እንደሚያደርገው አንድ ወንበር ከለቀቀለት 11 ቤተሰቦቹን ከእጩነት እንደሚሰርዝ የሚገልፅ ነበር።

በረከት በተቃራኒው ድርጅቱ አዲስ አቅጣጫ ማስቀመጡን ነገረን። አዲሱ ስትራቴጂ በምርጫው ውጤት ላይ ለውጥ የማያመጡ ፓርቲዎች በውድድሩ እንዲሳተፉ ማበረታታት እንደሆነ ተገለፀልን። ይህም በአንድ በኩል በምርጫ ቦርድ በኩል የሚመደበውና ለፓርቲዎች የሚከፋፈለው ገንዘብ በእጩ ብዛት እንዲሆን፣ ኢህአድግ ድርሻውን ውድድር ለሚገቡ ፓርቲዎች እንደሚያከፋፍል ነገረን። በመንግስት የተያዙት የሚዲያ ውጤቶች ለተቃዋሚዎች ሰፊ ሽፋን እንዲሰጡ አቅጣጫ መቀመጡን አስረዳን።

የዚህ ሁሉ ምክንያቱ ኢህአድግ ብቻውን ሮጦ አሸናፊ ሆነ ከሚለው ወቀሳ ለመዳን መሆኑን ማብራሪያ ሰጠ። ውሳኔውን ተከትሎ በሀገር ደረጃ ለአካባቢና ማሞያ ምርጫ ከሰላሳ ፓርቲዎች በላይ ተመዝግበዋል የሚለው መልእክት የምርጫውን አብዝሀነት ማሳያና በኢትዬጲያ መድብለ ፓርቲ ስርአት የማይቀለበስበት ደረጃ መድረሱን ማሳየት የቀጣይ ቀናት ቁልፍ ስራችን ሆኖ ተቀመጠ።

ኢቲቪም በመስተዳድሩ ፕሮግራም አቀርበዋለው ያለውን የፓርቲዎች ክርክር ሰርዞ ለመወዳደር የተመዘገቡ ፓርቲ አመራሮችን በተናጠል በመጋበዝ የመድብለ ፓርቲ ስርአቱ ይበልጥ እየተጠናከረ መሄዱን አበሰረ። እኛም ጓዛችንን ጠቅልለን መድብለ ፓርቲን ማሰስ ጀመርን... ላም ባልዋለበት!!

***

ጉዞ ወደ መድብለ ፓርቲ ቅስቀሳ!

በየጊዜው የሚጻፉ የኢህአድግ ሰነዶችን በዝርዝር ለመመልከት እድል ያገኘ ሰው ፓርቲው በተደጋጋሚ የመርህና አቋም ለውጦችን እያደረገ መሄዱን ለመረዳት ጊዜ አይወስድበትም። ርግጥ አንድ ተቋም ወይም ድርጅት የውስጡን፣ አገር አቀፍና የአለም ሁኔታን በማጥናትና ከተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር በማጣጣም እየተገላበጠና ልብሱን እየቀየረ ቢሄድ የሚያስከፋ አይደለም። እንደውም ህይወት ካለው ድርጅት የሚጠበቅ እርምጃ ነው። ከዚህ አንጻር ኢህአድግን የተለየ የሚያደርጉት ባህሪያት አሉት:

በመጀመሪያ ደረጃ ልብሱን የሚቀይሩት በጣት የሚቆጠሩ ካድሬዎች ናቸው። ሌላው ከፍተኛ ካድሬ በዲሞክራሲያዊ ማእከላዊ መርህ በመጠርነፍ ቃር ቃር እያለውም ቢሆን ይቀበላል። አብዛኛው የድርጅት አባል ደግሞ አልባሳቱ መቀየራቸውን እንኳን ስለማያውቁ በተምታታ አዙሪት ውስጥ ይዳክራሉ። በተለይም ከትጥቅ ትግሉ ጀምሮ ታጋይ የነበሩ ካድሬዎች የአይዲኦሎጂ ለውጦች በይፋ ስለማይነገራቸው ትላንትና ይዘውት ከነበረ አስተሳሰብ ጋር ተቸንክረው ይቀራሉ።

በሁለተኛ ደረጃ ኢህአድግ የተለየ የሚያደርገው ተቀባይነት ያላቸውን ነገሮች በመተው

የራስን ፍቺ መስጠት ነው። በአለም አቀፍ ደረጃ ስምምነት የተደረሰባቸው ትርጉሞችን ወደ ጐን ትቶ የራስ ትርጉም መስጠት ይታያል። ከዚህ አንጻር ፓርቲው " መድብለ ፓርቲ " በተመለከተ በየጊዜው የሚሰጠውን ትርጉም ማየት በቂ ይሆናል።

ኢህአድግ ከ1993 አ•ም• እና ከዛ በፊት ባወጣቸው የውስጠ ድርጅት ሰነዶ0ች ላይ የመድብለ ፓርቲ ስርአት ግንባታን አምኖ የተቀበለው ሳይሆን አሁን አለም የምትገኝበት ነባራዊ ሁኔታ አስገድዶት እንደሆነ ይገልጻል። ተቃዋሚዎች በዲሞክራሲ ስርአት ግንባታ ምንም አይነት አስተዋጽኦ የሌላቸውና በተቃራኒው አሉታዊ ተጽእኖ በማሳደር የአብዬታዊ ዲሞክራሲን የአስተሳሰብ ልእልና (Hagimony) እንዳይሰፍን የሚያደርጉ በማለት ይፈርጃቸዋል። በመሆኑም በዲሞክራሲያዊ መሳሪያዎች (Democratic Instruments) በመጠቀም ማዳከም አብዬቱ እደርስበታለሁ የሚለውን የመጨረሻ ግብ ያለአንዳች እንቅፋት እንዲመታ ያደርገዋል ይላል።

በተቃራኒው በረከት ጽፎ ባስነበበን የሁለት ምርጫዎች ወግ መጽሀፍ ላይ "የሚያዝያ ሰልፎች " በሚለው ርእስ ስር ከላይ የተቀመጠውን ሀቅ በመገልበጥ:

" ... ኢህአድግ ከሀያ አመታት በፊት የመድብለ ፓርቲ ስርአት ግንባታን የመረጠበት ምክንያት ዲሞክራሲያዊ ምርጫ የህዝብ መብት ከመሆኑ መሰረታዊ ጉዳይ የተነሳ ብቻ አልነበረም። የተቃዋሚ በተለይም ሀገ መንግስቱን ተቀብሎ በፓሊሲ ልዩነት ዙሪያ ተወዳድሮ ለመመረጥ የሚሻ ጠንካራ ታማኝ ተቃዋሚ መኖር ለዲሞክራሲ ስርአት ጤንነት የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ ስላለው ጭምር ነበር።" ይላል።

እነ በረከት በኢትዬጲያ የመድብለ ፓርቲ ስርአት (Multi-party system) አለ ብለው እየተከራከሩ ነው። የአለም ህዝብ ተቀብሎ እያደረበት ያለው የብዙሀን ፓርቲ ስርአት ደግሞ የራሱ የሆነ ቅድመ ሁኔታዎችና መመዘኛዎች አሉት።

የመድብለ ፓርቲ ስርአት የተለያዩ ፓርቲዎች በተናጠልና በጋራ መንግስታዊ ስልጣን ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ በምርጫ ውጤታቸው መሰረት የሚይዙበት ስርአት ነው። በዚህ ስርአት ውስጥ የሚኖሩ የፓለቲካ ፓርቲዎች ብዛት (effective number of parties) ከሁለት ያላነሱና ከአስር ያልበለጡ መሆን እንደሚገባቸው በዚህ ሙያ ላይ ያሉ ምሁራን ያስገነዝባሉ።

በአብዛኛው የመድብለ ፓርቲ ስርአት በገነቡ ሀገሮች ያለው የምርጫ ስርአት ከአብላጫ ድምጽ ይልቅ የተመጣጣኝ ውክልና አሰራር ማእከል ያደረጋል። የተመጣጣኝ ውክልና አሰራር በምርጫው የተወዳደሩ ፓርቲዎች ያገኙት ድምጽ ተቆጥሮ ባገኙት ፐርሰንቴጅ ልክ የምክር ቤት መቀመጫዎችን የሚከፋፈሉበት ስርአት ነው። ለአብነት ያህል አንድ ፓርቲ ከአጠቃላይ መራጩ 30% ድምጽ ቢያገኝ ከምክር ቤቱ መቀመጫዎች 30% ይወስዳል። ይህ የምርጫ ስርአት ብራዚልን ጨምሮ ከ80% በላይ የደቡብ አሜሪካ ሀገራት፣ ከአውሮፓ ደግሞ ጀርመን ፣ኔዘርላንድ፣ኖርዌይ፣ራሺያ፣ስፔንና ሌሎች በርካታ ሀገሮች፣ እንዲሁም እስራኤልና ደቡብ አፍሪካን የመሳሰሉ ሀገራት የሚሰራበት ነው።

በሌላ በኩል የአብላጫ ድምጽ ስርአት (first past the post) በሚከተሉ ሀገሮች ከተወዳዳሪ እጩዎች መካከል የመራጩን ህዝብ አብላጫ ድምጽ ያገኘ ህዝቡንና ፓርቲውን ወክሎ የምክር ቤቱን መቀመጫ ይወስዳል። ይህ የምርጫ ስርአት እንደ ተመጣጣኝ ውክልና ሁሉ ዲሞክራሲያዊ ቢሆንም የተለመደው ሁለትና ሶስት ፓርቲ ስርአት ባለባቸው እንደ አሜሪካና እንግሊዝ የመሳሰሉ ሀገሮች ላይ ይሆናል። በአሜሪካን ሀገር ያሉት ሁለት ግዙፍ ፓርቲዎች በመሆናቸው የምርጫ ፉክክሩ በእነሱ መካከል ይሆናል። በዲሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥ የኖረው የአሜሪካን ህዝብም በፓርቲዎቹ መካከል የእርስ በራስ ቁጥጥር ለማምጣት ህግ አውጭውን ለአንዱ፣ አስፈጻሚውን ለሌላ፣ አለያም በተቀራራቢ ቁጥር እንዲወከሉ በማድረግ የዳበረውን የዲሞክራሲያዊ ስርአት ያስጠብቃል።

የፓርላሜንት ስርአት የምትከተለው እንግሊዝ ሶስት ታላላቅ ፓርቲዎች የሆኑት ኮንሰርቫቲቭ፣ ሌበርና ሊብራል ዲሞክራቶች የሚፎካከሩባት ሀገር ናት። የቅርብ ጊዜውን

እንኳን ብንወስድ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ2010 የተካሄደው ሀገር አቀፍ ምርጫ እነዚህ ሶስት ፓርቲዎች ከአጠቃላይ 650 ወንበር ውስጥ 622 ያህሉን አሸንፈዋል። በዚህ ምርጫ አብላጫውን (23%) ያገኙት ሊብራል ዲሞክራቶች ቢሆኑም መንግስት ለመመስረት የሚያስችል ተጨማሪ 10% ስለሚያስፈልጋቸው ከኮንሰርቫቲቭ ጋር ጥምረት በመፍጠር መንግስት መስርተዋል።

ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው በኢትዬጲያ የመድብለ ፓርቲ ስርአት አለ ለማለት ከላይ የተቀመጡት መስፈርቶች መሞላት ይኖርባቸዋል። በመጀመሪያ ደረጃ በሀገራችን የፓለቲካ ፓርቲ መመስረት የመንደር ሱቅ ከመክፈት በላይ ቀላል ሆኗል። ጠቅላይ ሚኒስትር ሀይለማርያም እንደገለፀው በአሁን ሰአት ከዘጠና ዘጠኝ በላይ የፓለቲካ ፓርቲዎች ይገኛሉ። ይህም ሆኖ ከገዢው ፓርቲ ኢህአድግ በስተቀር ጮልቶ የወጣ ይህ የሚባል የፓለቲካ ፓርቲ የለም። ለሀይል ሚዛን ተስፉ ተጥሎባቸው የነበሩትም በራሳቸውና በኢህአድግ የዜሮ ድምር ጨዋታ ምክንያት በተወለዱ ማግስት ሰላሳ ቦታ ተሰነጣጥቀዋል። በመሆኑም መድብለ ፓርቲ ስርአት ለመመስረት ከሁለት እስከ አስር የፓለቲካ ፓርቲዎች መገኘትን እንደ መሰረታዊ ነገር የተቀመጠው በኢትዬጲያ የሚሰራ አይደለም።

ከሁሉም በላይ ኢህአድግ የሚመራበት አብዬታዊ ዲሞክራሲ ርእዬተ አለም የተፈጥሮ ባህሪው መድብለ ፓርቲን የሚያበረታታና የሚፈጥር አይደለም። ዜጐች ሲነሱና ሲቀመጡ ፣ሲበሉና ሲተኙ በህልማቸው ሳይቀር ስለአንድ ነገር ብቻ እንዲያስቡ ማድረግን እንደ ግብ የሚወስድ ፍልስፍና የተለየ አማራጭን ሊቀበል የሚችል ተክለ ሰውነት ሊኖረው አይችልም... ይህ አስተሳሰብ ገኖር ሆኖ የበላይነት ካላረጋገጠ በስተቀር ሀገሪቷ የመበታተን አደጋ ሊያጋጥማት ይችላል ፣ ከዚህ በፊትም ኢትዬጲያ አጋጥሞት የነበረውን መስቀለኛ መንገድ በድል የተሸጋገረችው በአብዬታዊ ዲሞክራሲ ነው ብሎ የሚያምን ድርጅት አብዛህነትን ሊከተል የሚችል መተክል የለውም።

***

ኢህአድግ እንደ መድብለ ፓርቲ ሁሉ አብዬታዊ ዲሞክራሲን አስመልክቶ የሚሰጠው ትርጉምና መፃኢ እድል ከሁኔታዎች ጋር የሚለዋወጥና ከዘመን ዘመን የሚለያይ ነው። ኢህአድግ ባጋጠመው የውስጠ ድርጅት ቀውስና የአለም አቀፍ ሁኔታ መቀያየር ምክንያት አብዬታዊ ዲሞክራሲ ለሶስት ያህል ጊዜያት ሙሉ ልብሱን ቀይሯል። በዚህም ምክንያት የኢህአድግ ትርጉም፣ መርሆዎች፣የጉዞ አቅጣጫና ቀጣይ እጣ ፋንታ በተመሳሳይ መልኩ ግልብጥብጡ ወጥቷል። ከ1993 አ•ም• በፊት፣ ከ1993 -1998 እና ከ1998 አ•ም• በኃላ ያለው ኢህአድግና አብዬታዊ ዲሞክራሲ አንድ አይነት አይደሉም።

ከ1993 አ• ም• በፊት የነበረው አብዬታዊ ዲሞክራሲ በአብዬታዊ ምሁራን የሚመራ ሆኖ ለመላው አርሶ አደር፣ለላብአደርና ለከተማው ጭቁን ህዝብ ቆሚያለሁ የሚል ነበር። የዚህ ስርአት የመጨረሻ መዳረሻው ዲሞክራቲክ ሶሻሊዝምን መገንባት ይሆናል። ዲሞክራቲክ ሶሻሊዝም በህብረተሰቡ ውስጥ በሚካሄድ ንቅናቄ የሚመጣን መዋቅራዊ ለውጥ እንደ መሰረት በመውሰድ ያልተማከለ ፓለቲካል ኢኮኖሚ መፍጠርን የመጨረሻ ግቡ ያደርጋል።

ከ93 በፊት የነበረው ኢህአድግና አብዬታዊ ዲሞክራሲ የመጨረሻ ግቡ ዲሞክራቲክ ሶሻሊዝም ተብሎ ቢጠቀስም በየትኛው አቅጣጫ? ለምን ያህል ጊዜ ተጉዞ መዳረሻው ላይ ይደርሳል የሚለው በዝርዝር አልተቀመጠም።

ከፓርቲ አመራር አንጻር ከ93 በፊት የነበረው አብዬታዊ ዲሞክራሲ በድርጅቱ ቁንጮ ላይ የተቀመጡትን ካድሬዎች አምባገነን እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። የሁሉ ነገር አድራጊና ፈጣሪ ቁንጮዎቹ ነበሩ። የተቀረው አባል እነሱ የሚወስኑትን ውሳኔ በዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት መርህ የመቀበል ግዴታ አለበት። የጐረበጠውና ለመቀበል ህሊናው ያልፈቀደለት ያለው ብቸኛ አማራጭ ድርጅቱን ለቆ መውጣት ይሆናል። በመሆኑም በዚህ ወቅት የነበረው ስርአት አይደለም ከውጭ በፓርቲው ውስጥ እንኳን ልዩነትን የሚያስተናግድ ባህሪ አልነበረውም።

በተግባርም እንደታየው እነዚህ ካድሬዎች በሂደት ራሳቸውን ወደ ገዥ መደብነት በመቀየር ዋነኛ የስልጣን ምንጭ ሆነው ነበር። ርግጥ በእነዚህ ገዥ መደቦች መካከል የጥቅም ግጭት መነሳቱና የስልጣን ሽኩቻ መካሄዱ ነባራዊ ሀቅ በመሆኑ ጊዜውን ተጠብቆ ተከስቷል። በወቅቱ የተፈጠረው የእርስ በራስ መጠላለፍና መጠፋፋት ከድርጅቱ አልፎ ጦሱ ለሀገሪቱ ተርፎ ነበር። በተለይ በኢትዬ ኤርትራ ጦርነት ወቅት ልዩነቱ ይፋ የሆነበት ነበር።

ከ1993-1998 አ• ም• የነበረው አብዬታዊ ዲሞክራሲ ከበፊቱ በተለየ መንገድ ዘርዘር ባለ ሁኔታ የተብራራ ነበር። ስለ አብዬታዊ ዲሞክራሲ በውስጠ ድርጅት ሰነዶች የተገለፀውና ወደ መንግስት ስትራቴጂዎች የተተረጐመው ለየቅል ቢሆንም ፓርቲውን ለመገንዘብ የተሻለ እድል ሰጥቷል። ስርአቱ እንደ ከዚህ ቀደሙ የሚመራው በአብዬታዊ ምሁራን (ንኡስ ከበርቴዎች) ሆኖ ወገንተኝነቱ ለሀብታም አርሶአደሮችና ጥገኛ ያልሆኑ የሚል ቅፅል ለተጨመረላቸው ባለሀብቶች እንደሆነ ተገለፀ።

ይሄኛው አብዬታዊ ዲሞክራሲ የሚገነባው የካፒታሊዝም ስርአት ሲሆን የመጨረሻ እጣ ፋንታው ሊብራል ዲሞክራሲ ሊደርስበት የሚችለው ጫፍ ማድረስ ይሆናል። በመጨረሻው ሰአት አብዬታዊ ዲሞክራሲ ራሱን በራሱ በመብላት የሚከስም ሲሆን በኢህአድግ ውስጥ ያሉ አባላቶች ለሁለት እንደሚከፈሉ ያስረዳል። የመጀመሪያዎቹ ሀብት የማካበት እድል ያጋጠማቸው ሲሆኑ እነዚህ ሀይሎች ሁሉንም ነገር ለገበያ ለሚሰጠው ነጭ ካፒታሊዝም መመስረት ይተጋሉ። የተቀሩት በተለይም ተራማጅ አስተሳሰብ ያላቸው ለዝቅተኛው ማህበረሰብ ማህበራዊ ዋስትና መረጋገጥ የሚታገሉ ሶሻል ዲሞክራቶች እንደሚሆኑ ያስረዳል። ይህም የኢህአድግና የአብዬታዊ ዲሞክራሲ ግብአተ መሬት የሚፈፀምበት ይሆናል።

ከፓለቲካል ኢኮኖሚም አንጻር ይሄኛው ኢህአድግ የመንግስትና የግሉን ክፍል ለይቶ የስራ ድርሻ የሚሰጥ ነበር። የመንግስት ጣልቃ ገብነት በተለይም በተመረጡ ፣ ትስስር በሚፈጥሩና ፍትሀዊነትን ለማረጋገጥ በሚያስችሉ ቦታዎች ላይ መኖር እንደሚገባው ያስገነዝባል። የኢኮኖሚ ልማቱ አንቀሳቃሽ መንግስት ቢሆንም ሞተሩ የግል ባለሀብቱ በመሆኑ ባለሀብቱን መደገፍ ዋነኛ የኢኮኖሚው አቅጣጫ እንደሚሆን ያስገነዝባል። ፍትሀዊ ስርጭትን ለማረጋገጥ እንደ ቴሌና መብራት የመሳሰሉ ተቋማት በመንግስት እጅ መሆን እንደሚገባቸው በግልፅ ተቀምጧል።

***

ከ1998 አ• ም• በኃላ ያለው አብዬታዊ ዲሞክራሲ የመለወጡ መሰረታዊ ምክንያት የውስጠ ድርጅት ሽኩቻ ሳይሆን የአለም አቀፍ የፓለቲካል ኢኮኖሚው በመቀየሩ ምክንያት የመጣ ነው። ከአለም አቀፍ የኢኮኖሚ ቀውሱ ጋር ተያይዞ በተለይም በሀገረ አሜሪካ የኒዬ ሊብራል ጐራው ክፉኛ መመታት ለአቶ መለስ ከፍተኛ ደስታ የፈጠረና ወደ አዲስ የፍልስፍና መስመር የወሰደው ነበር። ይህም ኢህአድግና አብዬታዊ ዲሞክራሲ ለሶስተኛ ጊዜ ለመገላበጥ መልካም አጋጣሚ የፈጠረ ነበር። በመሆኑም ፓርቲውና አብዬታዊ ዲሞክራሲ በ50 አመታት ውስጥ እድገታቸውን ጨርሰው የማይቀርላቸውን ግብአተ መሬት ይፈጽማሉ ተብሎ የተገለፀው ተገለበጠ። በምትኩ ኢህአድግ የአስተሳሰብ እድገት አምጥቷል በማለት አብዬታዊ ዲሞክራሲ እንደ አንድ የዲሞክራሲ አማራጭ ለዘላለም ይኖራል ተባለ። አዲሱ አስተሳሰብ በኢህአድግ የንድፈ ሀሳብ መጽሔት በሆነችው " አዲስ ራእይ" ላይ እንዲወጣና በበላይ ካድሬ ደረጃ ስልጠና ተሰጠበት። ቀጥሎም ፓርቲው ለዘላለም የሚኖርባቸው ስትራቴጂዎች ተቀርፀው መተግበር ተጀመሩ። ከእነዚህ ውስጥ ዋነኛው አቶ መለስ የጻፈው " የልማታዊ መንግስት " ፍልስፍና ዋነኛው ነበር።

ልማታዊ መንግስት የኒዬሊብራል ጊዜያዊ ውድቀቶችን በሰፊው በማጉላት ከሱ በተቃራኒ የሆነውን የመንግስት ሁሉንም የልማት ዘርፎች የመቆጣጠር አላማ ገቢራዊ የተደረገበት ነበር። ይህ አይዲኦሎጂ የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ ከጫወታ ውጪ በማድረግ መንግስት የሁሉም ነገሮች አድራጊና ፈጣሪ እንዲሆን ያደርጋል። ይህ አስገዳጅ በሆነ መልኩ

ልማት ማምጣትን በመገፋፋት የሚፈፀም ስትራቴጂ የግለሰቦችን ነጻነትና ዲሞክራሲያዊ መብቶች በመደፍጠጥ የሚተገበር ነው።

የልማታዊ መንግስት ፍልስፍና ከዲሞክራሲ ይልቅ ልማትን በማስቀደም የተቃኘ በመሆኑ ዜጐችን እንደ አንድ የልማት መሳሪያ ብቻ ይመለከታል። ዜጐች በመንግስት ጫማ ስር እንዲወድቁ፣የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ከጨዋታ ውጭ እንዲወጣ፣ የመንግስት ኢንቨስትመንት የትየለሌ እንዲሆን ያደርጋል። በተግባርም የሆነው ይህ ነው።

በ2005 አ• ም• የአለም ባንክ አጥንቶ ይፉ ባደረገው ሪፓርት ኢትዬጲያ ከአለማችን ሀገሮች የመንግስት ኢንቨስትመንት ከሚካሄድባቸው ሀገሮች በሶስተኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች። ሁኔታው በዚህ ከቀጠለ የግል ባለሀብቱ እየከሰመ መንግስት የሁሉም ነገሮች አድራጊ እንደሚሆን አለም ባንክ አስጠንቅቋል።

***

ኢህአድግና አብዬታዊ ዲሞክራሲ ለሶስት ያህል ጊዜያት ሲገላበጡና የአስተሳሰብ እድገት ሲያሳዩ በሁለት ነገር ላይ ግን ተመሳሳይ አቋም ነበራቸው። በመድብለ ፓርቲ ስርአት ግንባታና ተቃዋሚ ድርጅቶች ላይ። በሁሉም ወቅቶች የወጡት የድርጅቱ ሰነዶች ተቃዋሚ ድርጅቶችን በተፎካካሪ ሳይሆን በጠላትነት የሚፈርጁ ናቸው። ከዛም አልፎ ፀረ - ሰላምና የጥፋት ሀይሎች በሚሉ ቃላት በመግለጽ ኢህአድግ ለፓርቲዎቹ ያለውን ጥላቻ የሚሳይበት ሁኔታ እንመለከታለን።

ከ1993 አ•ም• በፊት ኢህአድግ ይመራ የነበረው ከጫካ ይዞት በመጣው ህግና አመለካከት በመሆኑ ፓርቲዎቹን ፀረ ዲሞክራሲያዊና አስተዳደራዊ በሆነ መንገድ ለማክሰም ተንቀሳቅሷል። በተለይም የመድብለ ፓርቲ ስርአት መስፈን እውን ለማድረግ ተቃርቦ የነበረው የኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ) ከመድረኩ ተገዶ መውጣቱ ለዚህ ጥሩ ማሳያ ይሆናል። ርግጥ የአብዛኛው ኦሮሞ ህዝብ ፍላጐት ኦነግ ከሚያራምደው አቋም የተለየ ቢሆንም ቁጥሩ ቀላል በማይባሉ የኦሮሚያ ዞኖች ፓርቲው ሰፊ ተቀባይነት ነበረው። ግንባሩ ይህንን ድጋፍ ተጠቅሞ የአቋም ለውጥ ሳያደርግ ቢንቀሳቀስ ኖሮ በፌደራል ፓርላማ ከፍተኛ ቁጥር በመያዝ በህግ አውጭነት የሚሳተፍበት በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ደግሞ የጥምር መንግስት አካል የሚሆንበት እድል ይፈጠር ነበር። የኦሮሞ ህዝብን የኢትዬጲያዊነት ግንድ መሆንን ዛሬ ተገንዝቦ የአቋም ለውጥ ባደረገበት ሁኔታ የኢትዬጲያ ፓለቲካ መድረክ ላይ ተገኝቶ ቢሆን ኖሮ በእነ እንግሊዝ ያየነው ጥምር መንግስት በሀገራችን እውን ይሆን ነበር። የኦሮሞ ወጣቶች ስደትና የእስር ቤት መታጐር ይቀንስ ነበር።

ከ1993 አ•ም• በኃላ በኢህአድግ ከፍተኛ ካድሬዎች ተነስቶ አከራካሪ የነበረው " ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለዲሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ አስተዋጽኦ አላቸው / የላቸውም?" የሚለው ነበር። ይህ ክርክር የመጨረሻውን ድምዳሜ ባይለውጠውም ኢህአድግ የስልት ለውጥ ያደረገበት ነበር። ይህም ተቃዋሚዎች በተዘዋዋሪ መንገድ ለዲሞክራሲ ግንባታ አስተዋጽኦ አላቸው የሚለው ነበር። በተዘዋዋሪ መንገድ ማለት ሀሳባቸውን በመግለፃቸው ምክንያት ፀረ - ህዝብና የጥፋት ሀይሎች መሆናቸው ይጋለጣል የሚል ነበር። በዚህ ምክንያት የአብዬታዊ ዲሞክራሲ ትክክለኛነት ይረጋገጣል የሚል ነበር። ከዚህ በተቃራኒው የመታፈን እድል ካጋጠማቸው ግን የአብዬታዊ ዲሞክራሲ የተሻለ አማራጭነት አብሮ ይታፈናል፣ ተቃዋሚዎችንም እርቃናቸውን ማስቀረት አይቻልም የሚል ነበር። በምርጫ 97 ኢህአድግ በሩን በልበ ሙሉነት ገርበብ አድርጐ የከፈተበት ዋነኛ ምክንያት ምንጩ ይሄ ነበር። ተቃዋሚዎችን ህዝቡ አይቀጡ ቅጣት በመቅጣት የአብዬታዊ ዲሞክራሲን ትክክለኛነት ያፀናል በሚል... ውጤቱ በተቃራኒው ቢሆንም።

ነጫጮቹ ዝሆኖች

ከምርጫ 97 በኃላ የኢህአድግ የፕሮፓጋንዳና ፓለቲካ ስራ በአቶ መለስና (ድርጅቱ) እና በረከት (ስትራቴጂስቱ) መካከል መግባባት ያልተደረሰበትና በጭቅጭቅ የተሞላ ነበር። አልፎ ተርፎም እስከ መዘላለፍና እጅ እሰከ መቀሳሰር የተደረሰበት ነበር። በኢህአድግ ካድሬነት ዘመኔ በሁለቱ ሰዎች መካከል ለወራት የዘለቀ አለመግባባት ያየሁት ለሁለት ያህል ጊዜያቶች ሲሆን ይህ የመጀመሪያው ነበር። አቶ መለስ ንዴቱን መቆጣጠር አቅቶት:

" በረከት! ከዳንኪራና አሼሼ ገዳሜ የምትወጣው መቼ ነው? " ብሎ ሲጠይቀው ፣ በረከት በበኩሉ " ድርጅቱ የExistance ጥያቄ እንዳጋጠመው ለማወቅ ወረድ ብሎ ማየት ይጠይቃል " ብሎታል። የሚገርመው ነገር በሁለቱም የጭቅጭቅ ወቅቶች አሸናፊ ሆኖ የወጣው በረከት ስምኦን ነበር። በመሀል ቤት ሳንዱች የሆነው እኛ ብንሆንም።

እስቲ ይህ አባባል የተገለፀበትን ሁኔታ አስቀድመን እናውጋ።ሌላኛው ለሌላ ጊዜ " ትዝታ -ዘመለስ " በሚል ርእስ ለተጻፈው ማስታወሻ ይቆየን።

ነገሩ እንዲህ ነው:

ምርጫ 97 ከተጠናቀቀ በኃላ በአዲሳባ የአባላት ምልመላ እንዴት ይፈፀም የሚል ጥያቄ ይነሳል። አቶ መለስ በከተማይቱ ኢህአድግ የሚባል ፍጡር ስለሌለ ዋነኛ አቅጣጫ ጥራት ያለው ድርጅት መፍጠር ይሆናል የሚል አቀረበ። ድርጅት ለመፍጠር ደግሞ መጀመሪያ አጥንት (Skeleton) የማቆም ስራ ቅድሚያ እንዲሰጠው አሳሰበን። የከተማው አጥንቶች የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው ወጣቶች በመሆናቸው እነሱን አድኖ በቀበሌ እስከ 25 አባል የማድረግ ስራ ቁልፍ ተግባራችን መሆን እንዳለበት ያስገነዝባል። በሂደት ስጋው እየመጣ እንደሚለጠፍባቸውና አጥንቶቹ ይህንን ለመሸከም የሚያስችል ቁመና እንዲኖረው ማድረግ እንደሚያስፈልግ ገለፀ። ስጋ የተባሉት ከወጣቶች ውጭ ያሉ የከተማው ነዋሪዎች ናቸው።

ከአቶ መለስ ባስቀመጠው አቅጣጫ ተስማምተን ለመተግበር የሚያስችል ማስፈፀሚያ ሰነድ አዘጋጀን። የዞንና ቀበሌ ካድሬዎቻችንን ጠርተን አጥንት እንዲፈልጉ ኦረንቴሽን ሰጠን። ለመፈፀም አስቸጋሪ መሆኑን ቢገልጹም ዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት ነውና ጭንቅላታቸውን እየፈተጉ ተቀብለው ሄዱ።

ካድሬዎቻችንን ባሰማራን በሰልስቱ በረከት ቢሮ ለአስቸኳይ ስብሰባ ተጠራን። እቅዳችንን እንድንቀይርና ከጥራት ይልቅ ብዛት ላይ እንድናተኩር አሳሰበን። ከብዛት ውስጥ ጥራትን ማግኘት እንደሚቻልና ድርጅቱ የቀድሞውን አቅጣጫ ሲያስቀምጥ በምድር ላይ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ እንዳላገናዘበ አስረዳን።እናም በአንድ ወር ውስጥ በእያንዳንዱ ቀበሌ 1,000 (በከተማ መቶ ሺህ) አዳዲስ አባላትን እንድንመለምል ትእዛዝ ሰጠን።

በድጋሚ የተገላበጠ እቅድ አውጥተን የበታች ካድሬዎችን አወያየን። ካድሬዎቻችን ስለ ጤንነታችን ጥርጣሬ ገባቸው። የነዋሪው አይን እየገረፈንና ተሸሽገን ባለበት ሁኔታ ለመጥራት የሚያስቸግር ቁጥር መልምሉ የምትሉን ምን ነክቷችሁ ነው በማለት ሞገቱን። አንድ ተስፉ የቆረጠ የቀበሌ ካድሬ " እናንተ ምን ታደርጉ በመኪና ወጥታችሁ በመኪና ትገባላችሁ!" አለን። ስለተቀጣጠለችው የከሰል ፍም አጫወተን። " አናንተ ከሰሉን አቀጣጥላችሁ ፍም ሲሆን ለዞን ትወረውራላችሁ። ዞኖች ሁለት ሶስቴ ከአንደኛው እጃቸው ወደ ሌላኛው ካመላለሱ በኃላ ለእኛ ይወርውራሉ። እኛ ቀበሌዎች ከአንደኛው እጃችን ወደ ሌላኛው እያንቀረቀብን እንኖራለን" አለ።

አንቴና የሌለው ህላዌ ተናደደ። ፍሬህይወት አያሌው ፈገግ አለች። ስብሰባው ሳያልቅ " ተንቀርቃቢው ፍም" የሚል የግጥም ስንኝ ጽፋ አስነበበችኝ።

በሁለተኛው ሳምንት ከአቶ መለስ ጋር የነበረን ስብሰባ አስደንጋጭ ነበር። ሪፓርታችንን ቀድሞ አንብቦ ስለሚመጣ እሳት ጎርሶ ጠበቀን። የያዘውን ሪፓርት ወረወረው። " እኔ ያልኳችሁን መፈፀም የማትፈልጉ ከሆነ ለምን መጣችሁ?" ብሎ አፈጠጠብን። ሁላችንም ፊታችንን ወደ በረከት አዞርን። በረከት ፍፁም በተረጋጋ ሁኔታ " ሰፉ አድርገን ከሁሉም ማህበረሰብ ብንመለምል የተሻለ ይሆናል በሚል ነው " የሚል ምላሽ ሰጠ።

አቶ መለስ መዳፉን በሌላኛው ጣቱ እየጠበጠበ " በረከት! ኢህአድግን ከዳንኪራና አሼሼ ገዳሜ

የምታወጣው መቼ ነው? " አለው። በረከትም ከላይ የተጻፈውን ምላሽ ሰጠ።

ከዛን ቀን በኃላ የአዲሳባ ኢህአድግ ክንፍ ሁለት የተለያዩ ሪፓርቶችን ለማዘጋጀት ተገደደ። ለድርጅቱና ስትራቴጂስቱ!

ምክንያቱን በውል ባላወኩት ሁኔታ ከወራቶች በኃላ የአቶ መለስ ሀሳብ ተሸንፎ የበረከት የምልመላ አቅጣጫ የመላ ኢህአድግ ዋነኛ ስትራቴጂ ሆኖ ብቅ አለ። በሚሊዬኖች ድርጅቱን እንዲቀላቀሉት የሚያስችል አቅጣጫ ተነደፈ። የትኩረት ቦታዎቹም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ፣የመንግስት ሰራተኞችና መምህራን እንዲሆኑ ተደረገ። ስትራቴጂው " በመንግስት ውስጥ የድርጅት ስራ መስራት " " Through -Which "የሚል ስያሜ ተሰጠው።

ይህ በዘመቻ መልክ የተካሄደው ምልመላ ድርጅቱን ለተጨማሪ ቀማኞች፣ ስራ ጠሎችና የቡድን ሌቦች አጋልጦ ሰጠው። ወትሮም ነቅዞ የነበረው ድርጅት በጠራራ ፀሀይ ሌቦች ተወረረ። በመንግስት ውስጥ የድርጅት ስራ መስራት በአንድ በኩል ኢህአድግን ወደ ቢሊየነርነት ቢያሸጋግረውም ፣ በሌላ በኩል የፓርቲው የመጀመሪያ መጨረሻ መዳረስ የሚያመላክት ፊሽካ የተነፋበት ሆነ።